# መጽሐፈ ሳሙኤል - አንደኛ

## መግቢያ

### አሰያየሙ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ 1ኛ ሳሙኤልና 2ኛ ሳሙኤል የሚለው ስም የመጣው እግዚአብሔር በእስራኤል ምድር ንጉሣዊ አገዛዝን ለመመሥረት ከተጠቀመበት ሰው ጋር በተያያዘ ምክንያት ነው:: ሳሙኤል የመጀመሪያዎቹን ሁለቱን የእስራኤል ነገሥታት የቀባ ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ያለውን አዲሱን ንጉሣዊ አስተዳደር የአመራር ስልት ያዋቀረ፣ መዋቅሩም ትርጉም እንዲያገኝ ያደረገ ሰው ነበረ:: ሳሙኤል በዚህኛው የእስራኤል ታሪክ ዋነኛው የእግዚአብሔር አገልጋይ ሆኖ መመረጡ ከሙሴ ጋር ያቀራርበዋል (መዝ 99፥6፤ ኤር 15፥1 ይመ)፤ ከመሳፍንት አገዛዝ ወደ ነገሥታት አገዛዝ በተደረገው ሽግግር፣ ሳሙኤል ከማንም ሰው ይልቅ ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ያደረገ ሰው ነበረ:: በመሠረቱ አንደኛ ሳሙኤልና ሁለተኛ ሳሙኤል እንደ አንድ መጽሐፍ የሚቈጠሩ ነበሩ፤ ሁለት ቦታ ተከፍለው፣ ሁለት መጽሐፍ የሆኑት ሰብዓ ሊቃናት (200 ዓ.ቅ.ክ. ገደማ) መጻሕፍተ ብሉያትን ከዕብራይስጥ ወደ ጽርዕ (ግሪክ) ቋንቋ በመለሱበት ጊዜ ነበር:: ከዚያ በኋላም ጀሮም የተባለው የላቲን ቤተ ክርስቲያን አባት ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደ ሮማይስጥ (ላቲን) ቋንቋ በመለሰበት ጊዜ ይህንኑ ፈለግ በመከተል በሁለት ከፍሎታል:: ከዚያ በኋላ የተተረጐሙት ቅዱሳት መጻሕፍትም ወደ እኛ የደረሱት በዚሁ መልክ ነው::

### ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያቱ፣ ጸሓፊውና የተጻፈበት ዘመን

የአንደኛ ሳሙኤልና ሁለተኛ ሳሙኤልን ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርይ፣ ጸሓፊውንና የተጻፈበትን ዘመን በተመለከተ አያሌ ጥያቄዎች ተነሥተዋል፣ መጽሐፉ የተዘጋጀው ራሳቸውን ከቻሉ የተለያዩ ምንጮች ለመሆኑ ከአንዳንድ የሥነ ጽሑፉ ባሕርያት መረዳት ይቻላል:: መጽሐፉ በተዘጋጀበትም ወቅት ጸሓፊው ከሌሎች ምንጮች በቀጥታ ሳይቀዳ በተቻለም መጠን ከመሠረታዊ ይዘቱ ሳያፋልስ እንዳለ በራሱ አቀራረብ አቀናጅቶ ሳይጽፈው እንዳልቀረ ይታመናል:: ጸሓፊው የንጉሥ ሰሎሞን ልዩ አማካሪ የነበረው ዛብድ ነው የሚሉ አሉ:: በእርግጥም ስለ ንጉሥ ዳዊት ዘመነ መንግሥት የሚያወሳ ዜና ከአባቱ፣ ከናታንና ከቤተ መንግሥቱ መዛግብት ማግኘት የሚችል ሰው ስለ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም፤ ብቻ ጸሓፊው ማንም ይሁን ከንጉሥ ሰሎሞን ሞት (930 ዓ.ቅ.ክ.) በኋላና እንዲሁም መንግሥቱ ከሁለት ከተከፈለ ("እስራኤልና ይሁዳ" የሚለውን አመለካከት ልብ ይሏል፤ በ11፥8፤ 17፥52፤ 18፥16፤ 2ሳሙ5፥5፤ 24፥1-9፤ ላይ የተጠቀሱትንና "የይሁዳ ነገሥታት" በሚል ጠንካራ አገላለጽ በ1ሳሙ27፥6፤ ላይ የተመለከተውን ይመ) በኋላ ጥቂት ቈየት ብሎ የእነርሱ ሰው ሳይሆን አይቀርም:: ጸሓፊው ከዚህም በቀር የሳሙኤልን፣ የሳኦልንና የዳዊትን ሕይወትና ዘመን በተመለከተ የተጻፉ መዛግብትን ሳያገላብጥ እንዳልቀረ እሙን ነው:: የያሳር መጽሐፍ ብቻ እንደ አንድ ምንጭ ተደርጎ በራሱ በመጽሐፉ ውስጥ በግልጽ ተመልክቶ አል (የያሳር መጽሐፍ፣ 2ሳሙ1፥18)፤ ይሁን እንጂ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ይህ ታሪክ ስለ ተፈጸመበት ዘመን፣ የሚናገሩ ሌሎች አራት መጻሕፍትን ጠቅሶአል (እነዚህም የዳዊት ዘመነ መንግሥት ታሪክ መጽሐፍ 1ዜና27፥24 የባለ ራእዩ የሳሙኤል የታሪክ መዛግብት፣ የነቢዩ የናታን የታሪክ መዛግብት፣ የባለ ራእዩ የጋድ የታሪክ መጻሕፍት 1ዜና29፥29 ናቸው)::

### የመጽሐፉ ይዘትና መሪ ሐሳብ

አንደኛ ሳሙኤል የነገሥታት አስተዳደር እንዴት በእስራኤል እንደ ተመሠረተ ይተርካል:: ጸሓፊው በመለኮታዊው አስተዳደር ውስጥ የተከሠተውን ፈጣን ለውጥ ከመግለጹ በፊትም የዐውዱን ውስብስብነት ያሳየናል:: የሚከተሉት ሁነቶች ስለ ንጉሣዊው አገዛዝ አጀማመር ታሪካዊና ትምህርተ መለኮታዊ ዐውዶችን ያቀርባሉ::

1. **የሳሙኤል ልደት፣ እድገትና መጠራት** (ም1-3):- በአብዛኛው ክፍሉ የመጀመሪያዎቹን ሁለት ነገሥታት የሳኦልንና የዳዊትን ታሪክ በሚያወሳ መጽሐፍ ጸሓፊው የሁለቱንም ነገሥታት ዜና ልደት ትቶ የእነርሱ ተቀዳሚ የነበረውንና ቅብዐ መንግሥት የቀባቸውን የነቢዩን የሳሙኤልን ልደትና እድገት ዘርዝሮ በመጻፉ ራሱን የቻለ አንድ የቍም ነገር ሥራ አከናውኖአል:: ይህ ራሱ ሳሙኤል ወደ ፊት ከሚፈጽማቸው ተግባሮች ጋር ጸሓፊው የያዘውን ቁም ነገር አስፈላጊነት ይበልጥ ያጐለብተዋል:: ሰዎች እንዲህ በቀላሉ ሊረዱት በማይችሉበት አገላለጽ የነገሥታት አገዛዝ ሥርዐት በሚመሠረትበት ሂደት ውስጥ ሥጋና ደም ለ"ቃል"እና ለ"መንፈስ" መገዛት ያለባቸው መሆኑን ሳይገልጽ እንዳልቀረ ይገመታል:: ንግሥና በመጀመሪያ ብቅ ያለው ከዚያም ያቈጠቈጠውና ሥር የሰደደው በነቢዩ በሳሙኤል የትንቢት ቃልና ሥራ ነው::

2. **ታቦቱን አስመልክቶ የሚያወሳው ታሪክ** (4-6):- ይህ ክፍል የአምላክ ታቦት በፍልስጥኤማውያን እንዴት እንደ ተማረከና እግዚአብሔር በፍልስጥኤም ከተሞች ላይ ታላቅ ጥፋት ካመጣ በኋላ ግን እንዴት ወደ እስራኤል እንደ ተመለሰ በዝርዝር ያቀርባል:: እስራኤላውያን ታቦቱን ይዘው ለጦርነት መውጣታቸው ብቻ በጠላት ላይ ድል እንደሚያጐናጽፋቸው መተማመናቸው ስሕተት መሆኑን ትረካው በግልጽ ያሳየናል:: ይህም ብቻ አይደለም፤ እጅግ በተከበረውና አስደንጋጭ በሆነው በእስራኤል አምላክ

(የእግዚአብሔር ታላቅ ኀይል) ፊት የፍልስጥኤማውያን አምላክ ዳጎን እንደ ኢምንት እንኳ የማይቈጠር ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ መሆኑንም ከታሪኩ መረዳት ይቻላል:: ፍልስጥኤማውያን የእስራኤልን ታቦት በመመለሳቸው የእግዚአብሔርን ኀይል ለመቋቋም የሚያስችላቸው ነገር አለመኖሩን ለመግለጽ ተገደዋል:: የታቦቱን ውጣ ውረድ ዝርዝር ታሪክ በትክክል ስንመለከት እስራኤላውያን ያለማቋረጥ የሚታይ ንጉሥ በመፈለግ የምኞት ኀጢአት እንዲያድርባቸው በማድረጉ ረገድ የጐላ ሚና ተጫውቶአል::

**3.የሳሙኤል ምስፍናና ትድግና ም7**:- ሳሙኤል እስራኤላውያን ንስሓ እንዲገቡና ራሳቸውን እንደ ገና ለእግዚአብሔር እንዲያስገዙ አሳሰባቸው፤ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ረዳቸው፤ በፍልስጥኤማውያንም ላይ ድልን አቀዳጃቸው:: ሳሙኤል በእግዚአብሔር ስለ ተመረጠ ሥልጣኑ ኀይል ያለው መሆኑንም ይህ ታሪክ ያረጋግጣል:: እንዲሁም ሕዝቡ በእግዚአብሔር እስከ ታመነና የቃል ኪዳኑን ግዴታ አክብሮ ለመኖር ፈቃደኛ እስከ ሆነ ድረስ የእግዚአብሔር ጥበቃ እንደማይለየው ያስገነዝባል::

በም1-7 የተጻፈው ክፍል ንግሥና በእስራኤል እንዴት እንደ ተጀመረ በም8-12 ላይ ለተጻፈው ታሪክ እንደ መግቢያ ሆኖ ያገለግላል፤ እንደ መግቢያ ሆኖ ማገልገሉም ደግሞ አስፈላጊነት አለው:: ጸሓፊው በም8-12 ላይ ያሉትን ታሪኮች አሳምሮ አቅርቦአቸዋል፤ ይህን ያደረገውም ታሪካዊ ክሥተቶቹን የከበቧቸው ዋና ዋናዎቹ የትምህርተ መለኮት ግጭቶች ይበልጥ ኀይል እንዲኖራቸው ነው:: ምሁራን እነዚህን ምዕራፎች በማጥናት፣ ንጉሣዊ አገዛዝን በተመለከተ ሁለት ተቃራኒ ኀይሎች ግራና ቀኝ በመሆን ገመድ በሚጓተቱበት ጊዜ ያለውን ውጥረት የመሰለ ለመምረጥ የሚያስቸግር ሐሳብ እንዳለበት ለመረዳት ችለዋል:: ሳሙኤል ለሕዝቡ ንጉሥ እንዲያነግሥ ከእግዚአብሔር ሲታዘዝ ይታያል (8፥7:9:22፤ 9፥16-17፤ 10፥24፤ 12፥13)፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝቡ ንጉሥ እንዲነግሥለት መጠየቁ እግዚአብሔርን እንደተወና ይህም ኀጢአት ሆኖ እንደተቈጠረበት ይታያል (8፥7፤ 10፥19፤ 12፥12:17:19-20):: ይህ የነገሥታቱን አገዛዝ በተመለከተ እርስ በርሱ የሚቃረን መስሎ የሚታየው ሐሳብ መገምገም ያለበት የእስራኤል ሕዝብ ከእግዚአብሔር ጋር በነበረው የቃል ኪዳን ትስስር ይዘት አንጻር መሆን አለበት::

እስራኤል በዙሪያዋ እንዳሉት አሕዛብ አንድ ቀን የራሷን ንጉሥ የማንገሥ ፍላጎት ሳያድርባት እንደማይቀር ሙሴ ዐውቆና ተረድቶ ነበር (ዘዳ 17፥18-20)፤ ይሁን እንጂ በእስራኤል የሚመሠረተው ንጉሣዊ አገዛዝ ታላቁና እውነተኛው ንጉሣቸው ከሆነው ከእግዚአብሔር የፍትሕ ርትዕ አገዛዝ ጋር ተጣጥሞ መቀጠል አለበት፤ በዚህ ፈንታ ግን የእስራኤል ሽማግሌዎች ሳሙኤል ንጉሥ እንዲያነግሥላቸው በጠየቀት ጊዜ (8፥5:19-20)፣ በእነርሱ ላይ ነግሦ በርትዕ ፍትሕ ሲመራቸው፣ ሲያስተዳድራቸው የነበረውን የእግዚአብሔርን ንጉሥነት ናቁ፤ አቃለሉ (8፥7፤10:19፤ 12፥17:19):: በዙሪያቸው ያሉ አሕዛብ እንደሚያደርጉት ሁሉ በጦርነት ጊዜ መርቶ እንዲያወጣቸው፣ ለእስራኤል ጸጥታና ደኅንነት ምክንያት፣ ለአንድነቷም ማሰሪያ ሰንሰለት እንዲሆን ፈልገው ንጉሥ እንዲያነግሥላቸው መጠየቃቸው እውነተኛ ንጉሣቸው ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር ያስተሳሰራቸውን የቃል ኪዳን ገመድ ቈርጦ እንደ መጣል ይቈጠራል:: ከዚህም ይልቅ እግዚአብሔር ተስፋ የሰጣቸው፣ ጋሻ መከታቸው መሆኑን ብቻ ሳይሆን፣ ስለ እነርሱ ሆኖ ኀይሉን በተደጋጋሚ እንደሚገልጥ አሳይቶአል፤ አሁን በቅርቡ እንኳ (በሳሙኤል ጊዜ ማለት ነው) ታቦቱን በተመለከተ የተፈጸመው ድርጊትና (ም4-6) በሳሙኤልም መሪነት በፍልስጥኤማውያን ላይ የተገኘው ድል (ም7) አለ::

ያም ሆኖ ግን ለሕዝቡ ንጉሥ ያነግሥላቸው ዘንድ እግዚአብሔር ሳሙኤልን አዘዘው (8፥7:9:22):: ሳኦል ከሳሙኤል ጋር እንዲገናኝ እግዚአብሔር ፈቀደ፤ ሳሙኤልም ሳኦልን ለብቻው ወስዶ ለንጉሥነት የሚያበቃውን ቅባት እንዲቀባው አዘዘው (9፥1-10፥16):: ከዚያም ሳሙኤል ሕዝቡን በምጽጳ ሰብስቦ፣ ንጉሥ እንዲነግሥላቸው መፈለጋቸው (10፥18-19) ኀጢአት መሆኑን አንሥቶ እንደ ገና ከወቀሳቸው በኋላ፣ ንጉሡን በዕጣ ለማስመረጥም ዋናው ሰው እርሱ ራሱ ሆነ፤ ዕጣው በሳኦል ላይ ወጣ፤ እግዚአብሔር የመረጠውም እርሱ መሆኑን ለሕዝቡ አሳወቀ (10፥24):: ሳኦል ይህ እንደ ሆነ ያኔውኑ የንጉሥነት ሥራውን አልጀመረም፤ በቀጥታ ወደ ቤቱ ሄደ ዕርሻውን ያርስ ጀመር (11፥5:7):: አሞናዊው ናዖስ የኢያቢስ ዘገለዓድ ሰዎች በፍርሀት እንዲዋጡ ባደረገ ጊዜ፣ "ሳኦል እኔ አለሁላችሁ" ብሎ ለመግጠም ሰራዊት አሰባሰበ፣ ወደ ጦር ግንባር ዘመተ፤ እስራኤልንም ድል አቀዳጀ:: ጦርነቱን በድል አድራጊነት መወጣቱም ሳኦል እንዲነግሥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለ መሆኑ የመጨረሻው ማረጋገጫ ማኅተም ሆነ (10፥24-12፥25 ይመ)::

እንግዲህ ዛሬም እንኳ ትክክለኛ መልስ የሚያሻው ጥያቄ በዚያን ጊዜ እስራኤል እስከዚህ ንጉሥ ያስፈልጋት ነበር ወይ? የሚል ነው:: ንጉሥ እንዲኖራቸው የፈቀደ እግዚአብሔር ለመሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም፤ ይሁን እንጂ ዛሬ ምድራዊ ንጉሥ በላያቸው ማንገሥ ከጀመሩ፣ ራሱ ንጉሥ ሆኖ ያስተዳድራቸው ከነበረው ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ቃል ኪዳን እንዴት አድርገው ሊጠብቁት ይችላሉ? የሳኦል በዓለ ንግሥ በተከበረበት ሰዓት፣ ሳሙኤል ሕዝቡ ንስሓ እንዲገባ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውንም ግንኙነት እንዲያድስ ያኔውኑ ባሳሰበ ጊዜ ይህ ችግር እንዲፈታ አድርጎአል (11፥14-12፥25፤ እንዲሁም የ10፥18-19 ማብ ይመ)::

ሳሙኤል ቃል ኪዳን አድሶ የንጉሥ አገዛዝ ሥርዐት ከመሠረተ በኋላ፣ በዙሪያው ካሉት የአሕዛብ ነገሥታት አገዛዝ ፈጽሞ ልዩ የሆነ ንጉሣዊ አስተዳደር በእስራኤል ምድር እንዲገኝ አድርጎአል:: ንጉሥ በእስራኤል ምድር ያሻውን ሁሉ ማድረግ የሚችል ሳይሆን ሥልጣኑም፣ ኀይሉም በእግዚአብሔር ሕግና በነቢያት ቃል የተገደበ ነበር( 10፥25፤12፥23)፤ ይህም ሳኦልን ብቻ ሳይሆን፣ ከእርሱ በኋላ በእስራኤል

ዙፋን ላይ የሚቀመጡትን ነገሥታት ሁሉ የሚመለከት ሥርዐት ነበር፤ ሥርዐቱም ንጉሥ መሣሪያ ሆኖ እግዚአብሔር በእርሱ አማካይነት የገዛ ሕዝቡን የሚገዛበት፣ ሕዝቡም በበኩሉ እንደ ንጉሡ ሁሉ ፍ ጹም ገዥአቸው እግዚአብሔር መሆኑን ዐውቀው የሚገዙበት ሥርዐተ መንግሥት ነበር (12፥14-15)::

ሳኦል ግን በእግዚአብሔር የበላይነት የሚተዳደረው መንግሥት ለሚጠይቀው ሕግ መገዛት አለ መፈለጉን ያሳየው ወዲያውኑ ነበር (ም13-15):: የነቢዩን የሳሙኤልን ቃል ጥሶ ፍልስጥኤማውያንን ለመ ውጋት በተዘጋጀና (13፥13) አማሌቃውያንን ፈጽሞ እንዲያጠፋቸው በሳሙኤል አማካይነት የተነገረ ውን የእግዚአብሔር ቃል (ም15) ለመስማት ፈቃደኛ ባልሆነ ጊዜ፣ ሳኦል የእግዚአብሔር መሣሪያ መሆኑ ቀረ፤ ሕዝቡንም በእርሱ አማካይነት መግዛቱ አበቃ፤ አለመታዘዙም በእግዚአብሔር ዘንድ መናቅን አስከተለበት (15፥23)

ቀሪው የመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ክፍል (ም16-31) ዳዊት በሳኦል ምትክ መመረጡን፣ እዚያ ቦታ ለመድረስም የተጓዘባቸውን አስቸጋሪ ጐዳናዎች የሚዘረዝር ነው:: የሳኦል አገዛዝ ከእግዚአብሔር መንገድ በየጊዜው እየወጣ መሄዱ ቢቀጥልም፣ ዳዊት መንግሥቱን በኀይል ሊቀማው አልፈለገም፤ ነገሩን ሁሉ ለእግዚአብሔር ተወው:: በኋላም ሳኦል ከፍልስጥኤማውያን ጋር ባደረገው ጦርነት ቈሰለ፤ በፍልስጥኤ ማውያን እጅ መውደቁን ስለፈራም በገዛ እጁ ራሱን ገደለ፤ ሦስቱ የሳኦል ወንዶች ልጆች በጦርነቱ ላይ ሞቱ:: ከነዚህም አንዱ የዳዊት የልብ ወዳጅ ዮናታን ነበር (ም3)

**የሁነቶች ቅደም ተከተል**

ምንም እንኳ የ1ኛ ሳሙኤልና የ2ኛ ሳሙኤል ታሪኮች አንዳንዶቹ የዘመናትን ቅደም ተከተል የጠበቁ ቢሆኑም (ለምሳሌ 1ሳሙ6፥1፤ 7፥2፤ 8፥1:5፤ 13፥1፤ 25፥1፤ 2ሳሙ2፥10-11፤ 5፥4-5፤ 14፥28፤ 15፥7 ይመ)፣ እንደ እውነቱ ግን ጥንቅር መረጃዎቹ የዚህኛውን ዘመን ዋና ዋናውን የእስራኤል ታሪክ ድርጊት ትክክለኛ የዘመናት ቅደም ተከተል ጠንቅቀው አስቀምጠዋል ለማለት ያስቸግራል:: በትክክል ከሚታወቀው (2ሳሙ5፥4-5)፣ ዳዊት ከተወለደበት ቀንና ከዘመነ መንግሥቱ ቍጥር ልክ በስተቀር፣ የቀረው የታሪክ ዘመናት ቅደም ተከተል እስከዚህ የጠነቀቀ አይደለም፤ ሳኦል ሲነግሥ ዕድሜው ስንት እንደ ነበርና የግዛት ዘመኑ የቈየበትንም ጊዜ ቅደም ተከተል መጽሐፉ ጠንቅቆ ባለ መመዝገቡ የተከሠተው ችግር የተወለደበትንና ነግሦ መግዛት የጀመረበትን ጊዜ በትክክል ላለማወቅ የራሱን አስተዋፅኦ አድርጎአል:: ስለ ሳሙኤል የልደትና (1ሳሙ 1፥1) የሞት ጊዜ የሚያስረዳ የተጻፈ ነገር የለም፤ ይነስም ይብዛ በከፊል፣ ከሳምሶን እንዲሁም ከሩት ከተወለደው ከዳዊት አያት ከቦዔዝ ዘመን ሳይጋጠም አልቀረም:: የእስራኤል ሽማግሌዎች ንጉሥ እንዲነግሥላቸው በጠየቁት ጊዜ፣ ሳሙኤል ዕድሜው ገፍቶ እንደ ነበር የሚያመለክት ነገር አለ (8፥1:5 ይመ):: የታሪኩ ቅደም ተከተል በትክክል ሊቀመጥ ካል ቻለባቸው ምክንያቶች አንዱ፣ ራሱ ጸሓፊው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው ድረስ ላለው ለሌላው ድርጊት እንጂ ለታሪኩ ሂደት ቅደም ተከተል እስከዚህ ሥራዬ ብሎ ትኵረት አለመስጠቱ ነው::

ለምሳሌ 2ሳሙ 7፥1 በቅደም ተከተሉ መሠረት ቦታው አሁን ያለበት ሳይሆን በ2ሳሙ 8፥1-14 ላይ እንደ ተጻፈው የዳዊትን ድል ማድረግ ተከትሎ መምጣት አለበት (የ2ሳሙ 7፥1፤8፥1 ማብ ይመ ):: ሌላው ደግሞ፣ ሳኦል ከገባዖን ሰዎች ጋር ያደረገውን ውል ስላፈረሰ፣ በዳዊት ዘመን የተከሠተው ራብ ታሪክ ተጽፎ የሚገኘው በ2ሳሙ21፥1-4 ላይ ነው:: እንደ ታሪኩ ሂደት ቅደም ተከተል ግን፣ ይህ ታሪክ የተጻፈው በ2ሳሙ 15-18 ላይ እንደ ተጻፈው (2ሳሙ21፥1-2 ማብ ይመ)፣ አቤሴሎም ከማመፁ በፊት ነበር፤ ይሁን እንጂ ከዚህ የሚቀጥለው የጊዜ ሰሌት ይብዛም ይነስም የሳሙኤልንና የዳዊትን ዋና ዋና የጊዜ ቅደም ተከተል የሚያ መለክት ነው::

1105 ዓ.ቅ.ክ- ሳሙኤል የተወለደበት ዘመን (1ሳሙ 1፥20)
1080 ዓ.ቅ.ክ - ሳኦል የተወለደበት ዘመን
1050 ዓ.ቅ.ክ- ሳኦል ለንጉሥነት ተቀባ (1ሳሙ10፥1)
1040 ዓ.ቅ.ክ- ዳዊት የተወለደበት ዘመን
1025 ዓ.ቅ.ክ- ዳዊት በሳኦል ምትክ ተቀባ (1ሳሙ16፥1-13)
1010 ዓ.ቅ.ክ- ሳኦል ሞተ፤ ዳዊት በኬብሮን ተቀምጦ በይሁዳ ሁሉ ላይ ነገሠ (2ሳሙ 1፥1፤2፥1:4:11)
1003 ዓ.ቅ.ክ- ዳዊት መላውን እስራኤልን ጠቅልሎ ገዛ፤ ኢየሩሳሌምንም ያዘ (2ሳሙ5)
997-992 ዓ.ቅ.ክ- ዳዊት የተዋጋቸው ጦርነቶች (2ሳሙ8፥1-14)
991 ዓ.ቅ.ክ- ሰሎሞን ተወለደ (2ሳሙ 12፥24፤1ነገ3፥7፤11፥42)
980 ዓ.ቅ.ክ- ዳዊት ሕዝቡ እንዲቈጠር አደረገ (2ሳሙ 24፥1)
970 ዓ.ቅ.ክ- የዳዊት ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ (2ሳሙ 5፥4-5፤ 1ነገ 2፥10–11)

**አስተዋፅኦ**

1. ንጉሥነት በእስራኤል እንዲመሠረት ያመቻቹ የታሪክ ቅደም ተከተል ሁኔታዎች ጅማሬ (1ሳሙ1-7)
   ሀ) የሳሙኤል ልደት፣ ወጣትነቱና ለነቢይነት መጠራቱ፤ በዔሊ ቤት ላይ የተወሰነ ፍርድ (1ሳሙ1-3)
   ለ) እስራኤል በፍልስጥኤማውያን ድል ሆነች፤ የእግዚአብሔር ታቦት ተማረከ፤ ተመለሰ፤ ሳሙኤል ዳኛና ታዳጊ በመሆን ያከናወናቸው ሥራዎች( 1ሳሙ4-7)
2. በነቢዩ በሳሙኤል አመራር ንጉሥነት በእስራኤል ተመሠረተ (1ሳሙ 8-12)

ሀ) ሕዝቡ ንጉሥ እንዲኖረው ጠየቀ፤ ይህም ኀጢአት ነበር:: እግዚአብሔርም ንጉሥ እንደሚያነግሥ ባቸው (እንደሚሰጣቸው) ፈቃዱ መሆኑን ገለጠ (1ሳሙ 8)::
ለ) ሳሙኤል ሳኦል ንጉሥ ይሆን ዘንድ ቀባው (1ሳሙ 9፥1-10፥16)
ሐ) ሳኦል ንጉሥ ይሆን ዘንድ ብዙ ሕዝብ ባለበት በምጽጻ ዕጣ ወጣለት (1ሳሙ 10፥17-27)
መ) ሳኦል ለንጉሥነት የመመረጡ ነገር፣ በአሞናውያን ላይ ባገኘው ድል ተቀባይነት አገኘ (1ሳሙ 11፥1-13)
ሠ) ሳሙኤል በጌልጌላ ላይ ሕዝቡን ሰብስቦ ቃል ኪዳኑን ባደሰበት ቀን፣ የሳኦል ንጉሥነት በታላቅ ሥነ ሥርዐት ተከበረ (1ሳሙ 11፥14-12፥25)

3. የሳኦል አገዛዝ ውድቀት (1ሳሙ 13-15)
4. ዳዊት በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ፤ የሳኦል መንግሥት በተከታታይ ኀይሉና ብርታቱ እየቀነሰና እየተዳከመ ሄደ፤ በመጨረሻም ወደቀ (1ሳሙ 16፥1-2ሳሙ 5፥5)፤
ሀ) ዳዊት ተቀባ፤ ንጉሥ ሳኦልን በወታደርነት አገለገለ፤ ሕይወቱን ለማትረፍ ሸሸ፤ (1ሳሙ 16-26)
ለ) ዳዊት በፍልስጥኤም ምድር ጥገኛ ሆነ፤ ሳኦልና ወንዶች ልጆቹ በጦርነት ላይ ሞቱ (1ሳሙ 27-31)
ሐ) ዳዊት በይሁዳ ላይ ነገሠ (2ሳሙ 1-4)
መ) ዳዊት በመላው እስራኤል ላይ ነገሠ (2ሳሙ 5፥1-5)
5. ዳዊት ያከናወናቸው ሥራዎችና ያገኘው ታላቅ ክብር (2ሳሙ 5፥6-9፥12)
ሀ) ዳዊት ኢየሩሳሌምን ድል አድርጎ ያዛት፤ ፍልስጥኤማውያንንም አሸነፈ (2ሳሙ 5፥6-25)
ለ) ዳዊት ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም አመጣ (2ሳሙ 6)
ሐ) እግዚአብሔር ለዘላለም ጸንቶ የሚኖር ሥርወ መንግሥት ለዳዊት እንደሚሰጠው ቃል ኪዳን ገባለት (2ሳሙ 7)::
መ) የዳዊት መንግሥት ሰፋ፤ በውስጥ አስተዳደሩም ፍትሕ ሰፈነ (2ሳሙ 8)
ሠ) ዳዊት ከዮናታን ጋር የገባውን ቃል ኪዳን እስከ መጨረሻው ጠበቀ (2ሳሙ 9)
6. የዳዊት ዘመነ መንግሥት ድክመቶችና ውድቀቶች (2ሳሙ 10-20)
ሀ) ዳዊት የዝሙት በደል ፈጸመ፤ነፍስም አጠፋ (2ሳሙ 10-12)
ለ) ዳዊት ልጆቹን አምኖንንና አቤሴሎምን በሞት አጣ (2ሳሙ 13–20)
7. የመጨረሻው የዳዊት ዘመነ መንግሥት ገጽታ (2ሳሙ 21-24)

## የሳሙኤል መወለድ

1 በተራራማው በኤፍሬም አገር በአር
ማቴም መሴፋ የሚኖር ሕልቃና የተባለ
አንድ ሰው ነበረ፤ እርሱም ኤፍሬማዊ ሲሆን፣
የኢያሬምኤል ልጅ፣ የኢሊዩ ልጅ፣ የቶሑ
ልጅ፣ የናሲብ ልጅ፣ ነበረ። [2]እርሱም አንዲቱ
ሐና፣ ሌላዪቱ ፍናና የተባሉ ሁለት ሚስቶች
ነበሩት፤ ፍናና ልጆች ሲኖሯት፣ ሐና ግን
ምንም ልጅ አልነበራትም።

[3]ያም ሰው ሁሉን ቻይ ለሆነው *ለእግዚአ
ብሔር* ለመስገድና መሥዋዕት ለመሠዋት
በየዓመቱ ከሚኖርበት ከተማ ወደ ሴሎ
ይወጣ ነበር። በዚያም ሁለቱ የዔሊ ልጆች
አፍኒንና ፊንሐስ *የእግዚአብሔር* ካህናት
ነበሩ። [4]ሕልቃና ወደ ሴሎ ሄዶ መሥዋዕት
የሚሠዋበት ወቅት በደረሰ ጊዜ ሁሉ፣
ለሚስቱ ለፍናና እንዲሁም ለወንዶችና ለሴ
ቶች ልጆቿ ሁሉ ከሥጋው ድርሻቸውን
ይሰጣቸው ነበር። [5]ሐናን ግን ይወዳት ስለ
ነበር፣ ዕጥፍ ድርሻ ይሰጣት ነበር፤ ይሁን
እንጂ *እግዚአብሔር* ማሕፀኗን ዘግቶት ነበር።
[6]*እግዚአብሔር* ማሕፀኗን ስለ ዘጋም ጣው
ንቷ ታስቈጣት፣ ታበሳጫትም ነበር። [7]ይህም
በየዓመቱ ይደጋገም ነበር፤ ሐና ወደ *እግዚአ
ብሔር* ቤት በምትወጣበት ጊዜ ሁሉ፣ እስክ
ታለቅስና መብላት እስኪያቅታት ድረስ
ጣውንቷ ታበሳጫት ነበር። [8]ባሏ ሕልቃ
ናም እርሷን፣ "ሐና ሆይ፤ ለምን ታለቅሻለሽ?
ለምንስ አትበዪም? ልብሽስ ለምን ያዝ
ናል? ከዐሥር ወንዶች ልጆች እኔ አልበል
ጥብሽምን?" ይላት ነበር።

[9]አንድ ጊዜ በሴሎ ሳሉ ከበሉና ከጠጡ
በኋላ ሐና ተነሥታ ቆመች፤ በዚያ ጊዜ
ካህኑ ዔሊ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ[ሀ]
መቃን አጠገብ በወንበር ላይ ተቀምጦ
ነበር። [10]ሐናም በነፍሷ ተመርራ አብዝታ
በማልቀስ ወደ *እግዚአብሔር* ጸለየች።
[11]እንዲህም ብላ ስእለት ተሳለች፤ "የሰራ
ዊት ጌታ *እግዚአብሔር* ሆይ፤ የአገልጋይ
ህን መዋረድ ተመልክተህ ብታስበኝና አገ
ልጋይህን ሳትረሳት ወንድ ልጅ ብትሰ
ጣት፣ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ *ለእግዚአ
ብሔር* እሰጠዋለሁ፤ ምላጭም በራሱ ላይ
አይደርስም።"

[12]ሐና ባለማቋረጥ ወደ *እግዚአብሔር* በጸለ
የች ጊዜ፣ ዔሊ አፏን ይመለከት ነበር።
[13]እርሷም በልቧ ትጸልይ ስለ ነበር፤ ከንፈሯ
ይንቀሳቀስ እንጂ ድምጿ አይሰማም ነበር፤
ዔሊም እንደ ሰከረች አድርጎ ቈጠራት
[14]እርሱም "ስካሩ የማይለቅሽ እስከ መቼ
ድረስ ነው? የወይን ጠጅሽን ከአንቺ አስወግ
ጂው" አላት።

[15]ሐናም እንዲህ ብላ መለሰችለት፤ "ጌታዬ

ሀ9 የማደሪያ ድንኳን ማለት ነው

1፥1 ኢሱ 17፥17-18፤
25፥21፥20-22
1ሳሙ 9፥5፤
1ዜና 6፥27:34
1፥2 ዘፍ 4፥19
1፥3 ቍ21፤
ዘፀ23፥14፤
ዘዳ12፥5-7፤
ኢሱ18፥1፤
1ሳሙ 2፥19፥31፤
14፥3፥20፥6:29፤
ሉቃ2፥41
1፥4 ዘፍ29፥34፤
ዘሌ7፥15-18፤
ዘዳ12፥17-18
1፥5 ዘፍ11፥30፤
29፥31፥37፥3
1፥6 ዘፍ16፥4
1፥7 2ሳሙ12፥17፤
መዝ102፥4
1፥8 ሩት4፥15
1፥9 1ሳሙ3፥3
1፥10 ኢዮ3፥20፤
7፥11፥10፥1፥21፥25፤
23፥2፥27፥2፤
ኢሳ38፥15፤
ኤር 20፥18
1፥11 ዘፍ 8፥1፤
17፥1፤ዘኍ6፥1-21፤
መሳ11፥30፥13፥5:7፤
መዝ24፥10፥46፥7፤
ኢሳ 1፥9፥ሉቃ1፥15
1፥15 2ነገ4፥27፤
መዝ42፥4፤
62፥8፥ሰቆ2፥19

1፥1 *በአርማቴም፤* ይህ ስም በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኘው እዚህ ላይ ብቻ ነው፤ "ራማ" ለሚለውም ስም ሌላው መጠሪያ ነው (1፥19፤ 2፥11፤ 7፥17፤ 19፥18፤ 25፥1 ይመ)። ምናልባትም ከኢየሩ ሳሌም በስተ ሰሜን ከኤፍሬምና ከብንያም ድንበር ስምንት ኪሎ ሜትር ርቃ ከምትገኘው ከኩረብታማዋ አገር ከብንያም ራማ (ኢሱ 18፥25 ይመ) ጋር ሳትመሳሰል አትቀርም። *የናሲብ፤* ይህ ስም ሰውንም ሆነ ቦታን የሚያመለክት ስለ መሆኑ በውል የሚታወቅ ነገር የለም። ሰውን የሚመለከት ከሆነ ናሲብ የተባለውን ዘር (1ዜና 6፥34-35)፣ ቦታን የሚያመለክት ከሆነ ደግሞ አርማቴም የተባለውን አካባቢ ያመለክታል (9፥5 ይመ)። *ኤፍሬማዊ፤* በዚህ ስፍራ ሕልቃና ኤፍሬማዊ ተብሎ ቢጠራም፣ ምናልባት ቤተሰቡ በኤ ፍሬም፣ ከተሞች ተሰጥተውት ከነበረው ከቀሃት ነገዶች የተገኘ ሌዋዊ ሳይሆን አይቀርም (ኢሱ 21፥20-21፤ 1ዜና 6፥22-26 ይመ)።

1፥2 *ሁለት ሚስቶች፤* የዘፍ 4፥19፥16፥2፥25፥6 ማብ ይመ።

1፥3 *በየዓመቱ ... ይወጣ ነበር፤* ወንድ የሆነ ማንኛውም እስራኤላዊ በዓመት ሦስት ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ወደ ቤተ መቅደስ መሄድ አለበት (ዘፀ 23፥14-19፤ 34፥23፤ ዘዳ16፥16-17 ይመ)። እዚህ ላይ የተጠቀሰው በዓል የዳስ በዓል ሳይሆን አይቀርም። ይህ በዓል የሚከበረው ከምድረ በዳ ወደ ከነዓን በተ ደረገው ጕዞ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ስላደረገው እንክብካቤ ብቻ ሳይሆን (ዘሌ23፥43)፣ ይበልጡኑ በዚሁ ዓመት እግዚአብሔር ሕዝ ቡን በእህል አዝመራ መባረኩን በማሰብ ጭምር በደስታና በፈንጠዝያ የሚከበር በዓል ነው (ዘፀ16፥13-15)። እንዲህ ያለ ታላቅ በዓል በሚከበርበት ጊዜ ሐና መካን በመሆኗ በጠለቀ ሐዘን ውስጥ መገኘቷ እጅግ ልብን የሚነካ ነው። *ሁሉን ቻይ ለሆነው ለእግዚ አብሔር፤* በሌላ አገላለጽ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ማለት ነው። እግዚአብሔር ለመጀመሪያ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ራሱን የገለጠበት ስም ነው። "ሰራዊት" የሚለው ቃል በዕብራይስጡ፣ (1) የጦር ሰራዊትን (ዘፀ 7፥4፤ መዝ 44፥9፤) (2) ሰማያውያን ፍጥረትን ማለ ትም ፀሓይን፤ ጨረቃንና ከዋክብትን (ዘፍ2፥1፤ዘዳ4፥19፤ኢሳ40፥26 ወይም (3) ልዩ ፍጥረታትን ማለትም መላእክትን (ኢሳ5፥14፥1ነገ 22፥19፤ መዝ 148፥2) የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። "የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር" የሚለው ስም በፍጥረተ ዓለማት ውስጥ ባሉት ፍጥረታት ሁሉ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት ያሳያል። እስራኤላው ያን የንጉሥን አስተዳደር ከመፈለጋቸው ጕዳይ ጋር ሲያያዝ እግዚአብሔር በሰማይ ሰራዊትና (ዘፀ33፥2፤ኢሱ5፥14፤መዝ68፥17፥ዕን 3፥8) በእስራኤል ሰራዊት (1ሳሙ 17፥45) ላይ "ጌታ ነው" መባሉ ትክክለኛ ይሆናል። *ሴሎ፤* መቅደሱና የቃል ኪዳኑ ታቦት የተቀ መጡበት በቤቴልና በሴኬም መካከል ያለ በኤፍሬም ውስጥ የሚ ገኝ ከተማ ነው (ኢሱ18፥1፤መሳ 21፥9)።

1፥4 *መሥዋዕት፤* እዚህ ላይ የተጠቀሰው መሥዋዕት ከእግዚ አብሔር ጋር ያለውን ኅብረትና አንድነት የሚመለከት ሲሆን፣ ስላደ ረገውም ምሕረት እርሱን በማመስገን የሚደረግ የደስታ መብል ነው (ዘሌ7፥11-18፤ ዘፀ12፥7:17-18)።

1፥5 *እግዚአብሔር ማኅፀኗን ዘግቶት ነበር፤* ልጆችን የሚሰጥም ሆነ የሚነሣ እግዚአብሔር ነው (ዘፍ18፥10፤ 29፥31፤ 30፥2:22)።

1፥6 *ጣውንቷ፤* የዘፍ16፥4ማብ ይመ።

1፥9 *ቤተ መቅደስ፤* እዚህና በ3፥3 ላይ የተጠቀሰው ማደሪያ "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ" የሚል መጠሪያ ተሰጥቶታል፤ ደግ ሞም "የእግዚአብሔር ቤት" (ቍ7:3፥15)፣ "የመገናኛው ድንኳን" 2፥22)፣ "መኖሪያዬ" (2፥32) ተብሎአል። ማደሪያው "ቤት"፣ "ቤተ መቅደስ" መባሉና በተጨማሪም መኝታ ክፍሎችና በሮች በውስጡ መኖራቸው (3፥2:15)፣ በዚህ ጊዜ ማደሪያው ትልቅና ቋሚ ሕንጻዎች መካከል መሆኑን ሲያመለክት፣ "ቤተ መቅደስ" መባሉ ትክክል ነው (ከኤር 7፥12:14:26፥6 ጋር ያነጻጽሩ)።

1፥11 *ተሳለች፤* ዘፍ28፥20-22፤ ዘኍ21፥2፤መዝ50፥14፤ 76፥11፥116፥14:18፤ 132፥2-5፤ ምሳ20፥25፤ 31፥2 ይመ። ሴቶች እንዴት መሳል እንዳለባቸው የሚገልጽ መመሪያ በዘኍ 30 ላይ ይገኛል። *ተመልክተህ፤* ሐና ያለችበትን ሁኔታ እንዲሁ ከማየት ያለፈ ነው (ቍ19፤ የዘፍ8፥1 ማብ ይመ)። *በሕይወት ዘመኑ ሁሉ፤* አንድ ሌዋዊ ከ25 ዓመት ዕድሜው ጀምሮ መላ ሕይወ ቱን ለአገልግሎት የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመለክታል (ዘኍ 8፥23-26 ይመ)። *ምላጭም በራሱ ላይ አይደርስም፤* ሐና፣ እግዚአ ብሔር ስለ ሶምሶን የተናገረውን ዐይነት ስእለት ተሳለች (መሳ 13፥5)። ረጅም ጠጕር ለጌታ አገልግሎት መለየትን የሚያመለክ ትና ከናዝራዊነት ስእለት አንዱ መታወቂያ ነው (ዘኍ 6፥1-21 ይመ)። ይህ ስእለት ለተወሰነ ጊዜ የሚፈጸም እንጂ የዕድሜ ልክ ስእለት አይደለም።

*1፥13 ሰከረች፤* እዚህ ላይ ዔሊ የፈጸመው ስሕተት በዚያ ዘመን የሰከሩ ሰዎች ወደ ቤተ መቅደስ መግባት የሚፈቀድላቸው መሆኑን ያመለክታል፤ የጊዜው ሃይማኖታዊና ግብረ ገባዊ አቋም የተበላሸ እንደ ነበረ የሚጠቍም ተጨማሪ ማስረጃ በመሳ 17፥21 ባሉት ታሪኮች ይገኛል።

ሆይ፤ ሰክሬ አይደለም፤ እኔ ልቧ ክፉኛ
የታወከባት ሴት ነኝ፤ ልቤን በእግዚአብሔር
ፊት አፈሰስሁ እንጂ፣ የወይን ጠጅም
ሆነ ሌላ የሚያሰክር መጠጥ አልጠጣሁም::
16ይህን ያህል ጊዜ የጸለይሁት ከባድ ከሆ
ነው ጭንቀቴና ሐዘኔ የተነሣ ስለ ሆነ፣
አገልጋይህን እንደ ምናምንቴ ሴት አት
ቍጠረኝ::"

17ዔሊም፣ "በሰላም ሂጂ፤ የእስራኤል
አምላክ የለመንሺውን ይስጥሽ" ሲል
መለሰላት::

18እርሷም፣ "አገልጋይህ በፊትህ ሞገስ
ታግኝ" አለች፤ ከዚያም መንገዷን ሄደች፤
ምግብም በላች፤ ከዚያም በኋላ በፊቷ
ላይ ሐዘን አልታየም::

19በማግስቱ ጠዋት ተነሥተው *በእግዚ
አብሔር* ፊት ሰገዱ፤ ከዚያም በራማ ወደ
ሚገኘው ቤታቸው ሄዱ:: ሕልቃና ከሚስቱ
ከሐና ጋር ተኛ፤ *እግዚአብሔርም* አሰባት፤
20ስለዚህ ሐና ፀነሰች፤ የእርግዝናዋ ወራት
በተፈጸመ ጊዜም ወንድ ልጅ ወለደች፤
ስሙንም፤ "ከእግዚአብሔር ለምኜዋለሁ"
ስትል ሳሙኤል[ሀ] አለችው::

## ሐና ሳሙኤልን ለእግዚአብሔር ሰጠች

21ሰውየውም ሕልቃና *ለእግዚአብሔር*
ዓመታዊውን መሥዋዕት ለመሠዋት ስእለ
ቱን ለማድረስ ቤተሰቡን ሁሉ ይዞ ወደ
ሴሎ ወጣ:: 22ሐና ግን አልሄደችም፤ እር
ሷም ባሏን፣ "ሕፃኑ ጡት ከተወ በኋላ፣
ወስጄ *በእግዚአብሔር* ፊት አቀርበዋለሁ፤
እስከ ሕይወቱ ፍጻሜም በዚያ ይኖራል"
አለችው::

23ባሏ ሕልቃናም፣ "መልካም መስሎ
የታየሽን አድርጊ፤ ጡት እስክታስጥዪው
ድረስ እዚሁ ቆዪ፤ ብቻ *እግዚአብሔር* ቃሉን[ለ]
ያጽናልሽ" አላት:: ስለዚህ ሐና ሕፃኑን ጡት
እስክታስጥለው ድረስ እያጠባችው በቤቷ
ተቀመጠች::

24ልጁ ጡት በተወ ጊዜ ከእርሱ ጋር አንድ
የሦስት ዓመት ወይፈን[ሐ]፣ አንድ የኢፍ መስ
ፈሪያ[መ] ዱቄትና አንድ አቍማዳ የወይን ጠጅ
ወስዳ፣ በሴሎ ወዳለው ወደ *እግዚአብሔር*
ቤት አመጣችው፣ ልጁም ገና ሕፃን ነበረ::
25ወይፈኑን ካረዱ በኋላም ልጁን ወደ ዔሊ
አቀረቡት:: 26ሐናም ዔሊን እንዲህ አለ
ችው፤ "ጌታዬ ሆይ፤ በነፍስህ እምላለሁ፤
እዚህ ቦታ ላይ በአጠገብህ ቆማ ወደ *እግዚ
አብሔር* ስትጸልይ የነበረች ያች ሴት እኔ
ነኝ:: 27ይህን ልጅ እንዲሰጠኝ ጸለይሁ፤ *እግዚ
አብሔርም* የለመንሁትን ሰጠኝ:: 28ስለዚህ
እኔም *ለእግዚአብሔር* እሰጠዋለሁ፤ በሕይ
ወት ዘመኑም ሁሉ *ለእግዚአብሔር* የተሰጠ
ይሆናል::" እርሱም በዚያ *ለእግዚአብሔር*
ሰገደ::

## የሐና የምስጋና ጸሎት

2 ሐናም እንዲህ ብላ ጸለየች፤
"ልቤ *በእግዚአብሔር* ጸና፤
ቀንዴም[ሠ] *በእግዚአብሔር* ከፍ ከፍ አለ፤
አፌ በጠላቶቼ ላይ ተከፈተ፤
በማዳንህ ደስ ይለኛልና::
2"እንደ *እግዚአብሔር* ያለ ቅዱስ[ረ] ማንም
የለም፤
ከአንተም በቀር ሌላ የለም፤
እንደ አምላካችን ያለ ዐለት የለም::
3"ይህን ያህል በመታበይ አትናገሩ፤
እንዲህ ያለውም የእብሪት ቃል

1፥16 መዝ 55፥2
1፥17ዘፍ25፥20፥21፤
ዘኍ 6፥26፤
1ሳሙ 20፥42፤
2ነገ5፥19፤
መዝ20፥3-5፤
ሐሥ15፥33
1፥18 ዘፍ18፥3፤
ሩት2፥13፤ሮሜ15፥13
1፥19 ዘፍ8፥1፤
29፥31፤ኢሱ18፥25
1፥20 ዘፍ17፥19፤
29፥32፤30፥6፤
ዘፀ2፥10፤
1ሳሙ7፥5፤12፥23፤
1ዜና6፥27፤ኤር15፥1፤
ማቴ1፥21፤
ዕብ11፥32
1፥21 ቍ3፤
ዘፍ28፥20፤
ዘኍ 30፥2፤
ዘዳ12፥11
1፥22 ዘፀ13፥2፤
ሉቃ2፥22
1፥23 ዘፍ21፥8፤
25፥21
1፥24 ዘኍ15፥8-10
1፥27 1ሳሙ2፥20፤
መዝ66፥19-20
1፥28 መሳ13፥7
2፥1 ዘኍ10፥35፤
መዝ6፥8፥10፤13፥5፤1፤
18፥2፤33፥21፤89፥17፤
24፤148፥14፤ዘካ10፥7፤
ሉቃ1፥46-55
2፥2 ዘፍ49፥24፤
ዘፀ8፥10፤15፥11፤33፥22፤
ዘሌ11፥44፤ዘዳ32፥37፤
2ሳሙ22፥2፥32፤23፥3፤
መዝ31፥3፤71፥3፤
ኢሳ40፥25፤46፥5
2፥3 ኢሳ22፥22፤
1ሳሙ16፥7፤1ነገ8፥39፤
1ዜና28፥9፤
2ዜና6፥30፤
መዝ17፥10፤31፥18፤
73፥8፤75፥4፤94፥4፤
ምሳ15፥11፤ 16፥2፤
24፥11-12፤
ኤር11፥20፤17፥10

[ሀ]20 በዕብራይስጡ ሳሙኤል የሚለው ቃል ድምፅ *እግዚአብሔር ሰማ* ከሚለው ሐረግ ጋር ይመሳሰላል::
[ለ]23 የሙት ባሕር ጥቅል፣ የሰብዓ ሊቃናትና የሱርስቱ ትርጕም ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የማሶሬቱ ቅጅ ግን *ቃልሽን* ይላል::
[ሐ]24 የሙት ባሕር ጥቅልል፤ የሰብዓ ሊቃናትና የሱርቱ ትርጕም ከዚህ፤ ጋር ይስማማል የማሰሬቱ ቅጅ ግን *ሦስት ወይፈን* ይላል::
[መ]24 22 ሊትር ያህል ነው::
[ሠ]1 በዚህ ስፍራና በቍጥር 10 ላይ *ቀንድ* የጥንካሬ ምልክት ነው
[ረ]2 ወይም *አንድ* ቅዱስ

1፥16 *ምናምንቴ፤* የዘዳ13፥13 ማብ ይመ::

1፥20 *ሳሙኤል፤* እግዚአብሔር ሰማኝ ማለት ነው::

1፥21 *ዓመታዊ መሥዋዕት፤* የቍ3-4 ማብ ይመ:: *ስእለ ቱን፤* በብሉይ ኪዳን ምስጋና ለማቅረብ ለእግዚአብሔር የተገባ ውን ስእለት መፈጸም የተለመደ የሃይማኖት ሥርዐት ነበረ (ዘሌ 7፥16፤ መዝ 50፥14፤ 56፥12፥66፥13-15፤ 116፥17-18፤ ኢሳ 19፥21):: በዚህም መሠረት ሕልቃና እንደማንኛውም ሰው እግዚ አብሔር እህሉንና ከብቱን እንዲባርክለት ተስሎ፣ ስእለቱ ከደ ረሰለት በኋላ በዓመቱ የቂጣ በዓል ላይ ምስጋና ሊያቀርብ ሳይ መጣ አልቀረም (የቍ 3 ማብ ይመ)::

1፥22 *ጡት ከተወ በኋላ፤* በምሥራቁ ዓለም አንድን ሕፃን ሦስት ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የእናቱን ጡት እንዲጠባ ማድ ረግ የተለመደ ነበር::

1፥23 *ቃሉን፤* እግዚአብሔር ከዚህ በፊት የተናገረው ቃል አልተጠቀሰም፤ ምናልባት ዔሊ በቍ17 ላይ የተናገረውን የሚመ ለከት ሊሆን ይችላል::

1፥26 *በነፍስህ እምላለሁ፤* የተናገሩትን ቃል እውነተኛነት ለማስረገጥ የሚነገር፣ የተለመደ ሐረግ ነው::

2፥1 *ጸለየች፤* የሐና ጸሎት፣ "የጸሎት መዝሙራት" እንደ ሚባሉት እንደ ዳዊት መዝሙራት ሁሉ፣ ለእግዚአብሔር የሚቀ ርብ የውዳሴና የምስጋና መዝሙር ነው (መዝ 72፥20):: የማር ያም የምስጋና ጸሎት (ሉቃ1፥46-55) "የአዲስ ኪዳን የምስጋና ቅኔ" እንደሚባል ሁሉ፣ ይህም ተመሳሳይ በመሆኑ አንዳንድ ጊዜ "የብሉይ ኪዳን የምስጋና ቅኔ" ተብሎ ይጠራል፤ ከዘካርያስ የቡ ራኬ መዝሙር ጋርም የሚመሳሰልበት መንገድ አለው (ሉቃ 1፥67-79):: የሐና የምስጋና መዝሙር በሁለተኛ ሳሙኤል መጨረሻ ላይ በሚገኘው የዳዊት መዝሙር ውስጥ በብዛት ተስተጋብቶአል (2ሳሙ 22):: በዚህ ስፍራና በ2ሳሙ22 ያሉት መዝሙሮች የመጽሐፉን ታሪክ ዋና ሐሳብ ሲያመለክቱ፣ የእግዚ አብሔርን መንገድ በማሳየት ምስጋናና ውዳሴ ላይ ያተኵራሉ:: ሐና በጸሎቷ እስራኤል ስለምትገባበት አዲስ ሕይወትና በልጇ በሳ ሙኤል በኩልም ስለሚመሠረተው ንጉሣዊ አስተዳደር ትንቢት ትናገራለች:: *ልቤ በእግዚአብሔር ጸና፤* የሐና በእግዚአብሔር መደገፍ የተመሠረተው ባገኘችው ልጅ ሳይሆን፣ ጸሎቷን በመለሰላት በእግዚአብሔር ላይ ነው:: *ቀንዴ ... ከፍ ከፍ አለ፤* ከዘዳ 33፥17፤ መዝ 75፥5፥10፤ 92፥10፤112፥9፤ ሉቃ1፥69 ጋር ያነጻጽሩ:: ቀንድ በእግዚአብሔር ከፍ ከፍ ሲል፣ አንድ ሰው ከውርደት ወደ ክብርና ኀይል ተሳልፎአል ማለት ነው::

2፥2 *ከአንተም በስተቀር ሌላ የለም፤* 2ሳሙ 7፥22፤ ዘፀ 4፥39፤ኢሳ45፥6ይመ:: *ዐለት፤* ይህ በዘይቤያዊ አነጋገር የቀረበው ቃል የእስራኤልን አምላክ ብርታትና ጽናት እንዲሁም ምን ጊዜም የማይናወጥ የሕዝቡ አለኝታ መሠረት መሆኑን የሚያመ ለክት ነው:: 2ሳሙ22፥32፤ ዘዳ32፥4፥31፤ መዝ18፥31፤ኢሳ30፥29፤ 44፥8 ይመ::

2፥3 *በመታበይ አትናገሩ፤* የፍናናን፣ (የዔሊን ልጆች፣ የፍልስጥኤማውያንን፣ የሳዖልን፣ የናባልን፣ የጎልያድን፣ የአቤ ሴሎምን፣ የሳሚንና፣ የሳባን) ባሕርይ ያመለክታል:: *እግዚአብሔር*

ከአፋችሁ አይውጣ፤
*እግዚአብሔር* ስምሳክ ዐዋቂ ነውና፤
ሥራም ሁሉ በእርሱ ይመዘናል።

4"የኀያላን ቀስቶች ተሰባብረዋል፤
ደካሞች ግን በኀይል ታጥቀዋል።
5ጠግበው የነበሩ ለእንጀራ ሲሉ ተገዙ፤
ተርበው የነበሩ ግን እንጀራ ጠገቡ፤
መካኒቱ ሰባት ልጆች ወልዳለች፤
ብዙ ወንዶች ልጆች ወልዳ የነበረችው
ግን መከነች።
6"*እግዚአብሔር* ይገድላል፤ ያድናልም፤
ወደ መቃብር[ሸ] ያወርዳል፤ያወጣልም።
7*እግዚአብሔር* ያደኸያል፤ ያበለጽጋልም፤
ያዋርዳል፤ ከፍ ከፍም ያደርጋል።
8እርሱ ድኻውን ከትቢያ ያነሣል፤
ምስኪኑንም ከጕድፍ ከፍ ከፍ ያደርጋል፤
ከመኳንንቱ ጋር ያስቀምጣቸዋል፤
የክብር ዙፋንም ያወርሳቸዋል።

"የምድር መሠረቶች የ*እግዚአብሔር* ናቸውና፣
ዓለምን በእነርሱ ላይ አድርጎአል።
9እርሱ የቅዱሳኑን እግር ይጠብቃል፤
ክፉዎች ግን በጨለማ ውስጥ ይጣላሉ፤

"ሰው በኀይሉ ድል አያደርግም፤
10*ከእግዚአብሔር* ጋር የሚጣሉ ይደቃሉ፤
እርሱ ከሰማይ ያንጐደጕድባቸዋል፤
*እግዚአብሔር* እስከ ምድር ዳርቻ ይፈርዳል።

"ለንጉሡ ኀይልን ይሰጣል፤

2፥4 2ሳሙ1፥27፤ መዝ37፥15፤46፥9፤ 76፥3፤ኢዩ17፥9፤ ኢሳ40፥31፤41፥1፤ 52፥1፤57፥10
2፥5 መዝ113፥9፤ ኢሳ54፥1፤ኤር15፥9፤ ሉቃ1፥53
2፥6 ዘዳ32፥39፤ ኢሳ 26፥19፤ ሕዝ37፥3፡12
2፥7 ዘዳ8፥18፤ ኢዮ 5፥11፤40፥12፤ መዝ 75፥7፤ ኢሳ2፥12፤ 13፥11፤22፥19፤ ዳን4፥37
2፥8 2ሳሙ7፥8፤ 1ነገ16፥2፤ኢዮ15፥7፤ 36፥7፤38፥4፤ መዝ 72፥12፤ 104፥5፤ 107፥41፤113፥7-8፤ 145፥14፤146፥8፤ ምሳ8፥29፤ኢሳ22፥23፤ 40፥12፤ኤር10፥12፤ ሕዝ21፥26፤ ያዕ2፥5
2፥9 1ሳሙ17፥47፤ ኢዮ10፥22፤ መዝ 33፥16-7፤91፥12፤ 121፥3፤ዘዳ18፥316፤ 7፥29-34፤ምሳ2፥8፤ 3፥26፤ኢሳ5፥30፤ 8፥22፤59፥9፤60፥2 ኤር13፥16፤አሞ5፥18፡ 20፤ሰፎ1፥14-15፤ ዘካ4፥6፤ማቴ8፥12 ኢዮ 37፥4፡5፤8፥1፤

*የመሲሑንም* ቀንድ ከፍ ከፍ ያደርጋል።"

11ከዚያ በኋላ ሕልቃና ወደ ቤቱ ወደ ራማ
ሄደ፤ ብላቴናው ግን በካህኑ በዔሊ ፊት
እግዚአብሔርን ያገለግል ነበር።

## የዔሊ ልጆች ክፉ ድርጊት

12የዔሊ ልጆች ምናምንቴዎች ነበሩ፤
*እግዚአብሔርንም* አይፈሩም ነበር። 13በዚ
ያን ጊዜ ካህናቱ ከሕዝቡ ጋር ባላቸው
ግንኙነት የሚፈጽሙት ወግ ነበር፤ ይኸ
ውም ማንም ሰው መሥዋዕት በሚያቀር
ብበት ጊዜ፣ ሥጋው እየተቀቀለ ሳለ የካህኑ
አገልጋይ ሦስት ጣት ያለውን ሜንጦ ይዞ
ይመጣል፤ 14ወደ ድስቱ ወይም ወደ ቶፋው
ወይም ወደ አፍላሉ፣ ወይም ወደ ምንቸቱ
ይሰደዋል። ከዚያም ካህኑ ሜንጦው ያወጣ
ውን ማናቸውንም ሥጋ ለራሱ ይወስደዋል።
ወደ ሴሎ የሚመጡትን እስራኤላውያን ሁሉ
የሚያስተናግዱት በዚህ ዐይነት ነበር። 15ነገር
ግን ሥቡ ገና ከመቃጠሉ በፊት የካህኑ አገ
ልጋይ መጥቶ መሥዋዕት የሚያቀርበውን
ሰው፣ "ካህኑ ጥሬውን እንጂ የተቀቀለውን
ሥጋ ከአንተ ስለማይቀበል፣ ለካህኑ የሚጠ
በስ ሥጋ ስጠኝ" ይለው ነበር።

2፥10 ዘፀ15፥6፤ 19፥16፤ዘዳ33፥17፤1ሳሙ7፥10፤12፥17፤ 2ሳሙ22፥14፤መዝ18፥1፡13፤21፥1፤29፥3፤59፥16፤89፥24፤96፥13፤98፥9፤ኢሳ66፥6፤ማቴ25፥31-32፤ሉቃ1፥69 2፥11 ቍ18፤ዘኍ16፥9፤ ኢሱ18፥25፤ 1ሳሙ3፥1 2፥12 ኤር2፥8፤9፥6 2፥13 ዘሌ7፥35-36፤

ሸ6 ዕብራይስጡ ሲኦል ይላል

*አምላክ ዐዋቂ ነውና፤* 16፥7፤ 1ነገ8፥39፤መዝ139፥1-6 ይመ።

2፥4-5፤ የፍጥረቱ ሁሉ ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ፣ ከተፈጥሮ ሕግ በላይ የሆኑ ድንቅ ሥራዎችን እንደሚሠራ ሐና የለት ተዕለት እይታዋን በማስታወስ የእግዚአብሔርን ታምረኛ ሥራ ትገልጣለች።

2፥5 *ሰባት ልጆች፤* የሩት 4፥15 ማብ ይመ።

2፥6-8፤ የሕይወትና የሞት፣ የብልጽግናና የድኽነት መፈራረቅ የሚወሰነው በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ኀይል መሆኑን ሐና ትናገራለች፤ ይህም እውነታ በሚከተሉት ትረካዎች ተገልጾአል (ዘፀ32፥29፤1ነገ17፥20-24፤2ነገ4፥32-35፤ዮሐ5፥21፤11፥41-44 ይመ)።

2፥6 *መቃብር፤* ሲኦል ማለት ነው፤ የዘፍ37፥35ማብ ይመ።

2፥8 *የምድር መሠረቶች፤* በብሉይ ኪዳን በተለይ ሰዎች የሚኖሩበትን የብስ የሚያመለክት የተለመደ አገላለጽ ነው (ዘፍ 1፥10)፤ ይሁን እንጂ ይህ ሐረግ የፍጥረተ ዓለምን አሠራር ንድፈ ሐሳብ የሚያስተምርም አይደለም (ኢዮ 9፥6፤38፥6፤ መዝ 75፥3፤104፥5፤ ዘካ12፥1 ይመ)።

2፥9 *የቅዱሳኑን፤* ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆኑትን ሰዎች የሚያመለክት ነው። የዕብራይስጡ ቃል እግዚአብሔርንና ሕዝቡን (2ሳሙ22፥26፤መዝ18፥25) በተለይም የርስ በርስ ግንኙነታቸውን የሚያሳይ ነው (መዝ12፥1፡3 2፥6፤ ምሳ12፥8 ይመ)። *እግር ይጠብቃል፤* በጥንቷ እስራኤል አብዛኛውን ጊዜ ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚሄደው በእግር ሲሆን፣ መሬቱም ድንጋያማና አስቸጋሪ ነበረ (መዝ 91፥11-12፡ 121፥3 ይመ)።

2፥10 *ይፈርዳል፤* ፍትሕንና ርትዕን ያስፍናል ማለት ነው (መዝ 96፥13፤ 98፥9 ይመ)።*እስከ ምድር ዳርቻ፤* መንግሥታትንና ሕዝቦችን ሁሉ ማለት ነው (ዘዳ 33፥17፤ ኢሳ45፥22 ይመ)። *ለንጉሡ፤* በዚህ ስፍራ በእስራኤል ስለሚመሠረተው ንጉሣዊ አስተዳደርና ከዳዊት ዘር ስለሚገኘው መሲሕ፣ ሐና በጸሎቷ ትንቢት ተናግራለች (ሉቃ 1፥69)። ትንቢቱም በክርስቶስና በእግዚአብሔር ጠላቶች ላይ ክርስቶስ ባገኘው ፍጹም ድል በመጨረሻ ተፈጻሚነትን አግኝቶአል። *ቀንድ፤* የቍ1 ማብ ይመ። *የመሲሑንም፤* "እግዚአብሔር የቀባው" የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ተጽፎ የምናገኘው እዚህ ቦታ ላይ ነው። ካህናትም እንዲሁ ለእግዚአብሔር ሥራ የተቀቡ ናቸው (ዘፀ28፥41፤ዘሌ4፥3 ይመ)። ንጉሥ ከይሁዳ ነገድ እንደሚወጣ መጀመሪያ በያዕቆብ ተተንብዮአል (ዘፍ49፥10)። ንግሥናውም በበለዓም ንግር ተገልጾአል (ዘኍ 24፥7፡17)። እንዲሁም ሕዝቡ ወደ ተስፋዪቱ ምድር ከገቡ በኋላ፣ እግዚአብሔር የመረጠውን ንጉሥ እንደሚያነግሥላቸው በዘዳ 17፥14-20 ላይ ተጽፎአል። በሁለቱም የሳሙኤል መጻሕፍት ይህን የመሰለ በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚመራ መንግሥት በዳዊት እንደሚመሠረት እናያለን፤ ስለዚህ ሐና፣ በእስራኤል ምድር ስለሚመሠረተው ንጉሣዊ አስተዳደር፣ ምክንያት የሆነውን ልጇን ለእግዚአብሔር ስትሰጥ፣ ስለ ንጉሣዊ አስተዳደር ትንቢት መናገሯ ሙሉ በሙሉ ትክክል ነበር።

2፥11 *ያገለግል ነበር፤* ሊቀ ካህናቱን በአገልግሎት ያግዝ ነበር ማለት ነው። *በእግዚአብሔር ፊት፤* "በእግዚአብሔር ቤት" (1፥24) ማለት ነው።

2፥12 *ምናምንቴዎች፤* የዘፀ 13፥13 ማብ ይመ። *እግዚአብሔርን የማይፈሩ፤* በቀጥታ ሲተረጐም፣ "እግዚአብሔርን አያውቁም" ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን አስተሳሰብ፣ "እግዚአብሔርን ማወቅ" ማለት እንዲሁ በአእምሮ ማወቅ ብቻ ማለት ሳይሆን፣ ከእርሱ ጋር ኅብረት ማድረግና በአንድ ሰው የግል ሕይወት እግዚአብሔር ያለውን መብት መቀበል ማለት ነው። ቃሉ ብዙውን ጊዜ የቃል ኪዳን ትስስር የሚያመለክት ነው (ኤር31፥34፤ሆሴ13፥4 ይመ)።

2፥13-16፤ ከቍ13-14 ያለው በግልጽ እንደሚያመለክተው፣ ሜንጦው ከኅብረት መሥዋዕቱ (ዘሌ7፥31-36፤10፥14-15፤ ዘዳ18፥1-5) ተመጣጣኝ የሆነውን የካህኑን ድርሻ መርጦ ያወጣል ታል ተብሎ የሚታመንበት አሠራር ነበር። ከ15-16 ያሉት ቍጥሮች ታዲያ የዔሊ ልጆች ከላይ የተጠቀሰውን ሕግና ልማድ እንዴት በትዕቢት እንደጣሱት ያሳያሉ።

2፥15 *ስቡ ገና ከመቃጠሉ በፊት፤* በመሠዊያው ላይ የእግዚአብሔር ድርሻ ሆኖ የሚቀበለውን ማለት ነው (ዘሌ3፥16፤4፥10፡ 26፡31፡35፤7፥28፡30-31፤17፥6 ይመ)። *የሚጠበስ፤* በሕጉ መሠረት የካህናቱ ድርሻ ከሚቀቀለው ላይ የሚነሣ ነው (ዘኍ 6፥19-20)። የካህናቱን ድርሻ መጥበስ ሕጉ በየትኛውም ስፍራ አይከለክልም፤ እዚህ ላይ በግልጽ የተጠቀሰው ግን የፋሲካውን በግ አስመልክቶ ነው (ዘፀ12፥8-9፤ዘዳ16፥7)። ይህ ክፍል የካህናቱን ድርሻ መጥበስ ሕጋዊ አይደለም የሚል ይመስላል።

2፥16 *በግድ፤* የካህኑን ድርሻ ማቅረብ በኀይል ሳይሆን

16ሰውየውም፣ “በመጀመሪያ ሥቡ ይቃጠል፤
ከዚያ በኋላ የምትፈልገውን ትወስዳለህ”
ቢለው እንኳ አገልጋዩ፣ “አይሆንም፤ አሁኑኑ
ስጠኝ፤ ያለዚያ በግድ እወስዳለሁ” ይለው
ነበር።
17*ለእግዚአብሔር* የሚቀርበውን *መሥዋዕት*
ይንቁ ስለ ነበር⁺፣ ይህ የወጣቶቹ ኀጢአት
*በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ታላቅ ነበረ።*
18ብላቴናው ሳሙኤል ግን ከበፍታ የተ
ሠራ ኤፉድ ለብሶ *በእግዚአብሔር ፊት* ያገ
ለግል ነበር። 19እናቱም ከባሏ ጋር ዓመ
ታዊ መሥዋዕት ለማቅረብ በምትሄድበት
ጊዜ ሁሉ ትንሽ መደረቢያ እየሠራች ይዛ
ለት ትሄድ ነበር። 20ዔሊም፣ “በጸሎት
ባገኘችውና *ለእግዚአብሔር* በሰጠችው ልጅ
ምትክ *እግዚአብሔር* ከዚህችው ሴት ዘር
ይስጥህ” እያለ ሕልቃናንና ሚስቱን ይመር
ቃቸው ነበር፤ ከዚያ በኋላ ወደ ቤታቸው
ይመለሱ ነበር። 21*እግዚአብሔርም* ሐናን
ባረካት፤ ፀነሰችም፤ ሦስት ወንዶች፣ ሁለት
ሴቶች ልጆችም ወለደች። ብላቴናውም ሳሙ
ኤል *በእግዚአብሔር ፊት* አደገ።
22በዚህ ጊዜ ዔሊ እጅግ አርጅቶ ነበር፤
ልጆቹም በመላው እስራኤል ያደርጉ የነበ
ረውን፣ በመገናኛውም ድንኳን ደጃፍ ከሚ
ያገለግሉ ሴቶች ጋር ዝሙት መፈጸማ
ቸውን ሰማ። 23ስለዚህም እንዲህ አላቸው፤
“ስለምትፈጽሙት ክፉ ድርጊት ከመላው
ሕዝብ እሰማለሁ፤ ለምን እንዲህ ያለ ነገር
ታደርጋላችሁ? 24ልጆቼ ሆይ፤ ትክክል
አይደላችሁም፤ *በእግዚአብሔር* ሕዝብ መካከል
ተሠራጭቶ የምሰማባችሁ ወሬ ጥሩ አይደ
ለም። 25አንድ ሰው ሌላውን ቢበድል፣ እግዚ
አብሔር⁼ ጣልቃ ገብቶ ይፈርዳል፤ ነገር ግን

2፥16 ዘሌ3፥3፡14-16፤ 7፥35-36፤
2፥17 ቍ22:29፤ ዘኍ16፥14፥11፤ኤር 7፥21፤ሕዝ22፥26፤ ሚል2፥7-9
2፥18 ቍ11:28፤ 1ሳሙ22፥18፤23፥9፤ 2ሳሙ6፥14፤ 1ዜና15፥27
2፥19 1ሳሙ 1፥3
2፥20 1ሳሙ 1፥27
2፥21 ዘፍ21፥1፤ መሳ13፥24፤ ሉቃ1፥80፤ 2፥40
2፥22 ቍ17፤ ዘፀ 38፥8
2፥25 ዘዐ4፥21፤ 32፥10፤ዘኍ11፥2፤ ኢሱ11፥20፤1ሳሙ 3፥14፤1ነገ13፥6፤ ኢዮ9፥33፤መዝ 106፥30፤ኢሳ1፥18፤ 22፥14፤ኤር15፥1፤ ዕብ10፥26
2፥26 መሳ13፥24፤ ምሳ3፥4፤ሉቃ2፥5
2፥27 ዘዳ33፥1፤ መሳ13፥6
2፥28 ዘፀ28፥1፤ 30፥7፤ዘሌ7፥35- 36፤1ሳሙ22፥18፤ 23፥6፡9፤30፥7
2፥29 ቍ12-17፤ ዘዳ 12፥5
2፥30 ዘፀ29፥9፤ መዝ50፥23፤91፥15፤ ምሳ8፥17፤ኢሳ53፥3፤ ኤር18፥10፤ናሆ3፥6፤ ሚል2፥9

ሰው *እግዚአብሔርን* ቢበድል፣ ማን ይማል
ድለታል?” ይሁን እንጂ *እግዚአብሔር* ሊያጠ
ፋቸው ስለ ፈለገ፣ ልጆቹ የአባታቸውን ተግ
ሣጽ አልሰሙም።
26ብላቴናውም ሳሙኤል በአካልና በሞገስ
*በእግዚአብሔርና* በሰው ፊት እያደገ ሄደ።

## በዔሊ ቤተ ሰብ ላይ የተነገረ ትንቢት

27በዚህ ጊዜ አንድ የእግዚአብሔር ሰው ወደ
ዔሊ መጥቶ እንዲህ አለው፤ “*እግዚአብሔር*
እንዲህ ይላል፤ ‘የአባትህ ቤት በግብፅ ምድር
በፈርዖን እጅ በነበረ ጊዜ ራሴን ገለጥሁ
ለት? 28የእኔ ካህን እንዲሆን፣ ወደ መሠ
ዊያዬ እንዲወጣ፣ ዕጣን እንዲያጥን፣
በፊቴም ኤፉድ እንዲለብስ ከእስራኤል
ነገዶች ሁሉ አባትህን መረጥሁት። ደግ
ሞም እስራኤላውያን በእሳት የሚያቀር
ቡትን ቍርባን ሁሉ ለአባትህ ቤት
ሰጠሁ። 29ታዲያ በማደሪያዬ እንዲቀርብ
ያዘዝሁትን መሥዋዕትና ቍርባን የናቃ
ችሁ ለምንድን ነው? አንተና ልጆችህ ሕዝቤ
እስራኤል ካቀረበው ቍርባን ሁሉ ምርጥ
ምርጡን በልታችሁ ራሳችሁን በማወፈር
ከእኔ ይልቅ ልጆችህን የምታከብራቸው ስለ
ምንድን ነው?”
30“ስለዚህ የእስራኤል አምላክ *እግዚአብ
ሔር* እንዲህ ይላል፤ ‘ቤትህና የአባትህ ቤት
በፊቴ ለዘላለም ያገለግሉኝ ዘንድ ተስፋ
ሰጥቼ ነበር፤’ አሁን ግን *እግዚአብሔር* እን
ዲህ ይላል፤ ‘ይህን ከእንግዲህ አላደርገውም፤

⁺17 ወይም የሚንቁ ሰዎች ስለነበሩ።
⁼25 ወይም መሳፍንት

በበጎ ፈቃድ ለአምልኮ በሚመጡ ሰዎች የሚፈጸም ተግባር ነው (ዘሌ 7፥28-36፤ዘዳ18፥3 ይመ)።

2፥18 *ሳሙኤል ግን፤* ጸሐፊው ከ 2፥11-4፥1 ባለው ክፍል የሳሙኤልንና የዔሊን ልጆች ጠባይና አድራጎት በዝርዝር እያነጻጸረ ያቀርባል። *ከበፍታ የተሠራ ኤፉድ፤* እግዚአብሔርን በቤተ መቅደሱ የሚያገለግሉት ካህናት የሚለብሱት ልብስ ተክህኖ ነው (22፥18፤ 2ሳሙ6፥14 ይመ)። ወጥ ሆኖ የተሰፋና ረጅም እጅጌ የሌለው ልብስ ሲሆን፣ ሊቀ ካህናቱ ከሚለብሰው ኤፉድ የተለየ ነው (የቍ 28 ማብ ይመ፤ ከዘፀ39፥1-26 ጋር ያነጻጽሩ)።

2፥19 *ዓመታዊ መሥዋዕት፤* የ1፥3 ማብ ይመ። *ትንሽ መደረቢያ፤* ጕልበት ላይ የሚደርስ እጅጌ የሌለው ልብስ ሲሆን፣ ከውስጥ ልብስ በላይ ከኤፉድ ሥር የሚለበስ ነው (15፥27፤ 18፥4 ይመ)።

2፥22 *በመገናኛውም ድንኳን ደጃፍ ከሚያገለግሉ ሴቶች ጋር ዝሙት መፈጸማቸውን፤* ዘፀ38፥8 ይመ። እንደ እነዚህ ዐይነቶቹን ሴቶች በሚመለከት እዚህ ላይ እንጂ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሌላ ስፍራ ላይ አናገኝም። ምናልባት ሴቶቹ ያከናውኑ የነበረው የጽዳት ሥራና የመሳሰለውን አነስተኛ ሥራ ሊሆን ይችላል፤ ይህ ግን በሙሴ መጻሕፍት ከተጠቀሰው የሌዋውያን አገልግሎት ጋር ፈጽሞ ሊገናኝ አይችልም (ዘኍ1፥50፤3፥6-8፤8፥15፤16፥9፤18፥2-3)። ይህ አስጸያፊ የዔሊ ልጆች ድርጊት ከነዓናውያን በቤተ ጣዖቶቻቸው ‘ዘርን የማፍራት ሥርዐት’ በሚል የሚፈጽሙትን የሚያመለክት ነው (1ነገ14፥24፤ 15፥12፤ 22፥46 ይመ)። ይህም ልማድ እግዚአብሔርን መድፈርና ቤቱንም ማርከስ እንደ ሆነ በሕጉ ተጽፎአል (ዘዳ23፥17-18)።

2፥23 *እንዲህ አላቸው፤* ዔሊ ልጆቹን ገሥጻቸው እንጂ ከአገልግሎቱ አላገደቻቸውም፤ እግዚአብሔር ግን አስወገዳቸው።

2፥25 *እግዚአብሔር፤* ዔሊ በዚህ ላይ የሚናገረው፣ አንድ ሰው ሌላውን ሰው ቢበድል፣ ሦስተኛ ሰው በመካከል ገብቶ ጕዳዩን ሊመለከትና ሊፈርድ እንደሚችል ነው። ሰው እግዚአብሔርን ቢበድል ግን ማን ሊቆምለት ይችላል? ተበዳዩም፣ ፈራጁም እግዚአብሔር ስለ ሆነ ጕዳዩ እጅግ አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል ይገልጻል። *እግዚአብሔር ሊያጠፋቸው ስለ ፈለገ፤* ጸሐፊው ይህን ሐሳብ ሲገልጽ የዔሊን ልጆች ለመደገፍ ሳይሆን፣ የአባታቸው የዔሊ ተግሣጽ የተሰነዘረው እጅግ ዘግይቶ እንደ ነበር ለማመልከት ነው። የዔሊም ልጆች በክፉ ድርጊታቸው ቀጠሉበት፤ እግዚአብሔርም በእነርሱ ላይ ፍርዱን አጸና (ቍ34፡ ኢሱ11፥20 ይመ)።

2፥26 *እያደገ፤* በእግዚአብሔርና በሰውም ፊት ሞገስ እያገኘ ሄደ፤ ከሉቃ2፥52 ጋር ያነጻጽሩ።

2፥27 *የእግዚአብሔር ሰው፤* አብዛኛውን ጊዜ ነቢያት ተለይተው የሚጠሩበት ስም ነው (9፥6፡10፤ዘዳ33፥1፤ ኢሱ 14፥6፤ 1ነገ13፥1፡6-8፡17፥18፡24፤2ነገ4፥7ይመ)። *የአባትህ ቤት፤* የአሮንን ዘሮች የሚመለከት ነው።

2፥28 *የእኔ ካህን እንዲሆን፤* ሦስት የካህናት ሥራዎች ተገልጸዋል፤ እነርሱም (1) *ወደ መሠዊያዬ እንዲወጣ፤* በቤተ መቅደሱ አደባባይ የሚቃጠለውን መሥዋዕት ማቅረብ ነው። (2) *ዕጣን እንዲያጥን፤* በቅዱስ ቦታ ዕጣን ማጠን ነው። (3) *ኤፉድ እንዲለብስ፤* የቍ18 ማብ ይመ። እዚህ ላይ የተገለጸው ሊቀ ካህኑ የሚለብሰውን የተለየ ኤፉድ ለማመልከት ነው (ዘፀ28፥4-13 ይመ)። ኡሪምንና ቱሚምን የያዘውም የደረት ኪስ በሊቀ ካህናቱ ኤፉድ ላይ ይደረባል፤ ኡሪምና ቱሚም ሊቀ ካህኑ መለኮታዊ በሆነ መንገድ ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኝበት ሲሆን፣ የሚቀመጠውም በሊቀ ካህናቱ ልዩ ግምጃ ቤት ነው (ዘፀ28፥30 እና ማብ ይመ፤ 1ሳሙ23፥9-12፤30፥7-8ይመ)።

2፥30 *ተስፋ ሰጥቼ ነበር፤* ዘፀ29፥9፤ዘሌ8፥9፤ዘኍ16-17፤ 25፥13 ይመ። *ይህን ከእንግዲህ አላደርገውም፤* ይህ ማለት እግዚአብሔር ለአሮን ቤት የሰጠውን ክህነት ተስፋ ሰርዞ

የሚያከብሩኝን አከብራለሁ፤ የሚንቁኝም
ፈጽሞ ይናቃሉ። 31እነሆ፤ በዘርህ ሽማግሌ
እንዳይገኝ ያንተን ኀይልና የአባትህን ቤተ
ሰብ ኀይል የምሰብርበት ጊዜ ይመጣል፤ 32በ
ማደሪያዬም መከራ ታያለህ፤ ምንም እንኳ
ለእስራኤል በጎ ነገር ቢደረግም፣ በቤተ
ሰብህ ውስጥ ሽማግሌ ፈጽሞ አይገኝም።
33ከመሠዊያዬ የማላስወግዳቸው ዘሮችህ በሕ
ይወት የሚተርፉትም ዐይኖችህን በእንባ ለማ
ፍዘዝ፣ ልብህን በሐዘን ለማደንዘዝ ብቻ
ነው፣ ሌሎቹ ዘሮችህ ግን በሙሉ በለጋነታ
ቸው ባጭር ይቀጫሉ።
34"በሁለቱ ልጆችህ በአፍኒንና በፊንሐስ
ላይ የሚደርሰው ላንተ ምልክት ይሆንሃል፣
ሁለቱም በአንድ ቀን ይሞታሉ። 35እንደ
ልቤና እንደ አሳቤ የሚያገለግል የታመነ
ካህን ለራሴ አስነሣለሁ፤ ቤቱን አጽንቼ አቆ
ማለሁ፣ እርሱም በቀባሁት ፊት ለዘላለም
ያገለግላል። 36ከዘሮችህም መካከል የተ
ረፈው ማንኛውም ሰው፣ ለአንዲት ጥሬ
ብርና ለቍራሽ እንጀራ ሲል በፊቱ
ወድቆ ይሰግዳል፤ 'የዕለት ጕርሴን እንዳ
ገኝ እባክህ በማንኛውም የክህነት ሥራ
ላይ መድበኝ' በማለት ይለምናል።"'

## *እግዚአብሔር ሳሙኤልን ጠራው*

3 ብላቴናው ሳሙኤል ከዔሊ በታች ሆኖ
*እግዚአብሔርን* ያገለግል ነበር። በዚ
ያም ዘመን *የእግዚአብሔር* ቃል ብርቅ
ነበረ፤ ራእይም አይታይም ነበር።
2ዐይኖቹ ከመድከማቸው የተነሣ ማየት
የተሳነው ዔሊ አንድ ሌሊት በስፍራው
ተኝቶ ነበር። 3ሳሙኤልም ደግሞ የእግዚ
አብሔር ታቦት ባለበት፣ *በእግዚአብሔር*
ቤተ መቅደስ+ ውስጥ ተኝቶ ነበር፤ የእግ
ዚአብሔር መብራትም ገና አልጠፋም ነበር።
4*እግዚአብሔርም* ሳሙኤልን ጠራው፤
ሳሙኤልም፣ "እነሆኝ" አለ፤
5ወደ ዔሊም ሮጦ በመሄድ፣ "እነሆኝ የጠ
ራኸኝ" አለው።
ዔሊ ግን፣ "እኔ አልተጣራሁም፤ ተመልሰህ
ተኛ" አለው፤ እርሱም ሄዶ ተኛ።
6ደግሞም *እግዚአብሔር*፣ "ሳሙኤል!"
ብሎ ጠራው።
ሳሙኤልም ተነሥና ወደ ዔሊ ሄዶ፣ "እነ
ሆኝ የጠራኸኝ" አለው።
ዔሊም መልሶ፣ "ልጄ ሆይ፤ እኔ አልተጣራ
ሁም፤ ተመልሰህ ተኛ" አለው።
7በዚያም ጊዜ ሳሙኤል *እግዚአብሔ
ርን* ገና አላወቀም ነበር፤ *የእግዚአብሔርም*
ቃል ገና አልተገለጠለትም ነበር።
8*እግዚአብሔር* ሳሙኤልን ለሦስተኛ
ጊዜ ጠራው፤ አሁንም ሳሙኤል ተነሥቶ
ወደ ዔሊ በመሄድ፣ "እነሆኝ የጠራኸኝ" አለው።
ዔሊ በዚህ ጊዜ ብላቴናውን ይጠራ የነ
በረው *እግዚአብሔር* መሆኑን ተረዳ። 9በዚያ
ጊዜ ዔሊ ሳሙኤልን፣ "ሂድና ተኛ፤ ከእንግዲህ
ቢጠራህ ግን፣ '*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ባሪያህ
ይሰማልና ተናገር' በል" አለው። ስለዚህም

+3 የማደሪያው ድንኳን ነው

2፥31 1ሳሙ4፥11-18፤
22፥16
2፥32 1ሳሙ4፥3፤
22፥17-20፤
1ነገ 2፥26-27፤
ኤር 7፥12፡14
2፥33 ኤር29፥32፤
ሚል2፥12
2፥34 ዘዳ13፥2፤
1ሳሙ 4፥11፤
1ነገ13፥3
2፥35 1ሳሙ9፥16፤
10፥1፤16፥13፤
2ሳሙ 2፥4፤8፥17፤
12፥7፤20፥25፤
23፥1፤1ነገ
1፥8፡32፡34፤2፥35፤
4፥4፤1ዜና16፥39፤
29፥22፤መዝ89፥20፤
ሕዝ 44፥15-16
2፥36 1ሳሙ3፥12፤
1ነገ2፥27፤
ሕዝ 44፥10-14
3፥1 1ሳሙ2፥11፤
መዝ74፥9ሰቆ2፥9፤
ሕዝ7፥26፤አሞ 8፥11
3፥2 ዘፍ27፥1፤
1ሳሙ4፥15
3፥3 ዘፀ25፥31-38፤
ዘሌ24፥1-4፤
ዘዳ10፥ 1-5፤
1ሳሙ1፥9፤
1ነገ 6፥19፤8፥1
3፥4 ዘፍ22፥1፤
ዘፀ3፥4
3፥7 ሥራ2፥6፤
1ሳሙ2፥12፤
ኤር1፥2፤አሞ3፥7

ታል፤ ወይም ከኀጢአታቸው የተነሣ ዔሊና ቤተ ሰቡ ከተነገረው በረከት ተካፋይ አይሆኑም ማለት አይደለም። *የሚያከብሩኝን አከብራለሁ፤* ቍ 29 ይመ። መንፈሳዊ ጥቅሞች ኀላፊነትንና ግዴታን ይጠይቃሉ፤ እነዚህም እንደማይደፈር መብት ሊታዩ አይገባቸውም (2ሳሙ 22፥26-27)።

2፥31 *በዘርህ ሽማግሌ እንዳይገኝ፤* ልጆቹ በመሞታቸው (4፥11)፣ ዘሮቹ በኖብ ላይ በሳኦል በመደምሰሳቸው (22፥18-19) እና አብያታር ከክህነት አገልግሎቱ በመወገዱ ምክንያት (1ነገ2፥26-27)። የዔሊ ክህነታዊ ቤተሰብ የሚጠፋ መሆኑን የሚተነብይ ነው። *ኀይል፤* በቁሙ "ክንድ" ማለት ነው። የዔሊ ክንድና የሚያገለግሉም የቤተሰቡ ክንድ ይሰበራል (ከ2ሳሙ 22፥35) ጋር ያነጻጽሩ።

2፥32 *በማደሪያዬም መከራ ታያለህ፤* ይህም የታቦቱን በፍልስጥኤማውያን መማረክ (4፥1-10)፣ የሴሎን መጥፋት (ኤር 7፥14 እንዲሁም ማደሪያው ወደ ኖብ (21፥1-6፤ የ21፥1 ማብ ይመ) መወሰዱን ያካትታል።

2፥33 ዳዊት ከሞተ በኋላ አዶንያስን ለማንገሥ ሞክሮ ያልተሳካለትንና በኋላም ከአገልግሎቱ በሰሎሞን የተባረረውን ካህኑን አብያታርን በተመለከተ የተጠቀሰ ነው (1ነገ2፥26-27)።

2፥34 *ላንተ ምልክት፤* የአፍኒንና የፊንሐስ ሞት አስቀድሞ በእነርሱ ላይ የተናገረውን ትንቢት (4፥11) የሚያስረግጥ ነው፤ እንዲህ ዐይነቱ ትንቢት ተነግሮ መፈጸሙ የተለመደ ነበር (10፥7-9፤ 1ነገ13፥3፤ ኤር28፥15-17፤ ሉቃ1፥18-20 ይመ)።

2፥35 *የታመነ ካህን ለራሴ አስነሣለሁ፤* ይህ ቃል መጀመሪያ በዳዊት ዘመን ካህን ሆኖ (2ሳሙ 8፥17፤ 15፥24፡35፤ 20፥25) በመጨረሻም በሰሎሞን ዘመን አብያታርን በመተካት ሊቀ ካህን ሆኖ ባገለገለው በሳዶቅ (1ነገ2፥35፤1ዜና29፥22 ይመ) ተፈጽሞአል። *ቤቱን አጽንቼ አቆማለሁ፤* በቁሙ "የታመነ ቤት እሠራለታለሁ" ማለት ነው። የታመነ ሊቀ ካህን "የታመነ" ዘላቂ የካህን ቤተ ሰብ ይኖረዋል (ስለ ዳዊት መንግሥት በተመሳሳይ መንገድ የተነገረውን (25፥28 እና 2ሳሙ7፥16፤ 1ነገ11፥38 ይመ)። የሳዶቅ ቤተ ሰብ በልጁ በአዛርያስ ቀጥሎአል (1ነገ4፥1 ይመ)፤ ከምርኮ መልስም የሳዶቅ ቤተ ሰብ አገልግሎቱን ይመራ ነበር (1ዜና6፥14-15፤ዕዝ3፥2 ይመ)። በሁለቱ ኪዳኖች መካከል ያለውም ዘመን ማለትም በራብዓዊው አንጥያኮስ ኤጲፋንስ ዘመን (175-164 ዓ.ም) ይህ የሳዶቅ ቤተ ሰብ በክህነት ያገለግል ነበር። *በቀባሁት፤* ዳዊትንና ዘሮቹን የሚያመለክት ነው (የቍ 10 ማብ ይመ)።

3፥1 *ብላቴናው ሳሙኤል፤* 2፥11፡18 ይመ። በዚህ ጊዜ ሳሙኤል ሕፃን ልጅ አይደለም (2፥21፡26 ይመ)። አይሁዳዊው የታሪክ ጸሓፊ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን፣ ሳሙኤል በዚህ ጊዜ ዕድሜው ዐሥራ ሁለት ዓመት እንደ ነበር ገልጾአል፤ ይሁን እንጂ ዕድሜው ከዚህም ሊበልጥ ይችላል። *የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ ነበር፤* ምሳ29፥18፤ አሞ8፥11 ይመ። በመሳፍንት ዘመን ሁሉ በ2፥27-36 ላይ ከተጠቀሰው ነቢይ ሌላ ሁለት ነቢያት (መሳ 4፥4፡6፥8) እና አምስት ራእዮች (መሳ2፥1-3፤6፥11-23፤ 7፥2-11፤10፥11-14፤13፥3-21) ብቻ እንደ ነበሩ ይታወቃል። ምና ልባትም 2ዜና 15፥3 ስለዚህ ዘመን ሳይናገር አይቀርም። *ራእይ፤* ከዘፍ15፥1 ጋር ያነጻጽሩ።

3፥3 *የእግዚአብሔር መብራትም ገና አልጠፋም ነበር፤* ይህ መብራት በተቀደሰው ስፍራ ገጸ ኅብስቱ ከሚቀመጥበት ጠረጴዛ አንጻር ያለው የወርቅ መቅረዝ ነው (ዘፀ25፥31-40)። *ጊዜው ገና ሌሊት ነው፤* መብራቱ ሊጠፋ ጭልጭል የሚለው ወይም ጨርሶ የሚጠፋው ሊነጋጋ ሲል ነበር (ዘፀ27፥20-21፤ 30፥7-8፤ ዘሌ24፥3-4፤ 2ዜና13፥11፤ ምሳ31፥18 ይመ)። ከንጋት በፊት መብራቱን ማጥፋት በሙሴ ሕግ መሠረት የተከለከለ ነበር። *መቅደስ፤* ማደሪያ ማለት ነው፤ የ1፥9 ማብ ይመ።

3፥6 *ዔሊም መልሶ፤* ሳሙኤልን እግዚአብሔር የጠራው መሆኑን ዔሊ ወዲያውኑ ማወቅ አለመቻሉ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት ደካማ መሆኑን ያሳያል።

3፥7 *እግዚአብሔርን ገና አላወቀም ነበር፤* ሳሙኤል ከእግዚአብሔር በቀጥታ ራእይ የመቀበል ልምምድ (ዘፀ 1፥8) አልነበረውም።

ሳሙኤል ወደ ስፍራው ተመልሶ ተኛ።
10እግዚአብሔርም መጥቶ በዚያ ቆመ፤
ቀደም ሲል እንዳደረገው ሁሉ "ሳሙኤል!
ሳሙኤል!" ብሎ ጠራው። ሳሙኤልም፣ "ባሪ
ያህ ይሰማልና ተናገር" አለ።
11እግዚአብሔርም ሳሙኤልን እንዲህ አለው፤
"እነሆ፤ የሰሚውን ሁሉ ጆሮ ጭው የሚያ
ደርግ አንድ ነገር በእስራኤል ላይ አደርጋ
ለሁ። 12በዚያም ቀን ከመጀመሪያ እስከ
መጨረሻ በዔሊና በቤተ ሰቡ ላይ የተናገር
ሁትን ሁሉ እፈጽማለሁ። 13ዔሊ በሚያው
ቀው ኀጢአት ምክንያት በቤተ ሰቡ ላይ
ለዘላለም እንደምፈርድ ነግሬው ነበር ልጆቹ
አስጸያፊ ነገር አድርገዋል*፤ እርሱ ግን
አልከለከላቸውም። 14ስለዚህ 'የዔሊ ቤት
በደል በመሥዋዕትም ሆነ በቍርባን ፈጽሞ
አይሰረይም' ብዬ በዔሊ ቤት ላይ ምያ
ለሁ።"
15ሳሙኤል እስኪነጋ ድረስ ተኛ፤ ከዚያም
ተነሥቶ የእግዚአብሔርን ቤት በሮች ከፈተ፤
ራእዩንም ለዔሊ መንገር ፈራ፤ 16ዔሊ ግን
ሳሙኤልን፣ "ልጄ ሳሙኤል ሆይ" ሲል
ጠራው።
ሳሙኤልም፣ "እነሆኝ" ሲል መለሰ።
17ዔሊም፣ "እግዚአብሔር የነገረህ ነገር ምን
ድነው? አትደብቀኝ፤ ከነገረህ ውስጥ አንዲቱን
እንኳ ብትደብቀኝ እግዚአብሔር እንደዚያው
ያድርግብህ፤ ከዚያ ለከፋም ይዳርግህ" አለው።
18ስለዚህ ሳሙኤል ምንም ነገር ሳይደብቅ
ሁሉንም ነገረው። ዔሊም፣ "እርሱ እግዚ
አብሔር ነው፤ መልካም መስሎ የታየውን
ያድርግ" አለ።
19ሳሙኤል እያደገ ሄደ፤ እግዚአብሔ
ርም ከእርሱ ጋር ስለ ነበረ፣ ከሚናገረው
ቃል አንዳች በምድር አይወድቅም ነበር።
20ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ያሉ እስራኤላውያን
በሙሉ ሳሙኤል በእርግጥ የእግዚአብሔር
ነቢይ መሆኑን ዐወቁ። 21እግዚአብሔር
በሴሎ ይገለጥ ነበር፤ በዚያም በቃሉ አማ
ካይነት ራሱን ለሳሙኤል ገለጠ።

4 የሳሙኤልም ቃል ወደ እስራኤል ሁሉ
ደረሰ።

## ታቦቱ በፍልስጥኤማውያን ተማረከ

በዚያ ዘመን እስራኤላውያን ፍልስጥኤማ
ውያንን ሊወጉ ወጡ፤ እስራኤላውያን በአ
ቤንኤዘር፣ ፍልስጥኤማውያን ደግሞ በአፌቅ
ሰፈሩ። 2ፍልስጥኤማውያን እስራኤልን ለመ
ግጠም ሰራዊታቸውን አሰለፉ፤ ጦርነቱ
እንደ ተፋፋመም፣ እስራኤላውያን በፍል
ስጥኤማውያን ተሸነፉ፤ በጦርነቱም ላይ
አራት ሺህ ያህል እስራኤላውያን ተገ
ደሉ። 3ሰራዊቱ ወደ ሰፈር በተመለሰ ጊዜ
የእስራኤል አለቆች፣ ዛሬ እግዚአብሔር
በፍልስጥኤማውያን እንድንሸነፍ ያደረገን
ለምንድን ነው? አብሮን እንዲወጣ፣ ከጠላ
ቶቻችንም እጅ እንዲያድነን የእግዚአብሔ
ርን የኪዳኑን ታቦት ከሴሎ እናምጣ" አሉ።
4ስለዚህ ሕዝቡ ሰዎችን ወደ ሴሎ ልከው፣

3፥10 ዘፀ3፥4
3፥11 2ነገ21፥12፤ ኢዮ15፥21፤ኤር19፥3
3፥12 1ሳሙ2፥27-36
3፥13 1ነገ1፥6
3፥14 1ሳሙ2፥25
3፥17 ሩት 1፥17፤ 1ነገ22፥14፤ኤር 23፥28፤38፥14፤ 42፥4
3፥18 መሳ10፥15
3፥19 ዘፍ21፥22፤ ዘኍ14፥43፤ መሳ13፥24፤ 1ሳሙ9፥6
3፥20 ዘዳ18፥22፤ መሳ20፥1፤ ሕዝ33፥33
3፥21 ዘኍ 12፥6
4፥1 ኢሱ12፥18፤ 1ሳሙ5፥1፤29፥2፤ 1ነገ20፥26
4፥3 ኢሱ6፥7፤7፥7፤ 18፥1፤1ሳሙ2፥32፤ 2 ዜና13፥8
4፥4 ዘፍ3፥24፤ ዘፀ25፥22

*13 የማሶሬቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ነገር ግን ጥንታዊው የዕብራይስጡ ጸሐፍት ትውፊት እንዲሁም የሰብዓ ሊቃናት፣ ልጆቹ እግዚአብሔርን ተዳፍረዋል ይላል።

3፥11-14፤ እግዚአብሔር ለሳሙኤል በመጀመሪያ የተናገረው ቃል፣ "የእግዚአብሔር ሰው" አስቀድሞ ለዔሊ የተናገረውን ነበር (2፥27-36)፤ ይህ እንግዲህ ወጣቱ ሳሙኤል የእግዚአብሔርን ቃል በእርግጥ መቀበሉን የሚያረጋግጥ ነው።

3፥13 *አስጸያፊ፤* አማራጭ ትርጕሙንና ዘሌ 24፥14 ይመ።

3፥15 *የእግዚአብሔርን ቤት በሮች፤* የ1፥9 ማብ ይመ። የማደሪያው ድንኳን ራሱ በር አልነበረውም፤ ይህ የሚያመለክተው ዙሪያውን የተጋረደበትን ሊሆን ይችላል (የቍ11-14 ማብ ይመ)።

3፥17 *እግዚአብሔር እንደዚያው ያድርግብህ፤ ከዚያ ለከፋም ይዳርግህ፤* እርግማን ነው (14፥44፤ 20፥13፤ 25፥22፤ 2ሳሙ3፥9:35፤ 19፥13፤ ሩት1፥17፤ 1ነገ2፥23፤ 2ነገ6፥31 ይመ)። ብዙውን ጊዜ አንድ ሰው እንዲህ ዐይነቱን ርግማን የሚናገረው በራሱ ላይ ነው፤ እዚህ ላይ ግን እግዚአብሔር ለእርሱ ከተናገረው አንዳች ደብቆ ቢያስቀርበት ዔሊ ሳሙኤልን ሲረግመው እናገኛለን (የ14፥24 ማብ ይመ)።

3፥18 *መልካም መስሎ የታየውን ያድርግ፤* ፍርዱ ትክክለኛ መሆኑን በማመን ዔሊ በእግዚአብሔር ፊት ራሱን ዝቅ አደረገ (ዘፀ34፥5-7 ይመ)።

3፥19 *ከሚናገረው ቃል አንዳች በምድር አይወድቅም ነበር፤* ሳሙኤል የተናገረው ቃል ሁሉ እርግጠኛ ሆኖ ስለ ተገኘ፣ የእግዚአብሔርን ቃል የሚናገር የተከበረ ነቢይ ሆነ (ቍ20-21 ይመ)።

3፥20 *ከዳን እስከ ቤርሳቤህ፤* በመጽሐፈ ሳሙኤል፣ በነገሥትና በዜና መዋዕል መጻሕፍት መላውን የእስራኤልን ምድር የሚያመለክት አገላለጽ ነው። ዳን ሰሜናዊውን ጫፍ ሲያመለክት፣ ቤርሳቤህ ደግሞ ደቡባዊውን ጫፍ ያመለክታል።

3፥21 *በሴሎ፤* ይህ ሁኔታ በም 4-6 ከሚገኙት ታሪካዊ ክሥተቶች በኋላ አልቀጠለም (ኤር7፥ 12-14:26፥6 ይመ)።

4፥1 *የሳሙኤልም ቃል ወደ እስራኤል ሁሉ ደረሰ፤* ከ3፥1 ጋር ያነጻጽሩ። *አቤንኤዘር፤* ማለት "የርዳታ ድንጋይ" ማለት ነው። ትክክለኛ ቦታው ባይታወቅም ከአፌቅ በስተ ምሥራቅ በቅርብ ርቀት ላይ (ቍ6 ይመ) እንደሚገኝ ይገመታል፤ ነገር ግን እስራኤላውያን በፍልስጥኤማውያን ላይ ያገኙትን ድል ለማክበር በምጽጳና በሲን መካከል (7፥12ይመ) ሳሙኤል አቤንኤዘር ብሎ በኋላ የተከለው ድንጋይ አይደለም። *በአፌቅ፤* በባሕር ጠረፍ ላይ ከምትገኘው ከኢዮጴ ከተማ በስተ ሰሜን ምሥራቅ ዐሥራ ዘጠኝ ኪሎ ሜትር ያህል የምትርቅ ከተማ ናት። ፍልስጥኤማውያን እስከዚህ ስፍራ ድረስ መዝለቃቸው፣ በመካከለኛው የከነዓን ምድር የሰፈሩትን እስራኤላውያንን ለመቈጣጠር ሙከራ ማድረጋቸውን ያመለክታል (ቍ9፤ መሳ15፥11ይመ)።

4፥3 *ዛሬ እግዚአብሔር ... እንድንሸነፍ ያደረገን ለምንድን ነው?* የተሸነፉበት ምክንያት ፍልስጥኤማውያን በጦር ኀይል ስለበለጧቸው ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ደስ ስላልተሰኘባቸው እንደ ሆነ የእስራኤል ሽማግሌዎች ተገንዝበዋል። ጣዖት የሚያመልኩ ጎረቤቶቻቸውም በጦርነት ድልን የሚሰጡ አማልክት መሆናቸውን እንደዚሁ ያምናሉ። *አብሮን እንዲወጣ፣ ... እንዲያድነን፤* የእስራኤል ሽማግሌዎች ከፍልስጥኤማውያን ጋር በሚዋጉበት ጊዜ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር መሆኑን ለማረጋገጥ ታቦቱ እንዲመጣላቸው መልእክተኞች ላኩ። በታቦቱና በእግዚአብሔር ህልዎት ከሕዝቡ ጋር መሆን መካከል ግንኙነት እንዳለ ማሰባቸው ትክክል ነበር (ከቍ4ጋር ያነጻጽሩ)። በቀድሞው የእስራኤል ታሪክ በተመዘገቡ ታላላቅ ድሎች ወቅትም ታቦቱ ከእነርሱ ጋር እንደ ነበር የሚያስታውሱ ለመሆናቸው ጥርጥር የለውም (ዘኍ10፥33-36፤ ኢሱ3፥3፤11:14-17፤6፥6:12-20 ይመ)፤ እግዚአብሔር በፈለገ ጊዜ በወደደው ቦታ ሊገኝ የሚችል መሆኑን በማመን ፈንታ ታቦቱ በተገኘበት ቦታ ብቻ እንደሚገኝ፣ ታቦቱ ከሌለም እግዚአብሔር በዚያ ሊገኝ እንደማይችል በማሰባቸው ትልቅ ስሕተት ፈጽመዋል። በዚህም ምስሉ ባለበት ቦታ አምላክም እዚያው ይገኛል፤ ርዳታውም ወዲያውኑ ይደርሳል የሚለውን የአረማውያንን አስተሳሰብ አንጸባርቀዋል።

በኪሩቤል መካከል በዙፋኑ ላይ የተቀ
መጠውን የሰራዊት ጌታ የእግዚአብሔርን
የኪዳን ታቦት አስመጡ፤ ሁለቱ የዔሊ
ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ ከኪዳኑ ታቦት
ጋር በዚያ ነበሩ።
5የእግዚአብሔር የኪዳኑ ታቦት ወደ
ሰፈር በገባ ጊዜ፣ ምድሪቱ እስክትናወጥ
ድረስ እስራኤላውያን ሁሉ ታላቅ የደስታ
ጩኸት አሰሙ። 6ፍልስጥኤማውያንም ይህን
ታላቅ ጩኸት ሲሰሙ፣ "በዕብራውያን ሰፈር
የምንሰማው ይህ ሁሉ ጩኸት ምንድ
ነው?" ሲሉ ጠየቁ።
የእግዚአብሔር ታቦት ወደ ሰር
መምጣቱን በተረዱ ጊዜ 7ፍልስጥኤማው
ያንም ፈርተው እንዲህ አሉ፤ "አምላክ ወደ
ሰፈሩ መጥቶአል፤ ወዮልን! እንዲህ ዐይ
ነት ነገር ገጥሞን አያውቅም። 8ወዮልን!
ከእነዚህ ኀያላን አማልክት እጅ ማን ያድ
ነናል? ግብፃውያንን በምድረ በዳ በልዩ
ልዩ መቅሠፍት የመቱ እነዚሁ አማልክት
ናቸው፤ 9ፍልስጥኤማውያን ሆይ፤ በርቱ!
ወንድነታችሁም ይታይ፤ ያለዚያ ባሪያ
እንዳደረጋችኋቸው ሁሉ፣ ዕብራውያን እና
ንተን መልሰው ባሪያ ያደርጓችኋል። ወን
ድነታችሁ ይታይ፤ ተዋጉ!"
10ስለዚህ ፍልስጥኤማውያን ተዋጉ፤ እስ
ራኤላውያንም ስለ ተሸነፉ እያንዳንዱ
ወደየድንኳኑ ሸሸ። ታላቅ እልቂት ሆነ፤
ከእስራኤልም ሠላሳ ሺህ እግረኛ ወታ
ድሮች ወደቁ። 11የእግዚአብሔር ታቦት
ተማረከ፤ ሁለቱም የዔሊ ልጆች አፍኒንና
ፊንሐስ ተገደሉ።

### የዔሊ መሞት

12በዚያች ዕለት አንድ ብንያማዊ ልብ
ሱን ቀዶ፣ በራሱም ላይ ትቢያ ነስንሶ፣
ከጦሩ ሜዳ እየበረረ ወደ ሴሎ መጣ።

4፥5 ኢሱ 6፥5:10
4፥6 ዘፍ 14:13
4፥7 ዘፀ 15፥14
4፥8 ዘፀ12፥30፤
1ሳሙ-5፥12፤
ራእ11፥6
4፥9 መሳ13፥1
4፥10 ዘዳ 28፥25
4፥11 መዝ78፥64፤
ኤር7፥12
4፥12 ኢሱ7፥6፤
2ሳሙ-1፥2፤
ሕዝ 24፥26፥33፥21

4፥13 ቍ-18
4፥15 1ሳሙ-3፥2
4፥17 1ሳሙ-22፥18፤
መዝ78፥61:64
4፥18 መሳ2፥16፤
16፥31፤1ሳሙ- 2፥31

13እዚያ እንደ ደረሰም፣ ዔሊ ስለ እግዚ
አብሔር ታቦት ልቡ ስለ ተጨነቀ፣ በመን
ገድ ዳር ወንበሩ ላይ ተቀምጦ ይጠባበቅ
ነበር። ሰውየውም ወደ ከተማው ገብቶ
የሆነውን ሁሉ ባወራ ጊዜ፣ ከተማው ሁሉ
በጩኸት ተናወጠ።
14ዔሊም ጩኸቱን በሰማ ጊዜ፣ "የምን
ጩኸት ነው?" ሲል ጠየቀ።
ሰውየውም ፈጥኖ መጣና ለዔሊ ነገረው፤
15ዔሊ የዘጠና ስምንት ዓመት ሽማግሌ ስለ
ነበር ዐይኖቹ ደክመው ማየት ተስኖአቸው
ነበር። 16ሰውየውም ዔሊን፣ "ከጦሩ ሜዳ ገና
አሁን መምጣቴ ነው፤ ከጦርነቱ አምልጬ
የወጣሁትም ዛሬ ውኑ ነው" ብሎ ነገረው።
ዔሊም፣ "ልጄ ሆይ፤ ታዲያ እንዴት
ሆነ?" ሲል ጠየቀ።
17ወሬውን ያመጣውም ሰው፣ "እስራኤል
ከፍልስጥኤማውያን ፊት ሸሸ፤ ሰራዊቱም
ከፍተኛ እልቂት ደርሶበታል፤ እንዲሁም
ሁለቱ ልጆችህ አፍኒንና ፊንሐስ ሞተዋል፤
የእግዚአብሔርም የኪዳኑ ታቦት ተማርኮአል"
ብሎ መለሰለት።
18ሰውየው ስለእግዚአብሔር ታቦት በተናገረ
ጊዜ፣ ዔሊ በቅጥሩ በር አጠገብ ከተቀመጠበት
ወንበር ላይ በጀርባው ወደቀ፤ እር ሱም
ያረጀና ሰውነቱም የሚከብድ ስለ ነበር፣ ዐ
ንገቱ ተሰብሮ ሞተ። እርሱም ለአ ርባ ዓ
መት በእስራኤል ላይ ፈራጅ ነበር።
19በዚያን ጊዜ ምራቱ የፊንሐስ ሚስት፣
ነፍሰ ጡር ነበረች፤ የምትወልድበትም ጊዜ
ተቃርቦ ነበር፣ የእግዚአብሔርን ታቦት መማ
ረክ፣ የዐማቷንና የባሏንም መሞት በሰ
ማች ጊዜ ምጡ ስለ ጠናባት ተንበርክካ
ወለደች። 20ለመሞትም በምታጣጥርበት
ጊዜ፣ በአጠገቧ የነበሩት ሴቶች፣ "አይዞሽ፤
ወንድ ልጅ ወልደሻልና በርቺ" አሏት።

18 ወይም እስራኤል መርቶ ነበር

4፥4 *በኪሩቤል መካከል በዙፋኑ ላይ የተቀመጠውን የሰራዊትን ጌታ የእግዚአብሔርን የኪዳን ታቦት፤* በቃል ኪዳኑ ታቦት የሥርየት መክደኛ ላይ ሁለቱን ክንፎቻቸውን ወደ ላይ የዘረጉ ከወርቅ የተሠሩ ኪሩቤል ነበሩ (ዘፀ 25፥17-22 ይመ)፤ በሁለቱም ኪሩቤል መካከል ያለው ባዶ ስፍራ፣ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል መገኘቱን በተለየ መንገድ ይገልጻል፤ ስለዚህ የስርየት መክደኛው የእስራኤል መለኮታዊ ንጉሥ ዙፋን መሆኑ ይታወቃል (2ሳሙ-6፥2፤ መዝ 80፥1:99፥1 ይመ)። ዕብ 4፥6፤ የዘፍ 14፥13 ማብ ይመ።

4፥7 *አምላክ ወደ ሰፈራቸው መጥቶአል፤* ፍልስጥኤማውያንም የእስራኤልን አምላክ፣ ከሚገለጥበት ከታቦቱ ጋር አንድ አድርገው ቈጠሩት (የቍ3 ማብ ይመ )።

4፥8 *ኀያላን አማልክት፤* ፍልስጥኤማውያን ብዙ አማልክትን ስለሚያመልኩ፣ በብዙ ቍጥር የተጠቀሙት ከዚህ የተነሣ ነው። *ግብፃውያንን...መቅሠፍት፤* የ6፥6 ማብ ይመ።

4፥11 *የእግዚአብሔር ታቦት ተማረከ፤* ይህ ሐረግ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በተለያየ መንገድ አምስት ጊዜ ተጠቅሶአል። ቍ17:19፥21-22፤ ይህም የትረካው ማዕከላዊ ሐሳብ ሲሆን፣ በዚህ አስደንጋጭ ሁኔታ በ3፥11 ላይ የተጠቀሰው የእግዚአብሔር ቃል ወዲያውኑ ተፈጻሚነትን አግኝቶአል። *አፍኒንና ፊንሐስ ተገደሉ፤* በ2፥34፤ 3፥12 ላይ የተጠቀሰው ቃል ተፈጸመ።

4፥12 *ልብሱን ቀዶ፣ በራሱም ላይ ትቢያ ነስንሶ፤* የሐዘንና የጭንቀት ምልክት ሲሆን፣ መልእክተኛው መጥፎ ወሬ ይዞ የመጣ መሆኑን ያመለክታል (2ሳሙ 1፥2:13፥19:15፥32 ይመ)።

4፥13 *ስለ እግዚአብሔር ታቦት ልቡ ስለተጨቀ፤* ዔሊ የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ጦር ሜዳ በድፍረት የመወሰዱ እርምጃ ያስከተለውን አደጋ ለማወቅ ዔሊ መንፈሳዊ ስሜት እንደ ነበረው ያሳያል። ከልጆቹ ይልቅ ለእግዚአብሔር ታቦት የተጨነቀ ይመስላል።

4፥18 *ዔሊ ... ሞተ፤* ኢያሱና አብረውት ያገለግሉ የነበሩ ሽማግሌዎች ከሞቱ በኋላ የተጀመረው የመሳፍንት ዘመን በዔሊ ሞት ተደመደመ (ኢሱ24፥29-31)። የእስራኤልን ሕዝብ ወይም ልጆቹን ከክፉ መንገዳቸው ሊመልስ ያልቻለው፣ በዕድሜ ብዛት የታወረውና የደከመው ሽማግሌ ካህን፣ አሁን በአሳዛኝ ሁኔታ ወደ ፍጻሜ ለተቃረበው የስሕተት ዘመን ተስማሚ ምልክት ሆነ። ለዚህ መጽሐፍ ትረካ ዐቢይ ትኵረት ለሆነው ለዳዊት አገዛዝም ትኵረትን የሚስብ ንጽጽር ለመሆን ቻለ። *ሰውነቱም የሚከብድ፤* የዔሊ ውድቀት ለምን በድንገተኛ ሞት እንዳበቃ ለመግለጽ ብቻ ሳይሆን፣ ሞቱን አስቀድሞ ከተሰጠው ፍርድ ጋር ለማያያዝም የሚረዳ መጠነኛ መረጃ በ2፥29 ላይ ይመ። *እርሱም ለአርባ ዓመ በእስራኤል ላይ ፈራጅ ነበር፤* በዚህ ስፍራ ላይ ከእርሱ በፊት ከኖሩት ከኢያሱና ከሽማግሌዎች ሞት በኋላ በእስራኤል ላይ ገዥ ሆነው ከሚቈጠሩት መሳፍንት ዔሊ የመጨረሻው እንደ ነበርና ከእርሱ ዘመንም በኋላ ንጉሣዊ አስተዳደር በእስራኤል እንደ ተጀመረ እንመለከታለን (2ሳሙ-7፥11፤ መሳ2፥16-19፤ሩት 1፥1ይመ)። አርባው ዓመት የዔሊ የአመራር ዘመን፣ ዮፍታሔ (ስድስት ዓመት)፣ ኢብጻን (ሰባት ዓመት)፣ ኤሎምን (ዐሥር ዓመት)፣ ዓብዶን (ስምንት ዓመት) እንዲሁም ሳምሶን (ሃያ ዓመት) እስራኤልን ከመሩበት ዘመን የበለጠ ነበር (መሳ12፥7-14፤ 13-16 ይመ)።

እርሷ ግን መልስ አልሰጠችም፤ ልብ ብላም
አላጻመጠችም።
21 የእግዚአብሔር ታቦት ስለ ተማረከ፣
ዐማቷና ባሏም ስለ ሞቱ፣ "ክብር ከእስ
ራኤል ተለይቶአል" ስትል የሕፃኑን ስም
ኢካቦድ' አለችው። 22 ከዚያም፣ "የእግዚአ
ብሔር ታቦት ተማርኮአልና ክብር ከእስራ
ኤል ተለይቶአል" አለች።

## ታቦቱ ወደ አሽዶድና ወደ አቃሮን ተወሰደ

5 ፍልስጥኤማውያን የእግዚአብሔርን ታቦት
ከማረኩ በኋላ፣ ከአቤንኤዘር ወደ አሽ
ዶድ ወሰዱት። 2 ከዚያም ወደ ዳጎን ቤተ
ጣዖት አግብተው፣ በዳጎን አጠገብ አኖሩት።
3 የአሽዶድም ሰዎች በማግስቱ ማለዳ ተነሥ
ተው ሲመለከቱ እነሆ፣ ዳጎን በእግዚአብሔር
ታቦት ፊት፣ መሬት ላይ በግንባሩ ተደፍቶ
አገኙት። ከዚያም አንሥተው ወደ ቦታው
መለሱት። 4 በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ተነሥ
ተው ሲመለከቱ፣ ዳጎን *በእግዚአብሔር*
ታቦት ፊት፣ መሬት ላይ በግንባሩ ተደፍቶ
ነበር፤ ራሱና እጆቹ ተሰባብረው በደጃፉ ላይ
የወደቁ ሲሆን፣ የቀረው ሌላው አካሉ ብቻ
ነበር። 5 የዳጎን ካህናትም ሆኑ ሌሎች
በአሽዶድ ወዳለው የዳጎን ቤተ ጣዖት የሚ
ገቡ ሁሉ እስከ ዛሬ ድረስ እግራቸው ደጃ
ፉን እንዳይረግጥ ተራምደው የሚያልፉት
በዚሁ ምክንያት ነው።
6 *የእግዚአብሔር* እጅ በአሽዶድ ሕዝብና
በአካባቢዋ ላይ ጠነከረ፤ እርሱም ጥፋት
አመጣባቸው፤ በዕባጭም መታቸው᷾። 7 የአ
ሽዶድ ሰዎች ይህን ባዩ ጊዜ፣ "እጁ በእ
ኛና በአምላካችን በዳጎን ላይ ጠንክሮአልና
የእስራኤል አምላክ ታቦት በእኛ ዘንድ መቈ
የት የለበትም" አሉ። 8 ስለዚህ በኋላ የፍልስ
ጥኤማውያንን ገዦች በሙሉ ጠርተው፣
"የእስራኤልን አምላክ ታቦት ምን እናድር
ገው?" ሲሉ ጠየቁ።
እነርሱም፣ "የእስራኤልን አምላክ ታቦት
ወደ ጌት ውሰዱት" አሏቸው። ስለዚህ የእስራ
ኤልን አምላክ ታቦት ወሰዱት።
9 ነገር ግን ታቦቱን ወደዚያ ከወሰዱት
በኋላ *የእግዚአብሔር* እጅ በከተማዪቱ
ላይ ሆነ፤ ታላቅ መሸበርም አመጣባቸው፤
ሕፃን ሽማግሌ ሳይል ሕዝቡን በዕባጭ
መታ^። 10 ስለዚህ የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ
አቃሮን ሰደዱት።
የእግዚአብሔር ታቦት እዚያ ሲገባም፣
የአቃሮን ሕዝብ፣ "የእስራኤልን አምላክ
ታቦት ያመጡብን እኛንና ሕዝባችንን ለማ
ስፈጀት ነው" በማለት ጮኹ። 11 የእግዚአብ
ሔር እጅ በርትቶባቸው ስለ ነበር፣ ሞት
ከተማዪቱን እጅግ አስደንግጦአት ነበ
ርና ሕዝቡ የፍልስጥኤማውያንን ገዦች
በሙሉ ጠርተው፣ "የእስራኤልን አምላክ
ታቦት ከዚህ አርቁልን፤ ወደ ገዛ ስፍራው
ይመለስ፤ ያለዚያ እኛንም ሕዝባችንንም ይፈ
ጃል" አሉ። 12 ያልሞቱትን ደግሞ ዕባጩ ያሠ
ቃያቸው ስለ ነበር፣ የከተማዪቱ ጩኸት
እስከ ሰማይ ወጣ።

4፥21 ዘፍ35፥18፤ ዘፀ24፥16፤ መዝ106፥20፤ ኤር2፥11፤ ሕዝ 1፥28፤ 9፥3፤10፥18
4፥22 ዘፀ24፥16፤ መዝ78፥61፤ ኤር7፥12
5፥1 ኢያ11፥22፤ 13፥3፤1ሳሙ 4፥1
5፥2 መሳ16፥23፤ ኢሳ2፥18፤19፥1፤ 46፥1
5፥3 ኢሳ40፥20፤ 41፥7፤46፥7፤ ኤር10፥4
5፥4 ሕዝ 6፥6፤ ሚክ 1፥7
5፥5 ሶፎ1፥9
5፥6 ዘፀ 9፥3፤ 15፥26፤1ሳሙ 6፥5፤ 2ሳሙ 6፥7፤ መዝ 78፥66፤ ሐሥ13፥11
5፥8 ኢያ11፥22፤ መሳ16፥18
5፥9 ዘፀ14፥24
5፥10 ኢያ 13፥3
5፥11 ቍ 8
5፥12 1ሳሙ 4፥8

'21 *ኢካቦድ ማለት ክብር የለም ማለት ነው።*
᷾6 *ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናት የሱልጊት ትርጒም ግን በምድራቸው ላይ ዐይጥ መታየት ጀመረ፤እንዲሁም ሞትና ጥፋት በከተማዪቱ ዙሪያ ነበር* ይላል።
^9 ወይም *ብልታቸውን አሳበጠባቸው*

4፥21 ***ክብር ከእስራኤል ተለይቶአል፤*** የእስራኤል ክብር የእስራኤል አምላክ እንጂ ታቦቱ አይደለም፤ የታቦቱም አለመኖር እግዚአብሔር ሕዝቡን ተለይቶአል ማለት አይደለም፤ ታቦቱ እግዚአብሔርን አይወስነውምና (ኤር3፥16-17)። ይሁን እንጂ የታቦቱ መማረክ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ያለውን ግንኙነት አሻክሮታል፤ ታቦቱን ወደ ጦር ሜዳ በመውሰድ ፈቃዳቸውን እንዲፈጽምላቸው እግዚአብሔርን የማስገደድ ኀይል እንደነበራቸው በማሰብ የፈጸሙት ስሕተት ከባድ መሆኑንም አሳይቶአል።

5፥1 ***አሽዶድ፤*** ከኢየሩሳሌም በስተ ምዕራብ አምሳ ስድስት ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ የምትገኝ ከአምስቱ የፍልስጥኤም ዋና ዋና ከተሞች አንዷ ናት (ኢያ13፥3)።

5፥2 ***ዳጎን፤*** በከነዓናውያን ሥነ ተረት ዳጎን የኤል ልጅ ወይም ወንድም እንዲሁም የበዓል አባት ነው። ዳጎን የፍልስጥኤማውያን ዋና አምላክ ነው፤ በጋዛ ባሉ (መሳ16፥ 21፡23፡26)፣ በአሽዶድ እና እዚህ ላይ እንደ ተመለከተው በቤትሻን (31፥10-12፤ 1ዜና10፥10) ባሉ ቤተ ጣዖታት ይመለክ ነበር። የዚህ ጣዖት አምልኮ በጥንቱ ዓለም ማለት ከመስጴጦምያ እስከ አራም ከዚያም እስከ ከነዓን ድረስ ባሉት አገሮች፣ ከ3000 ዓ.ቅ.ክ እስከ መቃብያን ዘመን ድረስ በከፍተኛ ደረጃ ተስፋፍቶ እንደ ነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሆኑ አንዳንድ ምንጮች ይተርካሉ። ዳጎን በምን ዐይነት ሁኔታ ይመለክ እንደ ነበር የታወቀ ነገር የለም። አንዳንዶች የዓሣ አምላክ ነው ይላሉ፤ በቅርብ የተገኙ ማስረጃዎች ደግሞ የማዕበል ወይም የእህል አምላክ መሆኑን ይናገራሉ። ዳጎን የሚለው ስም፣ "እህል" ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር ይቀራረባል።

5፥3 ***ዳጎን ... መሬት ላይ በግንባሩ ተደፍቶ አገኙት፤*** ታቦቱ ከዳጎን ምስል አጠገብ ተቀምጦ ነበር። ፍልስጥኤማውያን ይህን ያደረጉት ዳጎን ከእስራኤል አምላክ በላይ መሆኑን ለማሳየት ነበር። ይሁን እንጂ ዳጎን በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በግንባሩ ሲደፋ፣ የፍልስጥኤማውያን አስተሳሰብ ተለወጠ።

5፥5 ***እስከ ዛሬ፤*** ሁለቱ የሳሙኤል መጻሕፍት የተጻፉበትን ጊዜ ለማመልከት ነው (መግቢያውን ይመ)። ***ደጃፉን እንዳይረግጥ፤*** የበሩ ደጃፍ ተሰባብሮ ከወደቀው የዳጎን ምስል ጋር ከመነካካቱ የተነሣ ልዩ ኀይል ይኖረዋል ተብሎ ይታሰብ ነበር። ሶፎ1፥9 አጠቃላይ የሆነውንና "የበር ደጃፍ የመናፍስት ማደሪያ ነው"፣ የሚለውን እጅግ የተስፋፋ አረማዊ አስተሳሰብ የሚገልጥ ክፍል ነው።

5፥6 ***የእግዚአብሔር እጅ ... ጠነከረ፤*** የተሰበረው የዳጎን እጅ መሬት ላይ ተጋድሞአል (ቍ4)፤ እግዚአብሔር ግን በአሽዶድ ሕዝብና በአካባቢው ላይ (ቍ9፥11) መቅሠፍትን (የ6፥4 ማብ ይመ) በማምጣት እውነተኛውን ነገርና የክንዱን ብርታት አሳየ። የገዛ ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንደፈለገው ሊመራው አይችልም (የ4፥3 ማብ ይመ)፤ ፍልስጥኤማውያንም በእስራኤል ላይ ያገኙት ድልና ታቦቱን መማረካቸው፣ አምላካቸው በእስራኤል አምላክ ላይ የበላይነት አለው ብለው እንዲያስቡ አልፈቀደላቸውም።

5፥8 ***ገዦች፤*** አምስቱን የፍልስጥኤም ዋና ዋና ከተማ አለቆች ለማመልከት ነው (6፥16፤ኢያ13፥3፤መሳ3፥3 ይመ)። ***የእስራኤልን አምላክ ታቦት ወደ ጌት ውሰዱት፤*** የፍልስጥኤም መሪዎች ታቦቱ አሽዶድ በመሄዱ ምክንያት ችግር ስለ መድረሱ ቀደም ሲል የሚያውቁት ነገር አልነበረም፤ ችግሩ በአጋጣሚ የደረሰ መስሎ ታይቶአቸዋል (6፥9 ይመ)። ስለዚህ ታቦቱ ወደ ጌት እንዲወሰድ ያደረጉት፣ በአሽዶድ የተፈጸመው ሁሉ በአጋጣሚ ከሆነ፣ በዚያም ሌላ የሙከራ ዕድል እንዲኖር ነው።

5፥10 ***አቃሮን፤*** ከአምስቱ የፍልስጥኤም ዋና ዋና ከተሞች አንዱ ሲሆን ፣በስተ ሰሜን ያለና ወደ እስራኤላውያን ግዛት ቀረብ የሚል፣ ከአሽዶድም በስተ ሰሜን ምሥራቅ ዐሥራ ሰባት ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ የሚገኝ ከተማ ነው።

5፥11 ***የእስራኤልን አምላክ ታቦት...አርቁልን፤*** ፍልስጥኤማውያን በሦስቱ ከተማዎቻቸው ላይ በደረሰው ተደጋጋሚ መቅሠፍትና ታቦቱ በደረሰበት ስፍራ ሁሉ ጭንቀት በመፈጠሩ፣ ከእስራኤል አምላክ ኀያልነት የተነሣ ለመሆኑ መጠነኛ ጥርጣሬ

## የታቦቱ ወደ እስራኤል መመለስ

**6** *የእግዚአብሔር* ታቦት በፍልስጥኤማው
ያን ግዛት ሰባት ወር ቈየ:: 2ፍልስጥኤ
ማውያን ካህናትንና ጠንቋዮችን ጠርተው፣
"*የእግዚአብሔርን* ታቦት ምን እናድርገው?
ወደ ስፍራው እንዴት መመለስ እንደሚገ
ባን ንገሩን" አሏቸው::
3እነርሱም፣ "የእስራኤልን አምላክ ታቦት
የምትመልሱ ከሆነ ከበደል መሥዋዕት ጋር
ስደዱት እንጂ ባዶውን አትስደዱት፤ በዚያ
ጊዜ ትፈወሳላችሁ፤ እጁም ከእናንተ ላይ
ለምን እንዳልተነሣ ታውቃላችሁ" አሏ
ቸው::
4ፍልስጥኤማውያንም፣ "የምንልከው የበ
ደል መሥዋዕት ምን መሆን አለበት?" ሲሉ
ጠየቁ::
እነርሱም እንዲህ ሲሉ መለሱ፤ "እናን
ተንም ሆነ አለቆቻችሁን የመታው መቅ
ሠፍት አንድ ዐይነት በመሆኑ፣ በፍል
ስጥኤማውያን ገዦች ቍጥር ልክ አም
ስት የወርቅ ዕባጭና አምስት የወርቅ
ዐይጦች ላኩ:: 5አገሩን በማጥፋት ላይ
ባሉት ዕባጮችና ዐይጦች ዐይነት ምስ
ሎችን ሥርታችሁ፤ ለእስራኤል አምላክ
ክብር ስጡ:: ይህን ካደረጋችሁ እጁን ከእ
ናንተ፣ ከአማልክታችሁና ከምድራችሁ
ላይ ያነሣ ይሆናል:: 6እንደ ግብፃውያንና
እንደ ፈርዖን ልባችሁን የምታደነድኑት
ለምንድን ነው? እነርሱም እስራኤላውያንን
የለቀቋቸው እግዚአብሔር በጽኑ ከቀጣቸው
በኋላ አይደለምን?
7"ስለዚህ አዲስ ሠረገላና ቀንበር ያል
ተጫነባቸው ሁለት የሚያጠቡ ላሞች አዘ
ጋጁ:: ላሞቹን በሠረገላው ጥመዷቸው፤
እንቦሶቻቸውን ግን ወደ ቤት መልሷቸው::
8*የእግዚአብሔርን* ታቦት ወስዳችሁ በሠ
ረገላው ላይ አኑሩ፤ በታቦቱም አጠገብ
ባለው ሣጥን ውስጥ ለበደል መሥዋዕት
የምትልኩትን የወርቅ ምስሎች አስቀምጡ፤
በፈለገውም መንገድ እንዲሄድ ልቀቁት፤
9ነገር ግን ወዴት እንደሚሄድ ተመልከቱ፤

6፥2 ዘፀ7፥11፤ ኢሳ44፥25
6፥3 ቍ9፤ ዘፀ 22፥29፤34፥20፤ ዘሌ5፥15
6፥4 ኢሱ13፥3፤ 2ሳሙ24፥25
6፥5 ኢሱ7፥19፤ 1ሳሙ5፥6፤ራእ14፥7
6፥6 ዘፀ4፥21፤ 10፥2፤12፥33
6፥7 ዘኍ19፥2፤ 2ሳሙ6፥3፤ 1ዜና13፥7
6፥9 ኢሱ15፥10፤ 21፥16
6፥13 ዘፍ30፥14፤ ሩት2፥23፤ 1ሳሙ12፥17
6፥14 1ሳሙ11፥7፤ 2ሳሙ 24፥22፤ 1ነገ19፥21
6፥15 ቍ18፤ ኢሱ3፥3፤21፥16
6፥17 ኢሱ13፥3

ወደ ቤትሳሚስ አቅጣጫ ወደ ገዛ አገሩ
የሚሄድ ከሆነ፣ ይህን ታላቅ መከራ ያመጣ
ብን *እግዚአብሔር* ነው:: ወደዚያ ካልሄደ
ግን፣ መከራው በአጋጣሚ የደረሰብን እንጂ
የእርሱ እጅ እንዳልመታን እናውቃለን::"
10እነርሱም እንደዚሁ አደረጉ:: ሁለ
ቱን ላሞች ወስደው በሠረገላው ጠመዷ
ቸው፤ እንቦሶቻቸውንም በቤት ውስጥ
ዘጉባቸው:: 11*የእግዚአብሔርንም* ታቦት፣
የወርቁን ዐይጦችና የዕባጮቹን ምስ
ሎች በሠረገላው ላይ ጫኑ:: 12ከዚያም
ላሞቹ መንገዳቸውን ይዘው እምቧ! እምቧ!
እያሉ ቀጥ ብለው ወደ ቤትሳሚስ አመሩ::
የፍልስጥኤም ገዦችም እስከ ቤትሳሚስ
ድንበር ተከተሏቸው::
13በዚህ ጊዜ የቤትሳሚስ ሰዎች በሸ
ለቆው ውስጥ ስንዴአቸውን ያጭዱ
ነበር፤ ቀና ብለው ሲመለከቱም ታቦቱን
በማየታቸው በጣም ደስ አላቸው:: 14ሠረገ
ላውም ወደ ቤትሳሚስ ወደ ኢያሱ ዕርሻ
መጥቶ በአንድ ትልቅ ቋጥኝ አጠገብ
ቆመ:: ሕዝቡም የሠረገላውን ዕንጨት
ፈልጠው፣ ሁለቱን ላሞች የሚቃጠል
መሥዋዕት አድርገው *ለእግዚአብሔር* አቀ
ረቡ:: 15ሌዋውያኑም *የእግዚአብሔርን* ታቦት፣
የወርቅ ዕቃዎቹን ከያዘው ሣጥን ጋር አው
ርደው በትልቁ ድንጋይ ላይ አኖሩ:: በዚያ
ችም ዕለት የቤትሳሚስ ሕዝብ *ለእግዚአ
ብሔር* የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረቡ፤
መሥዋዕቶችንም ሠዉ: 16አምስቱ የፍልስጥ
ኤም ገዦችም ይህን ሁሉ ካዩ በኋላ በዚ
ያኑ ዕለት ወደ አቃሮን ተመለሱ::
17ፍልስጥኤማውያን ስለ በደል መሥዋዕት
*ለእግዚአብሔር* የላኳቸው የወርቅ ዕባጮች
አንዱ ስለ አሽዶድ፣ አንዱ ስለ ጋዛ፣ አንዱ
ስለ አስቀሎና፣ አንዱ ስለ ጌትና አንዱ ስለ
አቃሮን የቀረቡ ናቸው፤ 18የወርቅ ዐይጦቹም
ቍጥር፣ አምስቱ የፍልስጥኤም ገዦች
በሚያስተዳድሯቸው የተመሸጉ ከተሞችና
ከእነዚህ ውጭ ባሉት መንደሮቻቸው ቍጥር
ልክ ነው:: በቤትሳሚሳዊው በኢያሱ ዕርሻ

ሳያድርባቸው አልቀረም::

6፥2፤ ስለ ሃይማኖት ለየት ያለ ዕውቀት ያላቸው፣ የአማልክቶቻቸውን ካህናትና ሟርተኞቻቸውን በጥንቈላ የተደበቀን ነገር የሚያውቁና የሚተረጕሙ ሰዎች ምክር እንዲሰጡ ተጠይቀዋል (ዘዳ18፥10፤ኢሳ2፥6፤ሕዝ21፥21 ይመ)::

6፥3 *ከበደል መሥዋዕት፤* ካህናቶቻቸውና ሟርተኞቻቸው ታቦቱ ከስጦታ ጋር መመለስ እንዳለበት ሐሳብ አቀረቡ፤ ስጦታንም አብረው የሚልኩት ታቦቱን ከእስራኤል መውሰዳቸው በደል መሆኑን በማመንና የእግዚአብሔርንም ክብር ስለ ተዳፈሩ ካሳ እንዲሆናቸው ነው (ቍ5):: በእስራኤል ስለሚቀርበው የበደል መሥዋዕት ዘሌ5፥14-6፥7 ይመ::

6፥4 *አምስት የወርቅ እባጮችና፤* እነዚህ ከወርቅ የተሠሩ ምስሎች የመቅሠፍቱን ሁኔታ የሚያመለክቱ ናቸው (5፥6 ይመ):: *አምስት የወርቅ ዐይጦች፤* ከበሽታ ጋር የዐይጥ መንጋ ለጥፋት ተልኮ ነበር (ቍ5):: ከወርቅ የተሠሩት የዐይጥ ምስሎች መቅሠፍቱን የሚያመለክቱ ሲሆኑ፣ በሽታውን ያስተላለፉት ዐይጦች እንደ ሆኑ መገመት ይቻላል::

6፥5 *ዐይነት ምስሎችን ሥርታችሁ፣ ለእስራኤል አምላክ ክብር ስጡ፤* ከወርቅ የተሠሩት ምስሎች መቅሠፍቱና ዐይጦቹ፣ ከእስራኤል አምላክ የታዘዙ መሆናቸውን ያመለክታል (የቍ3 ማብ ይመ)::

6፥6 *እንደ ግብፃውያንና እንደ ፈርዖን፤* እግዚአብሔር በግብፃውያን ላይ ያወረደው መዓትና እስራኤላውያን ከግብፅ ሲወጡ ያደረጋቸው ታምራት፣ በአካባቢው ሕዝብ ዘንድ አድናቆት አስከትለዋል (4፥8፤ ኢሱ2፥10 ይመ)::

6፥7 *ቀንበር ያልተጫነባቸው፤* ጋሪ ለመጐተት ያልሠለጠኑትን ለማለት ነው:: *እንቦሶቻቸውን ግን ወደ ቤት መልሷቸው፤* ላሞች የሚጠቡ ጥጆቻቸው ተነጥቀው እንዲለዩአቸው አይፈልጉም::

6፥9 *ቤትሳሚስ፤* በፍልስጥኤማውያን ድንበር ላይ የምትገኝ የይሁዳ ከተማ ናት (ኢሱ15፥10 ይመ):: የስሟ ትርጕም "የፀሓይ አማላክ ማደሪያ ወይም ቤት" ማለት ነው::

6፥13 *ስንዴአቸውን ያጭዱ ነበር፤* ስንዴ የሚታጨድበት ወቅት ከሚያዝያ እስከ ሰኔ አጋማሽ ባለው ጊዜ ነው::

6፥14-15 የታቦቱ ጕዞ ቤትሳሚስ ሲደርስ መቋረጡ፣ በጕዞው ላይ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳለበት ያመለክታል፤ ምክንያቱም እስራኤላውያን ከነዓንን ድል አድርገው በያዙ ጊዜ፣ ይህ ስፍራ ለካህናት ርስት እንዲሆን የተሰጠ ነበር (ኢሱ21፥13-16 ይመ)::

ውስጥ የእግዚአብሔርን ታቦት ያስቀመጡ
በት ያ ትልቅ ድንጋይ እስከ ዛሬ ምስክር
ነው።
19ነገር ግን እግዚአብሔር ከቤትሳሚስ ሰዎች
ጥቂቱን መታ፤ ወደ እግዚአብሔር ታቦት
ውስጥ ተመልክተዋልና ከመካከላቸው ሰባ[ሀ]
ሰዎችን ገደለ፤ እግዚአብሔር እጅግ ስለ
መታቸውም ሕዝቡ አለቀሰ። 20የቤትሳሚስም
ሰዎች፣ "ታዲያ በዚህ ቅዱስ አምላክ በእግዚ
አብሔር ፊት ማን መቆም ይችላል? ታቦቱስ
ከዚህ ወጥቶ ወደ ማን ይሂድ?" አሉ።
21ከዚያም ወደ ቂርያትይዓሪም ሰዎች
መልእክተኞች ልከው፣ "ፍልስጥኤማውያን
የእግዚአብሔርን ታቦት መልሰውልናል፤ ውረ
ዱና ይዛችሁ ወደ ስፍራችሁ ውጡ" አሏ
ቸው።

7 የቂርያትይዓሪም ሰዎችም መጥተው የእ
ግዚአብሔርን ታቦት ይዘው ወጡ፤ ከዚ
ያም በኰረብታው ላይ ወዳለው ወደ አሚና
ዳብ ቤት ወሰዱት። የእግዚአብሔርን ታቦት
እንዲጠብቅም ልጁን አልዓዛርን ቀደሱት።

### የፍልስጥኤማውያን መሸነፍ

2ታቦቱ በቂርያትይዓሪም ከተቀመጠ ረዥም
ጊዜ ሆነው፤ በአጠቃላይ ሃያ ዓመት ቈየ።
የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ አዘነ፤ እግዚአብሔ
ርንም ፈለገ። 3ሳሙኤልም የእስራኤልን
ቤት ሁሉ፣ "በፍጹም ልባችሁ ወደ እግዚአ
ብሔር የምትመለሱ ከሆነ፣ ሌሎችን አማል
ክትና አስታሮትን ከመካከላችሁ አስወ
ግዱ፤ ራሳችሁንም ለእግዚአብሔር አሳል
ፋችሁ ስጡ፤ እርሱንም ብቻ አምልኩ፤ እር
ሱም ከፍልስጥኤማውያን እጅ ይታደጋች
ኋል።" አላቸው። 4ስለዚህ እስራኤላውያን
የበአልንና የአስታሮትን አማልክት አስወ
ግደው፣ እግዚአብሔርን ብቻ አመለኩ።
5ከዚያ በኋላ ሳሙኤል፣ "እስራኤልን ሁሉ
በምጽጳ ሰብስቡ፤ እኔም ስለ እናንተ ወደ
እግዚአብሔር እጸልያለሁ" አለ። 6እስራኤላ
ውያን በምጽጳ በተሰበሰቡ ጊዜ፣ ውሃ ቀድ
ተው በእግዚአብሔር ፊት አፈሰሱ፤ በዚ
ያች ዕለት ጾሙ፤ በዚያም "እግዚአብሔርን
በድለናል" ብለው ተናዘዙ። ሳሙኤልም
በምጽጳ እስራኤልን ይፈርድ ነበር።
7እስራኤል በምጽጳ መሰብሰባቸውን ፍልስ
ጥኤማውያን በሰሙ ጊዜ፣ የፍልስጥኤማው
ያን ገዦች ሊወጓቸው ወጡ፤ እስራኤላ
ውያንም ይህን ሲሰሙ፣ ፍልስጥኤማው
ያንን ፈሩ፤ 8ሳሙኤልንም፣ "አምላካችን እግ
ዚአብሔር ከፍልስጥኤማውያን እጅ ያድነን
ዘንድ ስለ እኛ ወደ እርሱ መጸለይህን
አታቋርጥ" አሉት። 9ሳሙኤልም አንድ የሚ
ጠባ የበግ ግልገል ወስዶ ሙሉ ለሙሉ የሚ
ቃጠል መሥዋዕት በማድረግ ለእግዚአብሔር
አቀረበው፤ ስለ እስራኤልም ወደ እግዚአ
ብሔር ጸለየ፤ እግዚአብሔርም መለሰለት።
10ሳሙኤል የሚቃጠለውን መሥዋዕት
በሚያሳርግበት ጊዜ፣ ፍልስጥኤማውያን እስ
ራኤልን ለመውጋት ቀረቡ። ይሁን እንጂ
በዚያ ዕለት እግዚአብሔር በፍልስጥኤማ
ውያን ላይ ከባድ የነጐድጓድ ድምፅ ስላን
ጐደጐደባቸው እጅግ ተሸበሩ፤ ድልም ተመ

6፥19 ዘፀ19፥21፤ 2ሳሙ6፥7
6፥20 ዘሌ11፥45፤ 2ሳሙ6፥9፤ መዝ 130፥3፤ ሚል3፥2፤ራእ6፥17
6፥21 ኢያ 9፥17
7፥1 ኢያ6፥7፤ 2ሳሙ6፥3፤ 1ዜና13፥7
7፥2 1ዜና13፥3፡5፤ መዝ 132፥6
7፥3 ዘዳ31፥19፤ ዘጸ 6፥13፤30፥10፤ ኢያ 24፥14፤ መሳ2፥12-13፡ 18፤1ሳሙ-12፥10፤ 31፥10፤2ነገ18፥5፤ 23፥25፤ ኤር24፥7፤ ኢዩ2፥12፤ ማቴ 4፥10፤ሉቃ4፥8
7፥5 ቍ8፤ ዘዳ20፥7፤ ዘጸ9፥19፤ኢያ11፥3፤ መሳ21፥5፤ 1ሳሙ1፥20፤10፥17፤ መዝ99፥6፤ኤር15፥1
7፥6 ኢያ11፥3፤ መሳ2፥16፤16፥31፤ ሰቆ2፥19
7፥7 1ሳሙ17፥11
7፥8 ቍ5፤ ዘፀ32፥30፤ዘኍ21፥7፤ 1ሳሙ12፥19፡23፤ 1ነገ18፥24፤ ኢሳ37፥4፤ ኤር15፥1፤27፥18
7፥9 ዘፀ32፥11፤ ዘጸ9፥19፤መዝ99፥6
7፥10 ዘዳ35፥5፤ ዘፀ9፥23፤14፥24፤1 ሳሙ2፥10

[ሀ] 19 ጥቂት የዕብራይስጥ ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆችና የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ግን አምሳ ሺህ ሰባ ይላል።

6፥17 *ስለ በደል መሥዋዕት፤* የቍ3 ማብ ይመ።

6፥18 *እስከ ዛሬ፤* ሁለቱ የሳሙኤል መጻሕፍት የተጻፉበት ጊዜ ነው። *ምስክር፤* ሁኔታውን የሚያመለክት ሐውልት ነው።

6፥19 *ሰባ፤* አንዳንድ የጥንት ትርጒሞች አምሳ ሺህ ያህል ሰዎች በዚህ ቍጥር ላይ ይጨምራሉ፤ ጭማሪው የዕብራይስጡን የሰዋስው ሕግ ስለሚጥስ የጸሐፊው (ገልባጭ) ስሕተት መሆኑ ግልጽ ነው። በዚህ ዘመን፣ በዚህች አነስተኛ ከተማ ይህን ያህል ሰው ሊኖር አይችልም። *ወደ እግዚአብሔር ታቦት ውስጥ ተመልክተዋልና፤* ሌዋውያንና ካህናት የነበሩት የቤትሳሚስ ሰዎች ያለፍርሃትና ያለ አክብሮት ታቦቱን ለማየት በመጓጓታቸው እግዚአብሔር ፈረደባቸው። እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል የእርሱን መኖር ከታቦቱ ጋር በቅርብ እንዲያያዝ ስላደረገው፣ ታቦቱ መያዝ የሚገባው በፍርሃትና በታላቅ አክብሮት ነው (2ሳሙ 6፥7፤ዘኍ4፥17-20 ይመ)። በዚህ መንገድ ለታቦቱ ክብር የመስጠቱ ሐሳብ ታቦቱን እንደ ምትሐት ዕቃ በመቍጠር ወደ ጦር ሜዳ እንዲወስዱት ካደረገው የእስራኤል ሽማግሌዎች የጥንቈላ አስተሳሰብ ጋር አይመሳሰልም (የቍ4፥3 ማብ ይመ)።

6፥20 *ወደ ማን ይሂድ?* ለእግዚአብሔር ፍርድ የቤትሳሚስ ሰዎች ምላሽ የሰጡት ልክ እንደ አዛጦን፣ እንደ ጌትና፣ እንደ አቃሮን ሰዎች ነው (5፥8-10 ይመ)።

7፥1 *ወደ አሚናዳብ ቤት፤* ዳዊት ወደ ኢየሩሳሌም እስኪያመጣው ድረስ፣ ታቦቱ በአሚናዳብ ቤት ተቀምጦ ነበር (2ሳሙ 6፥2-3)። ሴሎ በወደመች ጊዜ፣ የመገናኛው ድንኳንና የሚቃጠለው መሥዋዕት መሠዊያ፤ ከጥፋት ተርፈው ነበር (ኤር 7፥12፡ 14፡26፥6)። በመጀመሪያ ታቦቱ ከነበረበት ወደ ኖብ ተወስዶ (21፥1-9)፣ በዳዊትና በሰሎሞን ዘመን በገባዖን ተቀመጠ (1ዜና 16፥39፤ 21፥29፤ 2ዜና1፥3፡13)። *ገባዖን፤* በቤተ መቅደሱ ውስጥ ተራ ሥራ እንዲሠሩ የተመደቡ ሰዎች የሚኖሩባት ከተማ ነበረች (ኢያ9፥23፡27)። በኋላም ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ሠርቶ በጨረሰ ጊዜ፣ የመገናኛውን ድንኳን ወደዚያ አምጥቶታል (የ1ነገ 3፥4፤8፥4 ማብ ይመ)።

7፥2 *በአጠቃላይ ሃያ ዓመት ቈየ፤* ይህ ጊዜ ምናልባት ሳሙኤል በምጽጳ ሕዝቡን ጠርቶ በሰበሰበበትና ታቦቱ ወደ እስራኤል በተመለሰበት ጊዜ መካከል ያለው ጊዜ ሳይሆን አይቀርም።

7፥3 *አስታሮትን፤* አስታሮት ከነዓናውያንን ጨምሮ በመካከለኛው ምሥራቅ የፍቅር፣ ልጅ የምትሰጥና የጦርነት አምላክ ተብላ በተለያየ መንገድ በብዙ ሕዝብ የምትመለክ ናት (የመሳ 2፥13 ማብ ይመ)። አብዛኛውን ጊዜ የአስታሮት አምልኮ ከበአል አምልኮ ጋር ይያያዛል (ቍ4፤12፥10፤ መሳ2፥13፤3፥7፤10፥6)፤ ይኸውም ወንድና ሴት አማልክትን በማገናኘት ልጅ ይገኛል ተብሎ ስለ ሚታመን ነው።

7፥5 *በምጽጳ፤* ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን ዐሥራ አንድ ኪሎ ሜትር ርቃ በብንያም አገር የምትገኝ ከተማ ናት (ኢያ 18፥26)። እስራኤላውያን በዚህ ስፍራ ተሰብስበው፣ አንድም ሰው ከብንያም ነገድ ሚስት እንዳያገባ ተማማሉ (መሳ20፥1፤21፥1 ይመ)። በዚህ ስም ብዙ ስፍራዎች ይጠራሉ (2ሳሙ 22፥3፤ ዘፍ 31፥49፤ ኢያ 11፥3፡8፤ 15፥38 ይመ)። *እጸልያለሁ፤* 7፥8-9፤ 8፥6፤ 12፥17-19፡ 23፤15፥11 ይመ። ሳሙኤልም ልክ እንደ ሙሴ ለሕዝቡ ይማልድ ነበር (መዝ99፥6፤ኤር15፥1 ይመ)። ሁለቱም በእግዚአብሔር የተሾሙ፣ እግዚአብሔርን በመወከል የእርሱን አስተዳደር ወደ ሕዝቡ የሚያደርሱ ናቸው፤ ሕዝቡን በመወከል ስለ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ይናገራሉ።

7፥6 *ውሃ ቀድተው በእግዚአብሔር ፊት አፈሰሱ፤* በብሉይ ኪዳን ይህን የመሰለ ሥርዐት መኖሩን የሚያረጋግጥ ሌላ ማስረጃ የለም። ልብን በእግዚአብሔር ፊት በትህትናና በንስሓ የማፍሰስ ምሳሌ ነው፤ ተመሳሳይ ለሆኑ መግለጫዎች 1፥15፤ መዝ 62፥8፤ ሰቆ2፥19 ይመ። *ሳሙኤልም ... ይፈርድ ነበር፤* የ4፥18 ማብ ይመ።

7፥10 *እግዚአብሔር ... ከባድ የነጐድጓድ ድምፅ*

ተው ከእስራኤላውያን ፊት ሸሹ:: 11እስራ
ኤላውያንም ከምጽጳ ወጥተው ፍልስጥኤ
ማውያንን በየመንገዱ እየገደሉ ከቤትካር
በታች እስካለው ስፍራ ድረስ አሳደዷቸው::
12ከዚህ በኋላ ሳሙኤል አንድ ድንጋይ
ወስዶ በምጽጳና በሼን መካከል አቆመው፤
ስሙንም "*እግዚአብሔር* እስከ አሁን ድረስ
ረድቶናል" ሲል "አቤንኤዘር[†]" ብሎ ጠራው::
13በዚህ ሁኔታ ፍልስጥኤማውያን ድል ስለ
ተመቱ፣ የእስራኤልን ምድር ዳግመኛ አል
ወረሩም::

ሳሙኤል በሕይወት በነበረበት ዘመን ሁሉ፣
የ*እግዚአብሔር* እጅ በፍልስጥኤማውያን ላይ
ከብዳ ነበር:: 14ፍልስጥኤማውያን ከእስራኤል
የወሰዷቸው ከአቃሮን እስከ ጌት የነበሩ
ከተሞች ለእስራኤል ተመለሱላት፤ ግዛታ
ቸውም ከፍልስጥኤማውያን እጅ ነጻ ወጣች፤
በእስራኤልና በአሞራውያንም መካከል ሰላም
ነበረ::

15ሳሙኤል በሕይወት በነበረበት ዘመን
ሁሉ፣ እስራኤልን ይዳኝ ነበር:: 16በየዓመቱ
በቤቴል፣ በጌልገላና በምጽጳ እየተዘዋወረ፣
በእነዚህ ቦታዎች ሁሉ በእስራኤል ላይ ይፈ
ርድ ነበር:: 17ከዚያም በአርማቴም ወዳለው
ቤቱ ይመለስ ነበር፤ በዚያም ደግሞ በእስራ
ኤል ላይ ይፈርድ ነበር:: በዚያም ለ*እግዚአ
ብሔር* መሠዊያ ሠራ::

## እስራኤል ንጉሥ ለማንገሥ መጠየቁ

**8** ሳሙኤል በሸመገለ ጊዜ፣ ልጆቹን ፈራጆች
አድርጎ በእስራኤል ላይ ሾማቸው:: 2የበ
ኵር ልጁ ኢዮኤል ሲሆን፣ ሁለተኛው ልጁ
አብያ ነበረ፤ እነርሱም በቤርሳቤህ ይፈርዱ
ነበር:: 3ነገር ግን ልጆቹ የአባታቸውን
ፈለግ አልተከተሉም፤ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም
ለማግኘት ሲሉ ከመንገዱ ወጡ፤ ጉቦ ተቀ
በሉ፤ ፍርድም አጣመሙ::
4ስለዚህ የእስራኤል ሽማግሌዎች ሁሉ
በአንድነት ተሰብስበው ሳሙኤል ወዳለበት

7፥12 ዘፍ28፥22፤ ዘጸ27፥2፤ኢሱ4፥9፤ 1ሳሙ4፥1
7፥13 መሳ13፥5
7፥14 ኢሱ13፥3፤ መሳ1፥34
7፥15 ቍ6፤ መሳ 2፥16:18፤ 1ሳሙ 12፥11
7፥16 ቍ6፤ ዘፍ 12፥8፤ኢሱ10፥43፤ 1ሳሙ10፥8፤አሞ5፥5፤ ሐሥ13፥20
7፥17 ቍ6፤ ኢሱ 18፥25፤ 1ሳሙ8፥4፤ 9፥12፤14፥35፤15፥34፤ 19፥18፤20፥6፤25፥1፤ 28፥3፤2ሳሙ24፥25
8፥1 ዘዳ16፥18-19
8፥2 ዘፍ22፥19፤ 1ነገ19፥3፤1ዜና6፥28፤ አሞ5፥4-5
8፥3 ዘፀ23፥2:8፤ 1ሳሙ2፥12፤12፥3፤ ነህ9፥29፤ኢዮ8፥22፤ 34፥27፤መዝ14፥3፤ 58፥3፤ምሳ17፥23፤ ኢሳ53፥6
8፥4 መሳ11፥11፤ 1ሳሙ 7፥17፤11፥3
8፥5 ቍ19:20፤ ዘዳ 17፥14-20፤ 1ሳሙ3፥20፤10፥19፤ 12፥2:12:13፤ ሆሴ13፥11
8፥6 1ሳሙ12፥17፤ 15፥11፤16፥1፤ ሆሴ13፥10
8፥7 ቍ22፤ ዘፀ 16፥8፤ዘኍ11፥20፤ 1ሳሙ12፥1
8፥8 1ሳሙ12፥10፤ 2ነገ21፥22፤ኤር2፥17
8፥9 ቍ11-18፤ ዘዳ17፥14-20፤1ሳሙ 10፥25
8፥10 ዘፀ19፥7 ማሕ3፥7፤9፥25

ወደ አርማቴም መጡ:: 5እነርሱም፣ "አንተ
አርጅተሃል፤ ልጆችህ ያንተን ፈለግ አይከ
ተሉም፤ ስለዚህ ሌሎች ሕዝቦች እንደሚያ
ደርጉት ሁሉ የሚመራን[°] ንጉሥ አንግሥ
ልን" አሉት::
6ነገር ግን፣ "የሚመራን ንጉሥ አንግሥ
ልን" ማለታቸው ሳሙኤልን አላስደሰተ
ውም፤ ስለዚህ ወደ *እግዚአብሔር* ጸለየ፤
7እግዚአብሔርም ሳሙኤልን እንዲህ አለው፤
"ንጉሣቸው እንዳልሆን የናቁት እኔን እንጂ
አንተን አይደለምና ሕዝቡ የሚሉህን ሁሉ
አድምጥ:: 8ከግብፅ ምድር ካወጣኋቸው
ዕለት አንሥቶ እስከ ዛሬ ድረስ እኔን ትተው
ሌሎች አማልክትን በማምለክ ያደረጉትን
ሁሉ በአንተም ላይ እያደረጉ ነው:: አንተ
ግን 9የሚሉህን አድምጣቸው፤ በላያቸው
የሚነግሠው ንጉሥ ምን እንደሚፈጽምባቸውም
አሳውቃቸው፤ በሚገባም አስጠንቅቃቸው::"
10ሳሙኤልም *የእግዚአብሔርን* ቃል ሁሉ፣
ንጉሥ እንዲነግሥላቸው ለጠየቁት ሕዝብ
ተናገረ:: 11እንዲም አለ፤ "በላያችሁ የሚነ
ግሠው ንጉሥ የሚያደርግባችሁ ይህ ነው፤
ወንዶች ልጆቻችሁን ወስዶ ሠረገለኞችና
ፈረሰኞች ያደርጋቸዋል፤ በሠረገሎቹም ፊት
ይሮጣሉ:: 12አንዳንዶቹን ሻለቆችና አምሳ
አለቆች ያደርጋቸዋል፤ ሌሎቹን መሬቱን
እንዲያርሱና እህሉን እንዲያጭዱ፣ የቀሩ
ትን ደግሞ የጦር መሣሪያና ለሠረገላ የሚሆ
ኑትን ዕቃዎች እንዲሠሩ ያደርጋቸዋል፤ 13ሴቶች
ልጆቻችሁን ወስዶ ሽቶ ቀማሚ፣ ወጥ ሠሪ
ዎችና እንጀራ ጋጋሪዎች ያደርጋቸዋል::
14ከዕርሻችሁ፣ ከወይንና ከወይራ ተክል ቦታ
ዎቻችሁ ምርጥ ምርጡን ወስዶ ለባለሟ

8፥11 ዘፍ41፥46፤ ዘዳ17፥16፤1ሳሙ14፥52፤2ሳሙ15፥1፤ 1ነገ1፥5፤2ዜና1፥14፤1ሳሙ17፥25 8፥12 ዘዳ1፥15 8፥14 1ነገ21፥7:15፤2ነገ22፥12፤ሕዝ46፥18፤ ሚክ2፥2

[†]12 *አቤኔዘር* ማለት የርዳታ ድንጋይ ማለት ነው
[°]5 በዚም ሆነ በቍጥር 6 እና 20 ላይ በትውፊት *መተርጎም* ይቻላል

*ስላንጉደ ጉደባቸው፤* ሕዝቡ የገቡትን ቃል ኪዳን ከጠበቀ፣ እግዚ አብሔር እንደ ሚጠብቃቸው ቃል ገብቶአል (ዘፀ 23፥22፤ ዘዳ20፥1-4፤ 2ሳሙ 5፥19-25፤ ኢሱ10፥11-14፤ መሳ5፥20-21፤ 2ነገ7፥6፤ 19፥35፤ 2ዜና 20፥17:22 ይመ)::

7፥12 *አቤንኤዘር፤* የሚረዳ ዐለት ማለት ነው፤ የ4፥1 ማብ ይመ::

7፥13 *የእስራኤልን ምድር ዳግመኛ አልወረሩም፤* ይህ ዐረ ፍተ ነገር በ9፥16፤ 10፥5፤ 13፥3:5፤ 17፥1፤ 23፥27 ላይ ካለው ሐሳብ ጋር እንደሚቃረን፣ አንዳንድ ምሁራን ይናገራሉ፤ ይሁን እንጂ ዐረፍተ ነገሩ ፍልስጥኤማውያን ወዲያውኑ እስራ ኤላውያንን እንዳልወረሩ የሚያመለክት ነው፤ ስለ ተመሳሳይ ሁኔታ 2ነገ 6፥23-24 ይመ::

*7፥15፤* የሳሙኤልን አገልግሎትና ለእስራኤል የሰጠውን አመራር በተመለከተ ጸሐፊው ያስቀመጠው የማጠቃለያ ዐረፍተ ነገር ነው::

7፥16 *በእስራኤል ላይ ይፈረድ ነበር፤* የ4፥18 ማብ ይመ::

7፥17 *በአርማቴም፤* የ1፥1 ማብ ይመ::

8፥1 *ሳሙኤል በሸመገለ ጊዜ፤* ምናልባት ምጽጳ ላይ የተ ገኘው ድል ካለፈ ከሃያ ዓመት በኋላ፣ የሳሙኤል ዕድሜ ሥልሳ አምስት ዓመት ሲሆን ማለት ነው::

8፥3 *ጉቦ ተቀበሉ፤* በአምስቱ የሙሴ መጻሕፍት መሠረት ጉቦ በመቀበል ፍትሕን ማጣመም አጥብቆ የተከለከለ ነው (ዘፀ 23፥8፤ ዘዳ16፥19 ይመ)::

8፥5 *የሚመራን ንጉሥ አንግሥልን፤* የእስራኤል ሽማግ ሌዎች ይህን ጥያቄ ለማቅረብ ምክንያት ያደረጉት ሳሙኤል ዕድ ሜው ስለገፋ ልጆቹም ፍትሕ ስላዛቡ ነበር፤ ይሁን እንጂ ወዲ ያውኑ የታየው እውነተኛው ምክንያት እንደ አካባቢያቸው ሕዝብ በጦርነት ጊዜ የሚመራቸውንና ለነጻነታቸውም መተማመኛ የሚ ሆናቸውን ንጉሥ የማግኘቱ ጉዳይ ነበር (ቍ 20፤ 10፥19፤12፥12 ይመ)::

8፥7 *ንጉሣቸው እንዳልሆን የናቁት እኔን እንጂ አንተን አይደለምና፤* ከመሳ 8፥23 ጋር ያነጻጽሩ:: የእስራኤል ሕዝብ ኀጢ አት፣ ንጉሥ መፈለጋቸው ሳይሆን (10፥19፤12፥12፤ 17፥19-20 ይመ) ከሚፈልጉት የንጉሥ ዐይነትና ከንጉሡም ከሚጠብቁት ነገር የሚመነጭ ነው:: እነርሱ የሚፈልጉት ንጉሥ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን የቃል ኪዳን ግንኙነት የማይቀበል ንጉሥ ነው:: "እንደ ሌሎቹ ሕዝቦች የሚመራንና ከፊታችን የሚሄድ፣ ጦር ነታችንንም የሚዋጋልን ንጉሥ ያለን ሕዝቦች እንሆናለን" (ቍ20) በማለታቸው ቃል ኪዳኑን ያፈርሳሉ፤ ንጉሣቸው የሆነውን እግዚ አብሔርን ይንቃሉ (12፥12፤ ዘኍ23፥21፤ ዘዳ33፥5)፤ ባለፉትም ዘመናት ባለማቋረጥ ያደረገላቸውን ጥበቃ ይረሳሉ (10፥18፤ 12፥8-11):: *ሕዝቡ የሚሉህን ሁሉ አድምጥ፤* ሕዝቡ ንጉሥ የሚፈልጉ መሆናቸው በሙሴ መጻሕፍት ተገልጾአል (ዘፍ49፥10፤ ዘኍ24፥7:17፤ ዘዳ17፥14-20 ይመ)፤ ስለዚህ ሳሙኤል የሕዝቡን ቃል እንዲያደምጥ ትእዛዝ ተሰጠው (ቍ9፥22)::

8፥11 *በላያችሁ የሚነግሠው ንጉሥ የሚያደርግባችሁ፤* በዚያ ዘመን የነበሩትን የከነዓናውያን ነገሥታት አገዛዝ ሁኔታ በመግ

ሎቹ ይሰጣቸዋል:: 15ከእህላችሁና ከወይና
ችሁ ከዐሥር አንዱን ወስዶ ለሹማምቱና
ለባለሟሎቹ ይሰጣቸዋል:: 16ወንድና ሴት
አሽከሮቻችሁን እንዲሁም ምርጥ ከብቶቻ
ችሁንና[a] አህዮቻችሁን ለራሱ ያደርጋቸ
ዋል:: 17ከበግና ከፍየል መንጎቻችሁ አንድ
ዐሥረኛውን ለራሱ ይወስዳል፤ እናንተ ራሳ
ችሁም ባሪያዎቹ ትሆናላችሁ:: 18ያም ቀን
በደረሰ ጊዜ፣ ወዳችሁ ከመረጣችሁት ንጉሥ
የተነሣ ትጮኻላችሁ፤ ነገር ግን በዚያ ቀን
እግዚአብሔር አይመልስላችሁም::"

19ሕዝቡ ግን ሳሙኤልን መስማት እምቢ
በማለት፤ እንዲህ አሉ፤ "አይሆንም፤ ንጉሥ
እንዲነግሥልን እንፈልጋለን፤ 20እኛም እንደ
ሌሎቹ ሕዝቦች የሚመራንና ከፊታችን
የሚሄድ፣ ጦርነታችንንም የሚዋጋልን ንጉሥ
ያለን ሕዝቦች እንሆናለን::"

21ሳሙኤልም ሕዝቡ ያለውን ሁሉ ሰማ፤
ያንኑ በእግዚአብሔር ፊት ተናገረው:: 22እግ
ዚአብሔርም "አድምጣቸው፤ ንጉሥም አን
ግሥላቸው" አለው::

ከዚያም ሳሙኤል የእስራኤልን ሰዎች፣
"እያንዳንዳችሁ ወደ ከተማችሁ ተመለሱ"
አላቸው::

## ሳሙኤል ሳኦልን ለንጉሥነት ቀባው

9 ቂስ የተባለ አንድ ታዋቂ ብንያማዊ
ሰው ነበረ፤ እርሱም የአቢኤል ልጅ፣
የጽሮር ልጅ፣ የብኮራት ልጅ፣ የብንያ
ማዊው የአፌቅ ልጅ ነበር:: 2ቂስም ከእስራ
ኤል ልጆች መካከል በመልክ ቀናነቱ ተወ
ዳዳሪ የማይገኝለት፣ ቁመቱም ከሌሎቹ
ሁሉ ይልቅ ከትከሻው በላይ ዘለግ ያለ፣
ሳኦል የተባለ ወጣት ልጅ ነበረው::

3በዚያም ጊዜ የሳኦል አባት የቂስ አህ
ዮች ጠፍተው ነበር፤ ቂስም ልጁን ሳኦልን፣
"ከአገልጋዮቹ መካከል አንዱን ይዘህ ሂድና
አህዮቹን ፈልግ" አለው:: 4ስለዚህ በኰረብ
ታማው በኤፍሬም አገርና በሻሊሻ አካባቢ
ባለው ስፍራ ሁሉ ተዘዋወረ፤ ሆኖም አህዮ
ቹን አላገኙም:: ወደ ሻዕሊምም ግዛት ዘል
ቀው ገቡ፤ አህዮቹ ግን በዚያም አልነበሩም::
እንዲሁም በብንያም ግዛት በኩል ዐለፈ፤
ሆኖም አላገኟቸውም::

5ወደ ጹፍ ግዛት በደረሱ ጊዜ ሳኦል አብ
ሮት የነበረውን አገልጋይ፣ "አባቴ ይህን ጊዜ
ስለ አህዮቹ ማሰቡን ትቶ ስለ እኛ መጨ
ነቅ ስለሚጀምር፣ ና እንመለስ" አለው::

6አገልጋዩ ግን፣ "እነሆ፤ በዚህች ከተማ አንድ
የእግዚአብሔር ሰው አለ፤ እርሱም በጣም የተ
ከበረ ነው፤ የሚናገረውም ሁሉ በትክክል
ይፈጸማል፤ በየትኛው መንገድ መሄድ እን
ዳለብን ይነግረን ይሆናልና ወደዚያ እን
ሂድ" ሲል መለሰለት::

7ሳኦልም አገልጋዩን፣ "መሄዱን እንሂድ፤
ነገር ግን ለሰውየው ምን እንሰጠዋለን? በስ
ልቻዎቻችን የያዝነው ስንቅ አልቆአል::
ለእግዚአብሔር ሰው የምናበረክተውም ስጦታ
የለንም፤ ታዲያ ምን አለን?" አለው::

8አገልጋዩ፣ "እኔ የአንድ ሰቅል ጥሬ ብር
ሩብ[b] አለኝ፤ በየትኛው መንገድ መሄድ
እንዳለብን ይነግረን ዘንድ ገንዘቡን ለእግዚ
አብሔር ሰው እሰጠዋለሁ" ሲል በድጋሚ
መለሰለት:: 9ቀደም ሲል በእስራኤል ዘንድ
አንድ ሰው እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ሲሄድ፣
"ኑ ወደ ባለ ራእዩ እንሂድ" ይል ነበር፤
ዛሬ ነቢይ የሚባለው በዚያ ጊዜ ባለ ራእይ
ይባል ነበርና::

10ሳኦልም፣ "መልካም፤ ና እንሂድ" አለው::
ስለዚህ የእግዚአብሔር ሰው ወዳለበት ከተማ
ሄዱ::

11በከተማዪቱ መዳረሻ ያለውን ኰረብታ
በመውጣት ላይ ሳሉ፣ ውሃ ለመቅዳት የሚ
ወጡ ልጃገረዶችን አግኝተው፣ "ባለ ራእዩ
እዚህ ነውን?" ሲሉ ጠየቁ::

8፥15 ዘፍ41፥34፤
8፥18 1ሳሙ10፥25፤ 28፥6፤1ነገ12፥4፤ ኢዮ27፥9፤35፥12:13 1መዝ18፥41፤66፥18፤ ምሳ1፥28፤ኢሳ1፥15፤ 58፥4፤59፥2፤ አር 14፥12፤ ሕዝ8፥18፤ ሚክ3፥4
8፥19 ቍ5፤ ምሳ 1፥24፤ ኢሳ50፥2፤ 66፥4፤ ኤር7፥13፤8፥12፤13፥10፤ 44፥16፤ሐሥ13፥21
8፥20 ቍ5
8፥21 መሳ11፥11
8፥22 ቍ7
9፥1 እሱ18፥11-20፤ ሩት2፥1፤ 1ሳሙ 14፥51፤ 1ዜና8፥33፤ 9፥39፤ አስ2፥5፤ ሐሥ 13፥21
9፥2 ዘፍ39፥6፤ 1ሳሙ10፥23:24
9፥3 ቍ20፤ 1ሳሙ10፥14:16
9፥4 ኢሱ 24፥33፤ 1ሳሙ10፥2፤ 2ነገ4፥42
9፥5 1ሳሙ1፥1፤ 10፥2
9፥6 ዘዳ33፥1፤ መሳ13፥6፤1ሳሙ3፥19
9፥7 ዘፍ 32፥20፤ 1ነገ13፥7፤14፥3፤ 2ነገ4፥42፤5፥5:15፤ ኤር40፥5
9፥9 ዘፍ25፥22፤ 2ሳሙ15፥27፤ 24፥11 2ነገ17፥13፤ 1ዜና9፥22፤21፥9፤ 26፥28፤ 29፥29፤ 2ዜና19፥2፤ ኢሳ29፥10፤30፥10፤ አሞ7፥12
9፥11 ዘፍ24፥11፤13

[a] 16 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን ወጣቶቻችን ይላል::
[b] 8 ሦስት ግራም ያህል ነው::

ለጽ (ቍ11-17)፣ የሚናፍቁት ንጉሣዊ አስተዳደር ምን ያህል ከባድ ሸክም የሚጭንባቸው መሆኑን በመናገር ሳሙኤል ሕዝቡን ያስጠነቅቃቸዋል::

8፥15 *ከዐሥር አንዱን፤* ይህ እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ከሚሰጡት ዐሥራት የሚበልጥ የንጉሡ ድርሻ ነው (ዘሌ27፥30-32፤ዘኍ18፥26፤ዘዳ14፥22:28፤26፥12):: በዚህም ይሁን በዚያ ይህ ንጉሥ እስራኤላውያን እንዲሰጡት የሚጠብቀው እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር የሚሰጡትን ሁሉ ነው ::

8፥18 *ወዳችሁ ከመረጣችሁት ንጉሥ የተነሣ ትጮኻላችሁ፤* 1ነገ12፥4፤ ኤር22፥13-17 ይመ::

8፥20 *እንደ ሌሎቹ ሕዝቦች፤* የቍ 5:7 ማብ ይመ ::

9፥2 *ቁመቱም ከሌሎቹ ሁሉ ይልቅ ከትከሻው በላይ ዘለግ ያለ፤* ቁመቱ በጣም ረዥም ነበር ማለት ነው (10፥23 ይመ)::

9፥3 *አህዮች ጠፍተው ነበር፤* ሳኦልን በመጀመሪያ የምናገኘው የጠፉ አህዮችን እንዲፈልግ ሲታዘዝ ነው፤ ምናልባትም ንጉሥ እፈልጋለሁ ያለችውን ዐመፀኛዪቱን እስራኤልንና አህያ ሊፈልግ የወጣውን ሳኦልን በምሳሌነት ለማነጻጸር ሊሆን ይችላል (ከኢሳ1፥3 ጋር ያነጻጽሩ):: ዳዊትን በመጀመሪያ የምናገኘው የአባቱን በጐች ሲጠብቅ ነው፤ በኋላም የእግዚአብሔርን መንጋ ጠባቂ ሆኖ እናገኘዋለን (2ሳሙ5፥2፤ 7፥7-8፤ መዝ78፥71-72)::

9፥6 *አገልጋዩ ግን ... ሲል መለሰለት፤* በዚህ ስፍራ ሳኦል ሳሙኤልን አለማወቁ የግል ጠባዩን ያመለክታል:: *በዚች ከተማ፤* ምናልባትም ራማ የተባለችው፣ የሳሙኤል የትውልድ ስፍራ የሆነችው አርማቴም ሳትሆን (ቍ12፤ 7፥16 ይመ)፣ ሳኦል ከመንገድ ተመልሶ ያረፈበትም፣ ይህችው ቦታ ናት:: *የእግዚአብሔር ሰው፤* የ2፥27 ማብ ይመ፤ ሳሙኤልን ያመለክታል:: *የሚናገረውም ሁሉ በትክክል ይፈጸማል፤* 3፥19 ማብ ይመ::

9፥7 *ምን እንሰጠዋለን፤* ለነቢያት ስጦታን ስለ መስጠት የተጠቀሱ ሌሎች ማስረጃዎች አሉ (1ነገ14፥3፤ 2ነገ4፥42፤ 5፥15-16፤ 8፥8-9 ይመ):: ስጦታውን ሳሙኤል ይቀበለው ወይም እንደ ዚህ ዐይነቱ ስጦታ ለኑሮው ያስፈልገው አያስፈልገው የታወቀ ነገር የለም:: ኤልሳዕ የሶርያውን የጦር ጀኔራል የንዕማንን ስጦታ አልተቀበለም (2ነገ 5፥16):: በኋለኞቹ ዘመናት የሐሰት ነቢያት ትንቢታቸውን የሚናገሩት፣ ስጦታ ለሚሰጧቸው ሰዎች ነበር (1ነገ 22፥6:8:18፤ ሚክ3፥5:11)::

9፥8 *የአንድ ሰቅል ጥሬ ብር ሩብ፤* ሦስት ግራም ያህል ማለት ነው፤ ሳንቲሞች መገበያያ ከመሆናቸው በፊት፣ ወርቅ ወይም ብር ተመዝኖ ለእያንዳንዱ የገንዘብ ለውጥ ሥራ ላይ ይውል ነበር (13፥21፤ኢዮ28፥15 ይመ):: በሳኦል ዘመን የዚህ ብር ዋጋ መጠን አይታወቅም ነበር::

9፥9 *ዛሬ ነቢይ የሚባለው ... ባለ ራእይ ይባል ነበርና፤* በባለ ራእይና በነቢይ መካከል መሠረታዊ ልዩነት የለም:: ሁለቱም የሳሙኤል መጻሕፍት በተጻፉበት ዘመን፣ ነቢይ በመባል የሚታወቀው በሳኦል ጊዜ ባለ ራእይ ይባላል:: ይህ ማለት ደግሞ "ነቢይ"

12እነርሱም እንዲህ ሲሉ መለሱላቸው፤
“አዎን አለ፤ እነሆ፤ ከፊታችሁ ነው፤ ፈጠን
በሉ፤ ሕዝቡ በማምለኪያው ኰረብታ ላይ
መሥዋዕት ስለሚያቀርብ፣ ወደ ከተማችን
ገና ዛሬ መምጣቱ ነው፤ 13ወደ ከተማዪቱም
በገባችሁ ጊዜ፣ ለመብላት ወደ ማምለኪያው
ኰረብታ ከመውጣቱ በፊት ታገኙታላችሁ።
መሥዋዕቱን እርሱ መባረክ ስላለበት፣ እርሱ
እስኪመጣ ድረስ ሕዝቡ መብላት አይጀም
ርም፤ ከዚያ በኋላ የተጋበዘው ሕዝብ ይበ
ላል፤ አሁኑኑ ውጡ፤ ወዲያው ታገኙታላ
ችሁ።”
14እነርሱም ወደ ከተማዪቱ ወጡ፤ ወደ
ከተማዪቱም በመግባት ላይ ሳሉ፣ እነሆ፤
ሳሙኤል ወደ ማምለኪያው ኰረብታ ለመ
ውጣት እነርሱ ወዳሉበት አቅጣጫ መጣ።
15ሳኦል ከመምጣቱ ከአንድ ቀን በፊት
እግዚአብሔር ለሳሙኤል ይህንን እንዲህ
ሲል ገልጦለት ነበር፤ 16“ነገ በዚህ ጊዜ ከብ
ንያም ምድር አንድ ሰው ወደ አንተ እል
ካለሁ፤ በሕዝቤ በእስራኤል ላይ መሪ እንዲ
ሆን ቅባው፤ እርሱም ሕዝቤን ከፍልስጥኤ
ማውያን እጅ ይታደጋል። እነሆ፤ ሕዝቤን
ከላይ ተመልክቻለሁ፤ ጩኸቱ ከእኔ ዘንድ
ደርሶአልና።”
17ሳሙኤል ሳኦልን ባየው ጊዜ እግዚ
አብሔር፣ “ያ የነገርሁህ ሰው እነሆ፤ እር
ሱም ሕዝቤን ይገዛል” አለው።
18ሳኦልም በቅጥሩ በር ላይ ወደ ሳሙ
ኤል ቀረብ ብሎ፣ “የባለ ራእዩ ቤት የት
እንደ ሆነ ትነግረኛለህ?” ሲል ጠየቀው።
19ሳሙኤልም እንዲህ ሲል መለሰለት፤
“ባለ ራእዩ እኔ ነኝ፤ ዛሬ ከእኔ ጋር ስለ
ምትበሉ፤ ከፊቴ ቀድማችሁ ወደ ማምለኪ
ያው ኰረብታ ውጡ፤ ነገ ጠዋት አሰና
ብትሃለሁ፤ በልብህ ያለውንም እነግርሃለሁ።
20ከሦስት ቀን በፊት ስለ ጠፉብህ አህዮች
አትጨነቅ፤ ተገኝተዋልና። የእስራኤል

9፥12 ዘሌ 26፥30፤
ዘኍ28፥11-15፤
1ሳሙ7፥17
9፥13 ማቴ14፥19፤
1ቆሮ10፥16፤
1ጢሞ4፥3-5
9፥16 ዘፍ 16፥11፤
ዘፀ3፥8፤30፥25፤
1ሳሙ2፥35፤12፥3፤
15፥1፤23፥4፤26፥9፤
2ሳሙ3፥18፤7፥8፤
1ነገ8፥16፤2ነገ11፥12፤
1ዜና5፥2፤መዝ2፥2፤
102፥1
9፥17 1ሳሙ16፥12
9፥20 ቀኍ3፤
1ሳሙ 12፥13፤
ዕዝ6፥8፤ኢሳ 60፥4-9፤
ዳን2፥44፤ሐጌ2፥7፤
ሚል3፥1
9፥21 ዘፀ3፥11፤
መሳ6፥15፤20፥35፡
46፤1ሳሙ18፥18፤
መዝ 68፥27፤
ማቴ2፥6፤ ቆሮ15፥9
9፥24 ዘሌ7፥34
9፥25 ዘዳ22፥8፤
ኢሱ 2፥8፤
ማቴ24፥17፤
ሉቃ5፥19
10፥1 ዘፀ29፥7፤
34፥9፤1ሳሙ9፥16፤
16፥1፤2ሳሙ20፥19፤
1ነገ1፥39፤2ነገ9፥1፤
መዝ78፥62፡71

ምኞት ሁሉ ያዘነበለው ወደ አንተና ወደ
አባትህ ቤተ ሰብ ሁሉ አይደለምን?”
21ሳኦልም፣ “እኔ ከእስራኤል ነገዶች ውስጥ
በጣም አነስተኛ ከሆነው ከብንያም ወገን
አይደለሁምን? ጐሣዬስ ከብንያም ነገድ
ጐሣዎች ሁሉ የሚያንስ አይደለምን? ታዲያ
እንዲህ ያለውን ነገር ስለ ምን ትነግረኛ
ለህ?” ብሎ መለሰለት።
22ከዚያም ሳሙኤል ሳኦልንና አገልጋዩን
ወደ አዳራሹ አመጣ፤ ከተጋበዙትም ሠላሳ
ያህል ሰዎች ሁሉ በላይ አስቀመጣቸው።
23ሳሙኤልም ወጥ ቤቱን፣ “ለይተህ አስቀምጥ
ብዬ የሰጠሁህን የሥጋ ብልት አምጣው”
አለው።
24ወጥ ቤቱም የጭኑን ሥጋ እንዳለ
አምጥቶ በሳኦል ፊት አስቀመጠው። ሳሙ
ኤልም፣ “ይህ፣ ‘እንግዶችን ጋብዣለሁ’
ካልሁበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ተወሰነው ጊዜ
ድረስ ለአንተ ተለይቶ የተቀመጠልህ ስለ
ሆነ ብላው” አለው። ሳኦልም በዚያች ዕለት
ከሳሙኤል ጋር አብሮ በላ።
25ከማምለኪያው ኰረብታ ወደ ከተማዪቱ
ከወረዱ በኋላ ሳሙኤል በቤቱ ሰገነት ላይ
ከሳኦል ጋር ተነጋገረ። 26በማለዳ ተነሡ፤
ሳሙኤል ሳኦልን ከሰገነቱ ላይ ጠርቶ፣
“ላሰናብትህ ስለ ሆነ ተዘጋጅ” አለው።
ሳኦልም ተዘጋጅቶ እንዳበቃ፣ ከሳሙኤል
ጋር ተያይዘው ወደ ውጭ ወጡ። 27ወደ
ከተማዪቱ ዳርቻ እየወረዱ ሳለ፣ ሳሙኤል
ሳኦልን፣ “አገልጋይህ ወደ ፊት ቀድሞን
እንዲሄድ ንገረው” አለው፤ አገልጋዩም እንደ
ተነገረው አደረገ፤ ከዚህ በኋላ ሳሙኤል፣
“አንተ ግን ከእግዚአብሔር የተላከ መልእክት
እነግርህ ዘንድ ለጥቂት ጊዜ እዚህ ቈይ”
አለው።

10ከዚያም ሳሙኤል የዘይቱን ብርሌ
ወስዶ፣ ዘይቱን በሳኦል ራስ ላይ ካፈ
ሰሰ በኋላ እንዲህ ሲል ሳመው፤ “በርስቱ

የሚለው ቃል በሳኦል ዘመን አይታወቅም ወይም “ባለ ራእይ” የሚለው ቃል በኋለኞቹ ዘመናት አልነበረም ማለት አይደለም (ኢሳ 30፥10 ይመ)።

9፥12 *ኰረብታው ላይ፤* ዘሌ26፥30 ይመ። እስራኤላውያን ወደ ተስፋዪቱ ምድር ከገቡ በኋላ፤ ልክ እንደ ከነዓናውያን ልማድ መሠዊያቻውን በኰረብታ ላይ መሥራት ጀመሩ (በዚህ ጊዜ ታቦቱ ከማደሪያው ስለ ተለየ፣ ሴሎ ስለ ፈረሰ፣ ከዔሊ ልጆች ሞት በኋላ የካህናት ቤተ ሰብ ስለማያገለግል ዋናው ቤተ መቅደስ አልነበረም)። እንግዲህ በኋለኞቹ ዘመናት በኰረብታ ስፍራዎች ላይ የመሠዋት ልማድ ቀስ በቀስ እስራኤላውያንን ወደ ጣዖት አምልኮ ሳባቸው፤ ከዚህም የተነሣ ድርጊቱ ተወግዞአል (የ1ነገ 3፥2 ማብ ይመ)።

9፥13 *መሥዋዕቱን እርሱ መባረክ ስላለበት፤* ሳሙኤል የመሥዋዕቱን መብል በጸሎት ይባርካል (1፥4፤2፥13-16 ይመ)፤ ቡራኬው ምናልባት በአዲስ ኪዳን ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይ ሳይ ሆን አይቀርም (ማቴ26፥26-27፤ ዮሐ6፥11፡23፤ 1ጢሞ4፥3-5 ይመ)።

9፥16 *መሪ፤* ለዚህ ቃል አቻ ሆኖ የገባው የዕብራይስጡ ቃል በደረጃ ከፍ እንዲል እግዚአብሔር የመረጠው መሆኑን ያሳያል። በመሳፍንትና በነገሥታት፣ ዘመን መካከል የነበረውን የሽግግር ሁኔታ ለማረጋጋት ጠቃሚ ቃል ሆኖ አገልግሎአል። *ከፍልስጥኤማውያን፤* የ7፥13 ማብ ይመ። *ቅባው፤* ካህናትም ይቀበሉ (ዘፀ 29፥7፤ 40፥12-15፤ ዘሌ4፥3፤ 8፥12 ይመ)፤ ነገር ግን ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ቃሉ በብሉይ ኪዳን “እግዚአብሔር የቀባው” የሚለው ሐረግ ንጉሥን ያመለክታል (የ2፥10 ማብ ይመ፤ ከ12፥3፤ 24፥6፤ 26፥9፡ 11፡16፤ 2ሳሙ 1፥14፡16፤ 19፥21፤ 22፥51፤ 23፥1፤ መዝ2፥2፡6 ጋር ያነጻጽሩ፤ ዘካ4፥14 ይመ)። መቀባት ለልዩ የእግዚአብሔር ሥራ መለየትንና ለአገልግሎቱ የሚሆን መለኮታዊ ዝግጅትን ይጨምራል (ቈ6፤16፥13፤ ኢሳ61፥1 ይመ)።

9፥21 *ከእስራኤል ነገዶች ውስጥ በጣም አነስተኛ ከሆነው ... ወገን፤* ሳኦል የተገኘው በእስራኤል ካሉት የያዕቆብ ልጆች ዝቅተኛ ከሆነው ፣ በተለይም በመሳፍንት ዘመን ቍጥሩ እጅግ ከቀነሰው (መሳ20፥46-48) ከብንያም ነገድ ነው። የእርሱ ወደ ንጉሥነት ከፍ ማለት እግዚአብሔር “ችግረኛውን ከፍ ከፍ ያደርጋል” (2፥8) የሚለውን በተለይም በሳሙኤል መጽሐፍ ዋና ሐሳብ የሆነውን ቃል ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ ነው። እግዚአብሔር መንግሥቱን ለማስፋት ዐቅም በሌላቸው ሰዎች መንግሥቱ ከዚህ ዓለም እንዳይደለ የሚያሳይ ሐቅና በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠ ምስክርነት ነው።

9፥24 *የጭኑን፤* ቃሉ በዕብራይስጥ ወርቹን የሚያመለክት ሲሆን፣ ለጌታ ለተለዩ ካህናት የሚቀደስ ነው (ዘፀ 29፥22፡ 27፤ ዘሌ7፥32-33፡35፤ ዘኍ6፥20፤ 18፥18 ይመ)። ይህን የተመረጠ መሥዋዕት ለሳኦል ማቅረብ፣ ልዩ ክብር ይሰጠዋል፤ ለወደ ፊቱ በእግዚአብሔር የሚቀባ መሆኑንም ያመለክታል።

10፥1 *የዘይቱን፤* የተቀመመ የወይራ ዘይት ሊሆን ይችላል

ላይ ገዥ ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር ቀብ
ቶህ የለምን[*]? 2ዛሬ ከእኔ ተለይተህ ስት
ሄድ፣ በብንያም ወሰን ላይ በምትገኘው
ጼልጻህ በተባለች ስፍራ በራሔል መቃ
ብር አጠገብ ሁለት ሰዎች ታገኛለህ::
እነርሱም፣ ‘የምትፈልጋቸው አህዮች ተገኝ
ተዋል፤ አሁን አባትህ ስለ አህዮቹ ማሰቡን
ትቶ፣ “ስለ ልጄ ምን ባደርግ ይሻለኛል?”
እያለ በመጨነቅ ላይ ነው’ ይሉሃል::
3“አንተም ጕዞህን በመቀጠል በታቦር
እስካለው እስከ ትልቁ ዛፍ ድረስ ትሄዳለህ፤
እዚያም ሦስት ሰዎች፣ አንዱ ሦስት የፍ
የል ግልገል፣ ሌላው ሦስት ዳቦ፣ ሌላው
ደግሞ የወይን ጠጅ የተሞላበት አቁማዳ
ይዘው ወደ እግዚአብሔር ወደ ቤቴል ሲወጡ
ያገኙሃል:: 4እነርሱም ሰላም ይሉሃል፤ ሁለት
ዳቦ ይሰጡሃል፤ አንተም ትቀበላቸዋለህ::
5“ከዚያ በኋላ የፍልስጥኤማውያን ጦር
ወዳለበት ወደ እግዚአብሔር ተራራ ወደ
ጊብዓ ትሄዳለህ:: ወደ ከተማዪቱ እንደ
ደረስህም የነቢያት ጉባኤ በመሰንቆ፣ በከ
በሮ፣ በእምቢልታና በበገና ታጅበው ትን
ቢት እየተናገሩ ከማምለኪያው ኰረብታ
ላይ ሲወርዱ ታገኛቸዋለህ:: 6የእግዚአብሔር
መንፈስ በኀይል ይወርድብሃል፤ ከእነርሱ
ጋር ትንቢት ትናገራለህ፤ እንደ ሌላ ሰውም
ሆነህ ትለወጣለህ:: 7እነዚህ ምልክቶች በተ
ፈጸሙ ጊዜ እጅህ ማድረግ የምትችለውን
ሁሉ አድርግ፤ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና::
8“ከፊቴ ቀድመህ ወደ ጌልገላ ውረድ፤
እኔም የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የኅ
ብረት መሥዋዕቱን[†] ለማቅረብ ወደ አንተ
እመጣለሁ፤ ነገር ግን ወደ አንተ መጥቼ
ምን ማድረግ እንዳለብህ እስክነግርህ ድረስ
ሰባት ቀን መቆየት አለብህ::”

**ሳኦል ነገሠ**

9ሳኦል ከሳሙኤል ተለይቶ ለመሄድ ፊቱን
በመለሰ ጊዜ፣ እግዚአብሔር የሳኦልን ልብ
ለወጠው፤ ምልክቱም ሁሉ በዚያ ዕለት
ተፈጸመ:: 10ጊብዓ በደረሱ ጊዜ የነቢያቱ
ጉባኤ አገኙት፤ የእግዚአብሔር መንፈስ በኀ
ይል ወረደበት፤ ከእነርሱም ጋር ትንቢት
ተናገረ:: 11ቀድሞ የሚያውቁት ሁሉ ከነቢ
ያቱ ጋር ትንቢት ሲናገር ባዩት ጊዜ፣
እርስ በርሳቸው፣ “የቂስን ልጅ ምን ነካው?
ሳኦልም ከነቢያት ወገን ነውን?” ሲሉ ተጠ
ያየቁ::
12በዚያ ነዋሪ የሆነ አንድ ሰው፣ “የእነ
ርሱስ አባት ማን ነው?” ብሎ መለሰ:: ስለ
ዚህ፣ “ሳኦልም ከነቢያት ወገን ነውን?”
የሚል ምሳሌያዊ አነጋገር ሆነ:: 13ሳኦል
ትንቢት መናገሩን ከፈጸመ በኋላ ወደ
ማምለኪያው ኰረብታ ሄደ::
14በዚህ ጊዜ የሳኦል አጎት እርሱንና አገል
ጋዩን፣ “የት ነበራችሁ?” ሲል ጠየቃቸው::
እርሱም፣ “አህዮቹን ፍለጋ ሄደን ነበር፤
እንደማይገኙ በተረዳን ጊዜ ግን ወደ
ሳሙኤል ሄድን” አለው::
15የሳኦል አጎትም፣ “እባክህ፣ ሳሙኤል
ያለህን ንገረኝ” አለው::
16ሳኦልም መልሶ፣ “አህዮቹ መገኘታቸውን
ገልጦ ነገረን” አለው:: ይሁን እንጂ ስለ
መንግሡ ሳሙኤል የነገረውን ለአጎቱ አል
ተናገረም::
17ሳሙኤል የእስራኤልን ሕዝብ ወደ ምጽጳ
ወደ እግዚአብሔር ፊት ጠርቶ፣ 18እንዲህ
አላቸው፤ “የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፤ ‘እስራኤልን ከግብፅ አወጣ
ሁት፤ ከግብፃውያን እጅ ይጨቁኗችሁ ከነ

10፥2 ዘፍ35፥20፤ 1ሳሙ9፥4:5
10፥3 ዘፍ35፥8
10፥4 ቍ27፤ 1ሳሙ 16፥20፤ ምሳ18፥16
10፥5 ቍ10:26፤ ዘፍ31፥27፤ ዘሌ 26፥30፤ ዘኍ11፥29፤ 1ሳሙ11፥4፤13፥3፤ 15፥34፤16፥16፤ 18፥10፤ 19፥9:20፤ 1ነገ1፥40፤20፥35፤ 2ነገ 2፥3:15፤3፥15፤ 4፥1፤6፥1፤9፥1፤ 1ዜና25፥1፤መዝ92፥3፤ ኢሳ 30፥29፤ኤር31፥4፤ አሞ7፥14፤1ቆሮ14፥1
10፥6 ቍ9፤ ዘኍ 11፥25
10፥7 ኢሱ1፥5፤ መሳ9፥33፤ 2ሳሙ7፥3፤1ነገ8፥17፤ 1ዜና22፥7፤28፥2፤2 ዜና6፥7፤መክ9፥10፤ ሉቃ1፥28፤ዕብ13፥5
10፥8 ኢሱ4፥20፤ 10፥43፤1ሳሙ7፥16፤ 11፥14፤13፥8
10፥9 ቍ6:7፤ ዘጸ 13፥2
10፥10 ቍ5፤ ዘኍ 11፥25፤ 1ሳሙ11፥6
10፥11 ቍ12፤ 1ሳሙ19፥24፤ 2ነገ9፥11፤ኤር29፥26፤ ሆሴ9፥7፤ ማቴ 13፥54፤ ዮሐ7፥15
10፥12 ቍ 11
10፥13 1ሳሙ19፥23
10፥14 1ሳሙ9፥3፤ 14፥50
10፥16 1ሳሙ9፥3
10፥17 1ሳሙ 7፥5
10፥18 ዘፀ1፥14፤ ዘኍ 10፥9

*1 የዕራይስጥ ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ የሰብዓ ሊቃናትና የቩልጌት ትርጕም ግን፣ *የእግዚአብሔርን ሕዝብ ትገዛለህ ከከበቡት ጠላቶቹም እጅ ታድነዋለህ፤ እግዚአብሔር ለርስቱ ገዥ አድርጐ የሾመህ ምልክቱ ይህ ነው* የሚለውን ይጨምራሉ::
†8 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል::

(ዘፀ 30፥22-33 ይመ):: *እግዚአብሔር ቀብቶህ የለምን?* (የ9:16 ማብ ይመ) *ገዥ፤* 9፥16 እና ማብ ይመ:: *ለርስቱ፤* “ሕዝቤ እስራኤል” (9፥16) ማለት ነው:: የእግዚአብሔር ርስት ሕዝቡና (ዘፀ34፥9) መሬቱ (ዘፀ15፥17) ነው:: ሳኦል፣ ከሳሙኤል ከተለየ በኋላ ንጉሥ እንዲሆን በእግዚአብሔር እንደ ተመረጠና የሳሙኤልም ቃል እውነት መሆኑን ለመረዳት ሦስት ምልክቶች ተሰጥተውታል (ቍ2-7)::

10፥5 *ወደ እግዚአብሔር ተራራ ወደ ጊብዓ፤* የሳኦል አገሩ የብንያም ነገድ የሚኖርበት አገር ነው (ቍ26፡ 11፥4) (ኢሱ 18፥28፤ መሳ 19፥12-14):: “ጊብዓ” ወይም “የብንያም ጊብዓ” (13፥2:15)፣ እንዲሁም ሁለት ጊዜ “የሳኦል ጊብዓ” (15፥34፤ 2ሳሙ21፥6) ተብሎ ተጠርቶአል:: በዚህ ስፍራ ብቻ የሚገኘው አገላለጽ የከነዓናውያን ምድር የፍልስጥኤማውያን ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር መሆኑን ለሳኦል ለማሳየት ሲል ሳሙኤል የተጠቀመበት ነው (ዘፀ32፥43፤ኢሳ14፥2፤ ሆሴ9፥3 ይመ):: *ነቢያት፤* ከሳሙኤል ጋር የነበሩት ነቢያት፣ ኤልያስና ኤልሳዕ እንደ ነበሩበት “የነቢያት ጉባኤ” (የ1ነገ 20፥35 ማብ ይመ) ሁሉ መንፈሳዊ ውድቀት ሲያጋጥም ያላቸውን ሃይማኖታዊ ቅንዓት በአንድነት ለማሳደግ የተሰበሰቡ ሰዎች ኅብረት በመሆን ይታወቃል:: *ትንቢት እየተናገሩ፤* በዚህ ስፍራና በቍ 6:10-11:13 ላይ የተገለጸው፣ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል በመታገዝ ለእግዚአብሔር የሚቀርበውን ምስጋና የሚመለከት ነው (ዘኍ11፥24-30 ይመ)::

10፥7 *እጅህ ማድረግ የምትችለውን ሁሉ አድርግ፤* ሳኦል ሁኔታዎች በሚያስገድዱት ጊዜ፣ ንጉሣዊ አመራሩን ለማሳየት እንደ ሁኔታው ተገቢ የሆነውን ማናቸውንም ዐይነት እርምጃ ዎች መውሰድ ይችላል:: (11፥4-11 ይመ)::

10፥8 *ከፊቴ ቀድመህ ወደ ጌልገላ ውረድ፤* ወደ ፊት ባልታወቀ ጊዜ ለሚሆን፣ ምናልባትም ቀደም ብሎ ለተነገረ ጉዳይ (9፥25 ይመ)፣ ሳኦል ሰባት ቀን ሳሙኤልን ለመጠበቅ ወደ ጌል ገላ መውረድ ነበረበት (13፥7-14 ይመ)::

10፥11 *ሳኦልም ከነቢያት ወገን ነውን?* ቀደም ብለው የሳኦልን ባሕርይ የሚያውቁ ሰዎች በአድናቆት የገለጹት ነው (የቍ5 ማብ ይመ)፤ ስለ ባሕርዩ በፌዝ መልክ የተሰነዘረ አባባል ነው (የ9፥3 ማብ ይመ)::

10፥12 *የእነርሱስ አባት ማን ነው?* አንዳንዶች ይህ ጥያቄ ነቢያትን በአጠቃላይ ለማንኳሰስ ሲባል የቀረበ ገለጻ ነው ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ የነቢይነት አገልግሎት ከእግዚአብሔር እንደሚመጣ ለማመልከትና ይህም እግዚአብሔር ለመረጣቸው የሚሰጥ መሆኑን ለመግለጽ የተሰነዘረ ነው ይላሉ:: ይሁን እንጂ የቀደሙት ነቢያት አንዳንድ ጊዜ “አባቶች” (2ነገ2፥12፤ 6፥21፤ 13፥14) እንደሚባሉ ሁሉ፣ ተናጋሪው በሳሙኤል ላይ ተገቢ ያልሆነ መግለጫ ሰጥቶ ሊሆን ይችላል ወይም ሳኦልን በሽሙጥ ተናግሮት ይሆናል::

10፥17 *ሳሙኤል የእስራኤልን ሕዝብ ... ጠርቶ፤* ሳሙኤል በግሉ ሳኦል ንጉሥ እንዲሆን ከሾመውና ከቀባው በኋላ (9፥1-10፥16)፣ እግዚአብሔር የመረጠውን ለሕዝቡ ለማሳወቅና (ቍ 21) ለንጉሡ የሚገባውን ወግና ሥርዐት ለመግለጽ (ቍ25) ጉባዔ ተጠራ:: *ምጽጳ፤* የ7፥5 ማብ ይመ::

10፥18 *ታደግኋችሁ፤* በታሪካቸው ሁሉ እግዚአብሔር አዳ

በሩት ከሌሎቹ መንግሥታት ሁሉ እጅ
ታደግኋችሁ::" 19ዛሬ ግን ከመከራችሁና ከጭ
ንቀታችሁ ሁሉ የሚያድናችሁን አምላካችሁን
ንቃችሁ፤ 'የለም፤ ንጉሥ አንግሥልን' አላ
ችሁ:: ስለዚህ በየነገዳችሁና በየጐሣችሁ
ሆናችሁ *በእግዚአብሔር ፊት* ቅረቡ::
20ሳሙኤል የእስራኤልን ነገዶች ሁሉ
ባቀረበ ጊዜ፣ የብንያም ነገድ ተመረጠ::
21ከዚያም የብንያምን ነገድ በየጐሣው ወደ
ፊት አቀረበ፤ የማጥሪ ጐሣም ተመረጠ::
በመጨረሻም የቂስ ልጅ ሳኦል ተመረጠ::
እርሱ ግን ተፈልጎ አልተገኘም:: 22ሰዎ
ቹም፣ "ሰውየው መጥቶአልን?' ሲሉ *እግዚ
አብሔርን* ጠየቁ::
*እግዚአብሔርም*፣ "አዎን፤ ነገር ግን በዕቃ
መካከል ተሸሽጎአል" አለ::
23እነርሱም ሮጠው ከተደበቀበት አመጡት፤
በሕዝቡ መካከል በቆመ ጊዜም ቁመቱ
ከሌሎቹ ሁሉ ይልቅ ከትከሻው በላይ ዘለግ
ያለ ነበር:: 24ሳሙኤልም መላውን ሕዝብ፣
"*እግዚአብሔር* የመረጠውን ሰው አያችሁን?
ከሕዝቡ ሁሉ የሚስተካከለው ማንም የለም"
አለ::
ከዚያም ሕዝቡ፣ "ንጉሡ ለዘላለም ይኑር!"
ብለው ጮኹ::
25ሳሙኤልም ለንጉሥ የሚገባውን ወግና
ሥርዐት ለሕዝቡ ገልጦ ካስረዳ በኋላ በመ
ጽሐፍ ጽፎ *በእግዚአብሔር ፊት* አኖረው::
ከዚህ በኋላ ሳሙኤል እያንዳንዱን ሰው
ወደየቤቱ አሰናበተ::
26ሳኦልም ጊብዓ ወዳለው ቤቱ ሄደ፤ *እግዚ
አብሔርም* ልባቸውን የነካው ኀያላን ሰዎች

10፥19 ዘኍ11፥20፤ ዘዳ 17፥14፤33፥5፤ ኢሳ7፥14፤1ሳሙ8፥5፤ መዝ7፥10፤18፥48፤ 68፥20፤145፥19
10፥21 ሐሰ 3፥7፤ ምሳ16፥33
10፥22 ዘፍ25፥22፤ መሳ18፥5
10፥23 1ሳሙ 9፥2
10፥24 ዘዳ17፥15፤ 1ሳሙ9፥2፤2ሳሙ21፥6፤ 1ነገ1፥25:34:39፤ 2ነገ11፥12
10፥25 ዘዳ17፥14-20፤ 1ሳሙ8፥9:11-18፤ 11፥14፤2ነገ11፥12
10፥26 ቍ5፤ መሳ19፥14፤20፥44
10፥27 ቍ4፤ ዘዳ 13፥13፤ 1ሳሙ 20፥7፤ 1ነገ10፥25፤ 2ዜና17፥5፤32፥23፤ መዝ68፥29
11፥1 ዘፍ19፥38፤ ዘዐ23፥32፤መሳ21፥8፤ 1ሳሙ12፥12፤31፥11፤ 2ሳሙ2፥4:5፤10፥2፤ 17፥27፤21፥12፤ 1ዜና19፥1፤ኤር37፥1
11፥2 ዘፍ34፥15፤ ዘኍ 16፥14፤ 1ሳሙ 17፥26
11፥3 ቍ10፤ መሳ2፥16፤1ሳሙ8፥4
11፥4 ዘፍ27፥38፤ ዘኍ25፥6፤1ሳሙ 10፥5:26
11፥6 መሳ3፥10
11፥7 መሳ19፥29፤ 20፥1፤21፥5፤ 1ሳሙ6፥14

አብረውት ሄዱ:: 27አንዳንድ ምናምንቴ
ሰዎች ግን፣ "እንዲህ ያለ ሰው እንዴት
ሊያድነን ይችላል?" በማለት ናቁት፤ ስጦታም
አላመጡለትም:: ሳኦል ግን ዝም አለ::

## ሳኦል የኢያቢስን ከተማ ታደገ

11 አሞናዊው ናዖስ ወጥቶ ኢያቢስ ገለዓ
ድን ከበባት፤ የኢያቢስም ሰዎች
ሁሉ፣ "ከእኛ ጋር ቃል ኪዳን አድ
ርግ፣ እኛም እንገዛልሃለን" አሉት::
2አሞናዊው ናዖስ፣ "ከእናንተ ጋር ቃል
ኪዳን የማደርገው የእያንዳንዳችሁን ቀኝ
ዐይን አውጥቼ እስራኤልን ሁሉ ካዋረድሁ
በኋላ ብቻ ነው" ሲል መለሰ::
3የኢያቢስም ሽማግሌዎች፣ "ወደ መላው
እስራኤል መልእክተኞችን እንድንልክ የሰ
ባት ቀን ጊዜ ስጠን፤ ሊታደገን የሚመጣ ሰው
ከሌለ፣ ለአንተ እንገዛለን" አሉት::
4መልእክተኞቹም ሳኦል ወዳለበት ወደ
ጊብዓ መጥተው ይህን ለሕዝቡ በተናገሩ
ጊዜ፣ ሕዝቡ ሁሉ ድምፃቸውን ከፍ አድ
ርገው አለቀሱ፤ 5በዚህ ጊዜ፣ ሳኦል በሬዎ
ቹን እየነዳ ከዕርሻ ተመለሰ፤ እርሱም፣
"ሕዝቡ የሚያለቅሰው ምን ሆኖ ነው?" ሲል
ጠየቀ:: እነርሱም የኢያቢስ ሰዎች ያሏቸውን
ነገሩት::
6ሳኦል ይህን በሰማ ጊዜ የእግዚአብሔር መን
ፈስ በኀይል ወረደበት፤ እጅግ ተቈጣ:: 7ጥንድ
በሬዎች ወስዶ ቈራረጠ፤ ሥጋቸውንም በመ
ልእክተኞች እጅ ልኮ፣ "ሳኦልንና ሳሙኤ
ልን የማይከተል ሰው በሬው እንደዚህ ይቈ
ራረጣል" ሲል በመላው እስራኤል አስነ

ኛቸው መሆኑን በሳሙኤል በኩል አጥብቆ ይነግራቸዋል:: ከግብፅ ምድር አወጣቸው፤ በመሳፍንት ዘመን ከጠላቶቻቸው ሁሉ ታደጋቸው:: አንዳንድ ጊዜ መሳፍንትም የእስራኤል ታዳጊዎች (መሳ3፥9: 15:31፤ 6፥14፤ 10፥1፤ 13፥5) ተብለው ቢጠሩም እንኳ ይህ እውነት የሚሆነው በሁለተኛ ደረጃ ሲታይ ብቻ ነው፤ ምክንያቱም እነርሱ የእግዚአብሔር የማዳኑ ኀይል መሣሪያ ናቸውና (መሳ 2፥18 ይመ)፤ እነርሱን የላካቸውና የሾማቸው እግዚአብሔር ነው (12፥11፤ መሳ6፥14 ይመ)::

10፥19 *አምላካችሁን ንቃችሁ፤* የ8፥7 ማብ ይመ::

10፥20 *የብንያም ነገድ ተመረጠ፤* ምናልባትም ዕጣ በመጣል ነው (14፥41-42፤ኢሱ7፥15-18 ይመ):: ኡሪምና ቱሚም ለዚህ አገልግሎት ይውሉ ነበር (የ2፥28 ማብ ይመ እና ዘፀ 28፥30 ይመ)::

10፥24 *ንጉሡ ለዘላለም ይኑር፤* 2ሳሙ16፥16 ይመ::

10፥25 *ለንጉሥ የሚገባውን ወግና ሥርዐት፤* ሳሙኤል እዚህ ላይ እስራኤላውያን ስለ ንጉሣዊ አስተዳደር በነበራቸው የተሳሳተ አስተሳሰብና እግዚአብሔር በሚሰጣቸው ንጉሣዊ አስተዳደር መካከል ያለውን ልዩነት በመጀመሪያ ማስተካከል ነበረበት፤ ይህም የንጉሣዊ አስተዳደር ወግና ሥዐርት መግለጫ ለሕዝቡ ጥቅምና ለተመረጠው ንጉሥ ዋስትና ነው፤ ከዚህም በላይ የእስራኤል ንጉሥ በአካባቢው ካሉ የአሕዛብ ነገሥታት የተለየ መሆኑንና የእግዚአብሔር ንጉሥነት በእስራኤል ምድር ተስማሚ መሆኑን ለማሳየት ነው (ዘዳ17፥14 ይመ):: *በእግዚአብሔር ፊት አኖረው፤* ንጉሡ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ሕዝብ ለማስተዳደር የሚጠቀምበት ሕግ ተጽፎ በማደሪያው፣ በኋላም ቤተ መቅደስ በተባለው ውስጥ ይቀመጣል:: የእስራኤልን የኪዳን ግንኙነት በተመለከተ የተጻፉ ሌሎች ጽሑፎች በዘፀ24፥7፤በዘፀ 31፥26፤ እንዲሁም በኢሱ 24፥26 ተጠቅሰዋል::

10፥27 *ምናምንቴ ሰዎች፤* የዘዳ13፥13 ማብ ይመ:: *እንዲህ ያለ ሰው እንዴት ሊያድነን ይችላል?* ሕዝቡ በዚህ ስፍራ ላይ አሁንም በተቃውሞ መልክ የሚገልጸው፣ ብሔራዊ ደኅንነት የሚረጋገጠው በእግዚአብሔር ሳይሆን ሰው በመረጠው ንጉሥ ነው በማለት ነው::

11፥1 *አሞናዊው፤* አሞናውያን የሎጥ ዝርያዎች ሲሆኑ (ዘፍ 19፥38፤ዘዳ2፥19 ይመ)፣ የጋድ ነገድ ከሰፈረበት በስተ ምሥራቅ በያቦቅ ወንዝ ከፍተኛ ቦታዎች ላይ ይኖራሉ (ዘዳ2፥37፤ኢሱ 12፥2ይመ):: አሞናውያን ቀደም ባለው ጊዜ የእስራኤልን ግዛት ለመያዝ ያደረጉት ሙከራ በመሳ3፥13:11፥4-32 ተጠቅሶአል:: ፍልስጥኤማውያን በምዕራብ በኩል እስራኤልን ባጠቁ ጊዜ፣ አሞናውያንም ይህን አጋጣሚ በመጠቀም እስራኤልን በምሥራቅ በኩል ለማጥቃት ሞክረው ከጕዳት አምልጠዋል:: *ኢያቢስ ገለዓድ፤* ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ የምናሴ ነገድ በሚኖርበት ቦታ ያለች ከተማ ናት::

11፥2 *ቀኝ ዐይን አውጥቼ፤* ከማዋረድም በላይ (የመሳ 16፥21 ማብ ይመ) ቀኝ ዐይናቸውን ማውጣት እጅግ የከፋና ዘግናኝ ጭካኔ ነው::

11፥4 *ሳኦል ወዳለበት ወደ ጊብዓ፤* 10፥26 እና 10፥5 ማብ ይመ:: በኢያቢስ ለሚኖሩ ለብንያም ነገድ ሰዎች ቀረቤታ ስላላቸው ርዳታ ለማግኘት መልእክተኞችን ላኩ (መሳ 21፥12-14 ይመ)::

11፥5 *ሳኦል ... ከዕርሻ ተመለሰ፤* ሳኦል በምጽጳ የተመረጠው ንጉሥ እርሱ መሆኑ ለሕዝብ ከተገለጠ በኋላ (10፥17-27)፣ ወደ ቤቱ ተመልሶ (10፥26) ቀደም ብሎ ይሠራ የነበረውን የግል ሥራ እየሠራ ወደ ዙፋን ለመውጣት የሚያስፈልገውን የእግዚአብሔር አመራር ይጠባበቅ ነበር (የቍ15 እና 10፥7 ማብ ይመ)::

11፥6 *የእግዚአብሔር መንፈስ በኀይል ወረደበት፤* በእስራኤል ታዳጊዎች ላይ ስለ ወረደው ተመሳሳይ የእግዚአብሔር ኀይል 10፥6:10፤ መሳ14፥6:19፤ 15፥14 ይመ::

11፥7 *ሥጋቸውንም በመልእክተኞች ... በመላው እስራኤል፤* ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ስለሆኑ ነገሮች መሳ 19፥29 ይመ::

ገረ:: ታላቅ ፍርሀት ከእግዚአብሔር ዘንድ
በሕዝቡ ላይ ወደቀ፤ ሕዝቡም እንደ አንድ
ሰው ሆኖ ወጣ:: 8ሳኦል ቤዜቅ በተባለ ስፍራ
ሰራዊቱን በሰበሰበ ጊዜ፤ ቊጥራቸው ከእስ
ራኤል ሦስት መቶ ሺህ፣ ከይሁዳም ሠላሳ
ሺህ ነበር::
9ከዚያ ለመጡትም መልእክተኞች፣ "ለኢ
ያቢስ ገለዓድ ሰዎች፣ 'ነገ ፀሓይ ሞቅ በሚ
ልበት ጊዜ ነጻ ትሆናላችሁ' ብላችሁ ንገሯ
ቸው" አሏቸው:: መልእክተኞቹም ሄደው
ለኢያቢስ ሰዎች ይህንኑ በነገሯቸው ጊዜ
በደስታ ፈነደቁ:: 10ለአሞናውያንም፣ "እኛ
ነገ እጃችንን እንሰጣችኋለን፤ እናንተም መል
ካም መስሎ የታያችሁን ሁሉ ልታደርጉብን
ትችላላችሁ" አሏቸው::
11በማግስቱ ሳኦል ሰራዊቱን ከሦስት ቦታ
ከፈለው፤ ሊነጋጋ ሲል፣ የአሞናውያንን ሰፈር
ጥሰው በመግባት ፀሓይ ሞቅ እስኪል
ድረስ ፈጇቸው:: በሕይወት የተረፉትም
ሁለት እንኳን ሆነው በአንድ ላይ ሊሆኑ
እስከማይችሉ ድረስ ተበታተኑ::

### የሳኦል ንጉሥነት ተረጋገጠ

12ሕዝቡ ሳሙኤልን፣ "'ሳኦል እንዴት ሊገ
ዛን ይችላል!' ያሉት እነማን ነበሩ? እነዚህን
ሰዎች እንገድላቸው ዘንድ አምጣቸው" አሉት::
13ሳኦል ግን፣ "ይህ ዕለት እግዚአብሔር
እስራኤልን የታደገበት ቀን ስለሆነ ፣በዛ
ሬው ዕለት ማንም ሰው አይገደልም" አለ::
14ከዚያም ሳሙኤል ሕዝቡን፣ "ኑና ወደ
ጌልገላ እንሂድ፤ ንግሥናውን እናጽና" አለ::
15ሕዝቡ ሁሉ ወደ ጌልገላ ሄደ፤ የሳኦልንም
ንጉሥነት በእግዚአብሔር ፊት አጸና:: በዚ
ያም ሕዝቡ የኅብረት መሥዋዕት* በእግዚ
አብሔር ፊት አቀረበ፤ ሳኦልና እስራኤላ
ውያንም ሁሉ ታላቅ በዓል አደረጉ::

### ሳሙኤል ያደረገው የመሰነባበቻ ንግግር

12 ሳሙኤል ለመላው እስራኤል እን
ዲህ አለ፤ "እነሆ፤ ያላችሁኝን ሁሉ
ሰምቼ ንጉሥ አንግሼላችኋለሁ:: 2ንጉሥ ሆኖ
የሚመራችሁንም ሰው እነሆ፤ አግኝታችኋል::
እኔም ዕድሜዬ ገፍቶአል፤ ጠጒሬም ሸብቶ
አል፤ ልጆቼም አብረዋችሁ አሉ፤ ከወጣት
ነት ጊዜዬ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ስመ
ራችሁ ቈይቻለሁ:: 3እነሆ፤ ከፊታችሁ ቆሜ
አለሁ፤ በእግዚአብሔርና እርሱ በቀባው ፊት
መስክሩብኝ፤ የማንን በሬ ወሰድሁ? የማንን
አህያ ወሰድሁ? ማንን አታለልሁ? በማንስ
ላይ ግፍ ሠራሁ? አይቶ እንዳላየ ለመሆ
ንስ ከማን እጅ ጉቦ ተቀበልሁ? ከእነዚህ
ሁሉ አንዱን እንኳ አድርጌ ከሆነ እመል
ስላችኋለሁ::"
4እነርሱም፣ "አላታለልኸንም ወይም ግፍ
አልሠራህብንም፤ ከማንም እጅ አንዳች ነገር
አልተቀበልህም" ብለው መለሱለት::
5ሳሙኤልም፣ "በእጄ ምንም እንዳላገኛችሁ
እግዚአብሔርና እርሱ የቀባው ዛሬ በእና
ንተ ላይ ምስክሮች ናቸው" አላቸው::
እነርሱም፣ "እርሱ ምስክር ነው" አሉ::
6ከዚያም ሳሙኤል ለሕዝቡ እንዲህ አለ፤
"ሙሴንና አሮንን የመረጠ፣ የቀድሞ አባ
ቶቻችሁንም ከግብፅ ያወጣ እግዚአብሔር
ነው:: 7አሁንም ለእናንተና ለአባቶቻችሁ
እግዚአብሔር ስላደረገው የጽድቅ ሥራ ሁሉ

*15 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል::

11፥8 መሳ1፥4፤ 20፥2
11፥10 ቊ 3
11፥11 ዘፍ19፥38፤ መሳ7፥16
11፥12 ዘዳ13፥13፤ ሉቃ19፥27
11፥13 1ሳሙ19፥5 ፤ 2ሳሙ19፥22፤ 1ዜና11፥14
11፥14 ኢሳ10፥43፤ 1ሳሙ10፥8:25
11፥15 ኢሱ5፥9፤ 1ሳሙ12፥1፡ 2ሳሙ19፥15
12፥1 1ሳሙ8፥7፤ 11፥15
12፥2 1ሳሙ8፥3:5
12፥3 ዘፀ18፥21፤ 20፥17፤ዘሌ25፥14፤ ዘኍ16፥15፤1ሳሙ8፥3፤ 9፥16፤24፥6፤26፥9፡ 11፤2ሳሙ1፥14፤ 19፥21፤መዝ105፥15፤ ሐሥ20፥33
12፥5 ዘፍ31፥50፤ ዘፀ22፥4፤ሐሥ23፥9፤ 24፥20
2፥6 ዘፀ3፥10፤ ሚክ 6፥4
12፥7 ኢሱ24፥1፤ መሳ5፥11ኢሳ1፥18፤ 3፥14፤ኤር2፥9፤ 25፥31፤ሕዝ17፥20፤ 20፥35፤ሚክ 6፥1-5

11፥8 *ቤዜቅ፤* ከኢያቢስ ገለዓድ ብዙ ሳይርቅ፣ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምዕራብ በሰሜናዊ ሴኬም ይገኛል::

11፥11 *ሊነጋጋ ሲል፤* በአይሁድ የጊዜ አቈጣጠር ሦስተኛው ሰዓት ማለት ሲሆን፣ ይህም ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት እስከ ንጋቱ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ድረስ ያለው ጊዜ ነው (ማቴ 14፥25 ማብ ይመ)::

11፥13 *እግዚአብሔር እስራኤልን የታደገበት፤* ሳኦል እውነተኛና የእስራኤል ታዳጊ የሆነውን እግዚአብሔርን ዐውቆ አከበረው (የ10፥18ን ማብ ይመ):: የተገኘው ድል፣ ሳኦል ራሱ በአፉ ከመሰከረው ጋር፣ እርሱ በእግዚአብሔር የተመረጠ ሰው ለመሆኑ መለኮታዊ ማረጋገጫ ነው::

11፥14 *ወደ ጌልገላ እንሂድ፤ ንግሥናውን እናጽና፤* በዚህ ጊዜ ሳሙኤል ማረጋገጥ የፈለገው እግዚአብሔር ጌታቸው መሆኑን ሕዝቡ እንዲያውቁ ነው:: መንግሥቱ የእግዚአብሔር እንጂ የሳኦል አለመሆኑንም ማረጋገጡ ነበር:: ሳሙኤል ጉባኤ የጠራው ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን የቃል ኪዳን ግንኙነት እንዲያድስ ነው:: ከዚህም በላይ በዚህ በአዲሱ ዘመን እግዚአብሔር በእስራኤል ሕዝብ ላይ ያለው ንጉሥነት በምንም መን ገድ ሊሻር እንደማይችል ለመግለጽ አስቦ ነው:: በቍ14-15 ላይ ያለው አጭር መግለጫ በምዕራፍ ዐሥራ ሁለት ላይ በስፋት ከተገለጸው ጋር የሚያያዝ ነው:: *ጌልገላ፤* በዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ፣ ከኢያሪኮ በስተ ምሥራቅ የሚገኝ ስፍራ ነው፤ እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ያላቸውን ታማኝነት የሚያድሱትም በዚሁ ስፍራ ነበር (ኢሱ 4፥19-5፥11፤ 10፥8-15)::

11፥15 *የሳኦልንም ንጉሥነት በእግዚአብሔር ፊት አጸና፤* ቀደም ብሎ ሳኦል ብቻውን ሳለ በአርማቴም በነቢዩ ሳሙኤል ተቀባ (10፥1)፤ በሕዝብም ፊት እግዚአብሔር የመረጠው ንጉሥ መሆኑ በምጽዳ ተነገረለት (10፥17-27):: በተከታዩ ታሪክ፣ አሞናዊው ረብሻ ባስነሣ ጊዜ (ቍ1-13)፣ የሳኦል አመራር በተሰጠው የመንግሥት ሥልጣን የሕዝብ ዕውቅና አግኝቶ አልጸደቀም፤ ነገር ግን በተገኘው ወታደራዊ ድል በሕዝብ ተረጋገጠለት:: ሳኦል አሁን በጌልገላ እግዚአብሔር የመረጠው ንጉሥ መሆኑ በነቢዩ በሳሙኤል በዐዋጅ ተነገረለት፤ መብቱንና ግዴታውንም ወዲያውኑ የራሱ አደረገ፤ ሥራውንም ጀመረ:: *የኅብረት መሥዋዕትን፤* በሲና ተራራ ላይ ቃል ኪዳን በሚጸድቅበት ወይም በሚታደስበት ጊዜ፣ ይህን ዐይነት ሥርዐት መፈጸም የተለመደ ነበር (ዘፀ24፥5:11):: ሕዝቡ የቃል ኪዳን ግዴታቸውን ጠብቀው ሲኖሩ፣ በእነርሱና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ግንኙነትና ሰላም ያመለክታል (ዘሌ7፥11-17፤22፥21-23 ይመ):: *ታላቅ በዓል አደረጉ፤* ከአምላኩ ጋር ቃል ኪዳን ሳደሰ፣ ኀጢአቱን ለተናዘዘና ንጉሥ ለተሰጠው ሕዝብ ደስታ ዐይነተኛ መግለጫ ነው::

12፥3 *መስክሩብኝ፤* ሳሙኤል አዲስ የተመረጠውን ንጉሥ ለሕዝቡ በሚያሳውቅበት ጊዜ፣ ቀደም ባለው ዘመን የሕዝቡ መሪ በመሆን ለቃል ኪዳኑ ታማኝ እንደ ነበረም ጭምር ማረጋገጥ ነበረበት:: ዐላማውም ራሱን ነጻ ለማድረግና ለተመረጠውም ሳኦል የራሱን ምሳሌነት ለማሳየት ነበር:: *የማንን በሬ ወሰድሁ? የማንን አህያ ወሰድሁ?* ዘፀ 20፥17፤22፥1:4:9 ይመ:: ሳሙኤል የተሰጠውን ሥልጣን ለግል ጥቅሙ አላዋለውም (ዘኍ 16፥15 ይመ):: *ማንን አታለልሁ? በማንስ ላይ ግፍ ሠራሁ?* ዘሌ 19፥13፤ ዘዳ24፥14 ይመ:: *ከማን ... ጉቦ ተቀበልሁ?* ዘፀ23፥8፤ ዘዳ16፥19 ይመ::

12፥6 *ሳሙኤል ለሕዝቡ እንዲህ አለ፤* ሳሙኤል ቀደም ብሎ አትኵሮበት የነበረውን የራሱን የአመራር ጒዳይ ተወት በማድረግ፣ እግዚአብሔርን ማክድና ቃል ኪዳኑን ማፍረስ ነው ብሎ ወደ አመነበት ወደ ሕዝቡ የንጉሥ ጥያቄ ዘወር አለ:: *እግዚአብሔር ነው፤* በቀደሙት ዘመናት ተገቢውን አመራር የሰጠ፣ ሕዝቡንም የመራ እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ሳሙኤል አጥብቆ ይናገራል::

12፥7 *እግዚአብሔር ስላደረገው የጽድቅ ሥራ፤* እነዚህ የጽድቅ ሥራዎች (ቍ8-11 ይመ) ባለፉት ዘመናት እግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ሆኖ መዝለቁን ሲያመለክቱ፣ በተቃራኒው

*በእግዚአብሔር ፊት ስለምሟገታችሁ በዚህ*
*ቁሙ::*
8"ያዕቆብ ወደ ግብፅ ከገባ በኋላ፣ አባቶ
ቻችሁ እግዚአብሔር እንዲረዳቸው ወደ
እርሱ ጮኹ፤ እግዚአብሔርም የቀድሞ አባ
ቶቻችሁን ከግብፅ ምድር አውጥተው በዚህ
ስፍራ እንዲኖሩ ያደረጉትን ሙሴንና አሮ
ንን ላከላቸው::
9"እነርሱ ግን አምላካቸውን እግዚአብሔርን
ረሱት፤ ስለዚህ ለሐጾር የጦር አዛዥ ለሲ
ሣራ፣ ለፍልስጥኤማውያንና ለሞዓብ ንጉሥ
አሳልፎ ሸጣቸው:: 10እነርሱም፣ 'ኀጢአት
ሠርተናል፤ እግዚአብሔርን ትተን በአሊ
ምንና አስታሮትን አምልከናል:: አሁን ግን
ከጠላቶቻችን እጅ ታደገን፤ እኛም አንተን
እናመልካለን' ሲሉ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ::
11ከዚያም እግዚአብሔር ይሩበኣልን[ጀ]፣ ባር
ቅን[ገ]፣ ዮፍታሔንና ሳሙኤልን[መ] ልኮ በሰላም
ትኖሩ ዘንድ በዙሪያችሁ ካሉት ጠላቶ
ቻችሁ እጅ ታደጋችሁ::
12የአሞናውያን ንጉሥ ናዖስ እንደ መጣ
ባችሁ ባያችሁ ጊዜ ግን፣ ምንም እንኳ አም
ላካችሁ እግዚአብሔር ንጉሣችሁ ቢሆንም፣
'አይሆንም፤ የሚገዛን ንጉሥ እንፈልጋለን'
አላችሁ:: 13"አሁንም የጠየቃችሁትና የመረ
ጣችሁት ንጉሥ ይኸው፤ እነሆ፣ እግዚአ
ብሔር በላያችሁ ንጉሥ አንግሦአል:: 14እግ
ዚአብሔርን የምትፈሩና የምታመልኩ፣ የም
ትታዘዙትና በትእዛዙ ላይ የማታምፁ ከሆነ፣
እንዲሁም እናንተና በእናንተ ላይ የነገሠው
ንጉሥ አምላካችሁን እግዚአብሔርን ከተከተላ
ችሁ መልካም ይሆንላችኋል:: 15እግዚአብሔርን
የማትታዘዙና በትእዛዛቱም ላይ የምታምፁ
ከሆነ ግን፣ እጁ በአባቶቻችሁ ላይ እንደ
ነበረች ሁሉ በእናንተም ላይ ትሆናለች::
16"ስለዚህ ጸንታችሁ ቁሙ፤ እግዚአብሔር
በዐይናችሁ ፊት የሚያደርገውንም ይህን ታላቅ
ነገር ተመልከቱ! 17አሁን የስንዴ መከር ጊዜ
አይደለምን? እኔ ነጐድጓድና ዝናብ እንዲ
ልክ ወደ እግዚአብሔር እጮኻለሁ፤ እናን
ተም ንጉሥ እንዲነግሥላችሁ በመጠየቃችሁ
በእግዚአብሔር ፊት የቱን ያህል የከፋ
ድርጊት እንደፈጸማችሁ ያን ጊዜ ታውቃላ
ችሁ::"
18ከዚህ በኋላ ሳሙኤል ወደ እግዚአብሔር
ጮኸ፤ በዚያኑ ዕለት እግዚአብሔር ነጐድ
ጓድና ዝናብ ላከ:: ስለዚህ ሕዝቡ ሁሉ
እግዚአብሔርንና ሳሙኤልን እጅግ ፈሩ::
19ሕዝቡም ሁሉ ሳሙኤልን፣ "ሌላው በደ
ላችን ሳያንስ፣ ንጉሥ እንዲነግሥልን በመጠ
የቃችን ተጨማሪ ክፋት ስላደረግን እንዳን
ሞት፣ ለአገልጋዮችህ ወደ አምላክህ ወደ
እግዚአብሔር ጸልይልን" አሉት::
20ሳሙኤልም እንዲህ ብሎ መለሰ፤ "አት
ፍሩ፤ ይህን ሁሉ ክፋት አድርጋችኋል፤ ሆኖም
እግዚአብሔርን በፍጹም ልባችሁ አምል
ኩት እንጂ እግዚአብሔርን ከመከተል ፈቀቅ
አትበሉ:: 21ሊጠቅሟችሁ ወይም ሊያድኗችሁ
የማይችሉ ምናምንቴ ነገሮችን አትከተሉ፤
ከንቱ ናቸውና:: 22እግዚአብሔር የራሱ ሕዝብ
ያደርጋችሁ ዘንድ ስለ ወደደ፣ ስለ ታላቅ
ስሙ ሲል እግዚአብሔር ሕዝቡን አይተውም::

[ጀ]11 ጌድዎን በመባል ይታወቃል::
[ገ]11 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት የሱርስት ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማ ማሉ፤ ዕብርይስጡ ግን፣ ቢዳን ይላል
[መ]11 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት የሱርስቱ ቅጅ ግን ሳንሶን ይላሉ::

12፥8 ዘፍ46፥6፤ ዘፀ2፥23፤3፥10፤4፥16
12፥9 ዘዳ32፥18፡ 30፤ኢሱ11፥1፤ መሳ 3፥7፡12፤4፥2፤10፥7
12፥10 መሳ3፥9 1ሳሙ7፥3፤8፥8
12፥11 መሳ4፥6፤ 6፥32፤11፥1፤1ሳሙ7፥15
12፥12 1ሳሙ8፥5፤ 11፥1፤25፥30፤ 2ሳሙ 5፥2፤1ዜና5፥2
12፥13 1ሳሙ8፥5፤ 9፥20
12፥14 ኢሱ24፥14 ኤር4፥17፤ሰቆ1፥18
12፥15 ዘሌ26፥16፤ ኢሱ24፥20፤ኢሳ 1፥20፤ ኤር4፥17፤ 26፥4
12፥16 ዘፀ14፥13፡ 14
12፥17 ዘፍ7፥12፤ 30፥14፤ዘፀ9፥18፡23፤ 1ሳሙ2፥10፤6፥13፤ 8፥6፤1ነገ18፥42፤ ኢዮ37፥13፤ምሳ26፥11 ያዕ 5፥18
12፥18 ዘፍ3፥፥10፤ ዘፀ14፥31፤መዝ99፥6
12፥19 ዘፀ8፥8፤ ዘዳ9፥19፤1ሳሙ7፥8፤ ኤር37፥3፤ያዕ5፥18፤ 1ዮሐ5፥16
12፥20 ዘፀ32፥30
12፥21 ዘዳ11፥16፤ ኢሳ40፥20፤41፥24፡ 29፤44፥9፤ኤር2፥5፡ 11፤14፥22፤16፥16፤ ዕን2፥18፤ዮሐ2፥8፤ ሐሥ14፥15
12፥22 ዘሌ26፥11፤ ዘዳ7፥7፤31፥6፤ ኢሱ7፥9፤2ሳሙ7፥23፤ መዝ25፥11፤106፥8 ኢሳ48፥9፡11፤ ኤር14፥7፤ዳን9፥19፤ ዮሐ 7፥12፤1ጴጥ2፥9

ደግሞ ሕዝቡ አሁን ላሳየው ክህደት የክስ ማስረጃዎች ናቸው:: *ስለምሟገታችሁ፤* አባባሉ በቍ 2-5 እንዳለው የሕግ አሠራርን የተከተለ ሲሆን፣ አሁን ጉዳዩ የሚመለከታቸው ቡድኖች ግንኙነት ግን ተለውጦአል:: በዚህ ጊዜ ከሳሽ ሳሙኤል ሲሆን፣ ተከሳሽ ሕዝቡ፣ ዳኛው ደግሞ እግዚአብሔር ነው::

12፥11 *ታደጋችሁ፤* ንጉሥ መፈለጋቸው እግዚአብሔርን መክዳት መሆኑን በማሳየት እስከ ሳሙኤል ዘመን መጨረሻ ድረስ እግዚአብሔ እስራኤላውያንን በተደጋጋሚ ከጠላቶቻቸው እጅ አድኖአቸዋል (7፥3፡8፡10፡12)::

12፥12 *ናዖስ እንደ መጣባችሁ ባያችሁ ጊዜ፤* በእስራኤላውያን ከሁለት በኩል ማለትም ከምዕራብ ፍልስጥኤማውያን (9፥16)፣ ከምሥራቅ ደግሞ አሞናውያን (11፥1-13) በወረሯቸው ጊዜ ከእግዚአብሔር ይልቅ ምድራዊ ንጉሥ እንዲታደጋቸው ፈለጉ:: *እግዚአብሔር ራሱ ንጉሣችሁ፤* እስራኤላውያን ከግብፅ ምድር ወጥተው ወደ ከነዓን ባደርጉት የጉዞ እንዲሁም በመሳፍንት ዘመን እግዚአብሔር በታማኝነቱ ያደረገላቸውን ጥበቃ በመርሳት፣ የእርሱንም ንጉሥነት በመናቅ የሰውን አመራር በመፈለጋቸው እግዚአብሔር ንጉሣቸው እንደ ነበር እንደ ኀ ለመግለጽ የገባ አባባል ነው (8፥7 ማብ ይመ)::

12፥13 *እግዚአብሔርም በላያችሁ ንጉሥ አንግሦአል፤* የሕዝቡ ጥያቄ በዐመፅ የተሞላ ቢሆንም እግዚአብሔር በራሱ መንግሥታዊ አስተዳደር ውስጥ እንዲካተት የንጉሥን አገዛዝ ፈቀደላቸው፤ ሁነኛም ሰው መረጠላቸው:: ይህ የንጉሥ አስተዳደር የተፈቀደው ለእግዚአብሔር አስተዳደር ማስፈጸሚያ መሣሪያ በመሆን እንዲያገለግል ነው::

12፥14 *እግዚአብሔርን የምትፈሩ ... ከሆነ፤* እስራኤላውያን ከሚጀምሩት ከአዲሱ ንጉሣዊ አስተዳደር ጋር፣ የቀደመውን የቃል ኪዳን ግንኙነት ሁኔታ (ዘፀ19፥5-6፤ ዘዳ8፥19፤ 11፥13-15፡ 22-28፤ 30፥17-18፤ ኢሱ24፥20 ይመ) ሳሙኤል በዚህ ስፍራ ያገናዝበዋል:: *እናንተና በእናንተ ላይ የነገሠው ንጉሥ አምላካችሁን እግዚአብሔርን ተከተላችሁ መልካም፤* ምድራዊ አገዛዝ እንዲመሠረት እግዚአብሔር ቢፈቅድም፣ እስራኤልና ንጉሷ እግዚአብሔር እውነተኛ ንጉሣቸው እንደ ሆነ ማረጋገጥ እንዳለባቸው ይጠበቃል:: በአዲሱ የአስተዳደር ዘመን ለምድራዊ ንጉሥና ለእግዚአብሔር በመታዘዝ መካከል ግጭት ሊኖር እንደሚችል ቢታመንም፣ እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ያላቸው ታዛዥነት በምንም መንገድ መጣስ አይገባውም:: "መከተል" ስለሚለው ቃል ተመሳሳይ አገላለጽ 2ሳሙ2፥10፤15፥13፤1ነገ12፥20፤16፥21 ይመ::

12፥15 *የማትታዘዙና... ከሆነ ግን፤* ሙሴ ከዘመናት በፊት የተናገረውን ተመሳሳይ አማራጭ ሳሙኤልም ለእስራኤላውያን በመንገር ያለመታዘዝን ውጤት ያሳያቸዋል (ዘዳ28፤30፥15-20 ይመ):: ወደ እስራኤላውያን ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ሕይወት የገባው አዲሱ መንግሥታዊ አስተዳደር፣ እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን መሠረታዊ ግንኙነት አልለወጠውም::

12፥16 *ይህን ታላቅ ነገር ተመልከቱ፤* ሳሙኤል በተናገረው ቃል እግዚአብሔር እውነተኛነቱንና ታማኝነቱን ለማረጋገጥ በኀይል ራሱን የሚገልጽበትን ሁኔታ የእስራኤል ሕዝብ እንዲመለከት አደረገ::

12፥17 *የስንዴ መከር፤* የ6፥13 ማብ ይመ ::

12፥19 *ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይልን፤* የሳሙኤል ክስ (ቍ 6-15) በድርቅ ወቅት፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ አስፈሪ ነጐድጓድንና ዝናብን በሕዝቡ ላይ አመጣ (ቍ16-18)፤ ይህም ሁኔታ ሕዝቡ ኀጢአታቸውን እንዲናዘዙና ሳሙኤልም ለእነርሱ ይጸልይላቸው ዘንድ እንዲለምኑት አስገደዳቸው::

12፥20 *እግዚአብሔርን... ፈቀቅ አትበሉ፤* ንጉሣዊ አስተዳደርን በእስራኤል በመመሥረት ዙሪያ ያለውን ዐቢይ ጉዳይ እንደገና በመጥቀስ ትኵረት እንዲደረግበት ለእስራኤላውያን ያሳስባል::

12፥21 *ምናምንቴ ነገሮችን፤* ከእግዚአብሔር ጋር ሊፎካከሩ የሚችሉ አማልክት የሉም፤ እንዳቸውም ለደኅንነትና ለጥበቃ ዋስትና አይሰጡም::

23ከዚህም በላይ እኔ ለእናንተ ከመጸለይ
ወደ ኋላ በማለት እግዚአብሔርን መበደል
ከእኔ ይራቅ፤ እኔ መልካምና ቅን የሆነውን
መንገድ አስተምራችኋለሁ። 24ብቻ እግዚ
አብሔርን ፍሩ፤ በፍጹም ልባችሁ በታ
ማኝነት አምልኩት፤ ያደረገላችሁንም ታላላቅ
ነገሮች አትርሱ። 25በክፉ ሥራችሁ ብትጸኑ
ግን፣ እናንተም ንጉሣችሁም ትጠፋላችሁ።”

## ሳሙኤል ሳኦልን መገሠጹ

13 ሳኦል በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሠላሳ[ሙ]
ዓመት ነበረ፤ እስራኤልንም አርባ[ሽ]
ሁለት ዓመት ገዛ።
2ሳኦል[ቀ] ከእስራኤል ሦስት ሺህ ሰዎች
መረጠ። ሁለቱ ሺህ በማክማስና በኰረብታ
ማው አገር በቤቴል ከሳኦል ጋር፣ አንዱ
ሺህ ደግሞ በብንያም ግዛት በጊብዓ ከዮና
ታን ጋር ነበሩ። የቀሩትን ሰዎች ግን ወደ
የቤታቸው እንዲሄዱ አሰናበተ።
3ዮናታን ጊብዓ የነበረውን የፍልስጥኤማ
ውያን ጦር ሰፈር መታ፤ ፍልስጥኤማውያ
ንም ይህን ሰሙ። ሳኦልም፣ “ዕብራውያን ይስ
ሙት!” በማለት በምድሪቱ ሁሉ መለከት
አስነፋ። 4ስለዚህ እስራኤላውያን ሁሉ፣
“ሳኦል የፍልስጥኤማውያንን ጦር ሰፈር
መታ፤ እስራኤልም በፍልስጥኤማውያን ዘንድ
እንደ ርኩስ ተቈጥራ ተጠላች” የሚለውን
ወሬ ሰሙ፤ ሕዝቡም ሳኦልን ለመከተል
ወደ ጌልገላ ተሰበሰቡ።
5ፍልስጥኤማውያን ሦስት[ሰ] ሺህ ሠረገሎች፣
ስድስት ሺህ ፈረሰኞች ቍጥሩ እንደ ባሕር
አሸዋ የበዛ ሰራዊት ይዘው እስራኤልን
ለመውጋት ተሰበሰቡ፤ ወጥተውም ከቤት
አዌን በስተ ምሥራቅ ባለችው በማክማስ
ሰፈሩ። 6እስራኤላውያን፣ ያሉበት ሁኔታ
እጅግ የሚያሠጋ መሆኑንና ሰራዊታቸውም
በከባድ ጭንቀት ውስጥ መግባቱን ባዩ ጊዜ፣

12፥23 ዘኍ11፥2፤ 1ሳሙ1፥20፤7፥8፤ 1ነገ8፥36፤መዝ25፥4፤ 34፥11፤86፥11፤ 94፥12፤ምሳ4፥11፤ ሮሜ1፥10
12፥24 ዘዳ6፥2፡5፤ 10፥21፤ኢሱ24፥14፤ ኢዮ34፥27፤መክ12፥3፤ ኢሳ5፥12፤ 22፥11፤26፥10
12፥25 ዘዳ28፥36፤ ኢሱ24፥20፤1ሳሙ 31፥1-5፤1ነገ14፥10
13፥2 ቍ5፡11፡ 15፡23፤መሳ19፥14፤ ነህ11፥31፡ኢሳ10፥28
13፥3ዘሌ25፥9፤ ኢሱ 18፥24፤መሳ3፥27፤ 1ሳሙ10፥5
13፥4 ዘፍ34፥30
13፥5 ቍ2፡ ኢሱ 7፥2፤11፥4፤1 ሳሙ 17፥1፤ራእ20፥8
13፥6 መሳ6፥2፤ 1ሳሙ14፥11፡22፤ ሕዝ 33፥27
13፥7 ዘፍ35፥5፤ዘፀ 19፥16፤ዘኍ32፥33
13፥8 1ሳሙ10፥8
13፥9 ዘዳ12፥5- 14፤2ሳሙ24፥25፤ 1ነገ3፥4
13፥10 1ሳሙ15፥13 ፤25፥14
13፥11 ቍ2
13፥12 ዘዳ4፥29፤ ኢሱ10፥43፤መዝ 119፥58፤ኤር26፥19
13፥13 ቍ14፤ኢሱ 22፥16፤1ሳሙ15፥23፡ 24፤2ሳሙ7፥15፤ 1ዜና10፥13፤16፥9፤ መዝ72፥5

በየዋሻውና በየቍጥቋጦው፣ በየዐለቱ መካከ
ልና በየገደሉ እንዲሁም በየጕድጓዱ ሁሉ
ተደበቁ። 7ከዕብራውያንም አንዳንዶቹ ዮር
ዳኖስን ተሻግረው ወደ ጋድና ወደ ገለዓድ
ምድር ሄዱ።
ሳኦል ግን በጌልገላ ቈየ፣ አብሮት
የነበረውም ሰራዊት ሁሉ በፍርሀት ይንቀጠ
ቀጥ ነበር። 8እርሱም ሳሙኤል በሰጠው ቀጠሮ
መሠረት ሰባት ቀን ጠበቀው። ነገር ግን
ሳሙኤል ወደ ጌልገላ አልመጣም፤ የሳ
ኦልም ሰራዊት መበታተን ጀመረ። 9በዚህ
ጊዜ ሳኦል፣ “የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የኅ
ብረት መሥዋዕቱን[ኍ] አምጡልኝ” አለ። ከዚ
ያም የሚቃጠለውን መሥዋዕት አቀረበ።
10ልክ መሥዋዕቱን አቅርቦ እንዳበቃ፣ ወዲ
ያውኑ ሳሙኤል መጣ፤ ሳኦልም ሊቀበለው
ወጣ።
11ሳሙኤልም፣ “ያደረግኸው ምንድን
ነው?” ሲል ጠየቀው።
ሳኦልም እንዲህ ሲል መለሰ፤ ሰራዊቱ
መበታተኑን፣ አንተም በቀጠርኸው ጊዜ
አለመምጣትህን፣ ፍልስጥኤማውያንም በማ
ክማስ መሰብሰባቸውን አየሁ፤ 12‘ስለዚህ ፍል
ስጥኤማውያን ወርደው ወደ ጌልገላ ይመጡ
ብኛል፤ እኔም የእግዚአብሔርን ሞገስ አልለ
መንሁም’ ብዬ አሰብሁ። ስለዚህ የሚቃጠል
መሥዋዕት ማቅረብ ግድ ሆነብኝ።”
13ሳሙኤልም እንዲህ አለ፤ “የማይገባህን
አደረግህ፤ ስምላክህ እግዚአብሔር የሰጠህን
ትእዛዝ አልጠበቅህም፤ ጠብቀኸው ቢሆን

[ሙ]1 ጥንታዊ ያልሆኑ ጥቂት የሰብዓ ሊቃናት ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን ሠላሳ የሚለውን አይጨምርም
[ሽ]1 የዐሥር ብዜት የሆኑት ቍጥሮች በተመለከተ ቤሐሥ13፥21 ይመ፤ ዕብራይስጡ ግን አርባ የሚለውን አይጨምርም።
[ቀ]1፡2 ወይም እርሱ በእስራኤል ላይ ለሁለት ዓመት ከነገሠ በኋላ
[ሰ]5 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞችና የሱርስቱ ቅጅ ከዚህ ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን ሠላሳ ሺህ ይላል።
[ኍ]9 በትውፊት የሰላም መሥዋዕት ይባላል።

12፥23 *መልካምና ቅን የሆነውን መንገድ አስተምራችኋለሁ፤* ሳሙኤል አዲሱን ንጉሥ ለእስራኤል ሕዝብ ካስተዋወቀ በኋላ፣ ከነቢይነት አገልግሎቱ ዐርፎአል ማለት አይደለም፤ ለሕዝቡ በመማለድ ይጸልያል (ቍ19፤7፥8-9)፤ በቃል ኪዳን ውስጥ ያላቸውንም ግንኙነት በማሳወቅ ያስተምራቸዋል (ዘፀ6፥18፡12፥28)። ሳኦልና ከእርሱ ቀጥለው የሚመጡት ነገሥታት በእግዚአብሔር ነቢያት እየተመከሩና እየታረሙ ሥራቸውን ይሠራሉ።

12፥24 *እግዚአብሔርን ፍሩ፤* ሳሙኤል ሐሳቡን የሚያጠቃልለው እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ያለባቸው የመታዘዝ ግዴታ በሕይወታቸው ላደረገላቸው ታላላቅ ነገሮች የባለውለታነት መግለጫ እንደሆነ ነው።

12፥25 *እናንተም ንጉሣችሁም ትጠፋላችሁ፤* አንድ ሕዝብ የተሰጠውን ቃል ኪዳን በማፍረስ በኀጢአት ቢጸና፣ በራሱ ላይ ጥፋት ያመጣል።

13፥1 *ሠላሳ ዓመት… አርባ ሁለት ዓመት፤* የሐረጉቹ አቀማመጥ ከዚህ በኋላ በየጊዜው የሚነሡት የእስራኤል ነገሥታት በስንት ዓመታቸው ዙፋን ላይ እንደወጡና ምን ያህል ጊዜ እንደ ነገሡ የሚገልጽ ቋሚ አባባል ነው (ለምሳሌ 2ሳሙ2፥10፤ 1ነገ14፥21፤2ነገ8፥26 ይመ)።

13፥2 *በማክማስና፤* ከቤቴል ደቡብ ምሥራቅና ከጊብዓ ሰሜን ምሥራቅ መተላለፊያ አጠገብ የሚገኝ ስፍራ ነው (ቍ23 ይመ)። *ከዮናታን፤* የሳኦል የበኵር ልጅ ሲሆን (14፥49 ይመ)፣ ስሙ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው በዚህ ስፍራ ነው።

13፥3 *ጊብዓ፤* ከማክማስ በስተ ደቡብና ከሸለቆው ማዶ ያለ ስፍራ ነው።

13፥4 *እንደ ርኩስ … ተጠላች፤* ከፍተኛ ጥላቻን ለመግለጽ የገባ ዘይቤ ነው (ለምሳሌ 2ሳሙ10፥6፤16፥21፤ዘፍ34፥30፤ዘፀ 5፥21)። *ጌልገላ፤* የ11፥14 ማብ ይመ። ሳኦል ቀደም ብሎ በመዘጋጀት ሳሙኤልን በዚህ ስፍራ መጠበቅ እንዳለበት ትእዛዝ ተሰጠው (የቍ8 ማብ እና 10፥8 ይመ)።

13፥5 *ሦስት ሺህ ሠረገሎች፤* አንዳንድ የጥንት ቅጆች “ሠላሳ ሺህ ሠረገሎች” ይላሉ። በሲሣራ ይመሩ የነበሩት ከነዓናውያን (መሳ4፥13)፤ ዘጠኝ መቶ ሠረገሎች ነበሯቸው፤ እስራኤላውያን እስከ ሰሎሞን ዘመን ድረስ ሠረገሎች እንዳልነበሯቸው ተጠቅሶአል (1ነገ 4፥26 ይመ)።

13፥8 *ሳሙኤል በሰጠው ቀጠሮ መሠረት፤* የ10፥8 ማብ ይመ። ሳሙኤል በጌልገላ ሕዝቡን ጠርቶ ያደረገውን ስብሰባ፣ በዚያም የሰጠውን ትእዛዝ ሳኦል በሚገባ ያውቅ ነበር። *ሰራዊትም መበታተን ጀመረ፤* ሳሙኤል ሰባት ቀን መዘግየቱ፣ የእስራኤልን ወታደሮች ድንጋጤ እጅግ አባብሶታል።

13፥9 *ሳኦል የሚቃጠለውን መሥዋዕትና … አቀረበ፤* እስራኤላውያን ወደ ጦርነት ከመውጣታቸው በፊት (7፥9 ይመ)፣ ሳሙኤል ራሱ ይህን መሥዋዕት እንደሚያቀርብ ተናግሮአል፤ ከዚህም በላይ እስኪመጣ ድረስ እንዲጠብቀው ሳኦልን አዞታል።

13፥13 *የማይገባህን አደረግህ፤* እንደ ሞኝነትና እንደ ኀጢአት የተቈጠረው የሳኦል ድርጊት (26፥21፤2ሳሙ24፥10፤ 1ዜና21፥8፤ 2ዜና16፥9 ይመ)፣ የእግዚአብሔር ነቢይ የሆነውን የሳሙኤልን ትእዛዝ ቸል በማለት እስራኤላውያን በፍልስጥኤማውያን ላይ የመጠናከር ዕድል ያጋጥማቸው ይሆናል ብሎ ከማሰብ የተነሣ የተፈጸመ ስሕተት ነው። *እግዚአብሔር አምላክህ የሰጠህን ትእዛዝ አልጠበቅህም፤* ሳኦል የነቢዩን የሳሙኤልን ቃል ልክ እንደ እግዚአብሔር ቃል አድርጎ መቍጠር ነበረበት (3፥20፤15፥1፤የዘፀ

ኖሮ፣ መንግሥትህን በእስራኤል ላይ ለዘላለም
ባጸናልህ ነበር፤ 14አሁን ግን መንግሥትህ
አይጸናም፤ እነሆ፣ እግዚአብሔር እንደ ልቡ
የሚሆንለትን ሰው አግኝቶአል፤ አንተ የእግዚ
አብሔርን ትእዛዝ ባለመጠበቅህም፣ እርሱን
የሕዝቡ መሪ አድርጎ መርጦታል።"
15ከዚያ በኋላ ሳሙኤል ከጌልገላ ተነ
ሥቶ[T] በብንያም ግዛት ወዳለው ወደ ጊብዓ
ወጣ። ሳኦልም አብረውት የነበሩትን ሰዎች
ቈጠራቸው፤ ብዛታቸውም ስድስት መቶ
ያህል ነበረ።

## እስራኤል ያለ ጦር መሣሪያ

16ፍልስጥኤማውያን በማክማስ ሰፍረው
በነበረበት ጊዜ ሳኦል፣ ልጁ ዮናታንና አብ
ረዋቸው የነበሩት ሰዎች በብንያም ግዛት
በምትገኘው በጊብዓ ነበሩ። 17በሦስት ምድብ
የተከፈሉ ወራሪዎች ከፍልስጥኤማውያን
ሰፈር ወጡ፤ አንዱ ምድብ በሦጋል ግዛት
ወደሚገኘው ወደ ዖፍራ አቀና፤ 18ሌላው
ወደ ቤትሖሮን፣ ሦስተኛው ደግሞ በምድረ
በዳው ትይዩ ካለው ከስቦይም ሸለቆ ቍል
ቍል ወደሚያሳየው ድንበር ዞረ።
19ፍልስጥኤማውያን፣ "ዕብራውያን ሰይፍ
ወይም ጦር ለራሳቸው አይሥሩ" ብለው ስለ
ነበር፣ በመላው የእስራኤል ምድር ብረት
ቀጥቃጭ አልተገኘም። 20ስለዚህ እስራኤ
ላውያን ሁሉ፣ ማረሻቸውንና ዶማቸውን
ለማሾል፣ ጠገራቸውንና ማጭዳቸውን ለማሳል
ወደ ፍልስጥኤማውያን ይወርዱ ነበር። 21ማረ
ሻና ዶማ ለማሾል የሚከፈለው ዋጋ ሁለት
ሦስተኛ ሰቅል[ሀ] ሲሆን፣ መንሽና ጠገራ እን
ዲሁም የበሬ መንጃ ለማሾል ደግሞ አንድ
ሦስተኛ ሰቅል[ለ] ነበር።
22ስለዚህ ጦርነቱ በተደረገበት ዕለት ከሳ
ኦልና ከልጁ ከዮናታን በስተቀር፣ አብረዋ
ቸው ከነበሩት ወታደሮች መካከል ሰይፍ
ወይም ጦር የያዘ አንድም ሰው አልነበረም።

13፥14 1ሳሙ15፥26፡ 28፤16፥1፤18፥8፤ 24፥20፤25፥30፤ 2ሳሙ 5፥2፤6፥21፤ 12፥9፤1ነገ13፥21፤ 1ዜና10፥14፤ መዝ 18፥43፤ኢሳ16፥5፤ 55፥4፤ኤር30፥9፤ ሕዝ34፥23-24፤ 37፥24፤ዳን9፥25፤ ሆሴ3፥5፤13፥11፤ ሚክ5፥2፤ ሐሥ7፥46፤13፥22
13፥15 ቍ.2፤ 1ሳሙ14፥2
13፥16 ኢሱ18፥24
13፥17 ኢሱ18፥23 ፤1ሳሙ14፥15
13፥18 ኢሱ10፥10፤ ነህ11፥34
13፥19 ዘፍ4፥22፤ ዘኍ25፥7
13፥22 ዘኍ25፥7፤ 1ሳሙ14፥6፤17፥47፤ 1ዜና9፥39፤ዘካ4፥6
13፥23 ቍ.2፤ 1ሳሙ14፥4
14፥2 ዘፀ28፥33፤ መሳ4፥5፤1ሳሙ 13፥15፤ ኢሳ10፥28
14፥3 ዘፍ35፥18፤ 1ሳሙ1፥3፤22፥11፡ 20፤መዝ78፥60
14፥4 1ሳሙ13፥23
14፥5 ኢሱ18፥24
14፥6 መሳ7፥4፤ 14፥3፤1ሳሙ13፥22፤ 17፥26፡36፤31፥4፤ 1ነገ 19፥12፤ መዝ 33፥16፤ ኤር9፥26፤ሕዝ28፥10፤ ማቴ 19፥26፤ ዕብ11፥34

## ዮናታን በፍልስጥኤማውያን ላይ አደጋ መጣሉ

23በዚያ ጊዜ አንድ የፍልስጥኤማውያን
ጭፍራ ወደ ማክማስ መተላለፊያ ወጥቶ
ነበር።
14 አንድ ቀን የሳኦል ልጅ ዮናታን
ወጣት ጋሻ ጃግሬውን፣ "ና በሌላ
በኩል ወዳለው የፍልስጥኤማውያን ጦር
ሰፈር እንሻገር" አለው። ይህን ግን ለአባቱ
አልነገረውም ነበር።
2ሳኦልም በጊብዓ ዳርቻ መጌዶን በተባለ
ስፍራ ከአንድ የሮማን ዛፍ ሥር ሰፍሮ
ነበር፤ ስድስት መቶ ያህል ሰዎችም አብረ
ውት ነበሩ፤ 3ኤፉድ ይለብስ የነበረውም
አኪያ በመካከላቸው ነበር። እርሱም በሴሎ
የእግዚአብሔር ካህን የነበረው የዔሊ ልጅ፣
የፊንሐስ ልጅ የኢካቦድ ወንድም የአኪጦብ
ልጅ ነበር። ዮናታን አለመኖሩን ግን ያወቀ
ሰው አልነበረም።
4ዮናታን ወደ ፍልስጥኤማውያን ጦር
ሰፈር ለመሻገር በፈለገበት መተላለፊያ ግራና
ቀኝ አንዱ ቦጼጽ ሌላው ሴኔ የተባሉ ሁለት
ሾጣጣ ዐለቶች ነበሩ። 5አንዱ ዐለት በስተ
ሰሜን በኩል በማክማስ አንጻር፣ ሌላው
ደግሞ በስተ ደቡብ በኩል በጊብዓ አንጻር
ይገኝ ነበር።
6ዮናታን ወጣት ጋሻ ጃግሬውን፣ "ና፤
ወደነዚያ ሸለፈታሞች ጦር ሰፈር እንሻገር፤
ምናልባትም እግዚአብሔር ይዋጋልን ይሆ
ናል፤ በብዙም ሆነ በጥቂት ለማዳን እግዚአ
ብሔርን የሚያግደው የለምና" አለው።
7ወጣቱም ጋሻ ጃግሬ፣ "በልብህ ያሰብኸ
ውን ሁሉ አድርግ፤ ወደ ኋላም አትበል፤

[T]15 *ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ግን፣ ከጌልገላ ተነሥተው ወደ መንገድ ሄዱ፤ ከጦሩ ጋር ለመገናኘት የተቀረው ሕዝብ ሳኦልን ተከተለ፤ ከጌልገላም ወጥቶ ሄደ ይላል።*
[ሀ]21 በዕብራይስጡ፣ *ፒም* ይባላል፤ 8ግራም ያህል ነው
[ለ]21 4 *ግራም ያህል ነው።*

7፥1-2፤20፡18-19፤ ማብ ይመ)። የእግዚአብሔርን ነቢይ የሳሙኤልን ትእዛዝ ባለማክበሩ፣ ሳኦል የተሰጠውን ኀላፊነት መሠረታዊ ቍም ነገር ተላልፎአል። የተሰጠው የንጉሥነት ሥልጣን ከሕግና ከነቢያት ቃል ጋር ሊጣጣም ይገባው ነበር (12፥14፡23፤15፥11 ማብ ይመ )።

13፥14 *መንግሥትህ አይጸናም፤* ከሳኦል በኋላ ልጆቹ በዙፋኑን ተቀምጠው አይነግሡም ማለት ነው፤ ስሙንም የሚጠብቅ ሥርወ መንግሥት አይኖርም (እግዚአብሔር ለዳዊት ከተናገረው ቃል ጋር ያነጻጽሩ፤ 2ሳሙ 7፥11-16)። እግዚአብሔር ለዔሊ ከተናገ ረው ቃል ጋር ተመሳሳይነት አለው (2፥30፡35)። *እግዚአብሔር እንደ ልቡ የሚሆንለትን ሰው አግኝቶአል፤ ... እርሱን የሕዝቡ መሪ አድርጎ መርጦታል፤* ጳውሎስ ይህን ክፍል ወስዶ በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን አስተምሮአል (ሐሥ13፥22)። *መሪ፤* የ9፥16 ማብ ይመ።

13፥15 *ስድስት መቶ፤* የሰባቱ ቀን መዘግየት፣ የሳኦልን ሰራዊት ቍጥር በእጅጉ አመናምኖታል (ቍ 24፡6-8 ይመ)።

13፥17 *በሦስት ምድብ ... ወራሪዎች፤* የእነዚህ ሠርጎ ገብ የፍልስጥኤም ወራሪዎች ዋና ዐላማ፣ ከእስራኤላውያን ጋር ፊት ለፊት ጦርነት ለመግጠም ሳይሆን፣ ምድሪቱን ለመዝረፍና ነዋሪዎቹንም ተስፋ ለማስቈረጥ ነበር።

13፥18 *ከስቦይም ሸለቆ፤* በምሥራቅ በኩል በዮርዳኖስ ሸለቆ ማዶ የሚገኝ ቦታ ነው።

13፥19 *ብረት ቀጥቃጭ አልተገኘም፤* በዚያ ዘመን ፍልስጥኤማውያን የብረት ሥራና ምርት ባለሀብትና ባለሙያዎች ስለ ነበሩ፣ እስራኤላውያን የዕርሻና የጦር መሣሪያዎችን እንደ ልብ ማግኘት አልቻሉም ነበር።

13፥22 *ሰይፍ ወይም ጦር የያዘ አንድም ሰው አልነበረም፤* እስራኤላውያን የሚዋጉት በቀስትና በወንጭፍ ነበር።

14፥1 *በሌላ በኩል ወዳለው፤* ፍልስጥኤማውያን ከመተላለፊያው በስተ ሰሜን በኩል ሲሰፍሩ፣ እስራኤላውያን ደግሞ የሰፈሩት በስተ ደቡብ በኩል ነበር።

14፥2 *በጊብዓ፤* ሳኦል ከናሲብ (13፥3) በስተ ደቡብ ወዳለው ወደ ጊብዓ አፈገፈገ። *የሮማን ዛፍ ሥር፤* በጥንት ዘመን የእስራኤል መሪዎች በታወቀ ዛፍ ሥር ተቀምጠው ችሎት ማስቻላቸው የተለመደ ነበር (22፥6፤መሳ4፥5 ይመ)።

14፥3 *የኢካቦድ ወንድም፤* 4፥21 ይመ። *ኤፉድ ይለብስ የነበረውም፤* የ2፥28 ማብ ይመ። *አኪያ፤* የአኪጦብ ልጅ የአቢሜሌክ ታናሽ ወይም ታላቅ ወንድም (21፥1፤22፥9፡11 ላይ የሚጠቀሰው) ወይም ደግሞ የአቢሜሌክ ሌላ ስም ሊሆን ይችላል።

14፥6 *ወደ እነዚያ ሸለፈታሞች፤* የንቀት አባባል ነው (17፥26፡36፤ 31፥4፤ 2ሳሙ1፥20፤ መሳ14፥3፤ 15፥18፤ 1ዜና10፥4 ይመ)፤ ይህም እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ያላትን የቃል ኪዳን ግንኙነት ሲያሳይ (የዘፍ17፥10 ማብ ይመ)፣ ፍልስጥኤማውያን ደግሞ በምድሪቱ ላይ መኖር እንደማይገባቸው ያመለክታል። *በብዙም ሆነ በጥቂት፤* የ17፥47 ማብ ይመ። ዮናታን በእግዚአብሔር እምነት ላይ በመመሥረት (ከዕብ11፥33-34 ጋር ያነጻጽሩ) የወሰደው የድፍረት ዕቅድ ነው (9፥16)።

እኔም በሙሉ ልብ ካንተው ጋር ነኝ" አለው::
8ዮናታንም እንዲህ አለው፣ "እንግዲያ
ውስ ና፤ ወደ ሰዎቹ እንሻገርና እንታ
ያቸው:: 9እነርሱም፣ 'ወደ እናንተ እስክን
መጣ እዚያው ጠብቁን' ካሉን፣ ባለንበት
ሆነን እንጠብቃቸዋለን፤ ወደ እነርሱም
አንወጣም:: 10ነገር ግን፣ 'ወደ እኛ ውጡ'
ካሉን፣ እግዚአብሔር እነርሱን በእጃችን
አሳልፎ የሰጠን ለመሆኑ ምልክቱ ይህ ስለ
ሆነ፣ ወደ እነርሱ እንወጣለን::"
11ሁለቱም ለፍልስጥኤማውያን ጭፍራ
በታዩ ጊዜ፣ ፍልስጥኤማውያን፣ "እነሆ፤ ዕብ
ራውያን ከተደበቁባቸው ጉድጓዶች እየወጡ
ነው" አሉ:: 12የፍልስጥኤም ጦር ሰፈር
ሰዎችም፣ "ኑ ወደ እኛ ውጡ፤ አንድ ነገር
እናሳያችሁ" ሲሉ በዮናታንና በጋሻ ጃግ
ሬው ላይ ጮኹባቸው::
ስለዚህ ዮናታን ጋሻ ጃግሬውን፣ "ተከ
ትለኸኝ ውጣ፤ እግዚአብሔር በእስራኤላ
ውያን እጅ አሳልፎ ሰጥቶአቸዋልና" አለው::
13ዮናታን በእጁና በእግሩ ተፍጨርጭሮ፣
ጋሻ ጃግሬውን በማስከተል ወጣ:: ፍልስጥኤ
ማውያንም በዮናታን እጅ ወደቁ፤ ጋሻ ጃግ
ሬውም ከበስተኋላው እየተከተለ ገደላቸው::
14ዮናታንና ጋሻ ጃግሬው በመጀመሪያው
ቀን ባደረጉት ግዳይ አንድ ጥማድ በምታ
ውል የዕርሻ ቦታ[ሐ] ላይ ሃያ ያህል ሰዎች
ገደሉ::

## የፍስጥኤማውያን መሸነፍ

15በሰፈር በዕርሻ ላይና በሕዝብ ሁሉ መካ
ከል ሽብር ሆነ፤ ከተማ ጠባቂዎችና አደጋ ጣዮ
ችም ሁሉ ተቀጠቀጡ፤ ምድሪቱም ተናወጠች፤
ሽብሩም ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከ ነበር[ሠ]::
16በብንያም ግዛት በጊብዓ የነበሩ የሳኦል
ዘቦች፣ የፍልስጥኤም ሰራዊት በየአቅጣ
ጫው መበታተኑን አዩ:: 17ሳኦልም አብረ
ውት የነበሩትን ሰዎች፣ "እስኪ፣ ሰራዊቱን
ቍጠሩና ማን ከዚህ እንደ ሄደ እዩ" አላ
ቸው:: ይህን ባደረጉ ጊዜም ዮናታንና ጋሻ
ጃግሬው በዚያ አልነበሩም::
18ሳኦልም አኪያን፣ "የእግዚአብሔርን ታቦት
ወደዚህ አምጣ" አለው፤ በዚያን ጊዜ ታቦቱ
በእስራኤላውያን ዘንድ ነበር[ረ]:: 19ሳኦል ለካ
ህኑ በመናገር ላይ ሳለ፣ በፍልስጥኤማው
ያን ሰፈር ሁካታው እየጨመረ ሄደ:: ስለዚህ
ሳኦል ካህኑን፣ "እጅህን መልስ" አለው::
20ከዚያም ሳኦልና ሰዎቹ ተሰብስበው ወደ
ውጊያው ሄዱ:: እነርሱም ፍልስጥኤማውያን
በሰይፋቸው እየተጨፋጨፉ በታላቅ ትር
ምስ ላይ ሆነው አገኟቸው:: 21እነዚያ ቀድሞ
ከፍልስጥኤማውያን ጐን ተሰልፈው የነበሩ
ትና አብረዋቸውም ወደ ሰፈራቸው የወጡት
ዕብራውያን ከሳኦልና ከዮናታን ጋር ወደ
ነበሩት እስራኤላውያን ገቡ:: 22በኰረብታ
ማው የኤፍሬም አገር ተሸሽገው የነበሩት እስ
ራኤላውያን ሁሉ ፍልስጥኤማውያኑ በሽሽት
ላይ መሆናቸውን በሰሙ ጊዜ፣ አጥብቀው
በመከታተል አሳደዷቸው:: 23በዚያ ቀን እግዚ
አብሔር እስራኤልን ታደገው፤ ጦርነቱም
ከቤትአዌን ዘልቆ ሄደ::

## ዮናታን ማር በላ

24ሳኦል፣ "ዛሬ ጠላቶቼን ከመበቀሌ በፊት
እስከ ማታ ድረስ እህል የሚበላ ሰው የተረገመ
ይሁን" ብሎ ሕዝቡን አምሎ ስለ ነበር፣ በዚ
ያች ዕለት የእስራኤል ሰዎች ተጨንቀው
ዋሉ፤ ስለዚህ ከሕዝቡ አንድም እህል የቀ
መሰ አልነበረም::
25ሰራዊቱ[ሰ] ሁሉ ወደ ጫካ ሲገባ፣ ማር
በመሬቱ ላይ ይታይ ነበር:: 26ሕዝቡ
ወደ ጫካው በገባ ጊዜ፣ የማሩ ወለላ እየተ

14፥10 ዘፍ24፥14፤ ኢሱ2፥24
14፥11 ዘፍ14፥13፤1 ሳሙ13፥6
14፥12 መሳ8፥16፤ 1ሳሙ17፥46፤ 2ሳሙ5፥24
14፥15 ዘፍ 35፥5፤ ዘፀ14፥24፤19፥16፤ 1ሳሙ13፥17፤ 2ነገ 7፥5-7
14፥16 2ሳሙ 18፥24፤2ነገ9፥17፤ ኢሳ52፥8፤ሕዝ33፥2
14፥18 መሳ18፥5፤ 1ሳሙ30፥7
14፥19 ዘኍ27፥21
14፥20 መሳ7፥22፤ ሕዝ38፥21፤ ዘካ14፥13
14፥21 1ሳሙ29፥4
14፥22 1ሳሙ13፥6
14፥23 ዘፀ14፥30፤ ኢሱ7፥2
14፥24 ኢሱ6፥26

[ሐ]14 ዕብራይስጡ ግማሽ ቀንበር ይላል፤ ይኸውም በጥማድ በሬ በአንድ ቀን የሚታረሰውን መሬት የሚያሳይ ነው
[ሠ]15 ወይም ከፍተኛ የሆነ
[ረ]18 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ግን ኤፉዱን ወደዚህ አምጣ፤ በዚያ ጊዜ እርሱ ኤፉዱን በእስራኤል ፊት ለብሶት ነበር ይላል::
[ሰ]25 ወይም *እሁን የምድሩ ነዋሪዎች* በሙሉ

14፥10 *ምልክቱ፤* መሳ6፥36-40፤ ኢሳ7፥11 ይመ::

14፥11 *ዕብራውያን፤* 4፥6፤ 13፥3፡7 እና የዘፍ14፥13 ማብ ይመ::

14፥15 *ምድሪቱም ተናወጠች፤* 7፥10፤ ኢሱ10፥11-14፤ መዝ 77፥18 ይመ::

14፥18 *የእግዚአብሔርን ታቦት ... አምጣ፤* ሳኦል ከፍልስጥኤማውያን ጋር ጦርነት ከመግጠሙ በፊት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ፈለገ (ዘኍ27፥21፤ዘዳ20፥2 ይመ)፤ እዚህ ላይ የሰበዓ ሊቃናት ትርጒም የጥንቱን ዕብራይስጥ ተከትሎ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች "ኤፉዱን አምጣ" ሲል ጽፎአል፤ (1) በ7፥1 እንደ ተጠቀሰው ዳዊት ወደ ኢየሩሳሌም እስኪያመጣው ድረስ (2ሳሙ6)፣ ታቦቱ በቂርያትይዓሪም፣ ኤፉዱ ደግሞ በሳኦል ሰፈር በጊብዓ ነበር (ቍ3 ይመ):: (2) በብሉይ ኪዳን በየትም ስፍራ ታቦት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቂያ ሆኖ አላገለገለም፤ ኤፉድ ግን ከኡሪምና ከቱሚም ጋር የተሰጠው ለዚሁ አገልግሎት ነበር (23፥9፤30፥7 እና የ2፥18፡28 ማብ ይመ):: (3) ካህኑ እጁን ዘርግቶ የሚሰጠው ትእዛዝ (ቍ19)፣ ከኤፉድ ጋር እንጂ ከታቦት ጋር ግኑኙነት አልነበረውም::

14፥19 *እጅህን መልስ፤* የጊዜውን አጣዳፊነት በመመልከት፣ ሳኦል የእግዚአብሔርን ቃል መጠበቅ፣ ሊያገኝ ያሰበውን ወታደራዊ ድል የሚያሳጣው መሰለው:: በ13፥8-12 እንደ ተመለከተው በእግዚአብሔር ላይ በመታመን፣ ለቃሉም በመታዘዝ ሳይሆን በራሱ ሐሳብ በመመራት ያደረገው ውሳኔ ነው::

14፥23 *እግዚአብሔር እስራኤልን ታደገው፤* ጸሐፊው ሳኦልን ወይም ዮናታንን ሳይሆን (ቍ 6፡10፡15፤ 11፥13 ይመ)፣ እግዚአብሔርን የድሉ ባለቤት አደረገ::

*14፥24-46፤* ከተገኘው ትልቅ ድል በኋላ፣ ሳኦል እግዚአብሔር የሰጠውን ድል ከወሰዳቸው ርምጃዎች ጋር በማገናዘብ ንጉሥ ለመሆን የማይበቃ ሰው እንደ ሆነ ጸሐፊው ገልጾአል:: ከጦርነቱ በፊት ባለማስተዋል የተናገረው የርግማን ቃል (የቍ24 ማብ ይመ)፣ በእስራኤል ጦር ላይ ጭንቀት አመጣ፤ ዮናታንም እንደ ተናገረው፣ ከድል ይልቅ "በአገሪቱ ላይ ችግር ፈጠረ" (ቍ 29):: በኋላም ሳኦል ድሉን እንዲሰጠው እግዚአብሔርን በጠየቀ ጊዜ መልስ አላገኘም (ቍ 37)፤ ሳኦል በዚህ ፈንታ ምክንያቱ ልጄ ነው ብሎ ዮናታንን ሊገድል ተዘጋጀ፤ ሕዝቡ ግን ዮናታን ያደረገውን አስተዋጽዖ ስለ ተገነዘበ ከሞት አተረፈው (ቍ 45):: እያደገ የመጣው የሳኦል ራስ ወዳድነት ሁሉንም ራስ ወዳድ ስላደረጋቸው፣ ሕዝቡ ለከፋ ሁኔታ ተዳረገ፤ እግዚአብሔርንና ሕዝቡን የሚያገለግል ንጉሥ ከመሆን ፈንታ በአካባቢው እንዳሉት እንደ አሕዛብ ነገሥታት ሆነ (8፥5)::

14፥24 *ተጨንቀው ዋሉ፤* ወታደሮቹ እህል መቅመስ እንደሌለባቸው የሚያስገድደው የሳኦል የተጣደፈ ርምጃ፣ በጦርነቱ የማያስፈልግና ያልተጠበቀ ነገር እንዲደርስ አደረገ (ከቍ29፥30 ይመ):: *የተረገመ ይሁን፤* ሳኦል ንጉሥ እንደመሆኑ መጠን ሕዝቡን በከባድ ቃለ መሐላ አሰረው (ቍ 28):: መሐላ እጅግ ከባድ ነገር ነው፤ ምክንያቱም ምስክርነት መስጠትንም ሆነ (ዘፀ20፥7፤ ዘሌ19፥12)፣ ቃል መግባትን (ዘፍ21፥23-24፤ 24፥3-4) ወይም

ንጠባጠበ መውረዱን አየ፤ ሆኖም መሐላ
ውን ፈርቶ ስለ ነበር፣ እጁን ወደ አፉ የዘረጋ
ማንም አልነበረም:: 27ነገር ግን ዮናታን
አባቱ ሕዝቡን በመሐላ ማሰሩን አልሰማም
ነበር:: ስለዚህ በእጁ የያዘውን ዘንግ ጫፍ
በማሩ ወለላ ውስጥ በማስገባት እጁን ወደ
አፉ አደረገ፤ ዐይኑም በራ:: 28ከዚያም አንዱ
ወታደር፣ "አባትህ ሰራዊቱን፣ 'ዛሬ እህል
የሚቀምስ ማናቸውም ሰው የተረገመ ይሁን!'
በማለት በጽኑ መሐላ አስሮአል:: ሰው ሁሉ
የተዳከመው በዚሁ ምክንያት ነው" አለው::
29ዮናታንም እንዲህ አለ፤ "አባቴ በምድሪቱ
ላይ ችግር ፈጥሮአል፤ ከዚህ ማር ጥቂት
በቀመስሁ ጊዜ ዐይኔ እንዴት እንደ በራ[ሀ]
ተመልከቱ! 30ሕዝቡ ከጠላቶቻቸው እጅ
ከወሰዱት ምርኮ ዛሬ በልተው ቢሆን ኖሮ
ምንኛ በተሻለ ነበር፤ የተገደሉትም ፍልስ
ጥኤማውያን ቍጥር ከዚህ በበለጠ ነበር::"
31በዚያች ዕለት እስራኤላውያን ፍልስጥ
ኤማውያንን ከማክማስ እስከ ኤሎን ድረስ
ከመቷቸው በኋላ እጅግ ዝለው ነበር::
32በምርኮው ላይ ተረባርበው በጉን፣ በሬ
ውንና ጥጃውን በመውሰድ በመሬት ላይ ዐር
ደው ሥጋውን ከነደሙ በሉት:: 33ከዚያም
ለሳኦል፣ "እነሆ፤ ሕዝቡ ሥጋውን ከነደሙ
በመብላት *እግዚአብሔርን* እየበደለ ነው"
ተብሎ ተነገረው::
ሳኦልም፣ "ሕግ ተላልፋችኋል፤ በሉ አንድ
ትልቅ ድንጋይ አንከባላችሁ አቅርቡልኝ"
አለ:: 34እርሱም፣ "በሕዝቡ መካከል እየዞራ
ችሁ፣ 'እያንዳንዳችሁ በሬዎቻችሁንና በጎቻ
ችሁን አምጡ፤ እዚሁ ዐርዳችሁ ብሉ፤ ነገር
ግን ሥጋውን ከነደሙ በመብላት *እግዚ
አብሔርን* አትበድሉ' በሏቸው" አለ::
ስለዚህ በዚያች ሌሊት እያንዳንዱ ሰው
በሬውን አምጥቶ በዚያ ዐረደው:: 35ሳኦልም
*ለእግዚአብሔር* መሠዊያ ሠራ፤ መሠዊያ
ሲሠራም ይህ የመጀመሪያ ጊዜው ነበር::
36ሳኦልም፣ "ፍልስጥኤማውያንን ተከትለን
በሌሊት እንውረድና እስኪነጋ ድረስ እንበ
ዝብዛቸው፤ አንድም ሰው በሕይወት አናስ
ቀርላቸው" አለ:: እነርሱም፣ "መልካም መስሎ
የታየህን ሁሉ አድርግ" ብለው መለሱለት::
ካህኑ ግን፣ "እዚሁ እግዚአብሔርን እንጠይቅ"
አለ::
37በዚህ ጊዜ ሳኦል፣ "ፍልስጥኤማውያንን
ተከትዬ ልውረድን? በእስራኤላውያንስ
እጅ አሳልፈህ ትሰጣቸዋለህን?" ሲል እግዚ
አብሔርን ጠየቀ:: ነገር ግን እግዚአብሔር
በዚያች ቀን አልመለሰለትም::
38ስለዚህ ሳኦል እንዲህ አለ፤ "የሰራዊቱ
መሪዎች ሁላችሁም ወደዚህ ቅረቡ፤ ዛሬ
ምን ኀጢአት እንደ ተሠራ እንወቅ:: 39እስ
ራኤልን የታደገ ሕያው እግዚአብሔርን!
አድራጊው ልጄ ዮናታን እንኳ ቢሆን
መሞት አለበት::" ነገር ግን ከሕዝቡ መካ
ከል የመለሰለት አንድም አልነበረም::
40ሳኦልም እስራኤላውያንን ሁሉ፣ "እናንተ
በዚያ በኩል ቁሙ፤ እኔና ልጄ ዮናታን
ደግሞ በዚህ በኩል እንቆማለን" አላቸው::
ሰዎቹም፣ "መልካም መስሎ የታየህን አድ
ርግ" ብለው መለሱለት::
41ከዚያ በኋላ ሳኦል፣ "ትክክለኛውን መልስ
ስጠኝ"[ለ] ሲል ወደ እስራኤል አምላክ ወደ *እግ
ዚአብሔር* ጸለየ፤ ዕጣው በሳኦልና በዮናታን
ላይ ወደቀ፤ ሕዝቡም ነጻ ሆነ:: 42ሳኦልም
በእኔና በልጄ በዮናታን መካከልም ዕጣ ጣሉ"
አላቸው:: ዕጣውም በዮናታን ላይ ወደቀ::
43ከዚያም ሳኦል ዮናታንን፣ "እስቲ ያደ
ረግኸውን ንገረኝ" አለው::
ዮናታንም፣ "በዘንጌ ጫፍ ጥቂት ማር ቀም
ሻለሁ፤ እነሆ፤ ለመሞት ዝግጁ ነኝ" አለው::
44ሳኦልም፣ "ዮናታን፣ አንተ ካልተገደልህ
እግዚአብሔር ይፍረድብኝ፣ የከፋም ነገር ያም
ጣብኝ" አለ::
45ሕዝቡ ግን ሳኦልን፣ "ለእስራኤል ይህን
ታላቅ ድል ያስገኘ ዮናታን መሞት ይገባ
ዋልን? አይደረግም! ዛሬ ይህን ያደረገው
*በእግዚአብሔር* ርዳታ ስለ ሆነ፣ ሕያው

14፥27 ቍ43፤ መዝ19፥10፤ ምሳ 16፥24፤24፥13
14፥29 ኢሱ7፥25፤ 1ነገ18፥18
14፥31 ቍ5፤ ኢሱ10፥12
14፥32 ዘፍ9፥4፤ 1ሳሙ15፥19፤ አስ9፥10
14፥33 ዘፍ9፥4
14፥34 ዘሌ19፥26
14፥35 1ሳሙ7፥17
14፥36 ዘፍ25፥22፤ መሳ18፥5
14፥37 1ሳሙ28፥6፤ 15፤2ሳሙ 22፥42፤ መዝ 18፥41
14፥38 ኢሱ 7፥11
14፥39 ቍ44፤ ዘኍ14፥21፤ ኢሱ 7፥15፤ 2ሳሙ12፥5፤ ኢዮ19፥25፤ መዝ 18፥46፤42፥2፤
14፥41 ምሳ16፥33፤ ሐሥ1፥24
14፥42 ዮና1፥7
14፥43 ቍ27፤ ኢሱ7፥19
14፥44 ቍ39፤ ሩት1፥17
14፥45 2ሳሙ14፥11፤ 1ነገ1፥52፤ ማቴ10፥30

*[ሀ]29 ወይም ኀይሌ እንዴት እንደ ታደሰ*
*[ለ]41 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናት ትር ጕም ግን ዛሬ ለባሪያህ ያልመለስህለት ለምንድን ነው ጥፋቱ በእኔና በልጄ በዮናታን ላይ ከሆነ በኡሪም መልስልን፤ ነገር ግን ጥፋቱ በእስራኤል ሰዎች ላይ ከሆነ በቱሚም መልስ ይላል::*

ደግሞ አንድ ድርጊት እንዳይፈጸም የመከልከልን (እዚህና ኢሱ 6፥24) የሚመለከት ከሆነ፣ እግዚአብሔር በቀጥታ ጣልቃ እንዲገባ ስለሚሻ ነው፤ ይኸውም እግዚአብሔር የታላቅ ኀይል ምንጭና በሰው ድርጊቶች ላይ ሁሉን ዐዋቂ ፈራጅ መሆኑን የሚያመለክት ነው:: ዛሬ ጠላቶቼን ከመበቀሌ በፊት ሳኦል ከፍልስጥኤማውያን ጋር የነበረውን ግጭት እንደ ግል ቂም አድርጎ ወሰደው እንጂ (የ15፥12 ማብ ይመ)፣ ጦርነቱ የእግዚአብሔርን ክብር ለመጠበቅና የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመታደግ አልነበረም (በሳኦልና በልጁ በዮናታን አስተሳሰብ መካከል ስለ ነበረው ልዩነት በቍ 6፡10፡12 ላይ ያሉትን ማብ ይመ)::

14፥31 *ኤሎን፤* ለፍልስጥኤማውያን ግዛት ቅርብ የሆነ በስተ ምዕራብ የሚገኝ ስፍራ ነው (ኢሱ10፥12 ይመ)::

14፥33 *ሥጋውን ከነደሙ በመብላት፤* ለእስራኤላውያን ደም መብላት አልተፈቀደላቸውም (ዘፍ9፥4፤ ዘሌ17፥11፤ 19፥26፤ ዘዐ12፥16፤ ሕዝ33፥25፤ ሐሥ15፥20 እና ማብ ይመ):: *እግዚአብሔርን እየበደለ ነው፤* ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነው የዕብራይስጥ ቃል በመዝ 78፥57፤ ኤር3፥8–11 ላይ "ከዳተኛ" እና በኢሳ 48፥8 ላይ ደግሞ "ዐመፀኛ" ተብሎ ተተርጕሞአል::

14፥35 *የመጀመሪያ ጊዜው፤* ሳኦል ለመንፈሳዊ ነገር ደንታ የሌለው ሰው መሆኑን የሚያሳይ ሌላ ማረጋገጫ ነው የ9፥6፤10፥11 ማብ ይመ)::

14፥36 *ካህኑ፤* አኪያን ማለት ነው (ቍ 3 ይመ)::

14፥37 *ሳኦል ... እግዚአብሔርን ጠየቀ፤* ኤፉድ በኡሪምና በቱሚም አማካይነት የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚጠይቅበት ነገር ነው (ቍ3 እና ማብ ይመ እንዲሁም ቍ18 ይመ):: *ነገር ግን እግዚአብሔር ... አልመለሰለትም፤* በጦርነቱ ጊዜ ቃለ መሐላ ተጥሶ ስለ ነበር፣ ተጨማሪ ወታደራዊ እርምጃ ለመውሰድ ሳኦል ያቀረበውን ጥያቄ እግዚአብሔር አልተቀበለውም::

14፥39 *ሕያው እግዚአብሔርን፤* የመሐላ ቃል የሚሰጥበት አባባል ነው (የቍ24 ማብ ይመ ፤19፥6፤ኤር4፥2፤ሆሴ4፥15 ይመ)::

14፥41 *ዕጣው በሳኦልና በዮናታን ላይ ወደቀ፤* 10፥20-21፤ ኢሱ 7፥14-18፤ ምሳ16፥33 ይመ::

*14፥44፤* የመሐላ ቃል ነው (የቍ24 ማብ ይመ፤ 3፥17 እና ማብ ይመ)::

14፥45 *ዛሬ ይህን ያደረገው በእግዚአብሔር ርዳታ ስለ ሆነ፤* በሳኦል ጦር ሰራዊት ውስጥ ያሉ ሰዎች በእግዚአብሔር

እግዚስብሔርን! ከራስ ጠጕሩ አንዲቱ እንኳ
መሬት ላይ አትወድቅም" አሉት:: ስለዚህ
ሰዎቹ ዮናታንን ታደጉት፤ እርሱም ከመ
ሞት ዳነ::
46ሳኦል ፍልስጥኤማውያንን ከማሳደድ
ተመለሰ፤ እነርሱም ወደ አገራቸው ተመለሱ::
47ሳኦል በእስራኤል ላይ በትረ መንግሥ
ቱን ከጨበጠ በኋላ፣ በዙሪያው ያሉትን
ጠላቶቹን ማለትም ሞዓብን፣ አሞናውያንን፣
ኤዶምን፣ የሱባን ነገሥታትና[+] ፍልስጥኤ
ማውያንን ወጋቸው:: በሄደበት ሁሉ ድል
ይነሣ ነበር[n]:: 48በጀግንነት ተዋግቶ አማሌ
ቃውያንን አሸነፈ፤ እስራኤልንም ይዘርፏ
ቸው ከነበሩት እጅ ታደጋቸው::

## የሳኦል ቤተ ሰብ

49የሳኦል ወንዶች ልጆች ዮናታን፣ የሱዊ፣
ሜልኪሳ ነበሩ፤ ሴቶች ልጆቹም ትልቋ ሜ
ሮብ፣ ትንሿ ሜልኮል ይባሉ ነበር:: 50የሳ
ኦል ሚስት አኪናሆም የምትባል የአኪ
ማአስ ልጅ ነበረች፤ የሰራዊቱም አዛዥ
አበኔር የሚባል የአጎቱ የኔር ልጅ ነበረ::
51የሳኦል አባት ቂስና የአበኔር አባት ኔር
ሁለቱም የአቢኤል ልጆች ነበሩ::
52በሳኦል ዘመን ሁሉ ከፍልስጥኤማውያን
ጋር ከባድ ጦርነት ነበረ፤ ስለዚህ ሳኦል
ብርቱ ወይም ጀግና ሰው ባየ ቍጥር ወደ
ራሱ ወስዶ እንዲያገለግለው ያደርግ ነበር::

## እግዚአብሔር የሳኦልን ንጉሥነት መናቁ

15 ሳሙኤል ሳኦልን እንዲህ አለው፤
"በሕዝቡ በእስራኤል ላይ ቀብቼ
እንዳነግሥህ፣ *እግዚአብሔር* የላከው እኔን
ነው፤ ስለዚህ *ከእግዚአብሔር* የመጣውን
መልእክት አድምጥ:: 2የሰራዊት ጌታ *እግ
ዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ 'እስራኤል ከግ
ብፅ በወጣ ጊዜ፣ አማሌቃውያን በመንገድ
ላይ ስለ ተቃወሙት እቀጣቸዋለሁ:: 3አሁ
ንም ሂድ፤ አማሌቃውያንን ውጋ፤ ያላቸ
ውንም ሁሉ ፈጽመህ አጥፋ፤ አንዱንም
አታስቀር፤ ወንዱንና ሴቱን፣ ልጁንና ሕፃ
ኑን፣ የቀንድ ከብቱንና በጉን፣ ግመሉንና
አህያውን ግደል::" '[+]
4ስለዚህ ሳኦል ሰዎቹን ጥላኢም በተባለ
ቦታ ሰብስቦ ቈጠራቸው፤ እነርሱም ሁለት
መቶ ሺህ እግረኛ ወታደሮችና ከይሁዳም
ዐሥር ሺህ ሰዎች ነበሩ፤ 5ሳኦልም ወደ
አማሌቅ ከተማ ሄዶ በአንዲት ሸለቆ ውስጥ
አደፈጠ:: 6እርሱም፣ ቄናውያንን፣ "ከእ
ነርሱ ጋር እንዳላጠፋችሁ ከአማሌቃውያን
ራቁ፤ ተለዩአቸውም፤ እስራኤላውያን ከግ
ብፅ ምድር በወጡ ጊዜ፣ ቸርነት አድርጋ
ችሁላቸዋልና"' አላቸው:: ስለዚህ ቄናውያን
ከአማሌቃውያን ተለዩ::
7ከዚያም ሳኦል አማሌቃውያንን ከኤው
ላጥ አንሥቶ በምሥራቅ ግብፅ እስካለው
እስከ ሱር ድረስ ወጋቸው:: 8የአማሌቃው
ያንን ንጉሥ አጋግን ከነሕይወቱ ማረከው፤
ሕዝቡን ሁሉ በሰይፍ ስለት ፈጽሞ አጠ
ፋቸው:: 9ነገር ግን ሳኦልና ሰራዊቱ አጋግን፣
ምርጥ ምርጡን በግና የቀንድ ከብት፣
የሰባውን ጥጃና[*] ጠቦት፣ መልካም የሆነውን
ሁሉ ሳይገድሉ ተውት:: እነዚህን ፈጽመው
ለማጥፋት ፈቃደኞች አልነበሩም፤ ነገር

14፥47 ዘፍ19፥37፡38፤1ሳሙ21፥7፤2ሳሙ8፥3፤10፥6፤12፥31፤23፥36
14፥48 ዘፍ36፥12፤ ዘኍ13፥29፤መሳ3፥13፤1ሳሙ15፥2፥7፤27፥8፤28፥18፤30፥13፤2ሳሙ1፥13፤1ዜና 4፥43
14፥49 ዘፍ29፥26፤1ሳሙ31፥2፤1ዜና 8፥33
14፥50 1ሳሙ10፥14፤2ሳሙ2፥8፤3፥6፤1ነገ2፥5
14፥51 1ሳሙ9፥1
14፥52 1ሳሙ8፥11
15፥1 1ሳሙ9፥16
15፥2 ዘፍ 14፥7፤ 1ሳሙ14፥48፤ 2ሳሙ1፥8
15፥3 ቍ9:19፤ ዘፍ14፥23፤ ኢሱ 6፥17፤ 1ሳሙ22፥19፤ 27፥9፤28፥18፤ አስ3፥13፤9፥5
15፥6 ዘፍ15:19፤ ዘኍ24፥22፤መሳ1፥16፤1ሳሙ30፥29
15፥7 ዘፍ16፥7፤ 1ሳሙ14፥48
15፥8 ዘፀ17፥8-16፤ ዘኍ24፥7፤ኢሱ8፥23
15፥9 ቍ3

[+]47 የማሶሬቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሙት ባሕር ጥቅልና የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ግን ንጉሥ ይላል::
[n]47 ዕብራይስጡ *ያሠቃያቸው ነበር* ሲል፣የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ደግሞ *ድል ይነሣቸው ነበር* ይላል::
[+]3 በዚህም ሆነ በቍጥር 8:9:15:18:20 እና 21 ላይ የዕብራይስጡ ቃል አንድን ሰው ወይም ነገር ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠትን የሚያሳይ ነው::
[*]9 ወይም ያደገ ጥጃ የዚህ ሐረግ የዕብራይስጡ ትርጒም

ርዳታ ሕዝቡን የታደገውን ሰው ሕይወት ማጥፋት አግባብ እንዳልሆነ ተገነዘቡ::

*14፥47-48፤* ሳኦል በምሥራቅ በሞዓብና በአሞናውያን፣ በደቡብ በኤዶም፣ በምዕራብ በፍልስጥኤማውያን፣ በሰሜን በዞባ ላይ ያገኘው ወታደራዊ ድል ማጠቃለያ ነው::

14፥47 ***አሞናውያንን፤*** ዘዳ 2፥19-21 ይመ::

14፥48 ***አማሌቃውያንን፤*** የ15፥2 ማብ ይመ::

14፥49 ***የሳኦል ወንዶች ልጆች፤*** 2ሳሙ 2፥8:10፤ 1ዜና 9፥39፤10፥2 ይመ:: ***ሜሮብ ... ሜልኮል፤*** 18፥17:20:27፤19፥11-17፤ 25፥44፤ 2ሳሙ6፥16-23 ይመ::

14፥50 ***አኪናሆም፤*** በዚህ ምዕራፍና ቍጥር ላይ ብቻ ተጠቅሳለች:: ፊጽፋ የተባለችው ቍባቱ በ2ሳሙ3፥7፤ 21፥8-11 ላይ ተጠቅሳለች::

14፥52 ***በሳኦል ዘመን ሁሉ፤*** ዋናውን የሳኦል የአገዛዝ ዘመን ታሪክ ያጠቃልላል:: ***ወደ ራሱ ወስዶ እንዲያገለግለው ያደርግ ነበር፤*** ሳኦል ለየት ያለ ችሎታ ያላቸውን ሰዎች ወታደሮቹ እንዲሆኑ ያደርግ ነበር፤ ዳዊትም በኋላ ከዚህ የበለጠ አድርጎአል (22፥2፤ 23፥13፤ 25፥13፤ 27፥2-3፤ 29፥2፤ 20፥1:9፤ 2ሳሙ2፥3፤ 5፥6፤ 8፥18፤ 15፥18፤ 23፥8-39 ይመ)::

15፥1-35፤ ይህ ክፍል ሳኦል በእግዚአብሔር እንዴት እንደ ተናቀ የሚገልጽ ነው፤ ጊዜው ባይጠቀስም እንኳ ይህ የሆነው በ14፥47 ላይ ከተጠቀሱት ውጊያዎች በኋላ ሰላምና ደኅንነት በመጠኑም ቢሆን በምድሪቱ ከሰፈነ በኋላ ነበር:: ዳዊትም የተቀባው (16፥1-13) ሳኦል በእግዚአብሔር ከተናቀ ከጥቂት ጊዜ በኋላ (ቍ22:26:28) በ1025 ዓ.ቅ.ክ ላይ ሳይሆን አይቀርም::

15፥2 ***አማሌቃውያን፤*** ከዔሳው ዘር የሆኑ የምድረ በዳ ሰዎች (ዘፍ 36፥12:16) ሲሆኑ፣ የሚኖሩትም በኔጌብና በሲና ምድር ነበር (27፥8፤ 30፥1፤ ዘፍ14፥7፤ ዘፀ17፥8፤ ዘኍ13፥29 ይመ):: ***እስራኤል ከግብፅ በወጣ ጊዜ ... ስለ ተቃወሙት፤*** ዘፀ17፥8-13፤ ዘኍ14፥43:45፤ ዘዳ25፥17-19 ይመ፤ ከመሳ3፥13፤ 6፥3-5:33፤ 7፥12፤ 10፥12 ጋር ያነጻጽሩ::

15፥3 ***ያላቸውንም ሁሉ ፈጽመህ አጥፋ፤*** ዘሌ 27፥28-29፤ ዘፀ13፥12-18፤ ኢሱ6፥17-18 ማብ ይመ:: ሳኦል በተሰጠው ኀላፊነት ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ታማኝነቱን መግለጥ ነበረበት::

15፥4 ***ጥላኢም፤*** ከይሁዳ በስተ ደቡብ የሚገኘው በኢሱ 15፥24 ላይ የተገለጸው ስፍራ ሊሆን ይችላል::

15፥5 ***አማሌቅ ከተማ፤*** አማሌቃውያን የሰፈሩበት በጥላኢምና በቃዴስ በርኔ መካከል የሚገኝ ስፍራ ነው፤ የንጉሣቸው መቀመጫ ሊሆን ይችላል::

15፥6 ***ቄናውያን፤*** ከምድያማውያን ጋር ዝምድና ያላቸው የሲና በረሓ ዘላኖች ሳይሆኑ አይቀሩም:: ሙሴ ምድያማዊት ሴት አገባ (ዘፀ2፥16፤ 21፥22፤ ዘኍ10፥29)፤ ምድያማውያንና ቄናውያን እንደ አንድ ሕዝብ ተጠቅሰዋል (መሳ1፥16፤ 4፥11):: ከቄናውያንም መካከል አንዳንዶቹ እስራኤላውያንን ተከትለው በመሄድ በከነዓን ምድር ተቀምጠዋል (27፥10፤ መሳ1፥16፤ 4፥17-23፤ 5፥24፤1ዜና 2፥55)::

15፥7 ***ከኤውላጥ ... እስከ ሱር፤*** ኤውላጥ የት እንደ ምትገኝ አይታወቅም፤ ሱር ግን በግብፅ ምስራቅ ድንበር ላይ ትገኛለች (27፥8፤ ዘፍ16፥7፤ 20፥1 ይመ):: ይህን አካባቢ እስማኤላውያን ይዘውት ነበር (ዘፍ25፥18 ይመ)::

15፥8 ***ሕዝቡን ሁሉ፤*** ጦርነት የገጠሟቸውን አማሌቃውያንን በሙሉ ማለት ነው፤ አንዳንድ አማሌቃውያን ግን ከሞት ተርፈዋል (27፥8፤ 30፥1:18፤ 2ሳሙ8፥12፤ 1ዜና 4፥43 ይመ)::

*15፥9፤* እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሲቃወሙ

በትክክል አይታወቅም
ግን የተናቀውንና የማይጠቅመውን ሁሉ
አጠፉ::
10ከዚህ በኋላ *የእግዚአብሔር* ቃል እን
ዲህ ሲል ወደ ሳሙኤል መጣ፤ 11“ሳኦልን
በማንገሤ ተጸጽቻለሁ፤ እኔን ከመከተል
ተመልሶአልና፣ ትእዛዜንም አልፈጸመምና::”
ሳሙኤልም እጅግ ተጨንቆ፣ ሌሊቱን ሁሉ
ወደ *እግዚአብሔር* ጮኸ::
12ሳሙኤልም ጠዋት ተነሥቶ በማለዳ
ሳኦልን ለመገናኘት ሄደ፤ ነገር ግን፣ “ሳኦል
ወደ ቀርሜሎስ ሄዶአል፤ ለራሱ ክብር የመ
ታሰቢያ ሐውልት በዚያ ካቆመ በኋላ ተመ
ልሶ ወደ ጌልገላ ወርዶአል” ተብሎ ተነገ
ረው::
13ሳሙኤል ባገኘው ጊዜ ሳኦል፣ “*እግዚአ
ብሔር* ይባርክህ፤ *የእግዚአብሔርን* ትእዛዝ
ፈጽሜለሁ” አለው::
14ሳሙኤል ግን፣ “ታዲያ ይህ በጆሮዬ
የምሰማው የበጎች ጩኸትና የበሬዎች ግሣት
ምንድን ነው?” ሲል ጠየቀ::
15ሳኦልም፣ “ሰራዊቱ ከአመሌቃውያን
ማርከው ያመጧቸው ናቸው፤ ምርጥ ምር
ጦቹ በጎችና በሬዎች *ለእግዚአብሔር* ለአምላክህ
መሥዋዕት እንዲሆኑ ሳይገድሉ የተዉ
አቸው ናቸው፤ የቀሩትን ግን በሙሉ አጥፍ
ተናል” ብሎ መለሰ::
16ሳሙኤልም ሳኦልን፣ “ስማ! ትናንት ማታ
*እግዚአብሔር* የነገረኝን ልንገርህ?” አለው::
ሳኦልም፣ “ንገረኝ” ሲል መለሰለት::
17ሳሙኤልም እንዲህ አለው፤ “በዐይንህ
ፊት ታናሽ የነበርህ ብትሆንም፣ የእስራኤል

15፥11 ቍ35፤ ዘፍ6፥6፤ዘፀ32፥14፤ ኢሱ22፥16፤ 1ሳሙ 8፥6፤ ኢዮ21፥14፤ 34፥27፤መዝ28፥5፤ ኢሳ5፥12፤53፥6፤ ኤር 48፥10፤ ሕዝ18፥24
15፥12 ዘኍ32፥42፤ ኢሱ15፥55
15፥17 ዘዐ3፥11
15፥19 ዘፍ14፥23፤ 1ሳሙ14፥32
15፥20 1ሳሙ28፥18
15፥22 መዝ40፥6-8፤ 51፥16፤ምሳ21፥3፤ ኢሳ1፥11-15፤ ኤር 7፥22፤ሆሴ6፥6፤ አሞ 5፥25፤ ሚክ6፥6-8፤ ማር12፥33
15፥23 ዘዳ18፥10፤ 1ሳሙ13፥13
15፥24 ዘፀ9፥27፤ ዘኍ22፥34፤ 1ሳሙ 13፥13፤ መዝ51፥4፤ ምሳ29፥25፤ ኢሳ51፥ 12-13፤ ኤር42፥11

ነገዶች መሪ ሆነህ የለምን? *እግዚአብሔ
ርም* በእስራኤል ላይ ቀብቶ አንግሦሃል::
18እግዚአብሔርም፣ ‘ሂደህ እነዚያን ኀጢአ
ተኞቹን አማሌቃውያንን ፈጽመህ አጥፋ
ቸው፤ ጨርሰህ እስክታጠፋቸውም ድረስ
ውጋቸው’ ብሎ ልኮህ ነበር:: 19ታዲያ *እግዚ
አብሔርን* ለምን አልታዘዝህም? ለምርኮ
ውስ ተስገበገበህ *በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ
የሆነውን ነገር ለምን አደረግህ?”
20ሳኦልም መልሶ እንዲህ አለ፤ “*እግዚአ
ብሔር* ታዝዣለሁ፤ እግዚአብሔር በላከኝ መሠ
ረት ሄጃለሁ፤ አማሌቃውያንን በሙሉ አጥ
ፍቼ ንጉሣቸውን አጋግን አምጥቻለሁ:: 21ሰራ
ዊቱ ግን ከምርኮው ለእግዚአብሔር ከተለዩት
መካከል፣ ምርጥ ምርጡን በግና በሬ፣ በጌ
ልገላ ለአምላክህ *ለእግዚአብሔር* ይሠዉ ዘንድ
ወስደዋል::”
22ሳሙኤልም እንዲህ አለ፤
“ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ደስ
የሚለውን ያህል፣ *እግዚአብሔር*፣
በሚቃጠል ቍርባንና መሥዋዕት ደስ
ይለዋልን?
እነሆ! መታዘዝ ከመሥዋዕት፣
ማዳመጥም ከአውራ በግ ሥብ ይበልጣል::
23ዐመፅ እንደ ጥንቈላ ያለ ኀጢአት፣
እልኸኝነትም እንደ ጣዖት አምልኮ ያለ
ክፉ ነገር ነው፤ አንተ *የእግዚአብሔርን* ቃል
ስለ ናቅህ፣ እርሱም ንጉሥ እንዳትሆን ንቆ
ሃል::”
24ከዚያም ሳኦል ሳሙኤልን እንዲህ አለው፤
“ኀጢአት ሠርቻለሁ፤ *የእግዚአብሔርን* ትእ
ዛዝና የአንተን መመሪያ ጥሻለሁ፤ ሕዝቡን

(ቍ3)፣ በአማሌቃውያን ላይ ያወጁት ቅዱስ ጦርነት፣ ከነዓንን በወረሩበት ጊዜ አካን እንዳደረገው የግል ጥቅምን ወደ ማሳደድ ተለወጠ (ኢሱ7፥1 ይመ):: ምርጡን ሁሉ ለራስ አስቀርቶ የተናቀውንና ደካማውን በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠት ድፍረት የተሞላበት (ሚል1፥7-12 ይመ)፣ ይቅርታም የማይገኝለት (ቍ19 ይመ) ነው ፤ ይህም እጅግ የከበረውና የተሻለው ለእግዚአብሔር ሊሠዋ ይገባል በማለት (ቍ15:21 ይመ) የተፈጸመ ድርጊት ነው::

15፥11 ***ተጸጽቻለሁ፤*** የ ቍ 29 ማብ ይመ:: ***እኔን ከመከተል ተመልሶአልና፤*** ንጉሥ እንደ መሆኑ መጠን የሚጠበቅበትን መሠረታዊ ኀላፊነት ጥሶአል (2፥14-15 ማብ ይመ)::

15፥12 ***ቀርሜሎስ፤*** ከኬብሮን በስተ ደቡብ ዐሥራ አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ ይገኛል (25፥2፤ ኢሱ 15፥55 ይመ):: ***ለራሱ ክብር የመታሰቢያ ሐውልት፤*** እዚህ ላይ ሳኦል ራሱን ከፍ ከፍ ያደረገበት ሁኔታ፣ አሞናውያንን ድል ካደረገ በኋላ ካሳየው ትሕትና ጋር በእጅጉ የሚቃረን ነው (የ11፥13ን ማብ ይመ፤ ከቍ 17 ጋር ያነጻጽሩ፤ 2ሳሙ 18፥18 ይመ):: ***ጌልገላ፤*** ሳኦል ወደ ነገሠበትና ትእዛዝ ወደ ተቀበለበት ተመለሰ (11፥14-12፥25 ይመ)፤ በተጨማሪም ካለመታዘዙ የተነሣ ከዘሮቹ ንጉሥ እንደማይነሣ የተነገረው በዚህ ስፍራ ነው(13፥13-14)::

15፥13 ***የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ፈጽሜለሁ፤*** በዚህ ስፍራና በቍ 20 ላይ ሳኦል በሚናገረው ቃል ለሳሙኤል ታማኝ ሆኖ አልተገኘም::

15፥15 ***ሰራዊቱ ... ምርጥ ምርጦቹ ... መሥዋዕት እንዲሆኑ ሳይገድሉ የተዉአቸው፤*** ሳኦል ኀላፊነቱን ከራሱ አውርዶ ወደ ሰራዊቱ ሲያስተላልፍና ድርጊታቸው ይቅር እንዲባል ቅዱስ የሚመስል ሐሳብ ሲያቀርብ ይታያል:: ***ለእግዚአብሔርለ አምላክህ፤*** ሳኦል ምንም እንኳ ስለ መታዘዝና መሥዋዕት በማቅረብ እግዚአብሔርን ለማክበር ፍላጎት እንዳለው በአፉ ቢናገርም፣ በዚህ ስፍራና በቍ 21:30 ላይ “አምላኬ” ከማለት ይልቅ “አምላክህ” ማለቱ ከእግዚአብሔር መራቁን ያመለክታል (ለተመሳሳይ ጉዳይ 12፥19 ይመ)::

15፥17 ***በዐይንህ ታናሽ የነበርህ ብትሆንም፤*** 9፥21፤ 10፥22 ይመ::

*15፥22፤* ሳሙኤል መሥዋዕት ማቅረብ አይጠቅምም አላለም፤ ነገር ግን መሥዋዕቱ ተቀባይነት የሚኖረው በመታዘዝና በአክብሮት መንፈስ የቀረበ እንደ ሆነ ነው ለማለት ነበር (መዝ 15፤ ኢሳ1፥11-17፤ ሆሴ6፥6፤ አሞ5፥21-27፤ ሚክ6፥6-8 ይመ):: ***ከአውራ በግ ሥብ፤*** የሚሠዉ እንስሳት ሥብ ምንጊዜም ለእግዚአብሔር የሚሰጥ ነው (2፥15፤ ዘፀ23፥18፤ ዘሌ3፥14-16፤ 7፥30 ይመ)::

15፥23 ***ዐመፅ፤*** ሳሙኤል፣ ሳኦልን የሚገሥጸው ንጉሥ በሆነበት ጊዜ የገባውን ቃል ኪዳን መጣሱን በማሳየትና በእግዚአብሔር ላይ የፈጸመውን ጥፋት በመግለጥ ነበር (12፥14-15 ይመ):: ***እንደ ጥንቈላ ያለ ኀጢአት፤*** በእግዚአብሔር ላይ የሚፈጸም እጅግ የከፋ በደል ነው (ዘሌ 19፥26፤ ዘዳ 18፥9-12)፤ ይህ በደል ራሱ ሳኦል ያወገዘው በደል ነበር (28፥3:9):: ***የእግዚአብሔርን ቃል ስለ ናቅህ፤*** የእግዚአብሔርን መንግሥት ዐይነተኛ ባሕርይ በመሻር ከእግዚአብሔር ትእዛዝ በላይ የራሱን ፈቃድና ሐሳብ የሚያደርግ ንጉሥ፣ እግዚአብሔር የሚጠቀምበት የሕዝቡ መሪ መሆኑ ያበቃል:: ***እርሱም ንጉሥ እንዳትሆን ንቆሃል፤*** እዚህ ላይ የተሰጠው ፍርድ ቀደም ብሎ ከተሰጠው ፍርድ በላይ ነው (የ13፥14 ማብ ይመ):: ይህ ምንም እንኳ በቅርብ የማይፈጸም ቢሆንም፣ ራሱ ሳኦል በገዛ ፈቃዱ ዙፋኑን መልቀቅ አለበት፤ በም16፥31 ላይ እንደ ተመለከተው ሁኔታዎች ወደ ሞቱ ሲያመሩ እናያለን:: የእግዚአብሔር መንፈስ ከእርሱ መራቁ፣ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ማጣቱ (16፥14)፣ ወንድ ልጁ ዮናታንና ሴት ልጁ ሜልኮም እርሱን ክደው ዳዊትን መውደዳቸውና የእርሱ ባለሟል የነበሩትም ሁሉ ለዳዊት መገዛታቸው በዚህ ውስጥ ይጠቃለላል (22፥17)::

*15፥24፤* ሳኦል የገባው የንስሓ ዐይነት ራሱን በማዳንና በሕዝቡ በማሳበብ ላይ የተመሠረተ ነበር (ከ2ሳሙ12፥13፤ መዝ51

ፈርቼ ስለ ነበር፣ የጠየቁኝን ታዝዣለሁ::
25አሁንም፣ ኀጢአቴን ይቅር እንድትለኝ፣
*ለእግዚአብሔርም* እሰግድ ዘንድ አብረኸኝ
እንድትመለስ እለምንሃለሁ::"

26ሳሙኤል ግን፣ "ከአንተ ጋር አልመለ
ስም፤ አንተ *የእግዚአብሔርን* ቃል ንቀሃል፤
*እግዚአብሔርም* በእስራኤል ላይ ንጉሥ እን
ዳትሆን ንቆሃል" አለው::

27ሳሙኤል ለመሄድ ዘወር ባለ ጊዜ፣
ሳኦል የልብሱን ጫፍ ያዘ፤ ተቀደደም::
28ሳሙኤልም እንዲህ አለው፤ "*እግዚአብሔር*
የእስራኤልን መንግሥት ዛሬ ከአንተ ቀዶ
ታል፤ ከአንተም ለሚሻል ለጎረቤትህ አሳ
ልፎ ሰጥቶታል:: 29የእስራኤል ክብር የሆ
ነው *እግዚአብሔር* አይዋሽም፤ አይጸጸት
ምም፤ እርሱ ይጸጸት ዘንድ ሰው አይደለ
ምና::"

30ሳኦልም መልሶ፣ "ኀጢአት ሠርቻለሁ፤
ነገር ግን በሕዝቤ አለቆች ፊትና በእስራኤል
ፊት አክብረኝ፤ ስስምባክህ *ለእግዚአብሔር*
እሰግድ ዘንድ እባክህ አብረኸኝ ተመለስ"
አለው:: 31ስለዚህ ሳሙኤል አብሮት ተመ
ለሰ፤ ሳኦልም *ለእግዚአብሔር* ሰገደ::

32ከዚያም ሳሙኤል፣ "የአማሌቃውያንን
ንጉሥ አጋግን አምጡልኝ" አለ::

አጋግም፣ "በውኑ ሞት እንዲህ መራራ
ነውን? በማለት እየተንቀጠቀጠ መጣ::

33ሳሙኤልም፣

"ሰይፍህ ሴቶችን ልጅ አልባ እንዳደረገ
ቻቸው፣ እናትህም በሴቶች መካከል ልጅ
አልባ ትሆናለች"

ሲል አጋግን ጌልገላ ላይ *በእግዚአብሔር*
ፊት ቈራረጠው::

34ከዚያም ሳሙኤል ወደ አርማቴም ሄደ::
ሳኦል ግን ወደ ቤቱ ወደ ሳኦል ጊብዓ
ወጣ:: 35ሳሙኤል ለሳኦል ቢያለቅስለትም

15፥25 ዘፀ10፥17
15፥26 ዘኍ15፥31፤ 1ሳሙ13፥14፤ 1ነገ14፥10
15፥27 1ሳሙ28፥14፤ 1ነገ11፥11፡31፤14፥8፤ 2ነገ17፥21
15፥28 1ሳሙ13፥14፤ 28፥17፤2ሳሙ6፥21፤ 7፥15
15፥29 ዘኍ23፥19፤ ቲቶ1፥2፤ዕብ7፥21
15፥30 ዘኍ22፥34፤ ኢሳ29፥13፤ ዮሐ12፥43
15፥33 አስ9፥7-10፤ ኤር18፥21
15፥34 መሳ19፥14፤ 1ሳሙ7፥17፤10፥5
15፥35 ቍ11፤ ዘፍ6፥6፤1ሳሙ16፥1፤ 19፥24
16፥1 ሩት4፥17፤ 1ሳሙ8፥6፤10፥1፤ 13፥14፤15፥35፤ 2ሳሙ5፥2፤7፥8፤ 1ነገ 8፥16፤ 1ዜና 12፥23፤ መዝ78፥70፤ ሐሥ13፥22
16፥3 ዘፀ4፥15፤ ዘዳ17፥15
16፥4 ዘፍ48፥7፤ 1ሳሙ21፥1፤ 1ነገ2፥13፤2ነገ9፥17፤ ሉቃ2፥4
16፥5 ዘፀ19፥10፡22
16፥6 1ሳሙ17፥13፤ 1ዜና2፥13
16፥7 1ሳሙ2፥3፤ 2ሳሙ7፥20፤ መዝ44፥21፤139፥23፤ 147፥10፤ራእ2፥23

እንኳ እስከ ሞተበት ዕለት ድረስ ዳግመኛ
ሊያየው አልሄደም፤ *እግዚአብሔርም* ሳኦልን
በእስራኤል ላይ በማንገሡ ተጸጸተ::

## ሳሙኤል ዳዊትን መቀባቱ

16 *እግዚአብሔር* ሳሙኤልን፣ "በእስራ
ኤል ላይ እንዳይነግሥ ለናቅሁት
ለሳኦል የምታለቅስለት እስከ መቼ ነው? ወደ
ቤተ ልሔሙ ሰው ወደ እሴይ ስለምልክህ፣
ዘይት በቀንድ ሞልተህ ሂድ፤ ከልጆቹ
አንዱ ንጉሥ ይሆን ዘንድ መርጬዋለሁ"
አለው::

2ሳሙኤል ግን፣ "ሳኦል ከሰማ ስለሚገድ
ለኝ እንዴት መሄድ እችላለሁ?" አለ::

*እግዚአብሔርም* እንዲህ አለው፤ "አን
ዲት ጊደር ይዘህ ሂድና፣ '*ለእግዚአብሔር*
ልሠዋ መጥቻለሁ' በል:: 3እሴይን ወደ
መሥዋዕቱ ጥራው፤ ከዚያም የምታደርገውን
አሳይሃለሁ፤ የምነግርህንም ሰው ትቀባል
ኛለህ::"

4ሳሙኤል *እግዚአብሔር* ያለውን ነገር
አደረገ:: ቤተ ልሔም እንደ ደረሰም፣
የከተማዪቱ ሽማግሌዎች እየተንቀጠቀጡ
ሊገናኙት መጡ፣ እነርሱም "አመጣጥህ ለሰ
ላም ነውን?" ብለው ጠየቁት::

5ሳሙኤልም፣ "አዎን፤ ለሰላም ነው፤ የመጣ
ሁትም *ለእግዚአብሔር* መሥዋዕት ላቀርብ
ነው፤ እናንተም ራሳችሁን ቀድሳችሁ ከእኔ
ጋር ወደ መሥዋዕቱ ኑ" ሲል መለሰላቸው::
ከዚያም እሴይንና ልጆቹን ቀደሳቸው፤ ወደ
መሥዋዕቱም እንዲመጡ ጠራቸው::

6እዚያ በደረሱ ጊዜም፣ ሳሙኤል ኤል
ያብን አይቶ፣ "በእርግጥ *እግዚአብሔር* የቀ
ባው ሰው እነሆ፤ *በእግዚአብሔር* ፊት ቆሞ
አል" ብሎ አሰበ::

7*እግዚአብሔር* ግን ሳሙኤልን፣ "መል

ላይ ከተገለጠው የዳዊት ንስሓ ጋር ያነጻጽሩ):: ሳኦል ቀደም ሲል የወታደሮቹ ድርጊት ትክክል እንደ ሆነ ለማሳመን ሞክሮ ነበር (ቍ 15:21)::

15፥25 ***አብረኸኝ እንድትመለስ፤*** ሳኦልን በከፍተኛ ደረጃ ያስጨነቀው ከነቢዩ ከሳሙኤል ጋር ያለው ግንኙነት በይፋ መቋረጡና ንግሥናውን ማጣቱ እንጂ፣ እግዚአብሔርን የማምለክ ያለ ማምለኩ ጒዳይ አልነበረም (ቍ 30)::

15፥28 ***ለጎረቤትህ፤*** ዳዊትን ማለት ነው (የ13፥14 ማብ ይመ)::

15፥29 ***የእስራኤል ክብር፤*** የእግዚአብሔር ስም ሲሆን፣ በሚክ1፥15 ብቻ ይገኛል፤ በመዝ106፥20፤ ኤር2፥11፤ ሆሴ4፥7 "ክብር" ተብሎ ተጠርቶአል (የ4፥21 ማብ ይመ)፤ ከ2ሳሙ 1፥19፤ መዝ89፥17፤ ኢሳ13፥19 ጋር ያነጻጽሩ:: ***አይዋሽም፤ አይጸጸትም፤*** ዘኍ23፥19፤ መዝ110፥4፤ ኤር4፥28፤ ሚል3፥6 እና ማብ ይመ:: በዚህ ዐረፍተ ነገርና በቍ 11፡ 35 ላይ "አይጸጸትም" በሚለው ቃል መካከል በሐሳብ ግጭት የለም፤ እግዚአብሔር ስሜት አለውና (ስሜት የስብዕና መለያ ከሆኑት ነገሮች አንዱ ነው)::

15፥31 ***ሳሙኤል አብሮት ተመለሰ፤*** ሳሙኤል ከሳኦል ጋር ለመመለስ የተስማማው ሳኦልን ለማክበር ሳይሆን፣ በአማሌቃውያን ንጉሥ በአጋግ ላይ የተወሰነውን የእግዚአብሔር ፍርድ ለመፈጸምና የሳኦልን ከንጉሣዊ ማፈንገጥ በትኩረት ለማስገንዘብ ነበር::

15፥34 ***አርማቴም፤*** የሳሙኤል አገር ነው (7፥17 ይመ):: ***ሳኦል ጊብዓ፤*** የ10፥5 ማብ ይመ::

15፥35 ***ሳሙኤል ለሳኦል ቢያለቅስም፤*** ሳሙኤል፣ ሳኦልን የሞት ያህል ቈጥሮ አለቀሰ (በ6፥19 ላይ "አለቀሰ" የሚለውን ቃል ይመ):: ለሳኦል የነበረው ፍቅር እንዳለ ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ንጉሥ እንዳይሆን ስለ ናቀው ዳግመኛ ከእርሱ ጋር ለመገናኘት አልፈለገም:: ሳኦል ግን በአንድ ወቅት ወደ ሳሙኤል መጥቶ ነበር (19፥24 ይመ)::

16፥1 ***እግዚአብሔር ሳሙኤልን ... አለው፤*** ምናልባት ይህ የሆነው በ1025 ዓ.ቅ.ክ ሊሆን ይችላል (የ15፥1-35 ማብ ይመ):: ***እሴይ፤*** የእሴይን የትውልድ ሐረግ በሩት 4፥18-22፤ማቴ1፥3-6 ይመ:: ***ቤተ ልሔሙ፤*** ቀድሞ ኤፍራታ በመባል የምትታወቅ ከኢየሩሳሌም በስተ ደቡብ ስምንት ኪሎ ሜትር ያህል የምትርቅ ከተማ ናት (ዘፍ48፥7)፤ በኋላም "የዳዊት ከተማ" ተብላለች (ሉቃ 2፥4)፤ ክርስቶስም የተወለደው በቤተ ልሔም ነው (ሚክ5፥2፤ ማቴ2፥1፤ ሉቃ2፥4-7):: ***ከልጆቹ አንዱ ንጉሥ ይሆን ዘንድ መርጬዋለሁ፤*** የ13፥14 ማብ 15፥28 ይመ::

16፥2 ***ሳኦል ... ስለሚገድለኝ፤*** ሳሙኤል ከሚኖርበት ከአርማቴም (15፥34) ወደ ቤተ ልሔም የሚወስደው መንገድ ሳኦል የሚኖርበትን ጊብዓን አቋርጦ የሚያልፍ ነበር፤ ይሁን እንጂ ሳኦል አስቀድሞ በእርሱ ምትክ እግዚአብሔር ሌላ ሰው እንደሚያነግሥ ዐውቆ ነበር (15፥28):: እንግዲህ ሳሙኤል የፈራው፣ ቅናት ሳኦልን ለዐመፅ ያነሣሣው ይሆናል በማለት ነበር፤ በኋላ የተከሠቱት ሁኔታዎች (18፥10-11፤19፥10፤20፥33) የሳሙኤል ፍርሀት ትክክል እንደ ነበር አመልክተዋል::

16፥3 ***ትቀባልኛለህ፤*** የ9፥16 ማብ ይመ::

16፥5 ***ራሳችሁን ቀድሳችሁ፤*** በመንፈሳዊ ረገድ ራስን ማዘጋጀትን፣ በሥርዐቱ መሠረት መታጠብንና ንጹሕ ልብስ በመልበስ መንጻትን ያጠቃልላል (ዘፀ19፥10:14፤ ዘሌ15፤ ዘኍ19፥11-22 ይመ)::

16፥6 ***ኤልያብን፤*** የእሴይ ትልቁ ልጅ ነው (1፥13)::

16፥7 ***መልኩን ወይም ቁመቱን፤*** ከዚህ በፊት በሳኦል ላይ የታየውን መልክና ቁመና፣ በዳዊት ላይ መጠበቅ አልነበረበትም

ኩን ወይም ቁመቱን አትይ፤ እኔ ንቄዋለ
ሁና። እግዚአብሔር የሚያየው፣ ሰው እንደሚ
ያየው አይደለም። ሰው የውጭውን ገጽታ
ያያል፤ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል" አለው።
[8]ከዚያም እሴይ አሚናዳብን ጠርቶ በሳ
ሙኤል ፊት እንዲያልፍ አደረገ፤ ሳሙኤል
ግን፣ "እግዚአብሔር ይህንንም አልመረጠ
ውም" አለው። [9]እሴይም ሣማን አሳለፈ፤ ሳሙ
ኤልም፣ "እርሱንም እግዚአብሔር አልመረጠ
ውም" አለ። [10]እሴይም ሰባቱን ልጆቹን በሳሙ
ኤል ፊት እንዲያልፉ አደረገ፤ ሳሙኤል
ግን፣ "እግዚአብሔር እነዚህንም አልመረጣቸ
ውም" አለው። [11]ቀጥሎም እሴይን፣ "ልጆችህ
እነዚሁ ብቻ[ን] ናቸውን?" ሲል ጠየቀው።
እሴይም፣ "የሁሉም ታናሽ ገና አልመጣም፤
ነገር ግን በጎች እየጠበቀ ነው" ብሎ መለሰ።
ሳሙኤልም፣ "በል ልከህ አስመጣው፤
እስኪመጣ ድረስ አንቀመጥምና[ን]" አለው።
[12]ስለዚህ ልኮ አስመጣው፤ እርሱም ደም
ግባት ያለው፣ ዐይኑ የሚያምርና መልከ
መልካም ነበረ።
እግዚአብሔርም፣ "የመረጥሁት ይህ
ነውና ተነሥተህ ቅባው" አለው።
[13]ሳሙኤልም የዘይቱን ቀንድ ወስዶ በወን
ድሞቹ ፊት ቀባው። ከዚያ ቀን ጀምሮ የእግ
ዚአብሔር መንፈስ በዳዊት ላይ በኀይል
መጣ፤ ሳሙኤልም ወደ አርማቴም ሄደ።

## ዳዊት ሳኦልን ማገልገሉ

[14]የእግዚአብሔር መንፈስ ከሳኦል ስለ ራቀ፤
ከእግዚአብሔር ዘንድ የታዘዘ ክፉ[ነ] መንፈስ
ያሠቃየው ነበር።

16፥8 1ሳሙ 17፥13
16፥9 1ሳሙ 17፥13፤ 2ሳሙ 13፥3፤21፥21
16፥11 ዘፍ37፥2፤ 1ሳሙ 17፥12፤ 2ሳሙ 7፥8
16፥12 ዘፍ39፥6፤ 1ሳሙ 9፥17
16፥13 1ሳሙ 2፥35፤ 11፥6፤18፥12፣ 2ሳሙ 22፥51
16፥14 ቊ23፤ መሳ9፥23፤1፥16፥20፤ 1ሳሙ 18፥10፤ 2ሳሙ 7፥15

[ን]11 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጉሞች ከዚህ ጋር ይስማ ማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን እንሰበሰብምና ይላል።
[ነ]14 በዚህ እንዲሁም በቍጥር 15፡16 እና 23 ላይ ጉጂ

(9፥2፤ 10፥23-24 ይመ)። *ልብን፤* እግዚአብሔር የሚመረምረው ልብንና ኵላሊትን ነው (1ነገ8፥39፤ 1ዜና28፥9፤ ሉቃ16፥15፤ ዮሐ 2፥25፤ ሐሥ1፥24 ይመ)።

16፥8 *አሚናዳብን፤* የእሴይ ሁለተኛ ልጅ ነው።


16፥9 *ሣማን፤* የእሴይ ሦስተኛ ልጅ ነው።

16፥11 *በጎች እየጠበቀ ነው፤* እግዚአብሔር የመረጠው የበጎችን እረኛ ነው (የ9፥3 ማብ ይመ፤ 2ሳሙ 7፥7-8፤ መዝ 78፥71-72 ይመ)።

16፥13 *በወንድሞቹም ፊት፤* ዳዊት ሲቀባ እዚያ የነበሩት ጥቂት ሰዎች ነገ ንጉሥ እንደሚሆን እርግጠኞች ሆኑ፤ እንዲሁም ዳዊት በሳሙኤል የተቀባ መሆኑንና የሳኦልን መንግሥት ቀምቶ የወሰደበት አለመሆኑንም ወደ ፊት በሰፊው የሚመሰክሩ ናቸው። *የእግዚአብሔር መንፈስ በዳዊት ላይ በኀይል መጣ፤* 10፥5-6፤ 11፥6፤ መሳ15፥14 ይመ።

*16፥14-17:58፤* በሚቀጥሉት ሁለት ክፍሎች ዳዊት በሳኦል ቤተ መንግሥት ውስጥና በእስራኤልም ሁሉ ፊት ሲቆም፣ በገና የመደርደር ስጦታ ያለውና ጦረኛም እንደ ሆነ ታይቶ ነው። በእነዚህ በሁለቱ ስጦታዎቹ በእስራኤል ዘንድ የታወቀ ሆነ ለሕዝቡንም በጠንካራ መንፈሳዊና ፖለቲካዊ አመራር መራ (2ሳሙ 22፡ 23፥1-7 ይመ)፤ በእነዚህ ሁለት ስጦታዎቹ ዳዊት ሳኦልን አገለገሉታል።

16፥14 *የእግዚአብሔር መንፈስ ከሳኦል ስለ ራቀ፤* ከመሳ 16፥20 ጋር ያነጻጽሩ። የእግዚአብሔር መንፈስ ከሳኦል ተለይቶ መራቁና በታላቅ ኀይል በዳዊት ላይ ማደሩ ሕይወት ውስጥ



15የሳኦል አገልጋዮችም እንዲህ አሉት፤
“እነሆ፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ የታዘዘ ክፉ
መንፈስ እያሠቃየህ ነው:: 16እንግዲህ በገና
መደርደር የሚችል ሰው እንዲፈልጉ፣ ጌታ
ችን በፊቱ የሚቆሙትን አገልጋዮቹን ይዘዝ፤
ከዚያም ከእግዚአብሔር የታዘዘው ክፉ መን
ፈስ ባንተ ላይ በሚመጣ ጊዜ በገና ይደረ
ድርልሃል፤ ደኅናም ትሆናለህ::”
17ስለዚህ ሳኦል አገልጋዮቹን፣ “መልካም
አድርጎ በገና መደርደር የሚችል ሰው
ፈልጋችሁ አምጡልኝ” አላቸው::
18ከአገልጋዮቹም አንዱ፣ “መልካም አድ
ርጎ በገና መደርደር የሚችለውን የቤተ ልሔ
ሙን የእሴይን ልጅ አይቻለሁ፣ እርሱም
ጀግናና ተዋጊ ነው፤ በአነጋገሩ አስተዋይና
የደስ ደስ ያለው ነው፤ *እግዚአብሔርም*
ከእርሱ ጋር ነው” ብሎ መለሰ::
19ከዚያም ሳኦል፣ “ከበጎች ጋር ያለውን
ልጅህን ዳዊትን ላክልኝ” ሲል መልክተኞ
ችን ወደ እሴይ ላከ:: 20እሴይም እንጀራና
በወይን ጠጅ የተሞላ አቁማዳ በአህያ
አስጭኖ፣ የፍየል ጠቦትም አስይዞ ልጁን
ዳዊትን ወደ ሳኦል ላከው::
21ዳዊት ወደ ሳኦል መጥቶ አገልግሎቱን
ጀመረ፤ ሳኦልም እጅግ ወደደው፣ እርሱም
የሳኦል ጋሻ ጃግሬ ሆነ:: 22ከዚያም ሳኦል፣
“ዳዊትን ወድጄዋለሁና ከእኔ ዘንድ ሆኖ
እንዲያገለግለኝ ፍቀድልኝ” ብሎ ወደ እሴይ
ላከ::
23ክፉው መንፈስ ከእግዚአብሔር ዘንድ በሳ
ኦል ላይ በሚመጣበት ጊዜ፣ ዳዊት በገና
ውን ይዞ ይደረድር ነበር፤ ሳኦልም ይሻ
ለው ነበር፤ ክፉውም መንፈስ ከእርሱ ይርቅ
ነበር::

16፥16 ቊ23፤ 1ሳሙ10፥5:6፤ 2ዜና29፥26-27፤ መዝ49፥4
16፥18 ዘፍ39፥2፤ ሩት4፥17፤ 1ሳሙ 17፥37፤ 20፥13፤ 2ሳሙ17፥8፤ 1ዜና 22፥11፤ ማቴ1፥23
16፥19 1ሳሙ17፥15
16፥20 ዘፍ32፥13፤ 1ሳሙ10፥4
16፥21 ዘፍ41፥46
16፥23 ቊ14፤ መሳ9፥23
17፥1 ኢሱ10፥10:11፤15፥35፤ 1ሳሙ 13፥5፤ 2ዜና28፥18
17፥2 1ሳሙ21፥9
17፥4 1ሳሙ21፥9፤ 2ሳሙ21፥19
17፥6 ቊ45፤ 1ሳሙ18፥10
17፥7 ቊ41፤ 2ሳሙ21፥19፤ 1ዜና11፥23፤20፥5
17፥8 2ሳሙ2፥12-17
17፥10 ቊ23:26:45፤2ሳሙ21፥21

## ዳዊትና ጎልያድ

17 ፍልስጥኤማውያን ሰራዊታቸውን ለጦ
ርነት አሰባሰበው፣ በይሁዳ ምድር
በሰኮት ላይ አከማቹ፤ እነርሱም በሰኮትና
በዓዜቃ መካከል ባለው በኤፌስደሚም ሰፈሩ::
2ሳኦልና እስራኤላውያን ተሰብስበው፣ በዔላ
ሸለቆ ሰፈሩ፤ ፍልስጥኤማውያንንም ለመ
ግጠም ቦታ ቦታቸውን ያዙ:: 3ሸለቆ በመካ
ከላቸው ሆኖ ፍልስጥኤማውያን አንዱን
ኰረብታ እስራኤላውያን ደግሞ፣ ሌላውን
ኰረብታ ያዙ::
4ከጌት የመጣ ቁመቱ ከዘጠኝ ጫማ በላይ
የሆነ፣ ጎልያድ የተባለ አንድ ጀግና ከፍልስ
ጥኤማውያን ሰፈር ወጣ:: 5እርሱም ከናስ
የተሠራ የራስ ቍር ደፍቶ፣ ክብደቱ
አምስት ሺህ ሰቅል የሆነ የናስ ጥሩር ለብሶ
ነበር:: 6በእግሮቹ ላይ የናስ ገምባሌ አድ
ርጎ፣ በጫንቃው ላይ ደግሞ የናስ ጭሬ
ይዞ ነበር:: 7የጦሩም ዘንግ እንደ ሸማኔ
መጠቅለያ የወፈረ፣ የጦሩም ብረት ስድ
ስት መቶ ሰቅል ያህል የሚመዝን ነበር፤
ጋሻ ጃግሬውም ከፊት ከፊቱ ይሄድ ነበር::
8ጎልያድ ቆሞ ለተሰለፈው የእስራኤል
ሰራዊት እንዲህ ሲል ጮኾ ተናገረ፤ “ለው
ጊያ ተሰልፋችሁ መውጣታችሁ ስለ ምንድን
ነው? እኔ ፍልስጥኤማዊ፣ እናንተም የሳኦል
አገልጋዮች አይደላችሁምን? አንድ ሰው ምረ
ጡና እኔ ወደ አለሁበት ይውረድ፤ 9ከእኔ
ጋር ሊዋጋና ሊገድለኝ ከቻለ፣ እኛ ባሪያ
ዎቻችሁ እንሆናለን፤ እኔ ባሸንፈውና ብገድ
ለው ግን እናንተ ባሪያዎቻችን ትሆናላችሁ፤
ትገዙልናላችሁ::” 10ከዚያም ፍልስጥኤማዊው፣
“ዛሬ የእስራኤልን ሰራዊት እገዳደራለሁ፤
እንዋጋ ዘንድ ሰው ስጡኝ” አለ:: 11ሳኦልና
እስራኤላውያን ሁሉ የፍልስጥኤማዊውን ቃል

የሚታዩ ተቃራኒ ሂደቶችን ከወዲሁ ይጠቍማል:: *ከእግዚአብሔር ዘንድ የታዘዘ ክፉ መንፈስ፤* ይህና ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ሌሎች ዐረፍተ ነገሮች በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የሚያሳዩት፣ ክፉ መናፍስት በእግዚአብሔር ቍጥጥር ሥር እንደ ሆኑና እስከ ተፈቀደላቸው ገደብ ድረስ ብቻ እንደሚሠሩ ያመለክታል (መሳ 9፥23፤ 1ነገ22፥19-23፤ ኢዮ1፥12፤ 2፥6፤ 2ሳሙ24፥1፤ ከ1ዜና21፥1 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ሳኦል ባለመታዘዙ ምክንያት በክፉ መንፈስ ፍዳጻ ተቀጣ (ቍ15-16:23፤ 18፥10፤19፥9):: *ያሠቃየው ነበር፤* እየጐላ የመጣው የሳኦል ተስፋ መቍረጥና ጭንቀት፣ ቅንዓትና ዐመፅ ሊከሠት የቻለው ያለ ጥርጥር ንጉሥ እንዳይሆን ከመናቁ (13፥13-14፤ 15፥22-26፤ 18፥9፤ 20፥30-33፤ 22፥16-18) እና በሌላ በኩልም የዳዊት ተወዳጅነት እየጨመረ መሄዱን ከማወቁ የተነሣ ነው፤ በእነዚህም የሥነ ልቡና ችግሮች (18፥10-12፤ 19፥9-10) ውስጥ ክፉ መንፈስ ሠርቶአል::

16፥16 *ደኅናም ትሆናለህ፤* የሰውን መንፈስ የሚያረጋጉ አንዳንድ ዜማዎች እንዳሉ የታወቀ ነው (2ነገ3፥15 ይመ)፤ ይሁንና ከዚህ ከተለመደው ዜማ ሌላ ለጊዜውም ቢሆን ክፉውን መንፈስ ለማራቅ በዳዊት በገና የእግዚአብሔር መንፈስ ይሠራ ነበር (ቍ 23 ይመ)::

16፥19 *ልጅህን ዳዊትን ላክልኝ፤* ሳኦል ሳያውቀው እግዚአብሔር በእርሱ ምትክ የመረጠውን ሰው ወደ ቤተ መንግሥቱ እንዲመጣ ጠራው:: በዚህ ዐይነት ዳዊት ከሳኦልና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር መተዋወቅ ጀመረ::

16፥21 *እርሱም የሳኦል ጋሻ ጃግሬ ሆነ፤* ምናልባት ይህ ጊዜ ዳዊት በጎልያድ ላይ ድል ካገኘ በኋላ ቆይቶ ሊሆን ይችላል (18፥2 ይመ)::

17፥1 *በሰኮትና፤* ከፍልስጥኤማውያን ወሰን አጠገብ ከቤተ ልሔም በስተ ምዕራብ ሃያ አራት ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ ትገኛለች (2ዜና 28፥18 ይመ):: *ኤፌስደሚም፤* በ1ዜና 11፥13 ላይ ፈስደሚም ተብሎአል (2ሳሙ 23፥9 ይመ):: *በዓዜቃ፤* ከሰኩት በስተ ሰሜን ምዕራብ ከአንድ ኪሎ ሜትር ተኩል በላይ ርቃ የምትገኝ ስፍራ ናት::

17፥2 *በዔላ ሸለቆ፤* በዓዜቃና በሰኩት መካከል ባለው ደረቅ ወንዝ ላይ የሚገኝ ስፍራ ነው::

17፥4 *አንድ ጀግና፤* ከፍልስጥኤማውያን ጋር ይፋ ግንኙነት የነበራቸው ጥንታውያን ግሪኮች አንዳንድ ጊዜ ጦርነትን በሚመለከት የተመረጡ ሰዎች በሚያደርጉት ፍልሚያ አሸናፊና ተሸናፊ ይለዩ ነበር፤ የተፋላሚ ጀግኖቹን የመጨረሻ ውጤት የሚወስኑትም አማልክት ናቸው ተብሎ ይታመን ነበር:: እስራኤላውያንም እንዲህ ዐይነቱን ነገር ሳያውቁት አይቀሩም::

17፥11 *ሳኦልና እስራኤላውያን ሁሉ ... ፈሩ፤* የእስራኤል ትልቁ ተዋጊ (9፥2፤ 10፥23 ይመ)፤ በዋናው በፍልስጥኤማውያን ጀግና ፊት ተርበደበደ:: የሳኦልና የእስራኤል ሰራዊት ፍርሀት (ቍ24:32)፣ እግዚአብሔር በገባላቸው ቃል ኪዳን ላይ የነበራቸው እምነት መጥፋቱን አሳየ (ዘፀ23፥22፤ ዘዳ3፥22፤ 20፥1-4):: ፍርሀታቸው በእግዚአብሔር ከመደገፍ ውጭ ከምድራዊ ንጉሥ የሰላም ዋስትና ለማግኘት የነበራቸው ምኞት ከንቱ ሆኖ እንደ ቀረም አረጋግጦአል (የ8፥5:7 ማብ ይመ):: እስራኤላውያን እግዚአብሔር በገባላቸው የቃል ኪዳን ተስፋ መሠረት በእግዚአብሔር ሊታመኑ ይገባቸው ነበር እንጂ ጠላቶቻቸውን መፍራት አልነበረባቸውም (2ሳሙ

በሰሙ ጊዜ እጅግ ፈሩ፤ ደነገጡም።
12ዳዊት በይሁዳ የቤተ ልሔሙ ሰው የኤ
ፍራታዊው የእሴይ ልጅ ነበር። እሴይ ስም
ንት ወንዶች ልጆች ነበሩት፤ በሳኦልም
ዘመን ያረጀና ዕድሜው የገፋ ሰው ነበር።
13ሦስቱ የእሴይ ታላላቅ ልጆች ሳኦልን ተከ
ትለው ወደ ጦርነት ሄደው ነበር፤ እነር
ሱም ታላቁ ኤልያብ፣ ሁለተኛው አሚና
ዳብ፣ ሦስተኛውም ሣማ ይባላሉ፤ 14ዳዊት
የሁሉም ታናሽ ነበር። ሦስቱ ታላላቅ ወንድ
ሞቹ ሳኦልን ተከትለው ሄዱ፤ 15ዳዊት ግን
የአባቱን በጎች ለመጠበቅ ከሳኦል ዘንድ
ወደ ቤተልሔም ይመላለስ ነበር።
16ፍልስጥኤማዊውም አርባ ቀን ሙሉ ጠዋ
ትና ማታ ፊት ለፊት ብቅ እያለ ቆሞ ይታ
ያቸው ነበር።
17በዚህ ጊዜ እሴይ ልጁን ዳዊትን እንዲህ
አለው፤ "ይህን ዐሥር ኪሎ የተጠበሰ እሸትና
ዐሥር እንጀራ ለወንድሞችህ ይዘህ ወዳ
ሉበት የጦር ሰፈር በቶሎ ድረስ። 18ይህ
ንም ዐሥር የአይብ ጥፍጥፍ ለክፍል አዛዣ
ቸው፣ አብረህ ውሰድ፤ ወንድሞችህም እን
ዴት እንደሆኑ አይተህ፣ ደኅንነታቸውን
የሚያረጋግጥ ምልክት ከእነርሱ ዘንድ አም
ጣልኝ። 19እነርሱ ከሳኦልና ከእስራኤል ሰዎች
ሁሉ ጋር ሆነው በዔላ ሸለቆ ከፍልስጥኤማ
ውያን ጋር እየተዋጉ ናቸው።"
20ዳዊት በማለዳ በጎቹን ለጠባቂ ትቶ፣
እሴይ እንዳዘዘው ዕቃውን ይዞ ጕዞ ጀመረ።
ልክ ሰራዊቱ እየፎከረ ለውጊያ ቦታ ቦታ
ውን ለመያዝ በሚወጣበት ጊዜ ከጦሩ ሰፈር
ደረሰ። 21እስራኤልና ፍልስጥኤማውያን ቦታ
ቦታቸውን ይዘው ፊት ለፊት ተፋጠው
ይጠባበቁ ነበር። 22ዳዊት ዕቃውን ከስንቅ
ጠባቂው ዘንድ አስቀምጦ ወደ ጦሩ ግንባር
ሮጠ፤ ወንድሞቹንም አግኝቶ ደኅንነታቸውን
ጠየቀ። 23ከእነርሱም ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ፣
ከጌት የመጣው ፍልስጥኤማዊው ጀግና ጎል
ያድ ከሰልፉ መካከል ወጥቶ እንደ ለመደው
ሲደነፋ፤ ዳዊት ሰማ። 24እስራኤላውያንም
ሰውየውን ባዩት ጊዜ ሁሉም በታላቅ ፍር
ሀት ከፊቱ ሸሹ።
25እስራኤላውያንም እርስ በርሳቸው "ይህ
ሰው በየቀኑ እየመጣ እስራኤልን እንደሚገ
ዳደር ታያላችሁ? ይህን ሰው ለሚገድል፣
ንጉሡ ብዙ ሀብት ይሰጠዋል፤ ሴት ልጁን
ይድርለታል፣ የአባቱንም ቤት በእስራኤል
ዘንድ ከግብር ነጻ ያደርገዋል" ይባባሉ ነበር።
26ዳዊት በአጠገቡ የቆሙትን ሰዎች፣
"ለመሆኑ ይህን ፍልስጥኤማዊ ገድሎ እን
ዲህ ያለውን ውርደት ከእስራኤል ለሚያ
ስወግድ ሰው ምን ይደረግለታል? ደግሞስ
የሕያው እግዚአብሔርን ሰራዊት ይገዳደር
ዘንድ ይህ ያልተገረዘ ፍልስጥኤማዊ እርሱ
ማነው?" ሲል ጠየቀ።
27እነርሱም፣ "ለሚገድለው ሰው የሚደረግ
ለት ይህ ነው" ሲሉ አስቀድመው ያሉ
ትን ደግመው ነገሩት።
28ታላቅ ወንድሙ ኤልያብ፣ ዳዊት ከሰ
ዎች ጋር ሲነጋገር በሰማ ጊዜ እጅግ ተቈ
ጥቶ፣ "ለምን ወደዚህ ወረድህ? እነዚያንስ
ጥቂት በጎች በምድረ በዳ ለማን ተውሃ
ቸው? ትዕቢትህንና የልብህን ክፋት ዐው
ቃለሁ፤ የመጣኸው ጦርነቱን ለማየት ብቻ
ነው" አለው።
29ዳዊትም፣ "ታዲያ ምን አደረግሁ? መጠ
የቅ እንኳ አልችልም?" አለ። 30ከዚያም ወደ
ሌላ ሰው ዞር ብሎ፣ ያንኑ ጥያቄ ጠየቀ፤
ሰዎቹም እንደ ቀድሞው መለሱለት፤ 31ዳዊት
የተናገረው ነገር ወደ ሳኦል ጆሮ ደረሰ፤
ሳኦልም ልኮ አስጠራው።
32ዳዊትም ሳኦልን፣ "ከዚህ ፍልስጥኤማዊ
የተነሣ የማንም ሰው ልብ አይሸበር፤ ባሪያህ
ሄዶ ይዋጋዋል" አለው።
33ሳኦልም መልሶ "አንተ ገና አንድ ፍሬ
ልጅ ነህ፣ ሰውየው ግን ከልጅነቱ ጀምሮ
ውጊያ የተለማመደ ስለ ሆነ፣ ወጥተህ
ይህን ፍልስጥኤማዊ ልትገጥመው አትች
ልም" አለው።
34ዳዊት ግን ሳኦልን እንዲህ አለው፣ "አገ
ልጋይህ የአባቱን በጎች በሚጠብቅበት ጊዜ፤
አንበሳ ወይም ድብ መጥቶ ከመንጋው አንድ
በግ ነጥቆ ሲሄድ፣ 35ተከትዬ በመሄድ እመ
ታውና ከአፉ አስጥል ነበር፤ ፊቱን ወደ
እኔ በሚያዞርበትም ጊዜ ጕሮሮውን ይዤ
በመምታት እገድለው ነበር። 36ባሪያህ አንበ
ሳውንም ድቡንም ገድሎአል፤ ይህም ያልተገ
ረዘ ፍልስጥኤማዊ የሕያው እግዚአብሔርን ሰራ

17፥12 ዘፍ35፥16፤ 19፤48፥7፤ሩት4፥17፤ 1ሳሙ16፥11፤ መዝ 132፥6
17፥13 1ሳሙ16፥6፡ 8:9
17፥15 ዘፍ37፥2፤ 1ሳሙ16፥19
17፥17 ዘሌ19፥36፤ 23፥14፤1ሳሙ25፥18
17፥18 ዘፍ37፥14
17፥22 ኢሱ 1፥11
17፥23 ቍ8-10
17፥25 1ሳሙ8፥15፤ 18፥17
17፥26 ቍ10፤ ዘዳ5፥26፤ኢሱ3፥10፤ 1ሳሙ11፥2፤ 14፥6፤2ነገ18፥35
17፥28 ዘፍ27፥41፤ ምሳ18፥19
17፥32 ዘዳ20፥3፤ መዝ18፥45፤ ኢሳ7፥4፤ኤር4፥9፤ 38፥4፤ዳን11፥30
17፥33 ዘኍ13፥31
17፥34 ኢዮ10፥16፤ ኢሳ31፥4፤ ኤር49፥19፤ሆሴ13፥8፤ አሞ3፥12
17፥35 መሳ14፥6
17፥36 1ዜና11፥22

10፥12፤ ዘፀ14፥13-14፤ ዘኍ14፥9፤ ኢሱ10፥8፤ 2ዜና20፥17 ይመ)።

17፥12 *የኤፍራታዊው፤* የሩት 1፥2 ማብ ይመ።

17፥15 *ዳዊት ግን ... ከሳኦል ዘንድ ... ይመላለስ ነበር፤* ዳዊት በሳኦል ቤተ መንግሥት ውስጥ የነበረው አገልግሎት ቋሚ አልነበረም (16፥21-23)፤ ስለ ሆነም የቤተ መንግሥት አገልግሎቱ ዐልፎ ዐልፎ የሚከናወን ነበር (በም 16 እና 17 መካከል ሳለው ግንኙነት የቍ55 ማብ ይመ)።

17፥24 *ታላቅ ፍርሀት፤* የቍ11 ማብ ይመ።

17፥25 *ንጉሡ ብዙ ሀብት ይሰጠዋል፤* 8፥14:22፥7 ይመ። *ሴት ልጁን ይድርለታል፤* 18፥17-26፤ ከኢሱ15፥16 ጋር ይነጻጸሩ።

17፥26 *እርሱ ማነው?* ዳዊት ሁኔታውን በግልጽ ተረድቶታል፤ ይህም በዚያ የጦር ሜዳ ከሳኦልና ከሌሎቹ እስራኤላውያን የተለየ ሰው መሆኑን ያመለክታል።

17፥28 *እጅግ ተቈጥቶ፤* የኤልያብ ቍጣ የተነሣሣው በወንድሙ ላይ ስለ ቀና እና የእስራኤል ሰራዊት ሽንፈትና ውርደት ስለ ተሰማው ነው። የዳዊትን የማይሸነፍ መንፈስ ቢያውቀውም የነገሩን ምንጭ ግን ሊረዳ አልቻለም (16፥13)።

17፥32 *ከዚህ ፍልስጥኤማዊ የተነሣ የማንም ሰው ልብ አይሸበር፤* ዳዊት ይህን ቃል በድፍረት የተናገረው በራሱ ጀግንነት ተማምኖ ሳይሆን (ቍ 37:47)፣ ክብሩ በፍልስጥኤማውያን በተደፈረውና ቃል ኪዳኑ በእስራኤላውያውያን በተናቀው በሕያው እግዚአብሔር ኀይል ተማምኖ ነው።

17፥33 *አንተ ... አትችልም፤* ሳኦል ለዳዊት እንዲህ ብሎ ሲናገር የእግዚአብሔርን ኀይል ከግምት ውስጥ አላስገባውም (ቍ 37:47 ይመ)።

17፥34 *አንበሳ፤* በዚያ ዘመን ብዙ አንበሶች በከነዓን ምድር ይገኙ ነበር (2ሳሙ23፥20፤ መሳ14፥5-18፤ 1ነገ13፥24-26፤ አሞ3፥12 ይመ)። *ድብ፤* 2ሳሙ17፥8፤ 2ነገ2፥24፤ አሞ5፥19 ይመ።

17፥36 *ይህም ያልተገረዘ ፍልስጥኤማዊ፤* የ14፥6 ማብ ይመ።

17፥37 *እግዚአብሔር ... ያድነኛል፤* በእግዚአብሔር ለሚ

†18 ዕብራይስጡ ሻለቃ ይላል።

ዊት ተገዳድሮአልና መጨረሻው ከእነርሱ
እንደ አንዱ ይሆናል። [37]ከአንበሳ መዳፍና
ከድብ መንጋጋ ያዳነኝ *እግዚአብሔር* አሁንም
ከዚህ ፍልስጥኤማዊ እጅ ያድነኛል።"

ሳኦልም፣ "ሂድ፤ *እግዚአብሔር* ካንተ ጋር
ይሁን" አለው።

[38]ከዚያም ሳኦል ለዳዊት የገዛ ራሱን የጦር
ልብስ አለበሰው፤ ጥሩር አጠለቀለት፤ ከናስ
የተሠራ ቍርም ደፋለት። [39]ዳዊትም ይህን ዐይ
ነት ልብስ ለብሶ ስለማያውቅ፣ ሰይፉን በጦር
ልብሱ ላይ ታጥቆ ለመራመድ ሞከረ፤

እርሱም ሳኦልን፣ "ያልተለማመድሁት ስለ
ሆነ እንደዚህ ሆኜ መራመድ አልችልም"
አለው። ስለዚህ ሁሉንም አወለቀው። [40]ከዚ
ያም በትሩን በእጁ ያዘ፤ አምስት ድቡል
ቡል ድንጋዮች ከወንዝ መርጦ በእረኛ ኮረ
ጆው ከጨመረ በኋላ፣ ወንጭፉን በእጁ ይዞ፣
ወደ ፍልስጥኤማዊው ቀረበ።

[41]ፍልስጥኤማዊውም፣ ጋሻ ጃግሬውን እፊት
እፊቱ በማስቀደም፣ ወደ ዳዊት እየቀረበ
መጣ። [42]እርሱም ዳዊትን ትኵር ብሎ
ሲያየው፣ ደም ግባት ያለው፣ መልከ መል
ካምና አንድ ፍሬ ልጅ ነበር፤ ስለዚህ
ናቀው። [43]ፍልስጥኤማዊውም ዳዊትን፣ "በትር
ይዘህ የምትመጣብኝ እኔ ውሻ ነኝን?"
አለው፤ በአማልክቱም ስም ረገመው። እር
ሱም፣ "እስቲ ወደኔ ና! ሥጋህን ለሰማይ
አሞሮችና፣ ለምድር አራዊት እሰጣለሁ"
አለው።

[45]ዳዊትም ፍልስጥኤማዊውን እንዲህ
አለው፤ "አንተ ሰይፍ፣ ጦርና ጭሬ ይዘህ
ትመጣብኛለህ፤ እኔ ግን አንተ በተገዳደ
ርኸው የእስራኤል ሰራዊት አምላክ በሆ
ነው፣ ሁሉን በሚችል *በእግዚአብሔር* ስም
እመጣብሃለሁ። [46]*እግዚአብሔር* ዛሬ አንተን
በእጄ አሳልፎ ይሰጣል፤ እኔ መትቼ እጥ
ልሃለሁ፤ ራስህንም እቈርጠዋለሁ። በዚ

17፥37 1ሳሙ16፥18፤ 18፥12፤2ቆሮ 1፥10፤ 2ጢሞ4፥17
17፥38 ዘፍ41፥42
17፥41 ቍ7
17፥42 1ሳሙ16፥12፤ መዝ123፥3-4፤ ምሳ16፥18
17፥43 1ሳሙ24፥14፤ 2ሳሙ3፥8፤9፥8፤ 2ነገ8፥13
17፥44 ዘፍ40፥19፤ 2ሳሙ21፥10፤ኤር 34፥20፤ራእ19፥17
17፥45 ቍ6፡10፤ ዘዳ20፥1፤2ዜና13፥12፤ 14፥11፤32፥8፤ መዝ 20፥7-8፤ 124፥8፤ ዕብ11፥32-34
17፥46 ዘዳ28፥26፤ ኢሱ4፥24፤ 1ሳሙ 14፥12፤ 1ነገ18፥36፤ 2ነገ5፥8፤19፥19፤ ኢሳ 11፥9፤37፥20፤
17፥47 ዘፀ14፥14፤ ዘኍ21፥14፤ 1ሳሙ2፥9፤14፥6፤ 2ዜና14፥11፤20፥15፤ መዝ44፥6-7፤ ኤር39፥18፤ ሆሴ1፥7
17፥50 1ሳሙ25፥29
17፥51 1ሳሙ21፥9፤ 22፥10፤ዕብ11፥34
17፥52 ኢሱ15፥11፡ 36

ሀች ዕለት የፍልስጥኤማውያንን ሰራዊት
ሬሣ ለሰማይ አሞሮችና ለምድር አራዊት
እሰጣለሁ፣ ዓለምም ሁሉ በእስራኤል
ዘንድ ስምባክ መኖሩን ያውቃል። [47]እዚህ
የተሰበሰቡትም ሁሉ፣ *እግዚአብሔር* የሚያ
ድነው በሰይፍ ወይም በጦር እንዳልሆነ
ያውቃሉ፤ ሰልፉ *የእግዚአሔር* ስለ ሆነም
ሁላችሁን በእጃችን አሳልፎ ይሰጣል።"

[48]ፍልስጥኤማዊው ሊመታው በቀረበ ጊዜ፣
ዳዊትም ሊገጥመው ወደ ውጊያው ሜዳ በፍ
ጥነት ሮጠ። [49]እጁንም ወደ ኮሮጆው በመስ
ደድ አንድ ድንጋይ አውጥቶ ወነጨፈው፤
ፍልስጥኤማዊውንም ግንባሩ ላይ መታው።
ድንጋዩም ግንባሩ ውስጥ ገብቶ ተቀረቀረ፤
ፍልስጥኤማዊውም በግምባሩ ተደፋ።

[50]በዚህ ሁኔታ ዳዊት በወንጭፍና በድ
ናጋይ ብቻ ፍልስጥኤማዊውን አሸነፈው፤
በእጁም ሰይፍ ሳይዝ ፍልስጥኤማዊውን
መታው፤ ገደለውም።

[51]ዳዊት ሮጦ በላዩ ላይ ቆመ፤ ከዚያም
የፍልስጥኤማዊውን ሰይፍ ከሰገባው መዞ
አወጣው፤ እርሱንም ከገደለው በኋላ ራሱን
በሰይፍ ቈረጠው።

ፍልስጥኤማውያንም ጀግናቸው መሞቱን
ባዩ ጊዜ ሸሹ። [52]ከዚህ በኋላ የእስራኤልና
የይሁዳ ሰዎች ተነሥተው እየፎከሩ ፍልስጥኤ
ማውያንን እስከ ጌት መግቢያና እስከ ዔቅ
ሮን በሮች ድረስ አሳደዷቸው። የፍልስጥ
ኤማውያንም ሬሳ ከሸዓይራይም አንሥቶ እስከ
ጌት^ ከዚያም እስከ ዔቅሮን በሮች ባለው
መንገድ ላይ ወድቆ ነበር። [53]እስራኤላውያን
ፍልስጥኤማውያንን ከማሳደድ ተመለሱ፤ ሰፈራ
ቸውንም በዘበዙ። [54]ዳዊትም የፍልስጥኤ
ማዊውን ራስ ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም አመ
ጣው፤ ነገር ግን የፍልስጥኤማዊውን የጦር መሣ
ሪያዎች በራሱ ድንኳን ውስጥ አስቀመጠ።

^52 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራ ይስጡ ግን ሸለቆ ይላል።

*መራ ንጉሥ* በእግዚአብሔር መደገፍ አስፈላጊ ነገር ነው (10፥18፡ 11፥13 ማብ *ይመ*)። በዚህ ስፍራ ዳዊት በእግዚአብሔር ላይ የነበረው *መታመን* የተነጻጸረው ከሳኦል እምነት ማጣት ጋር ነበር (ሳኦል ቀደም ብሎ ስለ ነበረው እምነት 11፥6-7 *ይመ*)። *ሳኦልም፣ "ሂድ ... " አለው፤* ሳኦል በዳዊት የሚተማመነው በገና ደርድሮ ርኩስ መንፈሱን በማራቁ ብቻ ሳይሆን ለመንግሥቱም ደኅንነት እንደሚበጅ በማሰብ ነበር።

17፥40 *በትሩን፤* በእግዚአብሔር የተመረጠው አዲሱ የሕዝብ እረኛ (2ሳሙ5፥2፤ 7፥7፤ *መዝ*78፥72 *ይመ*) በፍርሃት የታመሰውንና የተጨነቀውን የእግዚአብሔርን *መንጋ* ሊታደግ ሄደ። *ድንጋዮች፤* አብዛኛውን ጊዜ የሚመረጡት ድንጋዮች ድብልብልና ከትንንሽ ኳሶች ከፍ ከፍ ያሉ ነበሩ፤ በሰዓት ከአንድ መቶ ሥልሳ ኪሎ ሜትር በላይ ይወረወራሉ። *ወንጭፉን፤* ብንያማውያን ወንጭፍ በመወንጨፍ የተካኑ ናቸው (*መሳ*20፥16 *ይመ*)።

17፥43 *እኔ ውሻ ነኝን?* የ2ሳሙ 9፥8 ማብ *ይመ*።

17፥45 *ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር ስም፤* የዳዊት ጥንካሬው በእግዚአብሔር ላይ *መታመኑ* ነበር (*መዝ*9፥10፤ ምሳ 18፥10 *ይመ*)። "የእግዚአብሔር ስም" ስለሚለው አገላለጥ የዘፀ 3፥13-14፤ የዘዳ12፥11 ማብ *ይመ*።

17፥46 *ዓለምም ሁሉ ... ያውቃል፤* ዳዊት በጕጉት የሚጠበቀው ድል የእስራኤልን አምላክ መኖርና ኀያልነቱን ለመላው ዓለም እንዲያሳይ ነው (ዘፀ7፥17፤ 9፥14፤ 16፥29፤ ዘዳ4፥34-35፤ ኢሱ2፥10-11፤ 4፥23-24፤ 1ነገ8፥59-60፤ 18፥36-39፤ 2ነገ5፥15፤ 19፥19 *ይመ*)።

17፥47 *ሰልፉ የእግዚአብሔር ስለ ሆነም፤* የእስራኤልም ሆነ የፍልስጥኤም ጦር ሰራዊት ለግልም ሆነ ለብሔራዊ ደኅንነት በሰው ብልኀትና ጥበብ በመደገፍ ስሕተት ውስጥ ገብተዋል (2፥10፤ 14፥6፤ 2ዜና14፥11፤ 20፥15፤ *መዝ*33፥16-17፤ 44፥6-7፤ *መክ*9፥11፤ ሆሴ 1፥7፤ ዘካ 4፥6 *ይመ*)።

17፥51 *ሸሹ፤* በቍ9 ላይ ጎልያድ የተናገረውን፣ ፍልትስጥኤማውያን ያስተዋሉ አይመስልም፤ የዋናው ጀግናቸው ተመቶ መውደቅ የአማልክት ፍርድ ስለ መሰላቸው ሸሹ።

17፥54 *ወደ ኢየሩሳሌም አመጣው፤* ኢየሩሳሌም በዚህ ጊዜ በእስራኤላውያን አልተያዘችም ነበር። ዳዊት ምናልባት የጎልያድን ራስ እንደ ድል ማረጋገጫና ማስታወሻ በመቍጠር ኢየሩሳሌምን ሲይዝና መናገሻ ከተማው ሲያደርጋት ወደዚያ ሳይወሰደው አልቀረም (2ሳሙ5፥1-9)፤ ወይም በኢያቡሳውያን ከተማ በኖረበት ጊዜ፣ የጎልያድን ራስ በዚያ ለሚኖሩት ተቀናቃኞቹ በማሳየት የእስራኤል አምላክ ያደረገውንና ወደ ፊትም የሚያደርገውን በመግለጽ በማስጠንቀቂያነት ተጠቅሞበት ሊሆን ይችላል። *ነገር ግን የፍልስጥኤማዊውን የጦር መሣሪያዎች በራሱ ድንኳን ውስጥ አስቀመጠ፤* እንደ ግል የምርኮ ንብረት ማለት ነው። ዳዊት የማረከው የጎልያድ ሰይፍ በኋላ በኖብ ከተማ በሚገኘው የካህኑ ግምጃ ቤት ውስጥ ተቀምጦ ነበር (21፥9)፤ ይህም በጦርነቱ እውነተኛ ድል አድራጊ ለሆነው ለእግዚአብሔር በመታሰቢያነት ዳዊት ሳያስቀምጠው እንዳልቀረ የሚያመለክት ነው (ከ31፥10 ጋር ያነጻጽሩ)።

17፥55 *ይህ ልጅ የማን ነው?* በቍ55-58 የተጠቀሰው ሐሳብ

[55]ዳዊት ፍልስጥኤማዊውን ለመግጠም በሚ
ሄድበት ጊዜ ሳኦል ተመልክቶ የሰራዊቱን
አዛዥ አበኔርን፣ “አበኔር ሆይ፤ ይህ ልጅ
የማን ነው?” ሲል ጠየቀው::
አበኔርም፣ “ንጉሥ ሆይ፤ በሕያው ነፍ
ስህ እምላለሁ፤ አላውቅም” ብሎ መለሰለት::
[56]ንጉሡም፣ “እንግዲህ ወጣቱ የማን ልጅ
እንደ ሆነ ተከታትለህ ድረስበት” አለው::
[57]ዳዊት ፍልስጥኤማዊውን ገድሎ እንደ
ተመለሰ፣ አበኔር ይዞ ንጉሡ ዘንድ አቀ
ረበው:: በዚህ ጊዜ ዳዊት የጎልያድን ራስ
በእጁ ይዞ ነበር::
[58]ሳኦልም፣ “አንተ ወጣት፣ የማን ልጅ ነህ?”
ሲል ጠየቀው::
ዳዊትም፣ “እኔ የአገልጋይህ የቤተ ልሔም
ሰው የእሴይ ልጅ ነኝ” ሲል መለሰ::

17፥55 1ሳሙ 16፥21፤ 26፥5
17፥58 ሩት4፥17
18፥1 ዘፍ44፥30፤ 1ሳሙ19፥1፤20፥16፤ 31፥2፤2ሳሙ1፥26፤ 4፥4
18፥3 1ሳሙ20፥8 ፡ 16:17:42፤22፥8፤ 23፥18፤24፥21፤ 2ሳሙ21፥7
18፥4 ዘፍ41፥42፤ 2ሳሙ18፥11
18፥5 ቁ30፤ 2ሳሙ 5፥2
18፥6 ዘፀ15፥20፤ 2ሳሙ1፥20፤ መዝ68፥25

## ሳኦል በዳዊት ቀና

**18** ዳዊት ከሳኦል ጋር የሚያደርገውን
ንግግር እንዳበቃ፣ የዮናታን ነፍስ
ከዳዊት ነፍስ ጋር ተቈራኘች፤ እንደራሱም
አድርጎ ወደደው:: [2]ከዚያች ዕለት አንሥቶ
ሳኦል ዳዊትን አብሮት እንዲኖር አደረገ፤
ወደ አባቱም ቤት እንዲመለስ አላሰናበ
ተውም:: [3]ዮናታን እንደ ራሱ አድርጎ ስለ
ወደደው፣ ከዳዊት ጋር ኪዳን አደረገ፤
[4]ዮናታን የለበሰውን ካባ አውልቆ ከነጦር
ልብሱ፣ በተጨማሪም ሰይፉን፣ ቀስቱንና
መታጠቂያውን ሰጠው::
[5]ሳኦል በሚልከው በማናቸውም ስፍራ፣
ዳዊት ተልእኮውን በሚገባ[ሀ] ይፈጽም ስለ
ነበር፣ በሰራዊቱ ላይ ሾመው፤ ይህም ሕዝ
ቡን በሙሉ፣ የሳኦልንም የጦር ሹማምንት
ደስ አሰኝ::
[6]ዳዊት ፍልስጥኤማዊውን ከገደለ በኋላ፣
ሰዎቹ ወደየቤታቸው በሚመለሱበት ጊዜ፣
ሴቶች ከበሮና መሰንቆ ይዘው እየዘፈኑ፣
እየጨፈሩና እልል እያሉ ንጉሥ ሳኦልን
ለመቀበል ከእስራኤል ከተሞች ሁሉ ወጡ::
[7]ሴቶቹም እንዲህ ሲሉ በመቀባበል ዘፈኑ፤
“ሳኦል ሺህ ገደለ፤
ዳዊት ግን ዐሥር ሺህ ገደለ::”
[8]ሳኦል እጅግ ተቈጣ፤ ይህም ነገር አላስ
ደሰተውም:: እርሱም፣ “ለዳዊት ዐሥር ሺህ
አሉለት፤ ለእኔ ግን ሺህ ብቻ! እንግዲህ
መንግሥት እንጂ ሌላ ምን ቀረው” አለ::
[9]ከዚያች ዕለት አንሥቶ ሳኦል ዳዊትን በቅ
ናት ዐይን ይመለከተው ጀመር::
[10]በማግስቱም ከእግዚአብሔር የታዘዘ ክፉ[ለ]
መንፈስ በሳኦል ላይ ኀይል መጣበት፣ በዚህ
ጊዜ ዳዊት ወትሮ እንደሚያደርገው ሁሉ
በገና ሲደረድር፣ ሳኦል በቤቱ ሆኖ ትንቢት
ይናገር ነበር:: ሳኦል በእጁ ጦር ይዞ ነበር፤
[11]እርሱም፣ “ዳዊትን ከግድግዳው ጋር አጣ
ብቀዋለሁ” ብሎ በማሰብ ጦሩን ወረወ
በት፤ ዳዊት ግን ሁለት ጊዜ ከፊቱ ዘወር
አለ::
[12]*እግዚአብሔር* ከእርሱ ተለይቶ ከዳዊት
ጋር ስለ ሆነ፣ ሳኦል ዳዊትን ፈራው:: [13]ስለ
ዚህ ዳዊትን ከአጠገቡ በማራቅ የሺህ አለቃ
አደረገው:: ዳዊትም ሰራዊቱን እየመራ
በፊታቸው ይወጣና ይገባ ነበር:: [14]*እግዚ
አብሔር* ከእርሱ ጋር ስለ ነበር የሚያደርገው
ነገር ሁሉ ይሳካለት[ሐ] ነበር:: [15]ሳኦልም፣
ዳዊት እንደ ተሳካለት[መ] ባየ ጊዜ ፈራው፤
[16]መላው እስራኤልና ይሁዳ ግን ዳዊትን
ወደዱት፤ በፊታቸው እየወጣና እየገባ
የሚመራቸው እርሱ ነበርና::

18፥7 ዘፀ15፥21፤ 1ሳሙ21፥11፤29፥5፤ 2ሳሙ18፥3
18፥8 1ሳሙ13፥14
18፥9 1ሳሙ19፥1
18፥10 መሳ9፥23፤ 1ሳሙ10፥5፤16፥14፡ 21፤17፥6፤19፥7
18፥11 ቁ25፤ 1ሳሙ 20፥7ለ33፤ 19፥10፤መዝ132፥1
18፥12 ቁ29፤ ኢሱ1፥5፤ መሳ 16፥20፤ 1ሳሙ16፥13፤17፥37፤ 20፥13፤ 1ዜና22፥11
18፥13 ዘኍ27፥17፤ 2ሳሙ5፥2
18፥14 ዘፍ39፥2:3፤ ዘኍ14፥43፤ 2ሳሙ 7፥9
18፥16 2ሳሙ5፥2

[ሀ]5 ወይም በብልኀት
[ለ]10 ወይም *የሚጐዳ*
[ሐ]14 ወይም *እጅግ ብልኅ ነበር*
[መ]15 ወይም *ብልኀ እንደሆነ*

ከ16፥14-23 ካለው ጋር ይቃረናል፤ ይሁን እንጂ ይህን ቅራኔ ከዚህ በፊት ዳዊት የሳኦል ቤተ መንግሥት ቋሚ ኗሪ አልነበረም በሚለው ሐሳብ ማስታረቅ ይቻላል (ቍ 15:18፥2፡ የ16፥21 ማብ ይመ)፤ ሳኦል ስለ ዳዊትና ስለ ቤተሰቡ ያለው ዕውቀት ውሱን ሊሆን የቻለውም ከዚህ የተነሣ ሳይሆን አይቀርም:: ከዚህም ሌላ ሳኦል የዳዊትን ድፍረት ማመን ስለ ተሳነው፣ ይህን ጥያቄ ያቀረበው የዳዊትን ልዩ ጠባይ፣ ቤተ ሰባዊ ሁኔታውና ማኅበራዊ አቋሙ ይገልጡታል ብሎ በማሰብ ሳይሆን አይቀርም::

18፥1፣ ዳዊት ከሳኦል ጋር ረዘም ላለ ጊዜ የተነጋገረ ይመስላል፤ በንግግሩም የገለጻቸው ነገሮች በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት የሚያሳዩ ናቸው፤ ከዚህ የተነሣም በዮናታን ዘንድ ተወዳጅነትንና ታማኝነትን ሊያተርፉለት ችለዋል (ቍ3፤ 14፥6፤ 19፥5 ይመ):: ዮናታን የአባቱን ዙፋን ዳዊት እንደሚወርስ ቢያውቅም በወዳጅነቱ እስከ መጨረሻው ዘለቀ::

18፥2 *ሳኦል ዳዊትን አብሮት እንዲኖር አደረገ፤* የ17፥15 ማብ ይመ::

18፥3 *ዮናታን ... ከዳዊት ጋር ኪዳን አደረገ፤* ግፊቱ የመጣው ከዮናታን ነው፤ የስምምነቱ ቃል በዚህ ስፍራ አልተገለጸም (19፥1፤20፥8:13-16:41-42፤23፥18 ይመ)፤ ይሁን እንጂ ስምምነቱ በእርስ በርስ በመተማመንና በወዳጅነት መንፈስ ላይ የተመሠረተ እንደ ሆነ ይታያል፤ ዮናታን ዳዊትን ቢያንስ እንደ እኩያ ጓደኛው አድርጎ አይቶታል::

18፥4 *የለበሰውንም ,ካባ አውልቆ ... ሰጠው፤* ዮናታን ራሱን ለዳዊት መስጠቱን በሚያሳይ ድርጊት ቃል ኪዳኑን ያጸናል፤ አድራጎቱም በእርሱ ፈንታ አባቱን ሳኦልን የሚተካው ዳዊት መሆኑን የሚያመለክት ነበር (20፥14-15:31፤ 23፥17 ይመ)፤ ይህንን ይበልጥ የሚያረጋግጥልን፣ “ሰይፉን፣ ቀስቱንና መታጠቂያውን” አንሥቶ ለዳዊት መስጠቱ ነበር (ከ13፥22 ጋር ያነጻጽሩ)::

18፥5 *ሳኦል በሚልከው በማናቸውም ስፍራ፤* በሚቀጥለው ዘመቻ ሁሉ ማለት ነው::

18፥7 *ዳዊት ግን ዐሥር ሺህ፤* በተለመደው የዕብራውያን ቅኔ “ዳዊትና ሳኦል ሺህ ገደሉ” እያሉ የሚቀኙት ሴቶች ነበሩ:: ዐሥር ሺህ ከአንድ ሺህ ጋር በተጓዳኝ መቅረቡ የተለመደ ነው (ዘፀ32፥30፤ መዝ91፥7፤ ሚክ6፥7 ይመ):: ነገር ግን ይህን አባባል ሳኦል አሉታዊ በሆነ ጐኑ ስለ ተመለከተው በዳዊት ላይ የበቀል ርምጃ እንዲወስድ አነሣሣው:: ሳኦል መጀመሪያ በዳዊት ላይ ያለው ጥላቻ የገነፈለበት ስሙ ከእርሱ ስም ጋር አብሮ በመጠቀሱ ሊሆን ይችላል (ፍልስጥኤማውያን ዘፈኑን እንዴት እንደተረጐሙት የ21፥11 ማብ ይመ )::

18፥10 *ከእግዚአብሔር የታዘዘ ክፉ መንፈስ፤* የ16፥14 ማብ ይመ:: *ትንቢት ይናገር ነበር፤* ይህን ቃል የሚተካው የዕብራይስጡ ቃል አንዳንድ ጊዜ ከቍጥጥር ውጭ የሆነ ልዩ መንፈሳዊ ስሜትን ይገልጣል (የ1ነገ 18፥29 ማብ ይመ)፤ በዚህ ዐውድ ቃሉ ያንኑ ፅንሰ ሐሳብ ይዞ ገብቶአል (የ10፥5 ማብ ይመ):: *ወትሮ እንደሚያደርገው፤* 16፥14:23 ይመ::

18፥12 *እግዚአብሔር ከእርሱ ተለይቶ ከዳዊት ጋር ስለ ሆነ፤* 16፥14 እና ማብ ይመ::

18፥13 *ስለዚህም ዳዊትን ከአጠገቡ በማራቅ፤* ሳኦል በጦርነቱ ውስጥ ዳዊት እንዲሞት ይፈልግ ነበር (ቍ17:21:25፤ 19፥1 ይመ)፤ ውጤቱ ግን የዳዊትን ታላቅነት የሚያረጋግጥ ሆነ (ቍ14:16:30 ይመ)::

17ሳኦል ዳዊትን፣ "ታላቋ ልጄ ሜሮብ
እነኋት፤ እርሷን እድርልሃለሁ፤ አንተ ግን
በጀግንነት አገልግለኝ፤ *የእግዚአብሔርንም*
ጦርነቶች ተዋጋ" አለው፤ ሳኦል በልቡ፣ "ፍል
ስጥኤማውያን እጃቸውን ያንሡበት እንጂ
እኔ በእርሱ ላይ እጄን አላነሣም" ብሎ ነበ
ርና::
18ዳዊት ግን ሳኦልን፣ "የንጉሥ ዐማች
እሆን ዘንድ እኔ ማን ነኝ? ቤተ ሰቤም ሆነ
የአባቴ ጐሣስ በእስራኤል ዘንድ ምንድን
ነው?" አለው:: 19ይሁን እንጂ[a] የሳኦል
ልጅ ሜሮብ ለዳዊት የምትዳርበት ጊዜ ሲደ
ርስ ለመሓላታዊው ለኤስድሪኤል ተዳረች::
20በዚህ ጊዜ የሳኦል ልጅ ሜልኮል ዳዊ
ትን ወደደችው፤ ሳኦልም ይህን ሲሰማ ደስ
አለው::21ሳኦልም በልቡ፣ "ወጥመድ እንድ
ትሆነው፣ በፍልስጥኤማውያንም እጅ እን
ዲጠፋ እርሷን እድርለታለሁ" ሲል አሰበ::
ስለዚህ ሳኦል ዳዊትን፣ "እነሆ፤ ዛሬ ለሁለተኛ
ጊዜ ዐማቼ ትሆናለህ" አለው::
22ከዚያም ሳኦል ባለሚሎቹን፣ "ለዳዊት፣
'እነሆ፤ ንጉሡ በአንተ ደስ ብሎታል፤ ባለ
ሚሎቹም ሁሉ ይወዱሃል፤ ስለዚህ ዐማቹ
ሁንለት' ብላችሁ በምስጢር ንገሩት" ብሎ
አዘዛቸው::
23እነርሱም ይህንኑ ለዳዊት ደግመው
ነገሩት፤ ዳዊት ግን፣ "ለመሆኑ የንጉሥ ዐማች
መሆንን እስከዚህ ትንሽ ነገር አድርጋችሁ
ትቈጥራላችሁን? እኔ አንድ ምስኪን ድኻና
እምብዛም የማልታወቅ ሰው ነኝ" አላቸው::
24የሳኦል ባለሚሎችም ዳዊት ያላቸውን
በነገሩት ጊዜ፣ 25ሳኦል፣ "ዳዊትን፣ 'ንጉ
ሡስ ለልጅቱ ካንተ የሚፈልገው ጥሎሽ ጠላ
ቶቹን ለመበቀል የመቶ ፍልስጥኤማውያ
ንን ሸለፈት እንጂ ሌላ አይደለም ብላችሁ
ንገሩት' " አላቸው:: ሳኦል ይህን ያቀደው
ዳዊት በፍልስጥኤማውያን እጅ እንዲወድቅ
ነበር::
26ባለሚሎቹ ይህን ለዳዊት በነገሩት ጊዜ
የንጉሥ ዐማች መሆኑ ደስ አሰኘው:: ስለ
ዚህ የተወሰነው ጊዜ ከማለፉ በፊት፣ 27ዳዊ
ትና አብረውት የነበሩት ሰዎቹ ሄደው ሁለት
መቶ ፍልስጥኤማውያንን ገደሉ፤ ለንጉሡ
ዐማች ይሆን ዘንድ፣ ሸለፈታቸውን አም
ጥቶ በቍጥራቸው ልክ ለንጉሡ አቀረበ፤
ከዚያም ሳኦል ልጁን ሜልኮልን ለዳዊት
ዳረለት::
28ሳኦል *እግዚአብሔር* ከዳዊት ጋር እንደ
ሆነና ልጁ ሜልኮልም እንደወደደችው በተ
ረዳ ጊዜ፣ 29ሳኦል ከቀድሞው ይልቅ ፈራው፤
እስከ ዕድሜውም ፍጻሜ ድረስ ጠላቱ ሆነ::
30የፍልስጥኤማውያን ጦር አዛዦች እንደ
ወትሮው ሁሉ፣ ለጦርነት ይወጡ ነበር፤
ዳዊትም ከቀሩት የሳኦል መኳንንት የበለጠ
ድል አገኘ[b]፤ ስሙም የታወቀ ሆነ::

## ሳኦል ዳዊትን ለመግደል ያደረገው ሙከራ

19ሳኦል ዳዊትን እንዲገድሉት ለልጁ
ለዮናታንና ለባለሚሎቹ ነገራቸው::
ዮናታን ግን ዳዊትን እጅግ ይወደው
ነበር፣ 2እንዲህ ሲል አስጠነቀቀው፤ "አባቴ
ሳኦል ሊገድልህ አጋጣሚ እየፈለገ ነው፤
ነገ ጠዋት ተጠንቀቅ፤ ወደ አንድ መደበ
ቂያ በታም ሂድ፤ በዚያም ቈይ:: 3እኔም
እወጣና አንተ ባለህበት ዕርሻ ከአባቴ አጠ
ገብ እቆማለሁ፤ ስለ አንተም አነጋግረዋለሁ፤
የተረዳሁትንም እነግርሃለሁ::"
4ዮናታን ለአባቱ ለሳኦል ስለ ዳዊት እን
ዲህ ሲል መልካም ነገር ተናገረ፣ "ንጉሥ
በአገልጋዩ በዳዊት ላይ ክፉ ነገር አያድ
ርግ፤ እርሱ አልበደለህም፤ ያደረገውም ነገር
በእጅጉ ጠቅሞሃል:: 5ዳዊት ፍልስጥኤማዊ
ውን የገደለው በገዛ ሕይወቱ ቈርጦ ነው::
*እግዚአብሔር* ለመላው እስራኤል ታላቅ
ድልን አቀዳጀ፤ አንተም አይተህ ደስ
አለህ:: ታዲያ እርሱን በከንቱ በመግደል
ዳዊትን በመሰለ ንጹሕ ሰው ላይ ለምን በደል
ትፈጽማለህ?"
6ሳኦልም ዮናታንን ካዳመጠው በኋላ፣
"ሕያው *እግዚአብሔርን!* ዳዊት አይገደልም"
ብሎ ማለ::
7ስለዚህም ዮናታን ዳዊትን ጠርቶ የተባ
ባሉትን ሁሉ ነገረው፤ ወደ ሳኦልም አመ
ጣው፤ ዳዊትም እንደ ቀድሞው በፊቱ ቆመ::
8እንደ ገና ሌላ ጦርነት ተነሣ፤ ዳዊትም

[a]19 ወይም *ስለዚህ ተብሎ*
[b]30 ወይም *ዳዊት....የበለጠ በብልኅት አደረገ*

18፥17 ቍ25፤ ዘፍ29፥26፤ ዘኍ 21፥14፤ 1ሳሙ 17፥25፤ 20፥33
18፥18 ቍ23፤ ዘፀ3፥11፤ 1ሳሙ9፥21
18፥19 መሳ7፥22፤ 2ሳሙ21፥8
18፥20 ቍ28:29፤ ዘፍ29፥26
18፥21 ዘፀ10፥7፤ ዘዳ7፥16
18፥23 ቍ18
18፥25 ቍ11:17፤ ዘፍ34፥12፤ መዝ8፥2፤44፥16፤ ኤር20፥10
18፥27 2ሳሙ3፥14፤ 6፥16
18፥28 ቍ20
18፥29 ቍ 12
18፥30 ቍ5
19፥1 1ሳሙ18፥1:9
19፥2 1ሳሙ20፥5: 19
19፥3 1ሳሙ20፥12
19፥4 1ሳሙ20፥32፤ 22፥14፤25፥21፤ ምሳ17፥13፤31፥8: 9፤ኤር18፥20
19፥5 ዘፍ31፥36፤ ዘዳ10፥10፥10-13፤ መሳ9፥17፤12፥3፤ 1ሳሙ11፥13
19፥7 1ሳሙ18፥10

18፥17 *ታላቋ ልጄ ... እነኋት፤* ዳዊት በጎልያድ ላይ ካገ ኘው ድል የተነሣ የሳኦልን የመጀመሪያ ልጅ እንደሚያገባት ቃል ተገብቶለት ነበር (17፥25 *ይመ*):: ይህ ቃል ለዳዊት አልተፈጸመ ለትም ነበርና፤ አሁን ደግሞ እንደ ገና ዳዊት ይገደልበታል ብሎ ተስፋ ሳደረገው ሌላ ወታደራዊ ግዳጅ እንደ ቅድመ ሁኔታ ሆኖ የቀረበ ሐሳብ ነው:: *የእግዚአብሔርንም ጦርነቶች፤* 25፥28 *ይመ*::

18፥25 *ሌላ አይደለም፤* አብዛኛውን ጊዜ ሙሽራ ለሙሽራ ዪቱ አባት ማጫ ይከፍላል (ዘፍ34፥12፤ዘፀ22፥16)፤ ይህም የሚ ደረገው ልጁን ለዳረው አባት ማካካሻና ምናልባትም ባሏ ቢሞት ለሴቲቱ ዋስትና ይሆናት ዘንድ ነው:: ሳኦል ግን በዚህ ምትክ ከዳዊት የሚፈልገው ይሞታል በሚል ተስፋ፣ ለታላቅ ተዋጊ የሚ ሰጠውን ከባድ የጦርነት ፈተና ማለፍን ነው (ቍ17፥21 *ይመ*)::

18፥28 *ሜልኮልም እንደ ወደደችው፤* በዳዊት ላይ የነበ ረው የእግዚአብሔር ሞገስ በወታደራዊ ድል ብቻ ሳይሆን፣ ከዮና ታን ቀጥሎ በወደደችው በሜልኮል ፍቅርም በሚገባ ታይቶአል:: ሳኦል ዳዊትን ለመጕዳት የሚያደርገው ማንኛውም ነገር ሁሉ ዳዊትን የሚጠቅም ሆኖ ተገኘ::

18፥29 *ሳኦል ከቀድሞው ይልቅ ፈራው፤* የእግዚአብሔር እጅ በዳዊት ላይ መሆኑን ሳኦል መረዳቱ ንስሓ እንዲገባና ዕድል ፈንታውን እንዲቀበል አላደረገውም (15፥26)፤ ነገር ግን ይበ ልጡኑ ዳዊትን ወደ መፍራትና ወደ ቅንዓት መራው::

19፥1 *ሳኦል ዳዊትን እንዲገድሉት ለልጁ ... ነገራቸው፤* በዚህ ጊዜ ሳኦል የዳዊትን ሕይወት ለማጥፋት የሚያደርገውን ቀጥተኛ ያልሆነ ሙከራ በመተው (18፥13:17:25 *ይመ*)፣ ዳዊ ትን በግልጥ ከቤተ መንግሥቱ በማባረርና ለእርሱ የሚሰጠውንም አገልግሎት እንዲያቋርጥ በማድረግ የበለጠ ቀጥተኛ የሆነ ዘዴን መጠቀም ጀመረ (ቍ 12:18፤ 20፥42 *ይመ*)::

19፥4 *ዮናታን ... ስለ ዳዊት ... መልካም ነገር ተናገረ፤* የዮናታን የግል ስሜት ስለ ዳዊት የሚያውቀውን እውነተኛና ጠን ካራ መንፈስ ሊያዛባበት አልቻለም (ቍ5 እና የ14፥6፤17፥11፤ 18፥1 ማብ *ይመ*)::

19፥6 *ሳኦልም ዮናታንን ካዳመጠው በኋላ ... ብሎ ማለ፤* 14፥24:44 *ይመ*፤ ሳኦል ስላልጠበቃቸው የቀድሞ መሐላዎች 14፥39 ማብ *ይመ*::

ወጥቶ ፍልስጥኤማውያንን ወጋቸው፤ ከፊ
ቱም እስኪሸሹ ድረስ እጅግ መታቸው።
9ነገር ግን ሳኦል ጦሩን ይዞ በቤቱ ተቀ
ምጦ ሳለ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ክፉ መን
ፈስ[ሀ] መጣበት፤ ዳዊት በገናውን ይደረድር
ነበር፣ 10ሳኦልም ከግድግዳው ጋር ሊያጣብ
ቀው ጦሩን ወረወረበት፤ ነገር ግን ዳዊት
ዘወር በማለቱ ሳኦል የወረወረው ጦር እግድ
ግዳው ላይ ተሰካ። በዚያች ሌሊት ዳዊት
ሸሽቶ አመለጠ።
11ሳኦልም የዳዊትን ቤት ከበው በማለዳ
እንዲገድሉት ሰዎችን ላከ። የዳዊት ሚስት
ሜልኮል ግን፣ "ሕይወትህን ለማትረፍ በዚ
ህች ሌሊት ካልሸሸህ፣ በነገው ቀን ትገደላ
ለህ" ብላ አስጠነቀቀችው። 12ሜልኮልም ዳዊ
ትን በመስኮት አሾልካ አወረደችው፣ እር
ሱም ሸሽቶ አመለጠ። 13ከዚያም ሜልኮል
የጣዖት[ለ] ምስል ወስዳ በዐልጋው ላይ አጋደ
መችው፤ በራስጌውም የፍየል ጠጕር አኖ
ረች፤ በልብስም ሸፈነችው።
14ሳኦል ዳዊትን እንዲይዙት ሰዎች በላከ
ጊዜ ሜልኮል፣ "እርሱ ታሞአል" አለቻቸው።
15ሳኦልም ሰዎቹ ዳዊትን እንዲያዩት መልሶ
ላካቸው፤ እርሱም፣ "እገድለው ዘንድ ከነዐል
ጋው አምጡልኝ" አላቸው። 16የተላኩትም
ሰዎች በገቡ ጊዜ እነሆ፤ የጣዖት ምስሉ በዐ
ልጋው ላይ ተጋድሞ በራስጌውም የፍ
የል ጠጕር ተደርጎለት ነበር።
17ሳኦልም ሜልኮልን፣ "እንዲህ አድርገሽ
ያታለልሽኝ፣ ጠላቴ እንዲያመልጥ ያሰደድ
ሽው ለምንድን ነው?" ሲል ጠየቃት።
ሜልኮልም፣ " 'እንዳመልጥ እርጂኝ፤
ያለዚያ እገድልሻለሁ' አለኝ" ብላ መለሰች
ለት።
18ዳዊት ሸሽቶ ካመለጠ በኋላ፣ ወደ አር
ማቴም ወደ ሳሙኤል ሄደ፣ ሳኦል ያደረ
ገበትን ሁሉ ነገረው። ከዚያም እርሱና ሳሙ
ኤል ወደ ነዋት ሄደው ተቀመጡ። 19ለሳ
ኦልም፣ "እነሆ፤ ዳዊት በአርማቴም በምት
ገኘው በነዋት ተቀምጦአል" ብለው ነገሩት።
20ስለዚህ ዳዊትን እንዲይዙ ሰዎችን ላከ፤
ይሁን እንጂ፣ የነቢያትም ጉባኤ በሳሙኤል
መሪነት ትንቢት ሲናገሩ ባዩ ጊዜ፣ የእግዚ
አብሔር መንፈስ በሳኦል ሰዎች ላይ ወረደ፤
እነርሱም እንደዚሁ ትንቢት ተናገሩ።

19፥9 መሳ9፥23፤ 1ሳሙ10፥5
19፥10 1ሳሙ18፥11
19፥11 መሳ16፥2፤ መዝ59
19፥12 ኢያ2፥15፤ ሐሥ9፥25፤ 2ቆሮ11፥33
19፥13 ዘፍ31፥19
19፥14 ዘፀ1፥19፤ ኢያ 2፥4
19፥18 1ሳሙ7፥17
19፥20 ዘኍ11፥25፡ 29፤1ሳሙ10፥5
19፥23 1ሳሙ10፥13
19፥24 1ሳሙ10፥11፤ 15፥35፤2ሳሙ6፥20፤ ኢሳ20፥2
20፥1 1ሳሙ22፥23፤ 23፥15፤24፥9፡11፤ 25፥29፤መዝ40፥14፤ 54፥3፤63፥9፤70፥2
20፥3 ዘዳ6፥13

21ሳኦልም ይህ በተነገረው ጊዜ ሌሎች
ሰዎች ላከ፤ እነርሱም ትንቢት ተናገሩ፤
ሳኦል ለሦስተኛ ጊዜ ሰዎች ላከ፣ እነርሱም
ደግሞ ትንቢት ተናገሩ። 22በመጨረሻም፣
እርሱ ራሱ ወደ አርማቴም ሄደ፤ ከዚያም
በሤኩ ወዳለው ትልቅ የውሃ ማጠራቀሚያ
ጕድጓድ እንደ ደረሰ፣ "ሳሙኤልና ዳዊት
የት ናቸው?" ሲል ጠየቀ።
አንድ ሰውም "በአርማቴም በምትገኘው
በነዋት ዘራማ ናቸው" ብሎ ነገረው።
23ስለዚህ ሳኦል በአርማቴም ወደምትገ
ኘው ወደ ነዋት ዘራማ ሄደ፤ የእግዚአብሔር
መንፈስ በእርሱም ላይ ደግሞ ወረደ፤ ወደ
ነዋት እስኪደርስ ድረስም ትንቢት እየተ
ናገረ ተጓዘ። 24እርሱም ልብሱን አውልቆ፣
በሳሙኤልም ፊት ደግሞ ትንቢት ተናገረ፤
በዚህ ሁኔታም ቀኑንና ሌሊቱን በሙሉ ራ
ቁቱን ተጋደመ። ሕዝቡ፣ "ሳኦልም ደግሞ
ከነቢያት እንደ አንዱ ሆኖ ተቈጠረ?"
ያለው በዚህ ምክንያት ነው።

## ዳዊትና ዮናታን

20 ከዚህ በኋላ ዳዊት በአርማቴም
ካለችው ከነዋት ዘራማ ሸሽቶ ወደ
ዮናታን በመሄድ፣ "ምን አድርጌአለሁ?
ምን በደልስ ፈጽምሁ? አባትህ ሕይወቴን
ለማጥፋት የሚፈልገውስ በፊቱ ምን ተገኝቶ
ብኝ ነው?" ሲል ጠየቀው።
2ዮናታንም፣ "ይህስ ከቶ አይሁንብህ፤ አት
ሞትም! እነሆ፤ አባቴ ትልቅም ይሁን ትንሽ
ማናቸውንም ነገር አስቀድሞ ሳይነግረኝ አያ
ደርገውም። ታዲያ አባቴ ይህን ለምን ይደ
ብቀኛል? ነገሩ እንዲህ አይደለም!" ብሎ
መለሰለት።
3ዳዊት ግን፣ "በፊትህ ሞገስ ማግኘቴን
አባትህ በሚገባ ያውቃል፤ እርሱም በልቡ፤
'ዮናታን እንዳያዝን ይህን ማወቅ የለበ
ትም' ብሎአል፤ ነገር ግን ሕያው *እግዚአ
ብሔርን!* በነፍስህ እምላለሁ! በእኔና በሞት
መካከል አንድ እርምጃ ብቻ ቀርቶአል" ብሎ
ማለ።
4ዮናታንም ዳዊትን፣ "እንዳደርግልህ የም
ትፈልገውን ማናቸውንም ነገር አደርግልሃ

[ሀ]9 ወይም የሚጎዳ
[ለ]13 በዚህና በቍጥር 13 ላይ ዕብራይስጡ *ተራፊም* ይላል።

19፥9 *ከእግዚአብሔር ዘንድ ክፉ መንፈስ መጣበት፤* 16፥14 ማብ ይመ፤ ከ18፥10-11 ጋር ያነጻጽሩ።

19፥10 *ጦሩን፤* 18፥10-11፤ 20፥33 ይመ።

19፥12 *በመስኮት፤* ለተመሳሳይ ታሪክ ኢያ2፥15፤ ሐሥ9፥25 ይመ።

19፥13 *የጣዖት ምስል፤* የዘፍ 31፥19 ማብ ይመ።

19፥18 *አርማቴም፤* የሳሙኤል አገር ነው (7፥17 እና የ1፥1 ማብ ይመ)። *ነዋት፤* መኖሪያዎች ወይም ማደሪያዎች ማለት ነው። ቃሉ በአርማቴም በአንድ አካባቢ ስብስብ ብለው የተሠሩትን ቤቶች በተለይም ነቢያት በአንድነት የሚኖሩበትን ሰፈር የሚያ መለክት ነው (ቍ 19፥20፡22-23)።

19፥20 *የነቢያትም ጉባኤ፤* 10፥5 እና ማብ ይመ። *ትንቢት ሲናገሩ፤* የ10፥5 እና 18፥10 ማብ ይመ።

19፥24 *በዚህ ሁኔታም ቀኑንና ሌሊቱን በሙሉ … ተጋደመ፤* ሳኦል የእግዚአብሔር መንፈስ ተስፋ ስላስቈረጠው የዳዊትን ሕይወት ለማጥፋት የነበረው ዕቅድ ተበላሸበት። ዳዊትን ለመግደል ያደረጋቸው የቀቢጸ ተስፋ ሙከራዎቹ፣ ማለትም በዳዊት ላይ ጕዳት ለማድረስ አለመቻሉና ዮናታን ለዳዊት ባሳየው ታማኝነት፣ በሜልኮል የማታለል ድርጊትና በራሱ በዳዊት ብልኀነት ጠቅላላ ዕቅዱ በመክሸፉ እዚህ ላይ ሁሉም ነገር በንረት ደረጃ ላይ ደረሰ። *ሳኦል ደግሞ ከነቢያት እንደ አንዱ ሆኖ ተቈጠረ፤* እዚህም ላይ ይህ ጥያቄ መነሣቱ የመጀመሪያውን ያጠናክረዋል (10፥11 እና ማብ ይመ)። ጥያቄው መደገሙ ደግሞ የሳኦል መንፈስ ከእነዚህ ትጉህ የእግዚአብሔር አገልጋዮች መንፈስ የተለየና ባዕድ መሆኑን ያመለክታል።

20፥1 *በአርማቴም ካለችው ከነዋት ዘራማ፤* የ19፥18 ማብ ይመ።

20፥3 *ሕያው እግዚአብሔር!* የ14፥39 ማብ ይመ።

ለሁ" አለው።
5ስለዚህ ዳዊት እንዲህ አለ፤ 'እነሆ፤ ነገ
የወር መባቻ በዓል ስለ ሆነ፣ ከንጉሡ ጋር
ምሳ መብላት ይጠበቅብኛል፤ ነገር ግን
እስከ ከነገ ወዲያ ማታ ድረስ ከዱር ልደ
በቅ፤ 6አባትህ ከፈለገኝ፣ 'ለቤተ ዘመዶቹ
ሁሉ ዓመታዊ መሥዋዕት የሚቀርብ ስለ
ሆነ፣ ዳዊት ወደ መኖሪያ ከተማው ወደ
ቤተ ልሔም ቶሎ ለመሄድ አጥብቆ
ፈቃድ ጠየቀኝ' ብለህ ንገረው። 7እርሱም
'መልካም ነው' ካለ፣ አገልጋይህን የሚያሰ
ጋው የለም፤ ከተቈጣ ግን፣ ክፉ ነገር
እንዳሰበብኝ ታረጋግጣለህ። 8አንተ ግን፤
ለአገልጋይህ በጎነትን አሳይ፣ ከአገልጋይህ
ጋር *በእግዚአብሔር* ፊት ቃል ኪዳን ገብ
ታችኋልና። እኔ በደለኛ ከሆንሁ፣ አንተው
ራስህ ግደለኝ፤ ለምንስ ለአባትህ አሳልፈህ
ትሰጠኛለህ!"
9ዮናታንም፣ "ይህ ከአንተ ይራቅ!
አባቴ ክፉ ነገር እንዳሰበብህ ባውቅ ኖሮ
እንዴት ሳልነግርህ እቀራለሁ?" አለው።

10ዳዊትም፣ "አባትህ ክፉ ቃል ቢመል
ስልህ ማን ይነግረኛል?" ብሎ ጠየቀው።
11ዮናታን፣ "በል ና፤ ወደ ሜዳ እንውጣ"
አለው፤ ተያይዘውም ወጡ።
12ከዚያም ዮናታን ዳዊትን እንዲህ አለው፤
"የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሔር* ምስክር
ይሁንብኝ፤ አባቴን ነገ መርምሬ ነገ ወይም
ከነገ ወዲያ በዚህ ሰዓት እልክብሃለሁ፤ ስለ
አንተ ያለው አመለካከት በጎ ከሆነም አሳው
ቅሃለሁ። 13ነገር ግን አባቴ ክፉ አስቦብህ፣
ይህን ሳላሳውቅህ ብቀርና በሰላም እንድት
ሄድ ባላደርግ፣ *እግዚአብሔር* ክፉ ያድርግ
ብኝ፤ ከዚያም የባሰ ያምጣብኝ። *እግዚአ
ብሔር* ከአባቴ ጋር እንደ ነበር እንደዚሁ
ከአንተም ጋር ይሁን። 14አንተም እኔ በሕ
ይወት እስካለሁ ድረስ እንዳልገደል *የእግዚ
አብሔርን* በጎነት አድርግልኝ። 15*እግዚአብሔር*
የዳዊትን ጠላቶች ሁሉ ከምድረ ገጽ በሚደ
መስስበት ጊዜ እንኳ የበጎነት ሥራህ ከቤተ
ሰቤ በፍጹም አይቋረጥ።
16ስለዚህ ዮናታን፣ "የዳዊትን ጠላቶች *እግ
ዚአብሔር* ይፋረዳቸው" በማለት ከዳዊት

20፥5 ዘኍ10፥10፤ 1ሳሙ19፥2
20፥6 ቍ28፤ 1ሳሙ1፥3፤17፥58
20፥7 1ሳሙ10፥27፤ 18፥11፤25፥17
20፥8 1ሳሙ18፥3፤ 2ሳሙ14፥32
20፥12 1ሳሙ19፥3
20፥13 ሩት1፥17፤ 1ሳሙ16፥18፤ 18፥12
20፥14 ዘፍ40፥14
20፥15 1ሳሙ24፥21፤ 2ሳሙ9፥7
20፥16 ኢሱ2፥23፤ 1ሳሙ 18፥1፡3

20፥5 *የወር መባቻ በዓል፤* በያመቱ ያለው እያንዳንዱ ወር ልዩ መሥዋዕት በማቅረብና (ዘኍ28፥11-15) መለከት በመን ፋት ዘኍ10፥10፤ መዝ81፥3)፣ ለእግዚአብሔርን ይቀደሳል። ይህ በዓል በተለይም በሰባተኛው ወር መባቻ ላይ ከማናቸውም የተለ መደ *ሥራ ማቁምን* ይጨምራል (ዘሌ23፥24-25፤ ዘኍ29፥1-6፤ 2ነገ 4፥23፤ ኢሳ1፥13፤ አሞ8፥5)።

20፥6 *ዓመታዊ መሥዋዕት፤* ይህ የዳዊት አባባል አዲስ ጨረቃ የምትታይበትን በዓል በዓመት አንድ ጊዜ ማክበር በየ ቤተ ሰቡ የተለመደ እንደ ሆነ ያመለክታል። ስለዚህ በዓል በብ ሉይ ኪዳን መጻሕፍት በሌላ ስፍራ የተጻፈ ነገር የለም።

20፥8 *ኪዳን፤* የ18፥3 ማብ ይመ።


20፥11 *በል ና፤ ወደ ሜዳ እንውጣ፤* ዮናታን ይህን ያደረ ገው ዳዊትን ከሞት ለማዳን ነበር፤ ቃየንም ይህንኑ የመሰለ ቃል ለወንድሙ ለአቤል ተናግሮ ነበር፤ ይሁን እንጂ ቃየን ይህን ያለው ወንድሙን ለመግደል ፈልጉ ነበር (ዘፍ 4፥8)።

20፥13 *እግዚአብሔር ክፉ ያድርግብኝ፤ ከዚያም የባሰ ያምጣብኝ፤* የተለመደ የእርግማን አባባል ነው .(የ3፥17 ማብ ይመ)። *እግዚአብሔር ከአባቴ ጋር እንደ ነበር እንደዚሁ ከአንተም ጋር ይሁን፤* ዳዊት ነገ ንጉሥ ሊሆን እንደሚችል ዮናታን ያውቅ እንደ ነበር ይህ አባባል በግልጽ ይመሰክራል።

20፥14 *እንዳልገደል፤* ጥንት በመካከለኛው ምሥራቅ አንድ አዲስ ንጉሥ መንግሥቱን ለማጽናትና ሥልጣኑን ለማደላደል ዙፋኑን የሚቀናቀኑትን የቀድሞውን ንጉሥ ዘሮች ሁሉ ማጥፋት የተለመደ ነበር (1ነገ15፥29፤ 16፥11፤ 2ነገ10፥7፤ 11፥1 ይመ)።

20፥15 *የበጎነት ሥራህ ከቤተ ሰቤ በፍጹም አይቋረጥ፤* ይህ ሐሳብ ቀደም ብሎ በዳዊትና በዮናታን ቃል ኪዳን ውስጥ የተካተተ ነበር (የ18፥3 ማብ ይመ)፤ በኋላም ዳዊት ይህንኑ ለዮና ታን ልጅ ለሜምፊቦስቴ ፈጽሞለታል (2ሳሙ9፥3:7፤ 21፥7 ይመ)።

20፥16 *የዳዊትን ጠላቶች እግዚአብሔር ይፋረዳቸው፤* ይህ አባባል የራሱን አባት ሳኦልን የሚመለከት ቢሆንም እንኳ፣ ዮናታን ራሱን የዳዊት ወገን በማድረግ የዳዊትን ጠላቶች እግዚአ ብሔር እንዲያጠፋቸው ይራገማል።



ቤት ጋር ቃል ኪዳን አደረገ። [17]ዮናታን
ከፍቅሩ የተነሣ ዳዊት እንደ ገና እንዲምል
ለት አደረገ፤ ዳዊትን የሚወደውም እንደ
ራሱ አድርጎ ነበርና።
[18]ከዚያም ዮናታን ዳዊትን እንዲህ አለው፤
"ነገ የወር መባቻ በዓል ነው፤ መቀመጫህ
ባዶ ስለሚሆን፣ አለመኖርህ ይታወቃል።
[19]ከነገ ወዲያ ምሽት ላይ ይህ ችግር በተ
ፈጠረ ዕለት ወደ ተደበቅህበት ስፍራ ሂድና
ኤዜል በተባለው ድንጋይ አጠገብ ቈይ።
[20]እኔም በአንድ ዒላማ ላይ እንደሚያነጣጥር
ሰው ወደ ድንጋዩ አጠገብ ሦስት ፍላጻ
እወረውራለሁ፤ [21]ከዚያም፣ 'ሂድና ፍላጾቹን
አምጣቸው' ብዬ አንድ ልጅ እልካለሁ፤ ልጁ
ንም፣ 'እነሆ፤ ፍላጾቹ ያሉት፣ ከአንተ ወደ
ዚህ ነው፤ ሄደህ አምጣቸው' ያልሁት እንደ
ሆነ፣ ሕያው እግዚአብሔርን! ክፉ ነገር
አያገኝህም፤ አደጋም የለም፤ ውጣና ና።
[22]ነገር ግን ልጁን፣ 'እነሆ፤ ፍላጾቹ ያሉት
ከአንተ ወዲያ ዐልፎ ነው' ያልሁት እንደ
ሆነ እግዚአብሔር እንድትሄድ ፈቅዶአልና
ሂድ። [23]አንተና እኔ ስለ ተነጋገርነው ነገር
እነሆ፤ *እግዚአብሔር* በመካከላችን ለዘላለም
ምስክር ነው።"
[24]ስለዚህም ዳዊት በዱር ተደበቀ፤ የወር
መባቻ በዓል በተከበረበት ጊዜ፣ ንጉሡ
ግብር ለመብላት ተቀመጠ፤ [25]ንጉሡ እንደ
ወትሮው በግድግዳው[*] አጠገብ ተቀመጠ፤
ዮናታን ከፊት ለፊቱ፣ አበኔር ደግሞ
ከአጠገቡ ተቀመጡ፤ የዳዊት መቀመጫ
ግን ባዶ ነበር። [26]ሳኦልም፣ "ዳዊት በሥር
ዐቱ መሠረት እንዳይነጻ የሚያደርገው
አንድ ነገር ገጥሞታል፤ በእርግጥም አልነ
ጻም" ብሎ ስላሰበ፣ በዚያ ቀን ምንም አል
ተናገረም። [27]በማግስቱም፣ ወር በገባ በሁለ
ተኛው ቀን የዳዊት መቀመጫ ባዶ ነበር፤
ከዚያም ሳኦል ልጁን ዮናታንን፣ "የእሴይ
ልጅ ትናንትናም፣ ዛሬም ግብር ላይ ያለተ
ገኘው ለምንድን ነው?" ሲል ጠየቀው።
[28]ዮናታንም እንዲህ ብሎ መለሰለት፤
"ዳዊት ወደ ቤተ ልሔም እንዲሄድ እፈቅ
ድለት ዘንድ አጥብቆ ለመነኝ። [29]እርሱም
'ቤተ ሰባችን በከተማዪቱ ውስጥ መሥዋዕት
ስለሚያደርግ በዚያ እንድገኝ ወንድሜ አዞ
ኛልና ልሂድ፤ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ እን
ደሆነ ወንድሞቼን ለማየት እንድሄድ አሰና
ብተኝ' አለኝ። በንጉሡ ግብር ላይ ሳይገኝ
የቀረውም በዚህ ምክንያት ነው።"
[30]ሳኦል በዮናታን ላይ እጅግ ተቈጣ፤ እንዲ
ህም አለው፤ "አንተ የዚያች ጠማማና ዐመፀኛ
ሴት ልጅ! ለአንተው ለራስህ ውርደት፣
ለወላጅ እናትህም ዕፍረት ከሚሆነው ከእ
ሴይ ልጅ ጋር መግጠምህን የማላውቅ መሰ
ለህ? [31]የእሴይ ልጅ በምድር ላይ በሕይ
ወት እስካለ ድረስ አንተም ሆንህ መንግሥ
ትህ አትጸኑም። መሞት ስለሚገባው፣ ሰው
ላክና አስመጣልኝ!"
[32]ዮናታንም፣ "ለምን ይገደላል? ጥፋቱስ
ምንድን ነው?" ሲል አባቱን ጠየቀ። [33]ሳኦ
ልም ዮናታንን ለመግደል ጦሩን ወረወረ
በት። ስለዚህ ዮናታን፣ አባቱ ዳዊትን ለመ
ግደል ቈርጦ መነሣቱን ዐወቀ።
[34]ዮናታንም በታላቅ ቍጣ ከግብሩ ላይ
ተነሣ፤ አባቱም ዳዊትን ስላዋረደው ወሩ
በገባ በሁለተኛው ቀን ምግብ አልበላም።
[35]በማግስቱ ጠዋት ዮናታን አንድ ትንሽ
ልጅ አስከትሎ፣ ከዳዊት ጋር ወደ ተቃጠ
ረበት ቦታ ሄደ፤ [36]ልጁንም፣ "ሩጥ! የምሰዳ
ቸውን ፍላጻዎች ፈልጋቸው" አለው፤ ልጁም
በሮጠ ጊዜ፣ ከእርሱ አሳልፎ አንድ ፍላጻ
ወረወረ። [37]ልጁም የዮናታን ፍላጻ ባረፈበት
ስፍራ እንደ ደረሰ፤ ዮናታን ጠራውና፣
"ፍላጻው ካንተ ወዲያ ዐልፎ የለምን?"
አለው። [38]እርሱም "ቶሎ በል! ፍጠን! አት
ቁም!" ሲል ጮኸበት፤ ልጁም ፍላጻዎቹን
ሰብስቦ ወደ ጌታው ተመለሰ። [39]ከዮናታ
ንና ከዳዊት በስተቀር ልጁ ስለዚህ ነገር
የሚያውቀው አንዳች አልነበረም። [40]ከዚያም
ዮናታን የጦር መሣሪያውን ለልጁ ሰጥቶ፣
"ይዘህ ወደ ከተማ ተመለስ" አለው።
[41]ልጁ ከሄደ በኋላ፣ ዳዊት ከድንጋዩ በስ
ተደቡብ ከተደበቀበት ቦታ ወጥቶ በዮናታን
ፊት ሦስት ጊዜ በምድር ላይ ተደፍቶ ሰገ
ደለት፤ ከዚያም ተሳሳሙ፤ ተላቀሱም፤ በይ
በልጥ ያለ ቀሰው ግን ዳዊት ነበር።
[42]ዮናታንም ዳዊትን፤ " 'በአንተና በእኔ፣
በዘሮችህና በዘሮቼ መካከል *እግዚአብሔር*
ለዘላለም ምስክር ነው' ተባብለን ወዳጅነ
ታችን እንዲጸና በእግዚአብሔር ስም ስለ
ተማማልን እንግዲህ በሰላም ሂድ" አለው።

20፥17 ኢሱ9፥18፤ 1ሳሙ18፥3
20፥18 ቍ25
20፥19 1ሳሙ19፥2
20፥20 2ነገ13፥15
20፥22 ቍ37
20፥23 ዘፍ31፥50
20፥24 ዘኍ10፥10
20፥25 ቍ18
20፥26 ዘሌ7፥20-21
20፥28 ቍ6
20፥29 ዘፍ 8፥20
20፥31 1ሳሙ23፥17፤ 24፥20
20፥32 ዘፍ31፥36፤ 1ሳሙ19፥4፤ ማቴ27፥23
20፥33 1ሳሙ18፥ 11:17
20፥37 ቍ22
20፥41 ዘፍ33፥3፤ ሩት2፥10፤ 1ሳሙ24፥8፤25፥23፤ 2ሳሙ1፥2
20፥42 ዘፍ31፥50፤ 40፥14፤1ሳሙ1፥17፤ 18፥3፤ 2ሳሙ1፥26፥9፥1፤ ምሳ18፥24፤ ኢሳ 48፥1፤ ሐሥ15፥33

[*]25 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ዮናታን ሲነሣ ይላል።

20፥17 *እንደ ገና እንዲምልለት አደረገ፤* ቍ14-15:42፤ 18፥3 ይመ። *ዳዊትን የሚወደውም እንደ ራሱ አድርጎ ነበርና፤* 18፥3፤ 2ሳሙ1፥26 ይመ።

20፥18 *የወር መባቻ በዓል፤* የቍ5 ማብ ይመ።

20፥19 *ወደ ተደበቅህበት ስፍራ፤* ምናልባት በቍ19፥2 ላይ የተጠቀሰው ስፍራ ሊሆን ይችላል።

20፥23 *አንተና እኔ ስለ ተነጋገርነው ነገር፤* ቍ15-17 ይመ። *እግዚአብሔር ... ምስክር ነው፤* ምስክርና ዳኛ ሆኖ በመካከላቸው ይሠራ ዘንድ የእግዚአብሔርን ስም መጥራታቸው በመካከለኛው የተደረገው ቃለ መሐላ የሚከበር መሆኑን ያረጋግጣል።

20፥25 *አበኔር፤* የሳኦል የአጎት ልጅና የጦር ሰራዊቱ አዛዥ ነው (14፥50 ይመ)።

20፥26 *በሥርዐቱ መሠረት እንዳይነጻ፤* የ16፥5 ማብ ይመ፤ ከዘሌ7፥19-21፤15፥16፤ዘዳ23፥19 ጋር ያነጻጽሩ።

20፥30 *የዚያች ጠማማና ዐመፀኛ ሴት ልጅ፤* የዕብራይስጡ አባባል የዮናታንን እናት ጠባይ ሳይሆን፣ የልጁን የዮናታንን ጠባይ ለመግለጥ የተሰነዘረ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።

20፥31 *አንተም ሆንህ መንግሥትህ አትጸኑም፤* ሳኦል በዚህ ጊዜ ዳዊት ካልተገደለ በእርሱ ምትክ ንጉሥ እንደሚሆን ዐውቆ አል (የ18፥13:17:29፤ 19፥1ማብ ይመ)፤ ይሁን እንጂ ልጁ ዮናታን በእርሱ ምትክ ንጉሥ ለመሆን አለ መፈለጉን ሊረዳ አልቻለም።

20፥33 *ጦሩን ወረወረበት፤*18፥11፤19፥10 ይመ።

20፥41 *ሦስት ጊዜ በምድር ላይ ተደፍቶ ሰገደለት፤* የመገዛትና የማክበር ምልክት ነው (ዘፍ 33፥3፤42፥6 ይመ)።

20፥42 *ወዳጅነታችን እንዲጸና ... ስለተማማልን፤* ቍ

ከዚያም ዳዊት ተነሥቶ ሄደ፤ ዮናታንም
ወደ ከተማ ተመለሰ::

### ዳዊት ወደ ኖብ ሄደ

21 ዳዊትም ካህኑ አቢሜሌክ ወዳ
ለበት ወደ ኖብ ሄደ:: አቢሜሌክም
እየተንቀጠቀጠ ዳዊትን ሊገናኘው መጣና፣
"ምነው ብቻህን? ሰውስ ለምን አብሮህ
የለም?" ሲል ጠየቀው::
[2]ዳዊት ካህኑን አቢሜሌክን እንዲህ አለው፤
"ንጉሡ፣ 'ስለ ላክሁህ ነገርና ስለ ሰጠሁህ
መመሪያ ማንም ሰው ምንም ነገር አይ
ወቅ' ብሎ አዞኛል:: ሰዎቼንም የት እን
ደምንገናኝ ነግሬያቸዋለሁ:: [3]ታዲያ አሁን
በእጅህ ምን አለ? አምስት እንጀራ ወይም
የተገኘውን ማንኛውንም ነገር ስጠኝ::"
[4]ካህኑም፣ "ሰው ሁሉ የሚበላው እንጀራ
የለኝም፤ ነገር ግን ሰዎቹ በቅርቡ ከሴት
የተጠበቁ ከሆነ፣ የተቀደሰ እንጀራ በዚህ
አለ" አለው::
[5]ዳዊትም "እንደተለመደው ሁሉ ከወጣሁ
ጊዜ ጀምሮ ሴቶች ከእኛ ተጠብቀዋል፤ ባል
ተቀደሰ ተልእኮ ውስጥ እንኳ የሰዎቹ ዕቃዎች[7]
የተቀደሱ ናቸው፤ ታዲያ ዛሬማ እንዴታ!"
ሲል መለሰ:: [6]ስለዚህ ካህኑ የተቀደሰውን
እንጀራ ለዳዊት ሰጠው፤ *ከእግዚአብሔር*
*ፊት* ተነሥቶ በትኩስ እንጀራ ከተተካው
ከኅብስተ ገጹ በስተቀር በዚያ ሌላ እንጀራ
አልነበረምና::
[7]በዚያችም ዕለት ከሳኦል አገልጋዮች አን
ዱና የእረኞቹ አለቃ የሆነው ኤዶማዊው
ዶይቅ እዚያው *በእግዚአብሔር ፊት* እንዲቈይ
ተገዶ ነበር::
[8]ዳዊት አቢሜሌክን፣ "የንጉሡ ጒዳይ
ስላስቸኰለኝ፣ ሰይፌንም ሆነ ሌላ የጦር
መሣሪያ አላመጣሁም፤ እዚህ ካንተ ዘንድ
ጦር ወይም ሰይፍ አይገኝምን?" ሲል ጠየ
ቀው::
[9]ካህኑም፣ "በኤላ ሸለቆ አንተ የገደልኸው
የፍልስጥኤማዊው የጎልያድ ሰይፍ እዚህ
አለ፤ ከኤፉዱ በስተኋላ በጨርቅ ተጠቅል
ሎአል፤ ከፈለግህ ውሰደው፤ ከእርሱ በስ
ተቀር ሌላ ሰይፍ እዚህ የለም" ብሎ መለ
ሰለት::
ዳዊትም "እንደ እርሱ ያለ የለምና
እርሱኑ ስጠኝ" አለው::

### ዳዊት ወደ ጌት ሄደ

[10]በዚያች ዕለት ዳዊት ከሳኦል ሸሽቶ
ወደ ጌት ንጉሥ ወደ አንኩስ ሄደ:: [11]የአ
ንኩስ አገልጋዮችም፣ "የምድሪቱ ንጉሥ
ዳዊት ይህ አይደለምን? ደግሞስ

'ሳኦል ሺህ ገደለ፤
ዳዊት ግን ዐሥር ሺህ ገደለ'

ብለው በጭፈራቸው የዘፈኑለትስ እርሱ
አይደለምን?" አሉት::
[12]ዳዊት ነገሩን በልቡ አኖረ፤ የጌትን
ንጉሥ አንኩስንም እጅግ ፈራው:: [13]ስለዚህ
በፊታቸው አእምሮውን እንደሳተ ሰው ሆነ፤
በያዙትም ጊዜ የከተማዪቱን ቅጥሮች
እየቦጫጨረ፣ ልጋጉንም በጢሙ ላይ እያዝረ
በረበ እንደ እብድ ሆነ::
[14]አንኩስም አገልጋዮቹን እንዲህ አላቸው፤
ሰውየውን እስቲ ተመልከቱት፤ እብድ እኮ
ነው! ታዲያ ወደ እኔ ያመጣችሁት ለምንድን
ነው? [15]በፊቴ እንዲህ ይሆን ዘንድ ይህን
ሰው እዚህ ያመጣችሁት እብድ አጥቼ
ነውን? እንዲህ ያለውስ ሰው ወደ ቤቴ
መግባት ይገባዋልን?"

### ዳዊት በዓዶላምና በምጽጳ

22 ዳዊት ከጌት ወደ ዓዶላም ዋሻ
ሸሸ፤ ወንድሞቹና የአባቱ ቤተ
ሰቦች ይህን በሰሙ ጊዜ፣ እርሱ ወዳለበት
ወደዚያው ወረዱ:: [2]የተጨነቁ፣ ዕዳ ያለባ
ቸውና የተከፉ አራት መቶ ያህል ሰዎች፣
ወደ እርሱ ተሰባሰቡ፤ መሪያቸውም ሆነ::
[3]ዳዊት ከዚያ ተነሥቶ፣ በሞዓብ ምድር
ወዳለችው ወደ ምጽጳ ሄደ፤ ለሞዓብ

21፥1 1ሳሙ16፥4፤ 22፥9፤19ነህ11፥32፤ ኢሳ10፥32
21፥4 ዘፀ19፥15፤ ዘሌ15፥18፤24፥8-9፤ ማቴ12፥4
21፥5 ዘዳ23፥9-11፤ ኢሱ3፥5፤ 2ሳሙ11፥11፤ 1ተሰ 4፥4
21፥6 ዘፀ25፥30፤ 1ሳሙ22፥10፤ ማቴ12፥3-4፤ ማር2፥25-28፤ ሉቃ6፥1-5
21፥7 1ሳሙ14፥47፤ 22፥9:22፤መዝ52
21፥9 1ሳሙ17፥2: 4:51
21፥10 1ሳሙ25፥13፤ 27፥2
21፥11 1ሳሙ18፥7
21፥13 መዝ34
22፥1 ዘፍ38፥1፤ መዝ57፤142
22፥2 1ሳሙ23፥13፤ 25፥13፤ 2ሳሙ 15፥20

[7]5 ወይም አካል

14-15:23፤18፥3 ይመ:: *ወደ ከተማ፤* ጊብዓ ናት (10፥26 ይመ)::

21፥1 *ካህኑ አቢሜሌክ፤* የ14፥3 ማብ ይመ:: በ22፥10:15 ተጠቅሶ እንደምናየው፣ ዳዊት ወደ ኖብ የመጣው በኡሪምና በቱሚም አማካይነት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ነበር (2፥28፤ ዘፀ28፥3 ማብ ይመ):: *ኖብ፤* ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን ምሥራቅና በጊብዓ በስተ ደቡብ ያለች ሴሎ ከጠፋች በኋላ ማደሪያው እንደ ገና የተተከለባት ከተማ ናት (4፥2-3፤ ኤር7፥12):: ታቦቱን ወደ መቅደሱ ለማምጣት የተደረገ ሙከራ የሌለ ቢመስልም (የ7፥1 ማብ ይመ)፣ ሊቀ ካህኑ አቢሜሌክ እንዲሁም ሌሎች 85 ካህናት (22፥17-18)፣ ኤፉድ (ቍ9)፣ ለተቀደሰው ኅብስት ማስቀመጫ የሆነው ጠረጴዛ (ቍ6) ከዚህ ጋር ተያይዘው ተጠቅሰዋል::

21፥2፤ ዳዊት ለአቢሜሌክ በሰጠው መልስ ላይ ሁኔታውን ለመደበቅ ሙከራ ማድረጉ እንደ ሆነ አይታወቅም፤ ምናልባት ዳዊት እንደዚህ የተናገረው ከሳኦል በመሸሹ ምክንያት አቢሜሌክን ከተባባሪነት ነጻ ለማድረግ ይሆናል፤ ሙከራው ከዚህ የተነሣ ቢሆንም እንኳ የተሳካ አልነበረም (22፥13-18 ይመ)::

21፥4 *የተቀደሰ እንጀራ፤* በተቀደሰው ስፍራ በማደሪያው በኋላም በቤተ መቅደስ፣ እግዚአብሔር የዕለት እንጀራን እንደሚሰጥ በምሳሌነት ለማሳየት፣ የምስጋና መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርበውን ኅብስተ ገጽ (ቍ6፤ዘፀ25፥30 ይመ) የሚያመለክት ነው:: *ነገር ግን ሰዎቹ ... ከሴት የተጠበቁ ከሆነ፤* እንጀራው የተፈቀደው ለካህናቱ ቢሆንም እንኳ፣ ዳዊትና የእርሱ ሰዎች በሥርዐቱ መሠረት ንጹሕ ከሆኑ (ዘፀ19፥15፤ ዘሌ15፥18)፣ አቢሜሌክ ሊሰጣቸው ተስማምቶ ነበር:: ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን እንደ ምሳሌ ወስዶ ሥርዐት እንደ ሕግ መቈጠር እንደሌለበት (ማቴ12፥3-4)፣ መልካም ማድረግና ሕይወትን ማዳን ምንጊዜም ሕግ እንደ ሆነ ጨምሮ አስተምሮአል (ሉቃ6፥9):: ይህን መሰል የርኅራኄ ተግባራት የሕጉ እውነተኛና ትክክለኛ መንፈስ ናቸው::

21፥9 *የጎልያድ ሰይፍ፤* የ17፥54 ማብ ይመ:: *ከኤፉዱ፤* የ2፥28 ማብ ይመ::

21፥10 *አንኩስ፤* የመዝ 34 ርእስ ማብ ይመ:: *ጌት፤* ከአምስቱ የፍልስጥኤማውያን ዋና ከተማዎች አንዱ ነው (ኢሱ 13፥3)::

21፥11 *የምድሪቱ ንጉሥ፤* "ዳዊት" በፍልስጥኤማውያን ንጉሥ ተብሎ መጠራቱ፣ በእስራኤል ዘንድ ዝናው እየገነነ መውጣቱን የሚያመለክት አገላለጥ ነው::

22፥1 *ዓዶላም ዋሻ፤* 2ሳሙ23፥13፤ ዘፍ38፥1፤ ኢሱ12፥15፤ 15፥35፤ 1ዜና11፥15 እና የመዝ142 ርእስ ማብ ይመ::

22፥2 *አራት መቶ ያህል ሰዎች፤* በሳኦል መንግሥት እንደ ወንጀለኛ የተቈጠረው ዳዊት በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ከነበሩ ሰዎች ድጋፍ አገኘ፤ እነዚህም ሰዎች ዳዊት በኋላ ንጉሥ ሆኖ ለሚመሠርተው መንግሥት የኀይል መሠረት ሆኑለት::

22፥3 *በሞዓብ ምድር ወዳለችው ወደ ምጽጳ፤* ትክክለኛው

ንጉሥ፣ እግዚአብሔር የሚያደርግልኝን እስካ
ውቅ ድረስ፣ አባቴና እናቴ መጥተው ካንተ
ዘንድ እንዲቀመጡ ፈቃድህ ነውን?" አለው::
4እርሱም በሞዓብ ንጉሥ ዘንድ አስቀመጣ
ቸው፤ ዳዊት በዐምባ ውስጥ እስከ ቈየበ
ትም ጊዜ ድረስ ከንጉሡ ዘንድ ተቀመጡ::
5ይሁን እንጂ ነቢዩ ጋድ ዳዊትን፣ "በዐ
ምባው ውስጥ አትቈይ፤ ሂድና ወደ ይሁዳ
ምድር ግባ" አለው:: ስለዚህ ዳዊት ተነ
ሥቶ ወደ ሔሬት ጫካ ገባ::

## ሳኦል የኖብን ካህናት መግደሉ

6ሳኦልም፣ ዳዊትና ከእርሱ ጋር የነበሩ
ሰዎች መገኘታቸውን በሰማ ጊዜ፣ በጊብዓ
ኰረብታ ላይ በአጣጥ ዛፍ ሥር፣ ጦሩን በእጁ
ይዞ ተቀምጦ ነበር፤ ሹማምንቱም ሁሉ በዙ
ሪያው ቆመው ነበር:: 7ሳኦልም እንዲህ
አላቸው፤ "እናንት የብንያም ሰዎች ስሙ!
በውኑ የእሴይ ልጅ ዕርሻና የወይን ቦታ
ለሁላችሁ ይሰጣችኋልን? ሁላችሁንስ ሻለቃ
ችና የመቶ አለቆች ያደርጋችኋልን? 8በእኔ
ላይ የዶለታችሁት ለዚህ ነውን? ልጄ ከእ
ሴይ ልጅ ጋር ቃል ኪዳን ሲያደርግ
ማንም አልነገረኝም፤ ዛሬ እንደሚያደርገው
ሁሉ፣ ልጄ አገልጋዬን በእኔ ላይ እንዲያ
ደባብኝ ማነሣሣቱን ከእናንተ ስለ እኔ
ተቈርቍሮ የነገረኝ ማንም የለም::"
9ነገር ግን እዚያ ከነበሩት የሳኦል ሹማም
ንት ጋር ቆሞ የነበረው ኤዶማዊው ዶይቅ
እንዲህ አለ፣ "የእሴይ ልጅ በኖብ ወዳለው
ወደ አኪጦብ ልጅ ወደ አቢሜሌክ ሲመጣ
አይቻለሁ:: 10አቢሜሌክም *እግዚአብሔርን*
ጠየቀለት፤ እንዲሁም ስንቅና የፍልስጥኤ
ማዊውን የጎልያድን ሰይፍ ሰጠው::"
11ከዚያም ንጉሡ፣ የአኪጦብን ልጅ ካህ
ኑን አቢሜሌክን፣ በኖብ ካህናት የነበሩትን
የአባቱን ቤተ ሰብ በሙሉ ልኮ አስጠራቸው፤
ሁሉም ወደ ንጉሡ መጡ:: 12ሳኦልም፤ "የአ
ኪጦብ ልጅ ሆይ፤ እንግዲህ ስማ" አለው::
አቢሜሌክም፣ "እሺ ጌታዬ" ብሎ መለሰ::
13ሳኦልም፤ "ዛሬ እንደሚያደርገው ሁሉ፣
በእኔ ላይ እንዲያምፅብኝና እንዲያደባብኝ፣

22፥4 ዘፍ19፥37
22፥5 2ሳሙ23፥14፤
24፥11፤1ዜና21፥9፤
29፥25፡29
22፥6 ዘፍ21፥33፤
መሳ4፥5
22፥7 ዘዳ1፥15
22፥8 ቍ13፤
1ሳሙ18፥3፤
23፥21፤2ሳሙ20፥1
22፥9 1ሳሙ14፥3፤
21፥1፡7
22፥10 ዘፍ25፥22፤
1ሳሙ17፥51፤21፥6፤
23፥2
22፥13 ቍ8
22፥14 1ሳሙ19፥4
22፥16 1ሳሙ2፥31
22፥17 ዘፀ1፥17
22፥18 1ሳሙ2፥18፤
4፥17
22፥19 1ሳሙ15፥3፤
21፥1
22፥20 1ሳሙ2፥32፤
14፥3፤23፥6፡9፤30፥7፤
2ሳሙ15፥24፤20፥25፤
1ነገ1፥7፤2፥22፡
26፡27፡4፥4፤
1ዜና15፥11፤27፥34
22፥22 1ሳሙ21፥7

እንጀራና ሰይፍ በመስጠት፣ እግዚአብሔርን
ስለ እርሱ በመጠየቅ ከእሴይ ልጅ ጋር
ለምን ዶለታችሁብኝ?" አለው::
14አቢሜሌክም ለንጉሡ እንዲህ ሲል መለሰ፤
"የንጉሥ ዐማች፣ የክብር ዘቦችህ አዛዥና
በቤተ ሰብህ ዘንድ እጅግ የተከበረው ዳዊ
ትን የመሰለ ታማኝ ከአገልጋዮችህ ሁሉ
ማን አለ? 15ስለ እርሱ እግዚአብሔርን ስጠ
ይቅስ ያ ቀን የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበርን?
ፈጽሞ አልነበረም፤ ይህን ጉዳይ በተመለከተ
አገልጋይህ የሚያውቀው ምንም ነገር ስለ
ሌለ ንጉሥ እኔን አገልጋዩን ወይም ከአባቴ
ቤተ ሰብ ማንንም ጥፋተኛ አያድርግ::"
16ንጉሡ ግን፣ "አቢሜሌክ ሆይ፤ አንተም
የአባትህም ቤተ ሰብ በሙሉ በእርግጥ
ትሞታላችሁ" አለው::
17ከዚያም ንጉሡ በአጠገቡ የቆሙትን
ዘቦች፣ "እነዚህም *የእግዚአብሔር* ካህናት
ከዳዊት ጋር ስላበሩ፣ ዳዊት መኰብለሉንም
እያወቁ ስላልነገሩኝ ዞሩና ግደሏቸው" ሲል
አዘዛቸው::
የንጉሡ ሹማምንት ግን እጃቸውን አን
ሥተው *የእግዚአብሔርን* ካህናት ለመግ
ታት ፈቃደኞች አልሆኑም::
18ንጉሡም ዶይቅን፣ "እንግዲያውስ አን
ተው ዞርና ካህናቱን ግደላቸው" ብሎ አዘ
ዘው:: ኤዶማዊው ዶይቅም ዞረና ገደላ
ቸው:: በዚያች ዕለት ሰማንያ አምስት የበ
ፍታ ኤፉድ የለበሱ ካህናትን ገደለ:: 19የካ
ህናቱንም ከተማ ኖብን በሰይፍ መታት፣
በዚያ የሚኖሩትንም ወንዶችንና ሴቶችን፣
ልጆችንና ጡት የሚጠቡ ሕፃናትን፣ እንዲ
ሁም በሬዎችንና አህያዎችን፣ በጎችንም
ሁሉ በሰይፍ ስለት ፈጃቸው::
20የአኪጦብ ልጅ፣ የአቢሜሌክ ልጅ አብ
ያታር ግን አምልጦ ዳዊት ወዳለበት ሸሸ::
21እርሱም ሳኦል *የእግዚአብሔርን* ካህናት
እንደ ገደላቸው ለዳዊት ነገረው:: 22ዳዊ
ትም አብያታርን እንዲህ አለው፤ "ያን ዕለት
ኤዶማዊው ዶይቅ እዚያ ስለ ነበር፣ ነገሩን
በትክክል ለሳኦል እንደሚናገር አውቄ አለሁ፤

ስፍራ አይታወቅም:: *አባቴና እናቴ መጥተው ካንተ ዘንድ እንዲቀመጡ፤* በሳኦል ውጊያ ተካሂዶበት ስለ ነበር የሞዓብም ንጉሥ ዳዊትን ደግፎታል (14፥47 ይመ)፤ ከዚህም በላይ የዳዊት ቅድመ አያት ሞዓባዊት ነበረች (ሩት 4፥13፡22)::

22፥4 *በዐምባ፤* ምናልባት የታወቀ ምሽግ ሊሆን ይችላል፤ ይሁን እንጂ በምልክዐ ምድራዊ አቀማመጡ መሸሸጊያ ሊሆን የሚችል የታወቀ ስፍራን የሚያመለክት ነው::

22፥5 *ነቢዩ ጋድ፤* ነቢዩ የተመረጠውን ንጉሥ አገልግሎታል፤ ቄይቶም ካህን ይመጣና (ቍ 20) ተገቢውን ንጉሣዊ አጀብ የተሟላ ያደርገዋል፤ ሁሉም ከሳኦል መንግሥታዊ አስተዳደር ሸሽተው ያመለጡ ናቸው:: ይህ ወቅት ነቢይ ለመጀመሪያ ጊዜ የታየበት ነው፤ በኋላም ዳዊትን በቤተ መቅደስ የሙዚቃ አገልግሎት ዝግጅት የረዳው (1ዜና29፥29)፣ ዳዊት እስራኤላውያንን በቈጠረ ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል ይዞ ፊት ለፊት ያወገዘው ይኸው ነቢይ ነበር (2ሳሙ 24፥11-25):: *ሔሬት ጫካ፤* በይሁዳ ነገድ ምድር የሚገኝ ነው::

22፥6 *በጊብዓ፤* የ10፥5 ማብ ይመ:: *በአጣጥ ... ዛፍ፤* የ14፥2 ማብ ይመ::

22፥7 *የብንያም ሰዎች፤* ብንያማዊው ሳኦል (9፥1-2፤10-21) ለነገዱ ያለውን ታማኝነት በማስቀደም ከሹማምንቱ ጋር ሥልጣኑን ማጠናከር ይፈልጋል:: ዳዊት ግን ከይሁዳ ነገድ ነበር (የ2ሳሙ 2፥4 እና የ16፥1 ማብ ይመ):: *ዕርሻና የወይን ቦታ ለሁላችሁም ይሰጣችኋል?* ሳሙኤል አስቀድሞ ተናግሮት የነበረውን፣ ሳኦል እንደ ሌሎች ሕዝቦች ነገሥታት በመሆን ይፈጽመዋል (8፥14 ይመ):: ድርጊቶቹ ስለ ንጉሥነት ከተሰጠው የቃል ኪዳን አሠራር ጋር የሚቃረኑ ናቸው ( የ8፥7 እና 10፥25 ማብ ይመ)::

22፥10 *አቢሜሌክም እግዚአብሔርን ጠየቀለት፤* የ21፥1 ማብ ይመ::

22፥17 *መኰብለሉንም እያወቁ፤* ካህናቱ ጉዳዩን ምን ያህል እንደሚያውቁት የተገለጠ ነገር የለም:: ዳዊት ራሱም የገለጠላቸው ነገር የለም (21፥2-3፥8 ይመ)::

22፥18 *የበፍታ ኤፉድ፤* የ2፥18 ማብ ይመ::

22፥19 *ኖብን በሰይፍ መታት፤* ስለዚህ በዔሊ ቤት ላይ የተነገረው የፍርድ ትንቢት ተፈጸመ (2፥31 ይመ)::

22፥20 *አብያታር ግን አምልጦ ዳዊት ወዳለበት ሸሸ፤* የቍ5 ማብ ይመ:: አብያታር ሊቀ ካህናት የሚለብሰውን ኤፉድ ይዞ መጣ (23፥6 ይመ)፤ በኋላም ለዳዊት "እግዚአብሔርን ጠየቀለት"

ለመሳው የአባትህ ቤተሰብ ዕልቂት ተጠ
ያቂው እኔ ነኝ። 23አሁንም ከእኔ ጋር ቈይ፤
አትፍራ፤ የአንተን ሕይወት የሚፈልግ የእ
ኔን ሕይወት የሚፈልግ ነውና። አብረኸኝ
በሰላም ትኖራለህ።"

## ዳዊት ቅዒላን መታደጉ

**23** ከዚህ በኋላ "እነሆ፤ ፍልስጥኤማ
ውያን በቅዒላ ላይ ጦርነት ከፍ
ተው፣ ዐውድማውን እየዘረፉት ነው" ብለው
ለዳዊት ነገሩት። 2እርሱም፣ "እነዚህን ፍልስ
ኤማውያን ሄጄ ልምታን?" ሲል *እግዚአ
ብሔርን* ጠየቀ።

*እግዚአብሔርም* "ሂድ፤ ፍልስጥኤማው
ያንን ምታ፤ ቅዒላንም አድናት" ብሎ መለ
ሰለት።

3የዳዊት ሰዎች ግን፣ "እዚሁ በይሁዳ
ምድር እያለን እየፈራን ነው፤ የፍልስጥኤ
ማውያንን ሰራዊት ለመውጋት ወደ ቅዒላ
የምንሄድ ከሆነማ ምን ያህል የሚያስፈራ
ነው?" አሉት።

4ዳዊት እንደ ገና *እግዚአብሔርን* ጠየቀ፤
*እግዚአብሔርም*፣ "ፍልስጥኤማውያንን በእ
ጅህ አሳልፌ ስለምሰጥ፣ ወደ ቅዒላ ውረድ"
አለው። 5ስለዚህ ዳዊትና ሰዎቹ ወደ ቅዒላ
ሄደው፣ ፍልስጥኤማውያንን ወጉ፤ እንስ
ሶቻቸውን ማርከው ወሰዱ፤ በፍልስጥኤማው
ያን ላይ ከባድ ጉዳት አደረሱ፤ ዳዊትም የቅ
ዒላን ሕዝብ ታደገ። 6የአቢሜሌክ ልጅ አብ
ያታር ወደ ቅዒላ ወደ ዳዊት በሸሸ ጊዜ፣
ኤፉዱን ይዞ ወርዶ ነበር።

## ሳኦል ዳዊትን ማሳደዱ

7ሳኦል የዳዊትን ወደ ቅዒላ መሄድ በሰማ
ጊዜ፣ "ዳዊት መዝጊያና የብረት መወርወ
ሪያ ወዳላት ከተማ መግባቱ፣ ራሱን በራሱ
እንደ ማሰር ስለ ሆነ፣ ይህን ሰው እግዚአብሔር
በእጄ አሳልፎ ሰጥቶኛል" አለ። 8ሳኦልም፣
ወደ ቅዒላ ወርደው ዳዊትንና ሰዎቹን እን
ዲከቡ፣ ሰራዊቱን በሙሉ ለጦርነት ጠራ።

9ዳዊትም ሳኦል ክፉ እንዳሰበበት ባወቀ
ጊዜ፣ ካህኑን አብያታርን፣ "ኤፉዱን አምጣ"
አለው። 10ከዚያም ዳዊት እንዲህ አለ፤ "የእስ
ራኤል ስምባክ *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ሳኦል
ወደ ቅዒላ መጥቶ፣ በእኔ ምክንያት ከተ
ማዪቱን ለማጥፋት ማሰቡን ባሪያህ በት
ክክል ሰምቶአል። 11የቅዒላ ሰዎች አሳል
ፈው ይሰጡኝ ይሆን? ባሪያህ እንደሰማውም
ሳኦል ወደዚህ ይወርድ ይሆን? የእስራኤል
ስምባክ *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ለባሪያህ እንድ
ትነግረው እለምንሃለሁ።"

*እግዚአብሔርም* "አዎን ይወርዳል" አለው።

12ዳዊትም እንደ ገና፣ "የቅዒላ ነዋሪዎች
እኔንና ሰዎቼን ለሳኦል አሳልፈው ይሰጡ
ናል?" ሲል ጠየቀ።

*እግዚአብሔርም* "አዎን አሳልፈው ይሰጡ
አችኋል" አለው።

13ስለዚህ ዳዊትና ስድስት መቶ የሚሆኑ
ሰዎቹ ከቅዒላ ተነሥተው መሄድ ወደ ሚች
ሉበት ቦታ ሁሉ ሄዱ፤ ዳዊት ከቅዒላ መሸሹን
በሰማ ጊዜ፣ ሳኦል ወደዚያ መሄዱን ተወ።

14ዳዊት በምድረ በዳ ባሉ ምሽጎችና በዚፍ
ምድረ በዳ ኰረብታዎች ተቀመጠ፤ ሳኦ
ልም በየዕለቱ ይከታተለው ነበር፤ ነገር
ግን እግዚአብሔር ዳዊትን አሳልፎ አልሰጠ
ውም።

15ዳዊት በዚፍ ምድረ በዳ ሖሬሽ በተባለ
ቦታ ሳለ፣ ሳኦል ሊገድለው መምጣቱን አየ።
16የሳኦል ልጅ ዮናታንም ዳዊት ወዳለበት
ወደ ሖሬሽ ሄዶ፣ በእግዚአብሔር ስም አበረታ
ታው፤ 17እርሱም፣ "አትፍራ፤ አባቴ ሳኦል እጁን
በአንተ ላይ አያሳርፍም፤ በእስራኤል ላይ ትነ
ግሣለህ፤ እኔም ካንተ ቀጥዬ ሁለተኛ ሰው
እሆናለሁ፤ ይህንም አባቴ ሳኦል እንኳ ያው
ቀዋል" አለው። 18ሁለቱም *በእግዚአብሔር
ፊት* ቃል ኪዳን አደረጉ። ከዚያም ዮናታን
ወደ ቤቱ ሄደ፤ ዳዊት ግን እዚያው ሖሬሽ
ተቀመጠ።

19የዚፍ ሰዎች ወደ ጊብዓ ወደ ሳኦል
ወጥተው እንዲህ አሉ፤ "እነሆ፤ ዳዊት ከየሴ
ሞን በስተደቡብ በኤኪላ ኰረብታ ላይ
በሖሬሽ ምሽጎች ውስጥ በመካከላችን ተደ
ብቆ የለምን? 20አሁንም ንጉሥ ሆይ፤ አንተ
ደስ ባለህ ጊዜ ና እንጂ፣ እርሱን ለንጉሡ
አሳልፎ ለመስጠት እኛ አለን።"

21ሳኦል እንዲህ ሲል መለሰ፤ "ለእኔ ስለ
ተቈረቈራችሁ *እግዚአብሔር* ይባርካችሁ፤
22አሁንም ሂዱና አጣሩ ዘወትር የት እንደ
ሆነና በዚያ ያየውን ሰው ለይታችሁ ዕወቁ፤
እጅግ ተንኰለኛ መሆኑን ሰምቻለሁና።

22፥23 1ሳሙ20፥1
23፥1 ዘኍ18፥27፤ ኢሱ15፥44፤መሳ6፥11
23፥2 ቍ4:12፤ 1ሳሙ22፥10፤30፥8፤ 2ሳሙ2፥1፤5፥19፤ መዝ50፥15
23፥4 ቍ2፤ ኢሱ 8፥7፤ 1ሳሙ9፥16
23፥6 1ሳሙ2፥28፤ 22፥20
23፥7 ዘዳ32፥30፤ መዝ31፥21
23፥9 1ሳሙ2፥18፤ 22፥20
23፥12 ቍ20
23፥13 1ሳሙ22፥2
23፥14 ኢሱ15፥24፤ መዝ32፥7፤54፥3-4፤ 55፥7
23፥15 1ሳሙ20፥1
23፥16 1ሳሙ30፥6፤ መዝ18፥2፤27፥14
23፥17 1ሳሙ20፥31
23፥18 1ሳሙ18፥3፤ 2ሳሙ9፥1
23፥19 1ሳሙ26፥1፡ 3፤መዝ54
23፥20 ቍ12
23፥21 ሩት2፥20፤ 1ሳሙ22፥8፤ 2ሳሙ2፥5

(23፥2 እና ማብ ይመ፤ 23፥4፡9፤ 30፥7-8፤ 2ሳሙ2፥1፤ 5፥19፡23)። ከአዶን ያስ ጋር ዐመፅ በመተባበሩ በንጉሥ ሰሎሞን ከአገልግሎቱ እስከ ተወገደበት ጊዜ ድረስ (1ነገ26፥27) ሊቀ ካህናት ሆኖ አገልግሎአል።

23፥2 *እግዚአብሔርን ጠየቀ፤* ዳዊት ይህን ያደረገው በሊቀ ካህኑ በአብያታር አማካይነት በኡሪምና በቱሚም ነው (ቍ6:9 እና የ2፥28 ማብ ይመ)።

23፥9 *ኤፉዱን አምጣ፤* የቍ 2 ማብ ይመ።

23፥13 *ስድስት መቶ፤* የዳዊት ሰዎች ቍጥር በእጅጉ ጨምሮአል ማለት ነው (ከ22፥2 ጋር ያነጻጽሩ)።

23፥14 *በምድረ በዳ...ምሽጎችና* የማይደረስባቸው ቦታዎች ናቸው (የ22፥4 ማብ ይመ )። *በዚፍ ምድረ በዳ፤* ከሔብሮን በስተድቡብ ይገኛል። *ነገር ግን እግዚአብሔር ዳዊትን አሳልፎ አልሰጠውም፤* እዚህ ላይ የተገለጸው እግዚአብሔር ለዳዊት ያደረገው ጥበቃ፣ በገዛ ፈቃዱ ከሚራመደው ከሳኦል የምኞት አስተሳሰብ ጋር በቍ 7ላይ በከፍተኛ ደረጃ ተነጻጽሮአል።

23፥17 *በእስራኤል ላይ ትነግሣለህ፤* የ18፥4 ማብ ይመ ፤ 20፥13:16:31 ይመ። *እኔም ከአንተ ቀጥዬ ሁለተኛ ሰው እሆናለሁ፤* ዮናታን ለዳዊት ያለው ፍቅርና አክብሮት ያለ አንዳች ቅናት የበታች ሆኖ ለማገልገል ፈቃደኛ መሆኑን እንዲገልጽ አድርጎታል (18፥3 ማብ ይመ 19፥4 ይመ)። በዳዊትና በዮናታን መካከል ተጽፎ የሚገኘው የመጨረሻው ግንኙነታቸው ይህ ነው። *ይህንም አባቴ ሳኦል እንኳ ያውቀዋል፤* 18፥8 እና 20፥31 ማብ ይመ።

23፥18 *ኪዳን፤* የ18፥3፤ 20፥14-15 ማብ ይመ።

23፥19 *ምሽጎች፤* የማይደረስባቸው ስፍራዎች ናቸው (የ22፥4 ማብ ይመ)።

23የሚደበቅባቸውን ቦታዎች ሁሉ ካያችሁ
በኋላ ግልጽ መረጃ ይዛችሁ ወደ እኔ ኑ፤
እኔም አብሬችሁ እሄዳለሁ፤ ብቻ በዚያ
አገር ይገኝ እንጂ በይሁዳ ነገዶች ሁሉ
መካከል ከገባበት ጉድጓድ ገብቼ አወጣዋ
ለሁ::"

24ስለዚህ ሰዎቹ ለመሄድ ተነሥተው ከሳ
ኦል በፊት ወደ ዚፍ ሄዱ፤ በዚህ ጊዜ
ዳዊትና ሰዎቹ ከየሴሞን በስተ ደቡብ በዓ
ረባ ውስጥ ባለው በማዖን ምድረ በዳ ነበሩ::
25ሳኦልና ሰዎቹም ዳዊትን ሊፈልጉት ሄዱ፤
እርሱም ይህን በሰማ ጊዜ፣ ወደ ዐለቱ
ወርዶ በማዖን ምድረ በዳ ተቀመጠ:: ሳኦ
ልም ይህን እንደሰማ፣ ዳዊትን በማሳደድ
ወደ ማዖን ምድረ በዳ ዘልቆ ገባ::

26ሳኦል በተራራው በአንዱ በኩል ሆኖ ሲያ
ሳድድ፣ ዳዊትና ሰዎቹ ደግሞ በተራራው
በሌላ በኩል ከሳኦል ለማምለጥ ይጣደፉ
ነበር:: ሳኦልና ወታደሮቹ ዳዊትንና ሰዎቹን
ከበው ለመያዝ ተቃርበው ሳሉ፣ 27አንድ
መልእክተኛ ወደ ሳኦል መጥቶ፣ "ፍልስጥኤ
ማውያን አገሩን ወረውታልና ቶሎ ድረስ!"
አለው:: 28ከዚያም ሳኦል ዳዊትን ማሳደዱን
ትቶ፣ ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሊዋጋ ሄደ::
ከዚህ የተነሣም የዚያን ቦታ ስም "የመለ
ያያ ዐለት" ብለው ጠሩት:: 29ዳዊትም ከዚያ
ወደ ላይ ወጥቶ በዐይንጋዲ ምሽጎች ተቀ
መጠ::

### ዳዊት ሳኦልን ከመግደል ታቀበ

24 ሳኦል ፍልስጥኤማውያንን ከማሳ
ደድ ከተመለሰ በኋላ፣ "እነሆ፤ ዳዊት
በዓይንጋዲ ምድረ በዳ አለ" ብለው ነገሩት::
2ስለዚህ ሳኦል ከመላው እስራኤል የተመ
ረጡ ሦስት ሺህ ሰዎችን ይዞ ዳዊትንና
ሰዎቹን ለመፈለግ "የሜዳ ፍየሎች ዐለት"
ወደ ተባለው ቦታ አቅራቢያ ሄደ::

3ሳኦልም በመንገድ ዳር ወዳለው ወደ
አንድ የበጎች ማደሪያ በደረሰ ጊዜ፣ ዋሻ
አግኝቶ ወገቡን ሊሞክር ወደዚያ ገባ::
ዳዊትና ሰዎቹም ከዋሻው በውስጠኛው ቦታ
ተቀምጠው ነበር:: 4የዳዊት ሰዎችም ዳዊ
ትን፣ "እግዚአብሔር፣ 'የወደድኸውን ታደ
ርግበት ዘንድ ጠላትህን በእጅህ አሳልፌ
እሰጥሃለሁ' ብሎ ለአንተ የተናገረው ቀን
ዛሬ ነው" አሉት:: ዳዊትም በልቡ እየተ
ሳበ ሄዶ የሳኦልን ልብስ ጫፍ ማንም ሳያ
ውቅ ቈርጦ ወሰደ::

5ዳዊት የሳኦልን ልብስ ጫፍ በመቍረጡ
ልቡ በሐዘን ተመታ:: 6ለሰዎቹም፣ "እግዚ
አብሔር በቀባው በጌታዬ ላይ እንዲህ ያለ
ውን ነገር ከማድረግና እግዚአብሔር የቀ
ባው ስለ ሆነም እጄን በእርሱ ላይ ከማን
ሣት እግዚአብሔር ይጠብቀኝ" አላቸው::
7ዳዊት ሰዎቹን በዚህ ቃል ገሠጻቸው፤ በሳ
ኦል ላይ አደጋ እንዲያደርሱበትም አልፈቀ
ደላቸውም:: ሳኦልም ከዋሻው ወጥቶ ሄደ::

8ከዚያም ዳዊት ከዋሻው ወጥቶ ሳኦልን፣
"ጌታዬ ንጉሥ ሆይ!" ብሎ ጠራው:: ሳኦ
ልም ወደ ኋላው ዞር ባለ ጊዜ፣ ዳዊት ወደ
መሬት ጐንበስ ብሎ እጅ ሲነሣው ተመ
ለከተ፤ 9ዳዊትም ሳኦልን እንዲህ አለው፤
"ሰዎች፣ 'እነሆ፤ ዳዊት ክፉ ነገር ሊያደር
ግብህ ይፈልጋል' ሲሉ ለምን ትቀበላቸዋ
ለህ? 10በዛሬው ዕለት በዋሻው ውስጥ እግዚ
አብሔር አንተን እንዴት አድርጎ በእጄ
ላይ እንደ ጣለህ እነሆ፤ በገዛ ዐይንህ አይ
ተሃል፤ አንዳንዶች እንድገድልህ ገፋፍተ
ውኝ ነበር፤ እኔ ግን፣ 'እግዚአብሔር በቀ
ባው በጌታዬ ላይ እጄን አላነሣም' በማ
ለት ራራሁልህ:: 11አባቴ ሆይ፤ የልብስህ
ቍራጭ ይኸው በእጄ ላይ ተመልከተው!
የልብስህን ጫፍ ቈረጥሁ እንጂ አንተን
አልገደልሁህም:: አሁንም ክፋት ወይም
ዐመፅ አለመፈጸሜን ዕወቅልኝ፤ ተረዳል
ኝም፤ እኔ ክፉ አልሠራሁብህም፤ አንተ ግን
ሕይወቴን ለማጥፋት እያሳደድኸኝ ነው::
12እግዚአብሔር በአንተና በእኔ መካከል ይፍ
ረድ:: ክፉ ስላደረግህብኝ እግዚአብሔር ይበ
ቀልህ እንጂ፣ እጄስ በአንተ ላይ አትሆ
ንም፤ 13በጥንት አባባል፣ 'ለክፉ አድራጊ
ዎች ክፉ ድርጊት ይወጣል' እንደ ተባለ፤
አሁንም እጄ በአንተ ላይ አትሆንም::

14 "የእስራኤል ንጉሥ የወጣው በማን ላይ
ነው? አንተስ የምታሳድደው ማንን ነው?
የሞተ ውሻን? ወይስ ቁንጫ? 15አሁንም
እግዚአብሔር ዳኛ ሆኖ በመካከላችን ይፍ
ረድ፤ ጉዳዬን ተመልክቶ እርሱው ይሟ
ገትልኝ፤ እኔንም ከእጅህ ነጻ በማውጣት
እውነተኛ መሆኔን ይግለጠው::"

16ዳዊት ይህን ተናግሮ ሲያበቃ ሳኦል፣
"ልጄ ዳዊት ሆይ፤ ይህ የአንተ ድምፅ
ነውን?" ሲል ጠየቀው፤ ጮኾም አለቀሰ::
17እንዲህም አለ፤ "ክፉ ሳደርግብህ፣ በጎ
መልሰህልኛልና፣ አንተ ከእኔ ይልቅ ጻድቅ

23፥23 ዘፍ31፥36
23፥24 ኢያሱ15፥55፤
1ሳሙ26፥1
23፥26 መዝ17፥9
23፥29 ኢያሱ15፥62፤
1ሳሙ24፥22፤
2ዜና 20፥2፤
ማሕ1፥14፤
24፥1 ኢያሱ15፥62
24፥2 1ሳሙ26፥2
24፥3 መሳ3፥24፤
መዝ57፤142
24፥4 ቍ10:11፤
1ሳሙ25፥28-30፤
2ሳሙ4፥8
24፥5 1ሳሙ24፥10፤
26፥9
24፥6 ዘፍ26፥11፤
1ሳሙ12፥3
24፥8 1ሳሙ20፥41
24፥9 1ሳሙ26፥9፤
2ሳሙ24፥10
24፥10 ቍ4
24፥11 ቍ4፤
ዘፍ 31፥36፤
1ሳሙ20፥1፤
25፥28፤26፥20፤
መዝ7፥3፤35፥7
24፥12 ዘፍ16፥5፤
ዘኍ31፥3፤
1ሳሙ 25፥38፤
ኢዮ9፥15
24፥13 ማቴ 7፥20
24፥14 1ሳሙ17፥43፤
26፥20
24፥15 ቍ12፤
ዘፍ16፥5፤መዝ26፥11
35፥1:23:24፤43፥1፤
50፥4፤54፥1፤119፥13፤
4:154፤135፥14፤
ኢሳ49፥25
24፥16 1ሳሙ26፥17
24፥17 ዘፍ38፥26፤
ዘጸ9፥27፤ማቴ 5፥44

24፥4 *እግዚአብሔር...ብሎ ላንተ የተናገረው ቀን፤* የዳዊት ሰዎች የተናገሩትን ነገር እግዚአብሔር መቼና የት እንደ ገለጠላቸው የተጻፈ ነገር የለም:: ምናልባት ሳኦልን ለመተካት ለዳዊት መቀባት የሰጡት የራሳቸው ትርጒም ሊሆን ይችላል ወይም ከሳኦል የበቀል ርምጃ ዳዊት ንጉሥ እንደሚሆን ለዳዊት የተሰጠውን ዋስትና የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም (16፥13-14፤ 20፥14-15፤ 23፥17):: ዛሬ እግዚአብሔር ይናገራል፤ የሚለው ተለዋጭ ሐረግ ዳዊት ቸል ሊለው የማይገባውን የእርሱ ሰዎች የእግዚአብሔር መገለጥ እንደ ሆነ የተረዱትን የራሱን የአጋጣሚውን ምቹነት እንጂ እግዚአብሔር በቃል የተናገረውን የሚመለከት አይደለም::

24፥6 *እግዚአብሔር የቀባው ስለ ሆነም፤* ሳኦል በእግዚ አብሔር የተቀባ ስለ ሆነና መንግሥቱም መለኮታዊ ፈቃድ ስለ ነበረው (የ9፥16 ማብ ይመ)፣ ዳዊት ንግሥናውን ከሳኦል በትግል ሊነጥቀው አልፈለገም፤ ነገር ግን ሥልጣኑን የሰጠው እግዚአብሔር ከሳ ኦል ወስዶ እስኪያስረክበው ድረስ ጠበቀ (ቍ12:15፤ 26፥10 ይመ)::

24፥11 *አባቴ ሆይ፤* ዳዊት እንደዚህ ያለው ሳኦል ዐማቱ ስለ ነበረ (18፥27 ይመ) ወይም ለአክብሮትና ለትሕትና ሊሆን ይችላል::

24፥16 *ጮኾም አለቀሰ፤* ሳኦል በዳዊት ላይ በፈጸመው ድርጊት ለጊዜው በደለኛ መሆኑ ተሰምቶታል (26፥21 ይመ)፤ ይሁን እንጂ ዳዊትን ለመግደል ፈጥኖ ወደ ቀድሞ ውሳኔው ተመለሰ (26፥2)::

ነህ:: 18ያደረግህልኝን በጎ ነገር ይኸው
ነግረኸኛል፤ እግዚአብሔር እኔን በእጅህ
ጥሎኝ ነበር፤ አንተ ግን አልገደልኸኝም::
19ለመሆኑ ጠላቱን አግኝቶ ጉዳት ሳያደ
ርስበት የሚለቀው ማን ነው? ዛሬ ስላደ
ረግህልኝ ቸርነት እግዚአብሔር ይመልስልህ::
20እነሆ፤ አንተ በእርግጥ እንደምትነግሥና
የእስራኤል መንግሥት በእጅህ እንደምት
ጸና ዐውቃለሁ:: 21ዘሮቼን እንዳታጠፋ ስሜ
ንም ከአባቴ ቤት እንዳትደመስስ አሁን
*በእግዚአብሔር* ማልልኝ::”

22ዳዊትም ለሳኦል ማለለት፤ ከዚያም ሳኦል
ወደ ቤቱ ተመለሰ:: ዳዊትና ሰዎቹ ግን
ወደ ዐምባው ወጡ::

### ዳዊት፣ ናባልና አቢግያ

**25** ሳሙኤልም ሞተ፤ እስራኤል ሁሉ
ተሰብስበው አለቀሱለት፤ አርማቴም
ባለው ቤቱም ቀበሩት::

ከዚያም ዳዊት ተነሥቶ ወደ ማየን
ምድረ በዳ ወረደ:: 2በማየን ምድር በቀርሜ
ሎስ ንብረት ያለው አንድ ባለጸጋ ሰው
ነበረ፤ እርሱም አንድ ሺህ ፍየሎችና በቀ
ርሜሎስ የሚሸልታቸው ሦስት ሺህ በጎች
ነበሩት:: 3የሰውየው ስም ናባል፣ የሚስቱም
ስም አቢግያ ነበረ:: እርሷም አስተዋይና
ውብ ነበረች፤ ባሏ ግን ባለጌና ምግባረ
ብልሹ ሰው ነበረ፤ እርሱም ከካሌብ ወገን
ነበር::

4ዳዊት በምድረ በዳ ሳለ ናባል በጎቹን
እንደሚሸልት ሰማ:: 5እርሱም ዐሥር ወጣ
ቶችን እንዲህ ሲል ላካቸው፤ “ወደ ቀርሜ
ሎስ ወደ ናባል ውጡ፤ በስሜም ሰላምታ
አቅርቡለት:: 6እንዲህም በሉት፤ ‘ዕድሜህ

24፥18 1ሳሙ 26፥23
24፥19 ሩት 2፥12፤ 2ዜና 15፥7
24፥20 1ሳሙ 13፥14፤ 20፥31
24፥21 ዘፍ 21፥23፤ 47፥31፤ 1ሳሙ 18፥3፤ 20፥14-15፤ 2ሳሙ 21፥1-9
24፥22 1ሳሙ 23፥29
25፥1 ዘሌ 10፥6፤ ዘዳ 34፥8፤ 1ሳሙ 7፥17፤ 28፥3
25፥2 ዘፍ 31፥19፤ ኢሱ 15፥55፤ 2ሳሙ 19፥32
25፥3 15፥13፤ ምሳ 31፥10
25፥6 1ዜና 12፥18፤ መዝ 122፥7፤ ማቴ 10፥12
25፥7 ቍ 15
25፥8 ነህ 8፥10
25፥10 መሳ 9፥28
25፥11 መሳ 8፥6
25፥13 ዘኍ 31፥27፤ 1ሳሙ 21፥10፤ 22፥2
25፥14 1ሳሙ 13፥10

ይርዘም! ሰላም ለአንተ ይሁን፤ ሰላም ለቤ
ተሰብህና የአንተ ለሆነው ሁሉ ይሁን::
7“በዚህ ጊዜ በጎች እንደምተሸልት
ሰምቻለሁ፤ እረኞችህ ከእኛ ጋር በነበሩበት
ጊዜ፣ ያደረስንባቸው ጉዳት የለም፤ ቀርሜ
ሎስ በነበሩበት ጊዜ ሁሉ፣ የጠፋባቸው
አንዳች ነገር አልነበረም:: 8የገዛ አገልጋዮች
ህን ጠይቅ፤ እነርሱም ይነግሩሃል:: ስለዚህ
አመጣጣችን በጥሩ ቀን በመሆኑ፣ እነዚህ
ወጣቶቼ በፊትህ ሞገስ ያግኙ:: እባክህን
ለአገልጋዮችህና ለልጅህ ለዳዊት የምትች
ለውን ያህል ስጥ::” ’

9የዳዊት ሰዎች ከዚያ እንደ ደረሱም፣
በዳዊት ስም ይህንኑ መልእክት ለናባል
ከተናገሩ በኋላ ምላሹን ይጠባበቁ ጀመር::
10ናባልም ለዳዊት አገልጋዮች እንዲህ
ሲል መለሰ፤ “ለመሆኑ ይህ ዳዊት ማነው?
የእሴይስ ልጅ ማን ነው? በአሁኑ ጊዜ ከጌቶ
ቻቸው የሚኰበልሉ አገልጋዮች ብዙ ናቸው::
11ታዲያ እንጀራዬንና ውሃዬን እንዲሁም
በጎቼን ለሚሸልቱልኝ ሰዎች ያረድሁትን
ፍሪዳ ከየት እንደመጡ ለማይታወቁ ሰዎች
የምሰጠውስ ለምንድን ነው?”

12የዳዊት ሰዎችም ወደ መጡበት ተመ
ለሱ፤ እዚያም እንደ ደረሱ የተባሉትን ሁሉ
ነገሩት:: 13ዳዊትም ሰዎቹን፣ “በሉ ሁላች
ሁም ሰይፋችሁን ታጠቁ” አላቸው:: ስለዚህ
ሁሉም ሰይፋቸውን ታጠቁ፤ ዳዊትም የራ
ሱን ታጠቀ:: አራት መቶ ያህል ሰዎች
ከዳዊት ጋር ሲወጡ መቶ ያህሉ ግን ጓዝ
ለመጠበቅ ቀሩ::

14ከአገልጋዮቹ አንዱ ለናባል ሚስት ለአ
ቢግያ እንዲህ አላት፤ “እነሆ፤ ዳዊት ሰላም

24፥21 ***ዘሮቼን እንዳታጠፋ፤*** የ20፥14-15 ማብ ይመ::

24፥22 ***ዐምባው፤*** ሊደረስበት የማይቻል ቦታ ነው (የ22፥4 ማብ ይመ):: ዳዊት ካለፈው ተመክሮ በመነሣት የሳኦልን የንስሓ ቃል ሊያምን ስላልቻለ፣ ከሰዎቹ ጋር ወደ መደበቂያው ቦታ ሄደ::

25፥1 ***እስራኤል ሁሉ...አለቀሱለት፤*** ሳሙኤል በእግዚአብሔር የሚመራ ንጉሣዊ አስተዳደር እንደ ገና በእስራኤል እንዲጀመርና ብሔራዊ አንድነት እንዲጠበቅ ታላቅ አስተዋጽዖ ያደረገ ሰው ስለ ነበር (ም8.12)፣ ሞቱ የእስራኤልን ሕዝብ እጅግ አሳዝኖ አል:: አመራሩን ማጣት ያስከተለው ጥልቅ ሐዘን በእስራኤል የጥንት ታሪክ ስማቸው በዋነኝነት ከሚጠቀሰው ከነያዕቆብ (ዘፍ 50፥20)፣ ከነአሮን (ዘኍ20፥29፤ እንዲሁም ከነሙሴ ጋር (ዘዳ34፥8) አስቈጥሮታል:: ***አርማቴም፤*** 7፥17 እና የ1፥1 ማብ ይመ::

25፥2-44፤ ***ናባል*** (ቍ25) በቀርሜሎስ አጠገብ ይኖር ነበር፤ ይህ ስፍራ ሳኦል ለራሱ ክብር ሐውልት ያቆመበት (15፥12) እንዲሁም በእግዚአብሔር እንዲናቅ ያደረገውን ድርጊት የፈጸመበት ስፍራ ነው (15፥26):: የናባል ታሪክ ጸሓፊው ለመግለጽ የፈለገውን ዐላማ በተለያየ መንገድ ለማሳየት ዕገዛ አድርጎአል፤ ይኸውም (1) ምንም እንኳ ዳዊት መንጎቹን ቢጠብቅለትም የናባል አጠቃላይ ባሕርይ ይኸውም ለዳዊት የነበረው ንቀትና በእግዚአብሔር እጅ በድንገት መሞቱ እነዚህ ሁሉ ዳዊት መንጎቹን የጠበቀለትን ሳኦልን የሚያጎዳኙት ናቸው:: ይህም ጸሓፊው ሳኦልን በተዘዋዋሪ መንገድ እንደ ጅል አድርጐ እንዲያቀርበውና (13፥13፤ 26፥21) መጨረሻውም ምን እንደሚመስል አስቀድሞ ለማሳየት ምቹ ሁኔታን ፈጥሮለታል፤ (2) ናባል ስላበሳጨው ሊበቀለው መነሣቱ የተፈጥሮ ባሕርዩን ዝንባሌ ያሳያል፤ እግዚአብሔር በቀባው ንጉሥ ላይ እጁን ላለማንሣት መወሰኑንም እጅግ አድርጎ ያጕላል፤ (3) ብልኅነትን የተሞላው፣ የአቢግያ ድርጊት፣ ዳዊት በግል ቂም ተነሣሥቶ የመሪነት ሥልጣኑን በመጠቀም የሰው ሕይወት እንዳያጠፋ አድርጎታል:: ይህም ዳዊት ከሳኦል የተለየ መሪ መሆኑን ያሳያል፤ በዚህ መንገድ ለባሪያዎቹ የሚበቀል እግዚአብሔር፣ የዳዊትን ሰይፍ ከደም ጠብቆታል፤ ይህም ለዳዊት የማይረሳ ትምህርት ሰጥቶታል:: (4) አቢግያ ወደ ፊት የሚነግሠው ዳዊት መሆኑን መገንዘቧ እግዚአብሔር ለዳዊት የጸና መንግሥት ሊመሠርትለት ቃል መግባቱን ያመለክታል (ቍ28፤ ከ2ሳሙ 7፥11-16 ጋር ያነጻጽሩ):: (5) ሳኦል ዳዊትን ለመጕዳት ለሚያደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ እግዚአብሔር እንዴት ምላሽ ይሰጥ እንደ ነበር ለማሳየት ሳኦል የዳዊትን ሚስት ልጁን ሜልኮልን ለሌላ ሰው ሲሰጥበት፣ እግዚአብሔር ደግሞ አቢግያን የመሰለች ብልኅና ጠቃሚ ሚስት ለዳዊት ሰጠው::

25፥3 ***ከካሌብ ወገን፤*** የካሌብ ዘር (ዘኍ14፥24) እስራኤላውያን ከነዓንን ድል አድርገው ከወረሱ በኋላ በኬብሮን ርስት የተሰጠው ወገን ነው (ኢሱ14፥13):: የካሌብ ስም ትርጕም “ውሻ” ማለት እስከ ሆነ ድረስ ናባል “ጅል” እና “ውሻ” መሆኑ በዘዴ ተገልጦአል ፤ በዳዊት ላይ ለስነዘረውም ስድብ እግዚአብሔር ሲፈርድበት እርሱም ወዲያውኑ “የሞተ ውሻ” ይሆናል (2ሳሙ 9፥8 ማብ ይመ):: ሳኦል በዳዊት ላይ የፈጸመውን በደል እግዚአብሔር በሚበቀልበት ጊዜ (24፥12፡15)፣ ንጉሡ ከእንግዲህ ወዲያ የሞተ ውሻ እንደማይከታተል (24፥14) እና ይልቁንም እርሱ ራሱ ተናካሽ ውሻ እንደሚሆን እዚህ ላይ የተሰጠው ፍንጭ ጠንካራ ነው:: ስለዚህ ሳኦል፣ እንደ ሞተ ውሻ መቈጠሩና ናባልም ከካሌብ ወገን መሆኑ የስሙ ትርጓሜና የዳዊት አባባል አንድን እውነታ እንዲያሳይ አድርገዋል::

25፥4 ***በጎቹን እንደሚሸልት፤*** ከግብዣ ጋር የተያያዘ ነው (ቍ8፤ 2ሳሙ13፥23-24 ይመ)::

25፥8 ***የምትችለውን ያህል ስጥ፤*** የናባልን እረኞችና በጎች ከዘራፊዎች ስለ ጠበቁ (ቍ15-16፡21)፣ ዳዊትና ሰዎቹ የጠየቁት ክፍያ ተገቢ ነው::

ታውን እንዲያቀርቡለት ከምድረ በዳ ወደ
ጌታችን መልእክተኞች ልኮ ነበር፤ እርሱ
ግን የስድብ ናዳ አወረደባቸው:: 15እነዚህ
ሰዎች ግን እጅግ መልካም ነበሩ፤ ጉዳትም
አላደረሱብንም፤ በዱር አብረናቸው በነበር
ንበት ጊዜም ሁሉ፣ ምንም ነገር አልጠፋ
ብንም:: 16በጎቻችንን እየጠበቅን አብረናቸው
ባሳለፍነው ጊዜ ሁሉ፣ ቀንም ሆነ ሌሊት
በዙሪያችን ዐጥር ሆነውን ነበር:: 17አሁንም
በጌታችንና በመላው ቤተ ሰቡ ላይ መከራ
እያንዣበበ ስለሆነ፣ አስቢበትና የምታደርጊ
ውን አድርጊ፤ እርሱ እንደ ሆን እንዲህ ያለ
ባለጌ ሰው ስለሆነ፣ ደፍሮ የሚነግረው አን
ድም ሰው የለም::

18አቢግያም ጊዜ አላጠፋችም፤ ሁለት
መቶ እንጀራ፣ ሁለት አቁማዳ የወይን ጠጅ፣
አምስት የተሰናዱ በጎች፣ አምስት መስፈ
ሪያ የተጠበሰᵐ እሸት፣ መቶ የወይን ዘለላና
ዘቢብ፣ ሁለት መቶ ጥፍጥፍ የበለስ ፍሬ
ወስዳ በአህዮች ላይ ጫነች:: 19ከዚያም አገ
ልጋዮቿን፣ "ቀድማችሁኝ ሂዱ፤ እኔም እከ
ተላችኋለሁ" አለቻቸው፤ ለባሏ ለናባል ግን
አልነገረችውም::

20እርሷም በአህያዋ ላይ ተቀምጣ ወደ
ሸለቆው በምትወርድበት ጊዜ ዳዊትና ሰዎቹ
ወደ እርሷ ወረዱ፤ እርሷም አገኘቻቸው::
21ዳዊትም እንዲህ ብሎ ነበር፤ "ምንም ነገር
እንዳይጠፋበት የዚህን ሰው ሀብት በምድረ
በዳ ያን ያህል መጠበቁ ለካ በከንቱ ኖሮ
አል፤ ደግ በሠራሁ ይኸው ክፉ መለሰልኝ::
22ነገ ጠዋት የእርሱ ከሆነው ሁሉ አንድ
ወንድ እንኳ በሕይወት ባስቀር እግዚአብሔር
በዳዊት ላይᵚ እንዲህ ያለውን ነገር ያድር
ግበት፣ ከዚህም የከፋ ይጨምርበት!"

23አቢግያም ዳዊትን ባየች ጊዜ ወዲያው
ከአህያዋ ወርዳ፣ በዳዊትም ፊት በግምባርዋ
ተደፍታ እጅ ነሣች:: 24በእግሩም ላይ ወድቃ
እንዲህ አለች፤ "ጌታዬ ሆይ፤ በደሉ በእኔ ላይ
ብቻ ይሁን፤ እባክህ አገልጋይህ ታናግርህ፤
የምትልህንም ስማ:: 25ጌታዬ፣ ያን ባለጌ
ሰው ናባልን ከቁም ነገር አይቍጠረው፤ ስሙ
ራሱ ጅል ማለት ስለሆነ፣ ሰውየውም ልክ
እንደ ስሙ ነው፤ ጅልነትም አብሮት የኖረ
ነው:: እኔ አገልጋይህ ግን ጌታዬ የላካቸውን

25፥15 ቍ 7:21
25፥16 ዘፀ14፥22፤
ኢዮ1፥10፤
መዝ139፥5
25፥17 ዘዳ13፥13፤
1ሳሙ20፥7
25፥18 ዘፍ42፥26፤
ዘሌ23፥14፤
1ሳሙ 17፥17፤
2ሳሙ16፥1፤
1ዜና12፥40፤
ኢሳ 30፥6
25፥19 ቍ36፤
ዘፍ32፥20
25፥21 ቍ15፤
1ሳሙ19፥4፤
መዝ109፥5
25፥22 ሩት1፥17፤
1ነገ14፥10፤21፥21፤
2ነገ9፥8
25፥23 ዘፍ19፥1፤
1ሳሙ20፥41
25፥24 2ሳሙ14፥9
25፥25 ምሳ12፥16፤
14፥16፥17፥12፤20፥3፤
ኢሳ32፥5:34፤
2ሳሙ 18፥32፤
ዕብ10፥30
25፥27 ዘፍ33፥11
25፥28 ቍ24፤
1ሳሙ18፥17፤24፥11፤
2ሳሙ7፥11:ዕ26፤
14፥9
25፥29 1ሳሙ17፥50፤
20፥1፤2ሳሙ4፥8፤
ኤር10፥18፤22፥26
25፥30 1ሳሙ12፥12፤
13፥14
25፥31 ዘፍ40፥14፤
2ሳሙ3፥10
25፥32 ዘፍ24፥27
25፥33 ቍ26
25፥34 ቍ26
25፥35 ዘፍ19፥21

ጉልማሶች አላየኋቸውም::
26"ጌታዬ ሆይ፤ ሕያው *እግዚአብሔርን*!
በሕያው ነፍስህም እምላለሁ፤ ደም ከማፍሰ
ስና በገዛ እጅህ ከመበቀል የጠበቀህ *እግዚ
አብሔር* ነው፤ አሁንም ጠላቶችህና ጌታዬን
ሊጐዱ የሚፈልጉ ሁሉ እንደ ናባል ይሁኑ፤
27አገልጋይህም ለጌታዬ ያመጣችው ይህ ስጦታ
አንተን ለሚከተሉ ጉልማሶች ይሰጥ:: 28ጌታዬ
*የእግዚአብሔርን* ጦርነት ስለሚዋጋ *እግዚ
አብሔርም* ለጌታዬ ሥርወ መንግሥቱን
በእርግጥ ለዘላለም የሚያጸናለት በመሆኑ፣
እባክህ የእኔን የአገልጋይህን በደል ይቅር
በል፤ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ ክፋት
አይገኝብህ:: 29ማንም ሰው ሕይወትህን ለማ
ጥፋት ቢያሳድድህ እንኳ፣ የጌታዬ ሕይ
ወት በሕያዋን አንድነት እስራት ውስጥ
በአምላክህ *በእግዚአብሔር* ዘንድ በሰላም ትጠ
በቃለች፤ የጠላቶችህን ሕይወት ግን፣ እንደ
ወንጭፍ ድንጋይ ይወነጭፉል:: 30*እግዚአ
ብሔር* ለጌታዬ በሰጠው ተስፋ መሠረት በጎ
ውን ነገር ሁሉ ባደረገለትና በእስራኤልም
ላይ ባነገሠው ጊዜ፣ 31ጌታዬ የምታዝንበት
ምክንያት ወይም የኅሊና ጸጸት አይኖር
ህም፤ በከንቱ ያፈሰስኸውም ደም ሆነ በገዛ
እጅህ የተበቀልኸው የለምና:: *እግዚአብሔር*
በጎ ነገር ባደረገልህ ጊዜ እኔን አገልጋይህን
አስበኝ::"

32ዳዊትም አቢግያን እንዲህ አላት፤ "ዛሬ
እንድታገኚኝ ወደ እኔ የላከሽ፣ የእስራኤል
አምላክ *እግዚአብሔር* የተመሰገነ ይሁን:: 33ደም
እንዳላፈስና በገዛ እጄ እንዳልበቀል ዛሬ
ስለ ጠበቅሽኝ ስለ በጎ ሐሳብሽ አንቺም
የተባረክሽ ሁኚ:: 34ጉዳት እንዳላደርስብሽ
የጠበቀኝ የእስራኤል አምላክ ሕያው *እግዚ
አብሔርን*! እንዲህ በቶሎ መጥተሽ ባታገ
ኚኝ ኖሮ፣ እስኪነጋ ድረስ ለናባል አንድ
ወንድ እንኳ ባልተረፈ ነበር::"

35ከዚያም ዳዊት ያመጣችለትን ከእጇ
ተቀብሎ፣ "በሰላም ወደ ቤትሽ ሂጂ፤ እነሆ፤
ቃልሽን ሰምቻለሁ፤ የጠየቅሽኝንም ተቀብ
ያአለሁ" አላት::

ᵐ18 37 ሊትር ያህል ነው::
ᵚ22 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች ከዚህ ጋር ይስማ
ማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን *በዳዊት ጠላቶች ላይ* ይላል::

25፥17 *ባለጌ ሰው፤* የዘዳ 13፥13 ማብ ይመ:: *ደፍሮ የሚ
ነግረው አንድም ሰው የለም፤* በዚህ መልኩ ናባል ከሳኦል ጋር
ይመሳሰላል (ለምሳሌ ከ20፥29-33 ጋር ያነጻጽሩ)::

25፥19 *ለባሏ ለናባል ግን አልነገረችውም፤* ሜልኮል
ለአባቷ ለሳኦል ከመለሰችለት መልስ ጋር ያነጻጽሩ (19፥11-14)::

25፥22 *እግዚአብሔር በዳዊት ላይ እንዲህ ያለውን ነገር
ያድርግበት፤ ከዚህም የከፋ ይጨምርበት፤* የ3፥17 ማብ ይመ::
ዳዊት በናባል ቤት ያለውን ወንድ ሁሉ ቢገድልና የናባልን ቤተ
ሰብ ቢያጠፋ፣ የእግዚአብሔርን ርግማን በራሱ ላይ ያመጣል::

25፥25 *ባለጌ ሰው፤* የዘዳ 13፥13 ማብ ይመ:: *ሰውየውም
ልክ እንደ ስሙ ነው፤* በጥንት ጊዜ የሰው ስም ተፈጥሮንና ባሕ
ርይን ያንጸባርቃል ተብሎ ይታመን ነበር:: *ስሙ ራሱ "ጅል"
ማለት ስለ ሆነ፤* በዕብራይስጥ "ናባል" ማለት ጅል ማለት ነው::

25፥26 *ሕያው እግዚአብሔርን፤* የ14፥39 ማብ ይመ::

25፥28 *እግዚአብሔርም ለጌታዬ ሥርወ መንግሥቱን በእ
ርግጥ ለዘላለም የሚያጸናለት በመሆኑ፤* ዳዊት በሳኦል ፈንታ
እንደሚነግሥ በሕዝቡ ዘንድ የታወቀ ቢሆንም፣ አቢግያ የነበራት
ግንዛቤ በባልዋ ላይ ከታየው ጋር እጅግ የሚጻረር ነው (ቍ 10)::
*የእግዚአብሔርን ጦርነት ስለሚዋጋ፤* አቢግያ ዳዊት በፍልስጥኤ
ማውያን ላይ በተደጋጋሚ ያገኘውን ድል ታውቃለች፤ ከዚህም
በላይ የሚዋጋው ስለ ራሱ ክብር ሳይሆን፣ እግዚአብሔርን ለማስ
ከበር እንደ ሆነ ተረድታለች (17፥26:45-47፤18፥16-17):: *ክፋት
አይገኝብህ፤* አቢግያ ይህን የተናገረችው ዳዊት በኋላ በሚኖረው
ሥልጣን ክብሩንና ስሙን የሚያጐድፍ አንዳች ነገር እንዳይፈጸም
በማሰብ ነው (ቍ 30-31:39 ይመ)::

25፥29 *በሕያዋን አንድነት እሥራት ውስጥ ... ትጠበ
ቃለች፤* ውድ የሆነ ዕቃ በጥንቃቄ በተጠበቀ ስፍራ እንደ
ሚያዝ፣ አቢግያ እግዚአብሔር ዳዊትን በአደጋ ውስጥ እንደሚጠ
ብቀው ታስገነዝበዋለች::

25፥30 *ባነገሠው ጊዜ፤* የ9፥16 ማብ ይመ::

25፥31 *በከንቱ ያፈሰስኸውም ደም፤* የቍ 28 ማብ ይመ::

25፥32 *ወደ እኔ የላከሽ፤* ዳዊት ከአቢግያ ጋር የሚያደር
ገውን ንግግር እንደ እግዚአብሔር ትድግና ቈጥሮታል (ቍ39)::

36አቢግያም ወደ ናባል በተመለሰች ጊዜ፣
እነሆ፤ በቤቱ እንደ ንጉሥ ግብዣ ትልቅ
ግብዣ አድርጎ አገኘችው፤ ከፉኛም ሰክሮ
ልቡ በደስታ ተሞልቶ ነበር፡፡ ስለዚህ እስኪ
ነጋ ድረስ ምንም አልነገረችውም፡፡ 37ነግቶ
የወይን ጠጁ ስካር ካለፈለት በኋላ የሆነ
ውን ሁሉ ስትነግረው ልቡ ቀጥ አለ፤ ሰውነ
ቱም እንደ ድንጋይ በድን ሆነ። 38ዐሥር ቀን
ያህል ካለፈ በኋላ፣ *እግዚአብሔር* ናባልን
ቀሠፈው፤ እርሱም ሞተ፡፡

39ዳዊትም ናባል መሞቱን በሰማ ጊዜ፣
"የናባልን ስድብ የተበቀለልኝና እኔን አገ
ልጋዩን ክፉ ከማድረግ የጠበቀኝ *እግዚአ
ብሔር* ይመስገን፤ ናባል የሠራውንም ክፉ
ነገር በራሱ ላይ መለሰበት" አለ፡፡

ዳዊትም አቢግያ ሚስት ትሆነው ዘንድ
በመጠየቅ መልእክት ላከባት፡፡ 40አገልጋዮ
ቹም ወደ ቀርሜሎስ ሄደው አቢግያን፣
"ሚስት ትሆኚው ዘንድ እንድንወስድሽ ዳዊት
ወደ አንቺ ልኮናል" አሏት፡፡

41እርሷም ተነሥታ በግምባሯ በመደ
ፋት እጅ ከነሣች በኋላ፣ "እነሆ፤ እኔ ገረ
ድህ አንተን ለማገልገል፣ የጌታዬንም አገል
ጋዮች እግር ለማጠብ ዝግጁ ነኝ" አለች፡፡
42አቢግያም ወዲያውኑ በአህያ ላይ ተቀ
ምጣ አምስት አገልጋዮቿን በማስከተል፣
ከዳዊት መልእክተኞች ጋር ሄደች፤ ለዳዊትም
ሚስት ሆነችው፡፡ 43እንዲሁም ዳዊት ኢይዝ
ራኤላዊቷን አኪናሆምን አገባ፣ ሁለቱም ሚስ
ቶቹ ሆኑ፡፡ 44ሳኦል ግን የዳዊት ሚስት የነ
በረችውን ልጁን ሜልኮልን፣ ለጋሊም ተወ
ላጅ ለሌሳ ልጅ ለፈልጢ ሰጥቶ ነበር፡፡

## ዳዊት ለሁለተኛ ጊዜ ሳኦልን ከመግደል ታቀበ

26የዚፍ ሰዎች ሳኦል ወዳለበት ወደ
ጊብዓ መጥተው፣ "እነሆ፤ ዳዊት
በየሴሞን ትይዩ በሚገኘው በኤኬላ ኰረብታ
ተደብቆአል" ብለው ነገሩት፡፡

2ስለዚህ ሳኦል ተነሣ፤ ከእስራኤል የተመ
ረጡትን ሦስት ሺህ ሰዎችን ይዞ፣ ዳዊትን
ፍለጋ ወደ ዚፍ ምድረ በዳ ወረደ፡፡ 3ሳኦ
ልም በየሴሞን ትይዩ በሚገኘው በኤኬላ
ኰረብታ ላይ በመንገድ ዳር ሰፈረ፤ ዳዊት

25፥36 ቊ19፤ ሩት 3፥7፤ምሳ20፥1፤ መክ 10፥17፤ ኢሳ5፥11፡ 22፤22፥13፤28፥7፤ 56፥12፤ሆሴ4፥11
25፥37 ዘፀ15፥16
25፥38 ዘዳ32፥35፤ 1ሳሙ24፥12፤26፥10፤ 2ሳሙ 6፥7፤12፥15
25፥42 2ሳሙ2፥2፤ 3፥3፤1ዜና3፥1
25፥43 1ሳሙ27፥3፤ 30፥5፤2ሳሙ2፥2፤ 3፥2፤1ዜና3፥1
25፥44 2ሳሙ3፥15፤ ኢሳ10፥30
26፥1 1ሳሙ23፥19፡ 24፤መዝ54
26፥2 1ሳሙ24፥2
26፥3 1ሳሙ23፥19
26፥5 1ሳሙ17፥55
26፥6 ዘፍ10፥15፤ 2ሳሙ2፥18፤10፥10፤ 16፥9፤18፥2፤19፥21፤ 23፥18፤1ዜና2፥16፤ 11፥20፤19፥11
26፥9 ቊ16፤ ዘፍ 26፥11፤ 1ሳሙ9፥16፤ 24፥5፤ሳሙ1፥14፤ 19፥21፤ሰቆ4፥20
26፥10 ዘፍ16፥5፤ ዘዳ31፥14፤ 1ሳሙ 25፥38፤31፥6፤ 2ሳሙ 1፥1፤ መዝ37፥13፤ ሮሜ12፥19
26፥12 መሳ 4፥21

ግን በምድረ በዳ ነበር፡፡ ዳዊትም ሳኦል
እዚያ ድረስ እንደ ተከተለው ባወቀ ጊዜ፣
4ሰላዮች ልኮ በትክክል ሳኦል መምጣቱን
አረጋገጠ፡፡

5ዳዊትም ተነሥቶ ሳኦል ወደ ሰፈረበት
ቦታ ሄደ፤ ሳኦልና የሰራዊቱ አለቃ፣ የኔር
ልጅ አበኔር የተኙበትን ስፍራ አየ፡፡ ሳኦል
በሰፈሩ መካከል ተኝቶ ሳለ፣ ሰራዊቱ በዙ
ሪያው ሰፍሮ ነበር፡፡

6ዳዊትም ኬጢያዊውን አቢሜሌክንና
የጽሩያን ልጅ የኢዮአብን ወንድም አቢ
ሳን፣ "ወደ ሳኦል ሰፈር አብሮኝ የሚወርድ
ማነው?" ሲል ጠየቃቸው፡፡

አቢሳም፣ "እኔ አብሬህ እወርዳለሁ" አለ፡፡
7ስለዚህ ዳዊትና አቢሳ በሌሊት ሰራዊቱ
ወዳለበት ሄዱ፡፡ እነሆ፤ ሳኦል በሰፈሩ ውስጥ
ተኝቶ ጦሩም ራስጌው አጠገብ በመሬት
ላይ ተተክሎ ነበር፤ አበኔርና ወታደሮቹም
በዙሪያው ተኝተው ነበር፡፡

8አቢሳም ዳዊትን፣ "ዛሬ እግዚአብሔር ጠላ
ትህን በእጅህ ላይ ጥሎታል፤ አሁንም እኔ
አንድ ጊዜ በጦር ወግቼ ከመሬት ጋር ላጣ
ብቀው፤ መድገምም አያስፈልገኝም" አለው፡፡

9ዳዊት ግን አቢሳን እንዲህ አለው፤ "አት
ግደለው! *እግዚአብሔር* በቀባው ላይ እጁን
አንሥቶ ከበደል ነጻ የሚሆን ማን ነው? 10ሕያው
*እግዚአብሔርን* ! *እግዚአብሔር* ራሱ ይቀሥ
ፈዋል፤ ወይም ቀኑ ደርሶ ይሞታል፤ ወይም
በጦርነት ይሞታል፡፡ 11*እግዚአብሔር* በቀባው
ላይ እጄን ከማንሣት *እግዚአብሔር* ይጠ
ብቀኝ! ነገር ግን በራስጌው አጠገብ ያለውን
ጦርና የውሃ መያዣውን ያዝና እንሂድ፡፡"

12ስለዚህ ዳዊት በሳኦል ራስጌ አጠገብ
የነበረውን ጦርና የውሃውን መያዣ ወሰደ፤
ከዚያም ሄዱ፤ ይህን ያየም ሆነ ያወቀ
ወይም የነቃ ማንም አልነበረም፡፡ *ከእግዚ
አብሔር* ዘንድ ከባድ እንቅልፍ ስለ ወደ
ቀባቸው ሁሉም ተኝተው ነበርና፡፡

13ከዚህ በኋላ ዳዊት ወደ ማዶ ተሻግሮ
በኰረብታው ጫፍ ላይ ራቅ ብሎ ቆመ፤
በመካከላቸውም ሰፊ ርቀት ነበር፡፡ 14ዳዊት
ሰራዊቱንና የኔርን ልጅ አብኔርን፣ "አበኔር
ሆይ፣ አትመልስልኝምን?" ሲል ተጣራ፡፡

አበኔርም፣ "በንጉሡ ላይ የምትጮኽ አንተ

25፥37 *እንደ ድንጋይ በድን ሆነ፤* ምናልባት በመቅሠፍት ተመቶ ሊሆን ይችላል፡፡ የራሱ የሞራል ብልሹነት የማይሰማው ሰው ልክ እንደ ድንጋይ ስሜት የለሽ ነው፡፡

25፥43 *አኪናሆምን፤* የዳዊት የመጀመሪያ ሚስት (27፥3፡ 30፥5፤ 2ሳሙ2፥2)፣ የበኵር ልጁ የአምኖን (2ሳሙ 3፥2 ይመ) እናት ናት፡፡ *ኢይዝራኤላዊቷን፤* በቀርሜሎስ አጠገብ ያለ ስፍራ ሲሆን (ቊ2፤ ኢሱ15፥15)፣ በሰሜን ተመሳሳይ ስም ካለው፣ እስራኤላውያን ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሲዋጉ ከሰፈሩበትና (29፥1፡11) በኋለኛውም ዘመን አክዓብ ከኖረበት ስፍራ (1ነገ18፥45-46) ጋር አንድ አይደለም፡፡

25፥44 *የዳዊት ሚስት ... ሜልኮልን፤* 18፥27 ይመ፡፡

26፥1 *የዚፍ ሰዎች፤* የ23፥14፡19 ማብ ይመ፡፡ *ጊብዓ፤* ሳኦል የሚኖርበት አገር ነው (10፥26 ይመ)፡፡

26፥2 *ሦስት ሺህ፤* የሳኦል መደበኛ ሰራዊት (24፥2 ይመ)፡፡

26፥5 *የተኙበትን ስፍራ፤* ሰዎቹ ሁሉ ተኝተው ሳለ ዳዊት በሌሊት ወደ ሳኦል ሰፈር መጣ፡፡ *አበኔር፤* የሳኦል ያጎቱ ልጅ ነው (14፥50 ይመ)፡፡

26፥6 *ኬጢያዊውን አቢሜሌክንና፤* በሌላ ስፍራ አልተጠቀሰም፡፡ ኬጢያውያን ጥንት በከነዓን ይኖሩ ነበር (የዘፍ10፥15 ማብ ይመ፤ ዘፍ15፥20፤ 23፡3-20፤ ዘዳ7፥1፤ 20፥17 ይመ)፡፡ ዳዊትን ሲያገለግል የነበረ ሌላው ኬጢያዊ ኦርዮ ነበር (2ሳሙ11፥3፤ 23፥39 ይመ)፡፡ *የጽሩያን ልጅ የኢዮአብን ወንድም አቢሳን፤* ጽሩያ የዳዊት ታላቅ እኅት ስትሆን (1ዜና 2፥16)፣ አቢሳና ኢዮአብ እንዲሁም ወንድማቸው አሣሄል (2ሳሙ 2፥18) የዳዊት የእኅቱ ልጆች ከመሆናቸውም በላይ የታመኑ የሰራዊቱ አለቆች ነበሩ፡፡ ኢዮአብ ለረዥም ጊዜ የዳዊት ሰራዊት ዋና አዛዥ ነው፡፡

*26፥9፤* የ24፥6 ማብ ይመ፡፡

26፥10 *ሕያው እግዚአብሔርን፤* የ14፥39 ማብ ይመ፡፡

26፥12 *ዳዊት ... ጦርና የውሃውን መያዣ ወሰደ፤* ዳዊት አሁንም ሳኦልን የመግደል ፍላጎት እንደሌለው ይታያል፡፡

ማነህ?” በማለት መለሰ።
15ዳዊትም እንዲህ አለ፤ “አንተ ብርቱ
ሰው ነህ? በእስራኤልስ ዘንድ አንተን
የሚመስል ማን ነው? እነሆ፤ አንድ ሰው
ንጉሡን ጌታህን ለመግደል መጥቶ ነበር፤
ታዲያ አንተ ንጉሥ ጌታህን ያልጠበቅኸው
ስለ ምንድን ነው? 16ያደረግኸው መልካም
አይደለም፤ ሕያው እግዚአብሔርን! አንተና
ሰዎችህ ሞት ይገባችኋል፤ እግዚአብሔር
የቀባውን ጌታችሁን አልጠበቃችሁምና።
እስቲ ተመልከት፤ በራስጌው የነበሩት የንጉ
ሡ ጦርና የውሃ መያዣ የት አሉ?”
17ሳኦል የዳዊትን ድምፅ ለይቶ ስላወቀ፣
“ልጄ ዳዊት ሆይ፤ ይህ ድምፅህ ነውን?”
አለው። ዳዊትም፣ “ንጉሥ ጌታዬ ሆይ፤ አዎን
ድምፄ ነው” ሲል መለሰ፤ 18በመቀጠልም፣
“ጌታዬ አገልጋዩን የሚያሳድደው ስለምን
ድን ነው? ምን አደረግሁ? ምን በደልስ
ፈጸምሁ? 19አሁንም ንጉሥ ጌታዬ የባሪያ
ውን ቃል ያድምጥ፤ እግዚአብሔር በእኔ ላይ
አነሣሥቶህ እንደ ሆነ፣ ቍርባን ይቀበል፤
ነገር ግን ይህን ያደረጉት ሰዎች ከሆኑ፣ በእ
ግዚአብሔር ፊት የተረገሙ ይሁኑ፤ ‘ሂድ
ሌሎችን አማልክት አምልክ’ ብለው በእግ
ዚአብሔር ርስት ድርሻ እንዳይኖረኝ ዛሬ
አሳደውኛልና። 20አንድ ሰው በተራራ ላይ
ቆቅ እንደሚያድን የእስራኤልም ንጉሥ ቍንጫ
ለመፈለግ ስለ ወጣ፣ ደሜ ከእግዚአብሔር
ፊት ርቆ በምድር ላይ እንዲፈስ አታድ
ርግ።”
21ሳኦልም፣ “በድያለሁ፤ ልጄ ዳዊት ሆይ፤
ተመለስ፤ ዛሬ ነፍሴ በፊትህ ስለ ከበረች፣
ከእንግዲህ ወዲያ አልጐዳህም፤ በእርግጥ
የሞኝ ሥራ ሠርቻለሁ፤ እጅግ ሲበዛም
ተሳስቻለሁ” አለ።
22ዳዊትም እንዲህ ሲል መለሰ፤ “የንጉሥ
ጦር እነሆ፤ ከወጣቶችህ አንዱ መጥቶ

26፥17 1ሳሙ 24፥16
26፥18 ኢዮ13፥23፤ ኤር37፥18
26፥19 ዘዳ4፥28፤ 11፥28፤20፥16፤ 32፥9፤1ሳሙ 24፥9፤ 2ሳሙ 14፥16፤16፥11፤ 20፥9፤21፥3
26፥20 1ሳሙ 24፥11፡ 14፤ኤር4፥29፤ 16፥16፤አሞ 9፥3
26፥21 ዘፀ9፥27፤ መዝ72፥14
26፥23 ዘፍ16፥5፤ ሩት2፥12፤ 1ሳሙ 24፥18፤ 2ሳሙ 22፥21፡ 25፤መዝ7፥8፤ 18፥20፡24፤62፥12
26፥24 መዝ54፥7
26፥25 ሩት2፥12
27፥2 1ሳሙ 21፥10፤ 30፥9፤2ሳሙ 2፥3፤ 1ነገ2፥39
27፥3 1ሳሙ 25፥43

ይውሰዳት። 23እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው
እንደ ጽድቁና እንደ ታማኝነቱ ይከፈለው።
እኔ ግን ዛሬ እግዚአብሔር አንተን በእጄ
አሳልፎ ሰጥቶኝ ሳለ እግዚአብሔር በቀባው
ላይ እጄን አላነሣሁም። 24እነሆ፤ ዛሬ ሕይ
ወትህ በፊቴ እንደ ከበረች ሁሉ፣ የእኔም
ሕይወት በእግዚአብሔር ዘንድ የከበረች
ትሁን፤ ከመከራም ሁሉ ያድነኝ።”
25ከዚያም ሳኦል ዳዊትን፣ “ልጄ ዳዊት
ሆይ፤ የተባረክህ ሁን፤ ታላቅ ነገር ታደር
ጋለህ፤ በእርግጥም ይከናወንልሃል” አለው።
ስለዚህም ዳዊት ወደሚሄድበት ሄደ፤
ሳኦልም ወደ ቤቱ ተመለሰ።

## ዳዊት በፍልስጥኤማውያን መካከል መኖሩ

27 ዳዊት ግን በልቡ፣ “ከእነዚህ ቀናት
በአንዱ በሳኦል እጅ መገደሌ ስለ
ማይቀር፣ የሚበጀኝ ወደ ፍልስጥኤማውያን
ምድር መሸሽ ብቻ ነው፤ ከዚያ በኋላም ሳኦል
በእስራኤል ሁሉ እኔን ማሳደዱን ይተዋል፤
እኔም ከእጁ አመልጣለሁ” ብሎ አሰበ።
2ስለዚህ ዳዊትና አብረውት ያሉት ስድ
ስት መቶ ሰዎች ተነሥተው የጌት ንጉሥ
ወደ ሆነው ወደ አሜህ ልጅ ወደ አንኩስ ሄዱ።
3ዳዊትና ሰዎቹ በጌት በአንኩስ ዘንድ
ተቀመጡ፤ እያንዳንዱ ሰው ከቤተሰቡ ጋር
ነበረ፤ ዳዊትም ከሁለቱ ሚስቶቹ ጋር፣
ከኢይዝራኤላዊቷ ከአኪናሆምና የናባል
ሚስት ከነበረችው ከቀርሜሎሳዊቷ አቢግያ
ጋር ነበር። 4ሳኦልም፣ ዳዊት ወደ ጌት
እንደ ሸሸ በሰማ ጊዜ፣ እርሱን ማሳደዱን
ተወ።
5ከዚያም ዳዊት አንኩስን፣ “በፊትህ ሞገስ
አግኝቼ እንደሆነ፣ በአገሪቱ ካሉት ከተሞች
በአንዲቱ እኖር ዘንድ ስፍራ ይሰጠኝ፤ ስለ
ምን አገልጋይህ ካንተ ጋር በንጉሥ ከተማ
ይቀመጣል?” አለው።

26፥19 ***ቍርባን ይቀበል፤*** ዳዊት እግዚአብሔር ይቈጣኛል ብሎ የሚያሠጋበት ምክንያት የለም፤ ይሁን እንጂ ሳኦል እርሱን ለመግደል ሲያሳድደው ከእግዚአብሔር ተቀባይነትን አግኝቶ እንደ ሆነ ማረጋገጫ ፈለገ (ከ16፥5 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለዚህ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን እግዚአብሔር በእርሱና በሳኦል መካከል ገብቶ ፍርዱን እንዲሰጠው ጠየቀ። ***በእግዚአብሔር ፊት የተረገሙ ይሁኑ፤*** በእርሱና በሳኦል መካከል ጣልቃ ገብተው እንዲጋደሉ የሚያደርጓቸው ሰዎች ካሉ ዳዊት ለእግዚአብሔር ፍርድ አሳልፎ ይሰጣቸዋል። ***በእግዚአብሔር ርስት፤*** የ10፥1 ማብ ይመ። በእግዚአብሔር ምድር በሰላም እንዳይኖርና ከሕዝቡም ጋር ግንኙነት እንዳያደርግ የተከለከለ መሆኑን ሳኦል እንዲገነዘብለት ዳዊት አጥብቆ ያሳስበዋል። ***ሂድ፤ ሌሎችን አማልክት አምልክ፤*** በዚያ ዘመን በነበረው አስተሳሰብ ከእግዚአብሔር ርስት መባረር፣ ከመቅደሱ እንደ መባረር የሚቈጠርና በሚሄድበት አገር ላሉት አማልክት መገዛትን የሚያመለክት ነበር (ኢሱ 22፥24-27 ይመ)።

26፥20 ***ቍንጫ ለመፈለግ፤*** 24፥14 ይመ። በደል የሌለበትንና በንጉሥ ላይ የዐመፅ ዕቅድ የሌለውን ሰው በማሳደድ ሳኦል ራሱን የሚያሞኝ መሆኑን ዳዊት ያሳስበዋል።

26፥21 ***በድያለሁ፤*** 24፥17 ይመ። ***የሞኝ ሥራ ሠርቻለሁ፤*** ሳኦል ጠባዩ ጥበብ የጐደለው ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር የማይወደውን ሥራ መሥራቱን ተናዘዘ (የ13፥13፤ 25፥2-44 ማብ ይመ)።

26፥23 ***እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጄን አላነሣሁም፤*** ቍ9 እና የ24፥6 ማብ ይመ ።

26፥25 ***ይከናወንልሃል፤*** ሳኦል የሚተካው ሰው ዳዊት መሆኑን በደፈናው ይናገራል (24፥20 ይመ)።

27፥1 ***በሳኦል እጅ መገደሌ ስለማይቀር፤*** ዳዊት ይህን ሲል መፍራቱንና እምነት ማጣቱን ያሳያል (23፥14፤25፥29 ይመ)፤ ከዚህም በላይ ሳኦል ከነበረው ከፍተኛ የጦር ኀይል የተነሣ ከእስራኤል አገር ውጪ የሆነ መሸሸጊያ ለመፈለግ ተገደደ። ***ወደ ፍልስጥኤማውያን ምድር፤*** ዳዊት ለሁለተኛ ጊዜ በፍልስጥኤም ምድር መሸሸግ ፈለገ (21፥10-15 ይመ)።

27፥2 ***የጌት ንጉሥ ወደ ... አንኩስ፤*** 21፥10 ይመ። ዳዊት ከዚህ ቀደም ወደ ፍልስጥኤም ምድር ሄዶ ከነበረበት ጊዜ ይልቅ፣ ሳኦል የዳዊት ጠላት መሆኑን የጌት ንጉሥ፣ ስለተረዳ ሊቀበለው ዝግጁ ነበር። ከዚህም በላይ ዳዊትና ሰዎቹ በጥገኝነት ካሉበት ሁኔታ የተነሣ፣ ማንኛውም የጦርነት ጥሪ ቢደርሳቸው፤ የጌትን ንጉሥ የመርዳት ግዴታ ነበረባቸው (28፥1 ይመ)።

27፥3 ***ከአኪናሆምና፤*** የ25፥43 ማብ ይመ። ***አቢግያ፤*** 25፥39-42 ይመ።

27፥4 ***እርሱን ማሳደዱን ተወ፤*** ሳኦል ወደ ፍልስጥኤም ምድር ገብቶ ዳዊትን ለመከታተልና ለመያዝ በቂ ወታደራዊ ኀይል አልነበረውም፤ ዳዊትም ከአገር ውጪ ስለሚገኝ ከዚያ ወዲያ ዙፋኑን በቅርብ ሊቀናቀን የሚችል ሰው አይኖርም።

27፥5 ***በአገሪቱ ካሉት ከተሞች በአንዲቱ፤*** እንደ ልቡ ለመንቀሳቀስ ነጻነት ይኖረው ዘንድ ዳዊት ከጌት ንጉሥ ፊት ዘወር ለማለት ፈለገ። ***ስለ ምን አገልጋይህ ካንተ ጋር በመናገሻ ከተማ ይቀመጣል?*** ዳዊት ይህ ክብር የማይገባው ሰው መሆኑን ገለጸ።

6ስለዚህ በዚያ ዕለት አንኩስ ጺቅላግን
ሰጠው፤ ጺቅላግም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የይ
ሁዳ ነገሥታት ይዞታ ሆነች። 7ዳዊት በፍ
ልስጥኤማውያን ምድር አንድ ዓመት ከአ
ራት ወር ተቀመጠ።
8በዚያ ጊዜም ዳዊትና ሰዎቹ ወጥተው
ጌሹራውያንን፣ ጌርዛውያንንና አማሌቃው
ያንን ወረሩ። እነዚህ ሕዝቦች ከጥንት
ጀምሮ፣ እስከ ሱርና እስከ ግብፅ ባለው
ምድር ላይ ይኖሩ ነበር። 9ዳዊትም ምድሪ
ቱን በመታበት ጊዜ፣ ወንድም ሆነ ሴት
በሕይወት አላስቀረም፤ ነገር ግን በጎችንና
ላሞችን፣ አህዮችንና ግመሎችን እንዲሁም
ልብሶችን ወሰደ፤ ወደ አንኩስም ተመለሰ።
10አንኩስም፣ "ዛሬ በማን ላይ ዘመታችሁ?"
ሲል በጠየቀው ጊዜ ዳዊት፣ "የዘመትነው
በይሁዳ ደቡብ፣ ወይም በይረሕምኤላውያን
ደቡብ፣ ወይም በቄናውያን ደቡብ ላይ
ነው" በማለት ይመልስ ነበር።" 11ዳዊት
"'እርሱ እንዲህ አድርጎአል' ብለው ይነግሩ
ብናል" ብሎ ስላሰበ፣ ወንድም ሆነ ሴት
በሕይወት አስቀርቶ ወደ ጌት አላመጣም።
በፍልስጥኤም ግዛት በኖረበት ዘመን ሁሉ፣
እንዲህ ማድረጉ የተለመደ ነበር።
12አንኩስም በልቡ፣ "እርሱ ራሱ የገዛ ሕዝቡ
የሆኑት እስራኤላውያን እጅግ እንዲጠሉት
ስላደረገ፣ ለዘላለም አገልጋዬ ይሆናል" ብሎ
ስላሰበ ዳዊትን አመነው።

## ሳኦልና የዓይንዶር ነዋሪዋ ሙታን ጠሪ

28በዚያን ዘመን ፍልስጥኤማውያን፣
እስራኤልን ለመውጋት ሰራዊታቸውን
ሰበሰቡ። አንኩስም ዳዊትን፣ "አንተና ሰዎችህ
አብራችሁኝ ለጦርነት መውጣት እንዳለባችሁ
ዕውቅ" አለው።
2ዳዊትም፣ "አገልጋይህ ምን እንደ ሚያ
ደርግ ያን ጊዜ አንተው ራስህ ታያለህ"
አለው።
አንኩስም፣ "መልካም፤ በዘመኔ ሁሉ የራሴ
የክብር ዘብ አደርግሃለሁ" ሲል መለሰለት።

27፥6 ኢሱ15፥31፤ 19፥5፤1ሳሙ30፥1፤ 1ዜና12፥20፤ ነሀ11፥28
27፥7 1ሳሙ29፥3
27፥8 ዘፍ16፥7 ዘፀ17፥14፤ኢሱ12፥5፤ 1ሳሙ14፥48፤30፥1፤ 2ሳሙ1፥8፤8፥12
27፥9 1ሳሙ15፥3
27፥10 መሳ1፥16፤ 1ሳሙ30፥29
27፥12 ዘፍ34፥30፤ 1ሳሙ29፥6
28፥1 1ሳሙ29፥1
28፥2 1ሳሙ29፥2

27፥6 *ጺቅላግም፤* ትክክለኛው ቦታ የት እንደ ሆነ አይታ ወቅም፤ ይሁን እንጂ በደባባዊ ይሁዳ ከሚገኙ ከተሞች እንደ አንዷ ተጠቅሳለች (ኢሱ 15፥31 ይመ)። ለስምዖን ነገድ ተሰጥታ ስለ ነበር (ኢሱ19፥1-5 ይመ)፣ እነርሱም ሳይኖሩባት እንዳልቀረ ይገመታል (ኢሱ 1-17-18)፤ በኋላ ግን ጊዜው በውል ተለይቶ በ ማይታወቅበት ወቅት ፍልስጥኤማውያን የስምዖን ነገድ አስለቅ ቀዋቸዋል። *የይሁዳ ነገሥታት ይዞታ ሆነች፤* የንጉሣዊ ይዞታ እንደ ነበረች መጠቀሷ፤ መጽሐፈ ሳሙኤል የተጻፈው እስራኤል የደቡብና የሰሜን መንግሥት ተብሎ ከተከፈለ በኋላ መሆኑን ያመለክታል፤ ይህም መጽሐፈ ሳሙኤል መቼ እንደ ተጻፈ ከሚጠቆሙ ክፍሎች ውስጥ ዋነኛው ነው።

27፥7 *ዳዊት በፍልስጥኤማውያን ምድር አንድ ዓመት ከአራት ወር ተቀመጠ፤* ዳዊት መኖሪያውን ከጺቅላግ ወደ ኬብሮን ያዛ ወረው ሳኦል ከሞተ በኋላ ነበር (2ሳሙ1፥1፤ 2፥13 ይመ)።

27፥8 *ጌሹራውያንን፤* እስራኤላውያን ከነዓንን ድል ባደረጉ ጊዜ ሳይሸነፉ የቀሩ ከፍልስጥኤም በስተ ደቡብ የሚኖሩ ሕዝቦች ናቸው (ኢሱ13፥1-3 ይመ)፤ እነዚህ በአራም ምድር በላይኛው ዮርዳኖስ (2ሳሙ3፥3፤ 13፥37-38፤ ዘዳ3፥14፤ ኢሱ12፥5 ይመ) አጠገብ ባለው በሰሜን ክፍል ከሚኖሩት ጌሹራውያን የተለዩ ናቸው። *ጌርዛውያንንና፤* በብሉይ ኪዳን በሌላ ቦታ አልተጠ ቀሱም። *አማሌቃውያንን፤* የ15፥3 ማብ ይመ። *ሱር፤* የ15፥7 ማብ ይመ።


27፥9 *ወንድም ሆነ ሴት በሕይወት አላስቀረም፤* ዳዊት ይህን ለምን እንዳደረገ በቊ 11 ላይ ተገልጾአል፤ ድርጊቱ ኢያሱ ከነዓንን ድል ባደረገ ጊዜ (ኢሱ6፥21 እና የኢሱ6፥17 ማብ ይመ) ከፈጸመው ጋር ይመሳሰላል።

27፥10 *በይሁዳ ደቡብ፤* ዕብራይስጡ "ኔጌብ" ይለዋል ትርጓሜውም "ደረቅ" ማለት ነው፤ ይህም ከቤርሳቤህ እስከ ሲና ልሳነ ምድር ኰረብታዎች ድረስ ያለውን ሰፊውን ደቡባዊ የፍልስጥኤም ምድር ያመለክታል። *በይረሕምኤላውያን፤* ይረሕ ምኤላውያን በኤስሮን በኩል የይሁዳ ዘሮች ናቸው (1ዜና 2፥9፡25 ይመ)። *በቄናውያን፤* የ15፥6 ማብ ይመ።

27፥12 *አንኩስም ... ዳዊትን አመነው፤* ዳዊትና ሰዎቹ በእስራኤል ድንበር ላይ ያሉትን ጌሹራውያንን፣ ጌርዛውያንንና፣ አማሌቃውያንን መውረራቸውን ሲያረጋግጥ፣ አንኩስ ዳዊትን ለማ መን በቃ (ቊ 8)።

28፥1 *ለጦርነት መውጣት ... ዕወቅ፤* በጥንታዊው የመካከ ለኛ ምሥራቅ ታሪክ፣ አንድ ሰው በአንድ አገር የፖለቲካ ጥገኛ ከሆነ፣ ጥገኝነት ለሰጠው መንግሥት ወታደራዊ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ነበረበት (የ27፥2 ማብ ይመ)።

28፥2 *አገልጋይህ ምን እንደሚያደርግ ያን ጊዜ አንተው ራስህ ታያለህ፤* ምናልባት መልሱ አሻሚ ሊሆን ይችላል። *የራሴ የክብር ዘብ አደርግሃለሁ፤* ይህ ድርጊት አብዛኛውን ጊዜ ዳዊት ለዘመቻ በተንቀሳቀሰበት ጊዜ በሚያሳየው ታማኝነትና ውጤታማነት ላይ የተመሠረተ ነበር።



3በዚህ ጊዜ ሳሙኤል ሞቶ ነበር፤ እስራ
ኤላውያንም ሁሉ በገዛ ከተማው በአር
ማቴም አልቅሰው ቀበሩት:: ሳኦል ሙታን
ሳቢዎችንና መናፍስት ጠሪዎችን ከምድሪቱ
አባሮአቸው ነበር::
4ፍልስኤማውያን ተሰብስበው በመምጣት
በሱነም ሲሰፍሩ፣ ሳኦል ደግሞ እስራኤላው
ያንን ሁሉ ሰብስቦ በጊልቦዓ ተራራ ላይ ሰፈረ::
5ሳኦል የፍልስጥኤማውያንን ሰራዊት ባየ ጊዜ
ፈራ፤ ልቡም እጅግ ተሸበረ:: 6እርሱም
*እግዚአብሔርን* ጠየቀ፤ *እግዚአብሔር* ግን
በሕልምም ሆነ በኡሪም ወይም በነቢያት
አልመለሰለትም:: 7ሳኦልም አገልጋዮቹን፣
"እስቲ ሙታን ሳቢ ሴት ፈልጉልኝና ሄጄ
ልጠይቃት" አላቸው::
እነርሱም፣ "እነሆ፤ ሙታን የምትስብ ሴት
በዓይንዶር አለች" አሉት::
8ስለዚህ ሳኦል ሌላ ልብስ በመልበስ መል
ኩን ለውጦ ከሁለት ሰዎች ጋር በሌሊት
ወደ ሴቲቱ ሄደ:: እርሱም፣ "እባክሽ፣
መናፍስትን ጠይቂልኝ፤ የምነግርሽንም ሰው
አስነሺልኝ" አላት::
9ሴትዮዋ ግን፣ "እነሆ፤ ሳኦል ሙታን ሳቢ
ዎችንና መናፍስት ጠሪዎችን ከምድሪቱ እን
ዴት እንዳጠፋና ያደረገባቸውን ታውቃለህ፤
ታዲያ፣ ታስገድለኝ ዘንድ በሕይወቴ ላይ
ወጥመድ የዘረጋኸው ለምንድን ነው?" አለ
ችው::
10ሳኦልም፣ "ሕያው *እግዚአብሔርን!* በዚህ
ነገር ቅጣት አያገኝሽም" ሲል *በእግዚአብሔር*
ስም ማለላት::
11ሴትዮዋም፣ "ማንን ላስነሣልህ?" ብላ
ጠየቀችው::

28፥3 ቍ9፤ ዘዐ22፥18፤1ሳሙ 7፥17፤25፥1
28፥4 ኢሱ19፥18፤ 1ሳሙ31፥1:3፤ 2ሳሙ1፥6:21፥12
28፥5 ዘፀ19፥16
28፥6 ዘፀ28፥30፤ ዘሌ8፥8፤ዘዳ13፥3፤ 1ሳሙ8፥18፤14፥37፤ ሕዝ20፥3፤ አሞ 8፥11፤ ሚክ 3፥7
28፥7 ኢሱ17፥11፤ 1ዜና10፥13፤ መዝ 83፥10፤ ሐሥ16፥16
28፥8 2ዜና18፥29፤ 35፥22፤1ነገ22፥30፤ 2ነገ1፥3፤ኢሳ8፥19
28፥9 ቍ3፤ ኢዮ 18፥10፤ መዝ31፥4፤ 69፥22፤ኢሳ8፥14
28፥12 ዘፍ27፥36፤ 1ነገ14፥6
28፥13 ቍ15፤ ዘሌ 19፥31፤ 2ዜና33፥6
28፥14 1ሳሙ15፥27
28፥15 ዘዳ13፥3፤ መሳ16፥20፤ 1ሳሙ14፥37
28፥17 1ሳሙ15፥28
28፥18 ዘፍ14፥7፤ ዘዳ9፥8፤1ሳሙ14፥48፤ 15፥3:20
28፥19 1ሳሙ31፥2፤ 1ዜና8፥33

እርሱም፣ "ሳሙኤልን አስነሺልኝ" አላት::
12ሴትዮዋም ሳሙኤልን ባየችው ጊዜ በታላቅ
ድምፅ ጮኸች፤ ሳኦልንም፣ "አንተ ሳኦል ሆነህ
ሳለ፣ ለምን አታለልኸኝ?" አለችው::
13ንጉሡም፣ "አትፍሪ፤ ለመሆኑ ምን እያ
የሽ ነው?" አላት::
ሴትዮዋም፣ "አንድ መንፈስ[a] ከምድር
ሲወጣ አያለሁ" አለችው::
14እርሱም፣ "መልኩ ምን ይመስላል?"
ሲል ጠየቃት:: እርሷም፣ "ካባ የለበሰ አንድ
ሽማግሌ ሰው እየወጣ ነው" አለችው::
ሳኦልም ሴትዮዋ ያየችው ሳሙኤል መሆ
ኑን ዐወቀ፤ በመሬትም ላይ ተደፍቶ እጅ
ነሣ::
15ሳሙኤልም ሳኦልን፣ "አስነሥተህ
የምታውከኝ ለምንድነው?" አለው
ሳኦልም፣ "እጅግ ተጨንቄአለሁ፤ ፍልስ
ጥኤማውያን እየወጉኝ ነው፤ እግዚአብሔርም
ከእኔ ርቆአል፤ በነቢያትም ሆነ በሕልም
አልመለሰልኝም፤ ስለዚህ ምን ማድረግ እን
ደሚገባኝ እንድትነግረኝ ጠራሁህ" አለው::
16ሳሙኤልም እንዲህ አለ፤ "ታዲያ *እግዚ
አብሔር* ከራቀህ፣ ጠላትም ከሆነህ ለምን
ትጠይቀኛለህ? 17*እግዚአብሔር* በእኔ የተና
ገረውን አድርጎአል፤ *እግዚአብሔር* መንግ
ሥትህን ከእጅህ ነጥቆ ለጐረቤትህ ለዳዊት
ሰጥቶታል። 18*ለእግዚአብሔር* ስላልታዘዝህ፣ ታላቅ
ቍጣውንም በአማሌቃውያን ላይ ስላልፈ
ጸምህ *እግዚአብሔር* ዛሬ ይህን አድርጎብ
ሃል:: 19*እግዚአብሔር* አንተንና እስራኤልን

[a]13 *ወይም መናፍስት ወይም አማልክት*

28፥3 *በዚህ ጊዜ ሳሙኤል ሞቶ ነበር፤* 25፥1 ይመ:: በዚያ በጭንቅ ጊዜ እንኳ ሳኦል ወደ እርሱ መምጣት አልቻለም:: *ሙታን ሳቢዎችንና መናፍስት ጠሪዎችን፤* ዘሌ19፥31፤ 20፥6:27፤ ዘዐ 18፥11 ይመ:: *ከምድሪቱ አባርአቸው ነበር፤* ተገድለው ነበር የሚለውን አገላለጥ ከሙሴ ሕግ ጋር በሚስማማ መልኩ በማለዘብ የቀረበ ሊሆን ይችላል (ቍ 9፥21 ይመ)::

28፥4 *ሱነም፤* ፍልስጥኤማውያን በይሳኮር ምድር (ኢሱ 19፥18 ይመ) በኢይዝራኤል ሜዳ ሰራዊታቸውን በስተ ሰሜን በኩል ያሰፈሩበት ቦታ ነው:: *በጊልቦአ፤* ከኢይዝራኤል ሜዳ በስተ ምሥራቅ የሚገኝ የተራራ ሰንሰለት ነው::

28፥5 *ልቡም እጅግ ተሸበረ፤* ከእግዚአብሔር ስለ ራቀና እንደ እውነተኛ ንጉሥም ማድረግ የሚገባውን ስላላደረገ ልቡ በፍርሀት ተሞልቶአል (የ17፥11 ማብ ይመ)::

28፥6 *እርሱም እግዚአብሔርን ጠየቀ፤* መቼም ሳኦል ይህን ያደረገው በካህን በኩል ሳይሆን አይቀርም፤ እንደዚህ ያደረገው የሚመጣው ጦርነት እጅግ ስላስፈራው ውጤቱን ማወቅ እንዲችል የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመጠየቅ ነበር:: *በሕልምም፤* በቀጥታ ለግለሰቡ የሚገለጥ መልእክት ነው (ዘኍ12፥6 እና ማብ ይመ):: *በኡሪም፤* በካህን በኩል የሚሰጥ መገለጥ ነው (የ2፥28 ማብ ይመ):: ትክክለኛው ኤፉድ ከነኡሪሙ ሳኦልን ከድቶ ከዳዊት ጋር ከተባበረው ከካህኑ አብያታር (23፥2:6:9) ዘንድ ይገኛል፤ ምናልባት በዚህ ስፍራ ላይ የተገለጸው ኡሪም ሳኦል በግሉ ባሠራው ኤፉድ ላይ የነበረ ሊሆን ይችላል፤ ወይም ደግሞ የመጽሐፉ ፀሓፊ ሐሳቡን ግልጥ ለማድረግ ሦስቱን የመገለጥ መንገዶች ጨምሮ አንድ አስማሚ ዐረፍተ ነገር ተጠቅሞአል ማለት ነው:: *በነቢያት፤* ዳዊት ነቢይ ነበረው (ነቢዩ ጋድ 22፣5)፤ ይሁን እንጂ ሳሙኤል ከተለየው በኋላ (15፥35)፣ ሳኦልን ያገለገለ ሌላ ነቢይ አልነበረም::

28፥7 *እስቲ ሙታን ሳቢ ሴት ፈልጉልኝና፤* ሳኦል ቀድሞ በሙሴ ሕግ መሠረት ሲያወግዘው (ቍ 3፤ ዘሌ 19፥26 ይመ)፣ እንዳልነበር ሁሉ ዛሬ ጭንቅ ሲይዘው ወደ ጣዖት አምልኮ ፊቱን አዞረ:: *በዓይንዶር፤* ከሱነም በስተ ሰሜን ምዕራብ ዐሥር ኪሎ ሜትር ያህል ትርቃለች (ቍ 4፤ ኢሱ17፥11 ይመ)::

28፥9 *በሕይወቴ ላይ ወጥመድ የዘረጋኸው ለምንድን ነው?* ሴትዮዋ እንዳትጋለጥ ሥራዋን የምታከናውነው ለሳኦል አሳልፈው እንዳይሰጧት በጥንቃቄ መሆኑን ያሳያል (የቍ 3 ማብ ይመ)::

28፥10 *ሕያው እግዚአብሔርን!* የ14፥39ን ማብ ይመ::

28፥12 *ሴትዮዋ ሳሙኤልን ባየችው ጊዜ፤* ትእይንቱ በተለያየ መንገድ ግንዛቤ አግኝቶአል፤ ከግንዛቤዎችም መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፤ (1) የሳሙኤል መንፈስ ለሴትዮዋ እንዲገለጥ እግዚአብሔር ፈቅዶ ይሆናል:: (2) ሴትዮዋ ከክፉ ወይም ከሰይጣን መንፈስ ጋር ግንኙነት ኖሯት በዚሁ መንፈስ ሳሙኤልን የመሰለ ሰው በምትሀት ተገልጦላት ሊሆን ይችላል:: የዚህ ምስጢራዊ ጉዳይ ትርጓሜ የተለያየ ቢሆንም፣ ሳኦል ሙታን ሳቢ አስፈልጎ ማግኘት ችሉአል:: እየገሠገሠ የመጣበት ሰራዊት ሞት እንደ ሚያስከትልበት፣ መንግሥቱን ለማጽናት የነበረውን ተስፋ እንደ ሚያጨልምበት፣ እስራኤልን አፈራርሶ አገዛዙን እንደሚያ ስወግድና ሕዝቡንም ዕድሜውን ሙሉ ሲታገላቸው ለነበሩ ፍልስጥኤማው ያን አሳልፎ እንደሚሰጥበት ተረድቶአል:: ይህም የሚደርስበት፣ ሳሙኤል አስቀድሞ እንደ ተናገረው (15፥26:28) ሳኦል ለእግዚአብሔር ታማኝ ስላልሆነ ነው:: *ሴትዮዋ ... በመጮኽ ሳኦልን "አንተ ሳኦል ሆነህ ሳለ ለምን አታለልኸኝ?"* ነገሩ በምን መንገድ እንደ ሆነ ባይታወቅም፣ የምትነጋገረው ከሳኦል ጋር መሆኑን ወዲያ ውኑ ዐውቃለች ::

28፥14 *ካባ የለበሰ አንድ ሽማግሌ፤* ሳሙኤል አዘውትሮ እንደዚህ ይለብስ ስለነበረ ሳኦል ለማስታወስ አልተቸገረም (15፥27 ይመ)::

ለፍልስጥኤማውያን አሳልፎ ይሰጣል፤ አን
ተና ልጆችህም ነገ ከእኔ ጋር ትሆናላችሁ፤
እንዲሁም *እግዚአብሔር* የእስራኤልን ሰራ
ዊት ለፍልስጥኤማውያን አሳልፎ ይሰጣል::"
20ሳሙኤል ከተናገረው ቃል የተነሣ፣ ሳኦል
በፍርሃት ተውጦ ወዲያውኑ በቁመቱ ሙሉ
መሬት ላይ ወደቀ፤ ቀኑንና ሌሊቱን ሁሉ
እህል ስላልቀመሰ ጉልበቱ ዝሎ ነበር::
21ሴትዮዋ ወደ ሳኦል መጥታ እጅግ መደ
ንገጡን ባየች ጊዜ እንዲህ አለችው፤ "እነሆ፤
አገልጋይህ ቃልህን ሰምቻለሁ፤ በነፍሴም
ቈርጬ የነገርኸኝን ፈጽሜአለሁ:: 22አሁ
ንም እባክህ አገልጋይህ የምትልህን ስማ፤
ብርታት አግኝተህ መሄድ እንድትችል፣
ጥቂት ምግብ ላቅርብልህና ብላ::"
23እርሱም፣ "አልበላም" በማለት እምቢ አለ::
ነገር ግን የራሱ ሰዎች ከሴትዮዋ ጋር
ሆነው አጥብቀው ስለ ለመኑት ቃላቸውን
ሰማ፤ ከመሬትም ተነሥቶ በአልጋ ላይ
ተቀመጠ::
24ሴትዮዋም በቤቷ የሠባ ጥጃ ስለነበራት፣
ፈጥና አረደችው፤ ዱቄት ወስዳ ለወሰች፣
እርሾ የሌለው እንጀራም ጋገረች:: 25ከዚ
ያም ለሳኦልና ለሰዎቹ አቀረበችላቸው፤
እነርሱም በሉ፤ በዚያም ሌሊት ተነሥተው
ሄዱ::

### አንኩስ ዳዊትን ወደ ጺቅላግ መልሶ መላኩ

**29** ፍልስጥኤማውያን ሰራዊታቸውን ሁሉ
በአፌቅ ሰበሰቡ፤ እስራኤላውያንም
በኢይዝራኤል ሸለቆ ባለው ምንጭ አጠገብ
ሰፈሩ፤ 2የፍልስጥኤማውያን ገዦች በመቶና
በሺህ ሆነው ሲዘምቱ፣ ዳዊትና ሰዎቹም
ከአንኩስ ጋር ደጀን ሆነው ይከተሉ ነበር::
3የፍልስጥኤም አዛዦችም፣ "እነዚህ ዕብራ
ውያን እዚህ ምን እያደረጉ ነው?" ብለው
ጠየቁ::
አንኩስም፣ "ይህ የእስራኤል ንጉሥ የሳኦል
አገልጋይ የነበረው ዳዊት አይደለምን?"
ከእኔ ጋር መኖር ከጀመረ እነሆ ዓመት
አለፈው፤ እኔን ከተጠጋበት ጊዜ ጀምሮ
እስከ አሁን ድረስ ምንም በደል አላገኘሁበ
ትም" አላቸው::
4የፍልስጥኤማውያን አዛዦች ግን በአን
ኩስ ላይ ተቈጥተው እንዲህ አሉ፤ "ይህን
ሰው ወደዚያው ወደ ሰጠኸው ቦታ ይመ
ለስ ዘንድ ስደደው፤ በውጊያው ጊዜ በእኛ
ላይ ተመልሶ ጠላት እንዳይሆን፣ አብሮን
ወደ ጦርነቱ መሄድ የለበትም፤ የእኛን
ሰዎች ራስ ቈርጦ ካልወሰደ ከጌታው ጋር
እንዴት ሊታረቅ ይችላል? 5በዘፈን እየተ
ቀባበሉ፣

'ሳኦል ሺህ ገደለ፤
ዳዊት ግን ዐሥር ሺህ'

ብለው የዘመሩለት ይኸው ዳዊት አይደለ
ምን?"
6ስለዚህ አንኩስ ዳዊትን ጠርቶ እንዲህ
አለው፤ "ሕያው *እግዚአብሔርን*! አንተ
ታማኝ ነህ፤ ወደ እኔ እዚህ ከመጣህበት
ቀን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ምንም
ጥፋት ያላገኘሁብህ ስለሆነ፣ አብረኸኝ ብት
ዘምት በበኩሌ ደስተኛ ነበርሁ፤ ነገር ግን
ገዦቹ አልተቀበሉህም፤ 7እንግዲህ ተመል
ሰህ በሰላም ሂድ፤ የፍልስጥኤማውያንን
ገዦች ደስ የማያሰኝ ምንም ነገር አታድ
ርግ"
8ዳዊትም፣ "ለመሆኑ ምን አደረግሁ?
እዚህ ከመጣሁበት ዕለት ጀምሮ እስካሁን
ድረስ፣ በአገልጋይህ ላይ ምን አገኘህበት?
ታዲያ፣ ከንጉሡ ከጌታዬ ጠላቶች ጋር
የማልዋጋው ስለ ምንድን ነው?" ብሎ ጠየቀው::
9አንኩስም እንዲህ አለው፤ "በእኔ ዘንድ
እንደ እግዚአብሔር መልአክ መልካም እንደ
ሆንህ ዐውቃለሁ፤ የፍልስጥኤማውያን አዛ
ዦች ግን፣ 'አብሮን ለጦርነት መውጣት የለ
በትም' ብለዋል:: 10አሁንም አብረውህ ከመ
ጡት ከጌታህ አገልጋዮች ጋር ማለዳ ተነሡ፤
በጥዋት ፀሐይ እንደ ወጣችም ሂዱ" አለው::
11ስለዚህ ዳዊትና ሰዎቹ ወደ ፍልስጥኤ
ማውያን ምድር ለመመለስ በማለዳ ተነሡ፤
ፍልስጥኤማውያንም ወደ ኢይዝራኤል ወጡ::

### ዳዊት አማሌቃውያንን አጠፋ

**30** በሦስተኛው ቀን ዳዊትና ሰዎቹ
ጺቅላግ ደረሱ፤ በዚህ ጊዜ አማሌ
ቃውያን ደቡቡን አገርና ጺቅላግን ወረው

28፥21 መሳ9፥17፤ 12፥3
28፥23 1ነገ21፥4
28፥24 ዘፍ18፥7
29፥1 ኢሲ17፥16፤ 1ሳሙ4፥1፤28፥1፤ 1ነገ18፥45፤21፥1፡23፤ 2ነገ9፥30፤ኤር50፥5፤ ሆሴ1፥4፡5፡11፤2፥22
29፥2 1ሳሙ28፥2
29፥3 1ሳሙ27፥7፤ 1ዜና12፥19
29፥4 1ሳሙ14፥21፤ 1ዜና12፥19
29፥5 1ሳሙ18፥7
29፥6 ቍ3፤ 1ሳሙ27፥8-12
29፥9 ቍ4፤ 2ሳሙ 14፥17፡20፤ 19፥27
29፥10 1ዜና12፥19
30፥1 ቍ14፤ 1ሳሙ27፥6፡8

28፥21 *ሴትዮዋ ወደ ሳኦል መጥታ፤* ይህ ዐረፍተ ነገር የሚያሳየው ሴትዮዋ ንግሯን ለሳኦል በምትነግርበት ጊዜ ካጠገቡ አለመኖሯን ያሳያል::

29፥1 *ፍልስጥኤማውያን ሰራዊታቸውን ሁሉ በአፌቅ ሰበሰቡ፤* በ28፥2 ላይ ተቋርጦ የነበረው ትረካ እዚህ ላይ ቀጥሎ አል:: *አፌቅ፤* ስሙ በ4፥1 ላይ ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይ ቢሆ ንም፣ ይህ ቦታ የሚገኘው በሱነም ትይዩ ነው (28፥4፤ 1ነገ 20፥26፡ 30፤ 2ነገ 13፥17 ይመ)::

29፥2 *የፍልስጥኤማውያን ገዦችም፤* የ5፥8 ማብ ይመ::

29፥3 *ምንም በደል አላገኘሁበትም፤* በ27፥10-12ላይ የተጠ ቀሱት የዳዊት ዘዴዎች፣ በዚህ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ ውጤት አስገኝተውለታል::

29፥4 *ወደዚያው ወደ ሰጠኸው ቦታ፤* 27፥6 *ይመ:: በውጊ ያው ጊዜ ተመልሶ ለእኛ ጠላት እንዳይሆን፤* ይህን የመሰለ ነገር ከዚህ በፊት አጋጥሞአቸው ስለነበር፣ ፍልስጥኤማውያን በዚህ ጊዜ ዳዊትንና ሰዎቹን ጠረጠሯቸው (14፥21 ይመ)::

29፥6 *ሕያው እግዚአብሔርን፤* የ14፥39 ማብ ይመ:: አንኩስ በእስራኤል አምላክ መማሉ ለዳዊት የቱን ያህል ግልጽ እንደነበር ያመለክታል::

29፥8 *ለመሆኑ ምን አደረግሁ?* እዚህ ላይ ዳዊት የማታ ለል ዕቅዱ እንዳይፈርስበት ነገሩን መሸፋፈን የፈለገ ይመስላል:: በእርግጥ ይህ ሁኔታ ዳዊትን ከጭንቅ አውጥቶታል:: *ታዲያ፣ ከን ጉሡ ከጌታዬ ጠላቶች ጋር የማልዋጋው ስለ ምንድን ነው?* ዳዊት አሁንም አሻሚ ትርጒም ያለው ሐሳብ ያቀርባል (28፥2 ይመ)፤ "ጌታዬ ንጉሡ" የሚለው አንኩስን ይሁን ወይም ሳኦልን ወይም ደግሞ እግዚአብሔርን አይታወቅም::

29፥9 *እንደ እግዚአብሔር መልአክ፤* የተለመደ ዘይቤያዊ ንጽጽር ነው::

30፥1-31፥13፤ ሳኦል በፍልስጥኤማውያን እጅ ሊገደል ወደ ሞት ሲሄድ፣ ዳዊት ግን ተመልሶ የእግዚአብሔርን ጦርነት ሊዋጋ አማሌቃውያንን አሳደደ (15፥2-3 እና ማብ ይመ)::

30፥1 *ጺቅላግ፤* የ27፥6 ማብ ይመ:: *አማሌቃውያን፤* 27፥8 እና የ15፥2 ማብ ይመ:: በዚህ ጊዜ ዳዊትና ሰዎቹ ስለሌሉ፣ አማ

ነበር፤ ጺቅላግንም ወግተው አቃጥለው ነበር።
2ሴቶቹን፣ በዚያ የነበሩትን ወጣቶችና ሽማግ
ሌዎቹን ሁሉ ማርከው ወሰዱ፤ የማረኩት
ንም ይዘው ከመሄድ በስተቀር አንዱንም
አልገደሉም ነበር።
3ዳዊትና ሰዎቹ ወደ ጺቅላግ እንደ ደረ
ሱም፣ እነሆ፤ ከተማዪቱ በእሳት ጋይታ፣
ሚስቶቻቸው፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው
ተማርከው አገኙ። 4በዚህ ጊዜ ዳዊትና ሰዎቹ
ማልቀስ እስከሚያቅታቸው ድረስ ድምፃቸ
ውን ከፍ አድርገው አለቀሱ፤ 5ሁለቱ የዳ
ዊት ሚስቶች ማለትም ኢይዝራኤላዊቷ
አኪናሆምና የቀርሜሎሳዊው የናባል ሚስት
የነበረችው አቢግያም ተማርከው ነበር።
6ሰዎቹ ስለ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው
ነፍሳቸው ተመሬ ሊወግሩት ስለ ተመካከሩ
ዳዊት በጣም ተጨነቀ፤ ነገር ግን ዳዊት
በአምላኩ *በእግዚአብሔር* በረታ።
7ከዚያም ዳዊት የአቢሜሌክን ልጅ ካህ
ኑን አብያታርን፣ "ኤፉዱን አምጣልኝ" አለው፤
አብያታርም አመጣለት፤ 8ዳዊትም፣ "ይህን
ወራሪ ሰራዊት ልከተለውን?' እደርስባቸዋ
ለሁን?" ሲል *እግዚአብሔርን* ጠየቀ።
*እግዚአብሔርም*፣ "በእርግጥ ትደርስባቸዋ
ለህ፤ ምርኮውንም ትመልሳለህ፤ ተከተል" ሲል
መለሰለት።
9ስለዚህ ዳዊትና አብረውት የነበሩት ስድ
ስት መቶ ሰዎች ወደ ቦሦር ወንዝ መጡ፤
ጥቂቶቹም በቦሦር ወንዝ ቈዩ፤ 10ሁለት
መቶዎቹ እጅግ ዝለው ስለ ነበር ወንዙን
መሻገር አልቻሉምና። ነገር ግን ዳዊትና
አራት መቶ ሰዎች መከታተላቸውን ቀጠሉ።
11እነርሱም በምድረ በዳ አንድ ግብፃዊ
አገኙ፤ ወደ ዳዊትም አመጡት፤ የሚጠ
ጣውን ውሃና የሚበላውን ምግብ ሰጡት።
12እንደዚሁም የበለስ ጥፍጥፍ ቍራሽና
ሁለት ደረቅ የወይን ዘለላዎች ሰጡት።
ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ምንም እህል
ስላልበላ፣ ውሃም ስላልጠጣ ይህን ከበላ
በኋላ ነፍሱ ተመለሰች።
13ዳዊትም ፣ "አንተ የማን ነህ? የመጣኸ
ውስ ከየት ነው?" ብሎ ጠየቀው። እርሱም
እንዲህ አለው፤ "እኔ ግብፃዊ ስሆን፣ የአ
ንድ አማሌቃዊ ባሪያ ነኝ፤ ከሦስት ቀን
በፊት ታምሜ በነበረበት ጊዜ ጌታዬ ጥሎኝ
ሄደ። 14የከሊታውያንን ደቡብ፣ የይሁዳን
ግዛትና የካሌብን ደቡብ ወረርን፤ ጺቅላግ
ንም በእሳት አጋየናት።"

30፥3 ዘፍ31፥26
30፥4 ዘፍ27፥38
30፥5 1ሳሙ25፥43
30፥6 ዘፀ17፥4፤ ሩት1፥13፤ 1ሳሙ 23፥16፤ ዮሐ8፥59፤ ሮሜ 4፥20
30፥7 1ሳሙ2፥28፤ 2፥20
30፥8 ዘፍ14፥16፤ ዘፀ2፥17፤ 1ሳሙ23፥2
30፥9 1ሳሙ27፥2
30፥10 ቊ21
30፥12 መሳ15፥19
30፥13 1ሳሙ14፥48
30፥14 ቊ1፤ ኢሱ14፥13፤15፥13፤ 2ሳሙ8፥18፥15፥18፤ 20፥7:23፤1ነገ1፥38: 44፤ሕዝ25፥16፤ሶፎ2፥5
30፥15 ዘዳ 23፥15
30፥16 ቊ7፤ ኢሱ22፥8፤ ሉቃ12፥19
30፥17 ቊ16፤ 1ሳሙ11፥11፤ 2ሳሙ1፥1:8
30፥18 ዘፍ14፥16
30፥21 ቊ10
30፥24 ዘኍ31፥27፤ መሳ5፥30
30፥26 ዘፍ33፥11

15ዳዊትም፣ "ታዲያ ወራሪው ሰራዊት
ወዳለበት መርተህ ታደርሰኛለህ?" ሲል
ጠየቀው። እርሱም፣ "እንደማትገድለኝ ወይም
ለጌታዬ አሳልፈህ እንደማትሰጠኝ በእግዚአ
ብሔር ማልልኝ እንጂ እነዚህ ወራሪዎች ወዳ
ሉበት አደርስሃለሁ" አለው።
16ዳዊትን ወደ ታች መርቶ ባደረሰው
ጊዜም፣ ወራሪዎቹ ከፍልስጥኤማውያንና ከይ
ሁዳ ምድር ከወሰዱት ታላቅ ምርኮ የተነሣ
በየቦታው ተበታትነው ይበሉ፣ ይጠጡና ይዘ
ፍኑ፣ ይጨፍሩም ነበር። 17ዳዊት፣ ከዚያች
ዕለት ማታ ጀምሮ እስከ ማግሥቱ ምሽት
ድረስ ወጋቸው፤ በግመል ተቀምጠው ከሸሹት
አራት መቶ ወጣቶች በስተቀር፣ ከመካከላ
ቸው ያመለጠ አንድም አልነበረም። 18ዳዊት
አማሌቃውያን የወሰዱትን ሁሉ አስጣለ፣
ሁለቱንም ሚስቶቹን አስመለሰ። 19ትንሽም
ሆነ ትልቅ፣ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ልጆች፣
ምርኮም ሆነ ሌላ፣ አማሌቃውያን ከወሰ
ዱት ነገር ምንም የጐደለ አልነበረም፤ ዳዊት
ሁሉንም አስመለሰ። 20እንዲሁም ዳዊት የበ
ጉን፣ የፍየሉንና የላሙን መንጋ ሁሉ ወሰደ፤
ሰዎቹም "ይህ የዳዊት ምርኮ ነው' እያሉ
መንጋውን ከሌሎች ከብቶች ፊት ለፊት
ይነዱ ነበር።
21ከዚያም ዳዊት፣ እጅግ በመድከማቸው
ምክንያት ሊከተሉት ወዳልቻሉት በቦሦር
ወንዝ ቀርተው ወደ ነበሩት ወደ ሁለቱ
መቶ ሰዎች መጣ፤ እነርሱም ዳዊትንና አብ
ረውት የነበሩትን ሰዎች ለመቀበል ወጡ።
ዳዊትና ሰዎቹ ወደ እነርሱ እንደ ቀረቡም
ዳዊት ሰላምታ ሰጣቸው። 22ከዳዊት ተከ
ታዮች ክፉዎቹና ምናምንቴዎቹ ሁሉ ግን፣
"አብረውን ስላልዘመቱ ካመጣነው ምርኮ
አናካፍላቸውም፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ሚስ
ቱንና ልጆቹን ይዞ መሄድ ይችላል" አሉ።
23ዳዊትም እንዲህ አለ፤ "ወንድሞቼ ሆይ፤
የጠበቀን፣ የመጣብንንም ወራሪ በእጃችን
የጣለልን *እግዚአብሔር* ነው፤ እርሱ በሰጠን
ነገር፣ ይህን ማድረግ አይገባችሁም። 24የም
ትሉትን ማን ይቀበላችኋል? ከጓዝ ጋር የቀ
ረው ሰው ድርሻ ለጦርነት ከወጣው ሰው
ድርሻ ጋር አይበላለጥም፤ ሁሉም እኩል
ይካፈላሉ።" 25ዳዊትም ከዚያ ቀን ጀምሮ
እስከ ዛሬ ድረስ ይህን ለእስራኤል ደንብና
ሥርዐት አደረገው።
26ዳዊት ወደ ጺቅላግ በመጣ ጊዜ፣ ወዳ
ጆቹ ለሆኑት ለይሁዳ ሽማግሌዎች፣ "*ከእግ*

ሌቃውያን ጺቅላግን ለመምታት ዕድል አገኙ።
30፥2፤ በዚህ ክፍል እንደሚታየው የማረኳቸውን ሁሉ ባሪያ ለማድረግ ይዘዋቸው ሄዱ።
30፥5 *አኪናሆምና፤* የ25፥43 ማብ ይመ። *አቢግያ፤* 25፥42 ይመ።
30፥7 *ካህኑን አብያታርን፤* የ22፥20 ማብ ይመ። *ኤፉዱን፤* የ2፥28 ማብ ይመ።
30፥14 *ደቡብ፤* የ27፥10 ማብ ይመ። *የከሊታውያንን፤* እነዚህ በኋለኛው ጊዜ ከፈሊታውያን ጋር በዳዊት ሰራዊት ውስጥ ምርጥ የግል ተዋጊዎች ሆነዋል (2ሳሙ15፥18፤ 20፥7፤ 1ነገ1፥38 ይመ)። ቀደም ሲል ከቀርጤስ ደሴት የመጡ መሆናቸውን ስማቸው ያመለክታል (አሞ9፥7 ይመ)። *የካሌብን ደቡብ፤* ከኬብሮን በስተ ደቡብ ያለው ስፍራ ነው (ኢሱ14፥13 ይመ)።
*30፥20፤* ዳዊት በይሁዳ ላሉ ወዳጆቹ፣ ከማረከው ምርኮ አከፋፈላቸው (ቍ 26፥31)።
30፥22 *ምናምንቴዎቹ፤* የዘፀ 13፥13 ማብ ይመ።
30፥23 *እርሱ በሰጠን ነገር፤* ዳዊት ድሉ የተገኘው በእኛ ጕብዝና ነው የሚለውን ሐሳብ በየዋሃትና በጽናት ተቃወመ። ድል የሰጣቸው ራሱ እግዚአብሔር ስለ ሆነ፣ ከዳዊት ሰራዊት አንድም ሰው በራሱ ጕብዝና ድል እንዳገኘ ሊያስብ አይገባውም።
30፥26 *ወዳጆቹ ለሆኑት ለይሁዳ ሽማግሌዎች፤* ዳዊት ከሳኦል በሸሸ ጊዜ (ቍ31) ለረዱት፣ ካገኘው ምርኮ ከምስጋና ጋር ስጦታ ላከላቸው፤ ይህን በማድረግም በይሁዳ ለመንገሥ መንገዱን

*ዚአብሔር* ጠላቶች የተገኘ ስጦታ እነሆ፤”
በማለት ከምርኮው ላይ ከፍሎ ላከላቸው::
27ይህንም፣ በቤቴል፣ በደቡብ ራሞትና
በየቲር ለነበሩ፣ 28በአሮዔር፣ በሢፍሞት፣
በኤሽትሞዓና 29በራካል እንዲሁም በይረሕ
ምኤላውያንና በቄናውያን ከተሞች ለሚ
ኖሩ፣ 30በሔርማ፣ በቦራሣን፣ በዓታክ፣ 31በኬ
ብሮን እንዲሁም ዳዊትና ሰዎቹ በተዘዋወሩ
ባቸው ስፍራዎች ሁሉ ለነበሩት ላከላቸው::

## የሳኦል መሞት

31፥1-13 ተጓ ምብ-2ሳሙ1፥4-12፤ 1ዜና10፥1-12

31 በዚህ ጊዜ ፍልስጥኤማውያን እስራ
ኤልን ወጉ፤ እስራኤላውያን ከፊ
ታቸው ሸሹ፤ ብዙዎቹም በጊልቦዓ ተራራ
ላይ ተወግተው ወደቁ:: 2ፍልስጥኤማውያን
ሳኦልንና ልጆቹን አጥብቀው ተከታተሉ፤
የሳኦልንም ልጆች ዮናታንን፣ አሚናዳ
ብንና ሜልኪሳን ገደሉ:: 3ውጊያው በሳኦል
ላይ በረታበት፤ ቀስተኞችም ደርሰው እጅግ
አቈሰሉት::
4ሳኦልም ጋሻ ጃግሬውን፣ “እነዚህ ያል
ተገረዙ ሰዎች መጥተው እንዳይወጉኝ፣ እንዳ
ያዋርዱኝ፣ አንተው ሰይፍህን መዘህ ውጋኝ”
አለው::
ጋሻ ጃግሬው ግን እጅግ ፈርቶ ስለ
ነበር፣ እምቢ አለው:: ስለዚህ ሳኦል የራሱን
ሰይፍ ወስዶ በላዩ ላይ ወደቀበት:: 5ጋሻ
ጃግሬውም ሳኦል መሞቱን ባየ ጊዜ፣ እር
ሱም እንደዚሁ በሰይፉ ላይ ወድቆ አብሮት
ሞተ:: 6ሳኦልና ሦስቱ ልጆቹ፣ አብረውት
የነበሩ ሰዎች ሁሉና ጋሻ ጃግሬው የሞቱት
በዚያኑ ቀን ነበር::
7በሸለቆው ማዶና ከዮርዳኖስ ባሻገር ያሉ
እስራኤላውያን የእስራኤል ሰራዊት መሸ
ሹን፣ ሳኦልና ልጆቹም መሞታቸውን ባዩ
ጊዜ ከተሞቻቸውን ለቀው ሸሹ፤ ፍልስጥኤ
ማውያንም መጥተው ተቀመጡባቸው::
8በማግስቱ ፍልስጥኤማውያን የሞቱትን
ሰዎች ለመግፈፍ ሲመጡ፣ ሳኦልና ሦስቱ
ልጆቹ በጊልቦዓ ተራራ ላይ ወድቀው አገኟ
ቸው:: 9ከዚያም የሳኦልን ራስ ቈርጠው፣
የጦር መሣሪያውንም ገፈው፣ የምሥራቹን
በየቤተ ጣዖቶቻቸውና በሕዝባቸው መካከል
እንዲናገሩ ወደ ፍልስጥኤም ምድር ሁሉ
መልክተኞች ላኩ:: 10የጦር መሣሪያውን
በአስታሮት ቤተ ጣዖት ውስጥ አኖሩት፤
ሬሳውን ደግሞ በቤትሳን ግንብ ላይ አንጠ
ለጠሉት::
11የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ፍልስጥኤ
ማውያን በሳኦል ላይ ያደረጉትን በሰሙ ጊዜ፣
12ጀግኖቻቸው ሁሉ በሌሊት ወደ ቤትሳን
ሄዱ:: የሳኦልንና የልጆቹን ሬሳ ከግንቡ ላይ
አውርደው ወደ ኢያቢስ አምጥተው አቃጠሉ::
13ከዚያም ዐጥንቶቻቸውን ወስደው በኢያ
ቢስ ባለው የአጣጥ ዛፍ ሥር ቀበሩ፤ ሰባት
ቀንም ጾሙ::

30፥27 ኢሱ7፥2፤ ኢሱ10፥40፤15፥48
30፥28 ዘኍ32፥34፤ ኢሱ13፥16፤ 15፥50፤1ዜና27፥27
30፥29 1ሳሙ15፥6፤ 27፥10
30፥30 ዘኍ14፥45፤ 21፥3፤ኢሱ15፥42
30፥31 ዘኍ13፥22፤ ኢሱ10፥36፤ 2ሳሙ 2፥1:4
31፥1 1ሳሙ28፥4
31፥2 1ሳሙ14፥49፤ 18፥1፤28፥19
31፥3 1ሳሙ28፥4
31፥4 ዘፍ34፥14፤ መሳ9፥54፤ 1ሳሙ14፥6
31፥6 1ሳሙ26፥10
31፥8 2ሳሙ1፥20
31፥9 መሳ16፥24፤ 2ሳሙ1፥20፤4፥4
31፥10 ኢሱ17፥11፤ መሳ2፥12-13፤1ሳሙ7፥3
31፥11 መሳ21፥8፤ 1ሳሙ11፥1
31፥12 ዘፍ38፥24፤ መዝ76፥5፤ ዘሞ 6፥10
31፥13 ዘፍ21፥33፤ 2ሳሙ21፥12-14

---

አመቻቸ (2ሳሙ 2፥1-4 ይመ)::

30፥26-31፤ ዳዊት በይሁዳ ከሚኖሩት ጋር እንደ ገና ግን ኙነቱን አጠናከረ፤ ከዚያም በኋላ አነገሡት (2ሳሙ2፥1-4)፤ እዚህ ላይ የተጠቀሱት አገሮች በሙሉ በይሁዳና በስምዖን ግዛት ያሉ ናቸው::

30፥27 *በቤቴል፤* በብንያም አገር ያለው ሳይሆን በኢሱ 19፥4 ላይ በቱል የተባለው ስፍራ ሳይሆን አይቀርም::

30፥29 *በይረሕምኤላውያን፤* የ27፥10 ማብ ይመ:: *በቄናውያን፤* የ15፥6 ማብ ይመ::

30፥31 *በኬብሮን፤* በደቡባዊ ይሁዳ ያለች የታወቀች ከተማ ናት:: በዚህ ስም የተጠቀሱት ሌሎቹ ስፍራዎች ከኬብሮን በስተ ምሥራቅና በስተ ምዕራብ ይገኛሉ::

*31፥1፤* የጊልቦዓ ተራራ በኢይዝራኤል ሸለቆ የሚገኝ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ስድስት ጫማ ከፍታ ያለው ቦታ ነው::

31፥2 *ዮናታንን፣ አሚናዳብንና ሜልኪሳን፤* የ14፥49 ማብ ይመ:: ከሞት የተረፈው የሳኦል ልጅ ሚምፊቦስቴ ወይም በ1ዜና 8፥33፤ 9፥39 ላይ አስቦአል የተባለው አባላቱን እንዲተካ በአበኔር ተገፋፍቶ ነበር (2ሳሙ2፥8-9):: በሳኦልና በልጆቹ የደረሰው ይህ አሰቃቂ ሞት የሳሙኤል ትንቢት (28፥9) ፍጻሜ ነው::

31፥4 *እነዚህ ያልተገረዙ ሰዎች፤* 14፥6 እና ማብ ይመ:: *እንዳያዋርዱኝ፤* ፍልስጥኤማውያን የሳምሶንን ዐይኖች አውጥተው ይዘባበቱበትና ይሣለቁበት እንደ ነበር ሁሉ (መሳ 16፥23-25)፣ ሳኦል እንዲህ ዐይነቱ ነገር እንዳይገጥመው ስለፈራ ነበር:: *የራሱን ሰይፍ ወስዶ በላዩ ላይ ወደቀበት፤* አሰቃቂ በሆነ መንገድ ሳኦል የራሱን ሕይወት አጠፋ::

31፥6 *አብረውት የነበሩ ሰዎች፤* ሳኦል በሚያስተዳድርበት ጊዜ አብረውት ሲሠሩ የነበሩትን ሁሉ ሊመለከት ይችላል (ነገር ግን የቍ 2 ማብ ይመ)::

31፥7 *በሸለቆው፤* በኢይዝራኤል ይገኛል::

31፥9 *የሳኦልን ራስ ቈርጠው፤* ዳዊት በጎልያድ ላይ ይህንኑ አድርጎ ነበር (17፥51 ይመ):: *ወደ የፍልስጥኤም ምድር ሁሉ መልእክተኞች ላኩ፤* ምናልባትም የሳኦልን ራስና የጦር መሣሪያዎች የያዙት የድላቸው ማረጋገጫ እንዲሆን አስበው ይሆናል::

31፥10 *የጦር መሣሪያውን በአስታሮት ቤተ ጣዖት ውስጥ አኖሩት፤* አስታሮት የከነዓናውያን የወሊድ አምላክና በኣል ለተባለው ጣዖት ሚስት ናት:: ቤተ ጣዖቷም የዮርዳኖስን ሸለቆዎችና ኢያዝራኤልን በሚያገናኝ መንገድ ላይ ቤትሳን በሚባል የታወቀ ከተማ ውስጥ ይገኝ ነበር:: ፍልስጥኤማውያን የሳኦልን የጦር ዕቃ ወደዚህ ቤተ ጣዖት ማምጣታቸው የተጐናጸፉት ድል ከአማልክታቸው ርዳታ የተነሣ የተገኘ መሆኑን ለማመልከት ነበር:: በጦርነቱ የወደቁ እስራኤላውያን ሬሳም በቤትሳን ከተማ ቅጥር ላይ ተሰቅሎ ነበር (ከ2ሳሙ 21፥12 ጋር ያነጻጽሩ)::

31፥11 *የኢያቢስ ገለዓድ፤* የ11፥1 ማብ ይመ::

31፥12 *የሳኦልንና የልጆቹን ሬሳ … አውርደው፤* አሞናውያን መጥተው ባስጨነቋቸው ጊዜ (ም11)፣ ሳኦል እንዴት እንደተከላከላቸውና እንዳዳናቸው የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች አልረሱም ነበር:: *አቃጠሉ፤* በጥንት የእስራኤል ታሪክ ሬሳ ማቃጠል የተለመደ አልነበረም፤ በዚህ ስፍራ የተደረገው ምናልባት የሳኦልንና የሰዎቹን ሬሳ ከፍልስጥኤማውያን ርኵሰት ለማንጻት ሊሆን ይችላል::

31፥13 *ዐጥንቶቻቸውን ወስደው … ቀበሩ፤* በኋላም ዳዊት ዐፅማቸውን ከኢያቢስ ወስዶ በብንያም ውስጥ ጼላ በተባለችው ቦታ በሚገኘው በሳኦል ቤተ ሰብ መቃብር ውስጥ አኖረው (2ሳሙ 21፥12-14):: *ሰባት ቀንም ጾሙ፤* ለሳኦል የነበራቸውን ሐዘን ለመግለጽ ነው (ከ2ሳሙ1፥12፤ 3፥35፤12፥16:21-23 ጋር ያነጻጽሩ)::